# ሽምግልና




ባህላዊ ሽምግልና እና አመቻች ሽምግልናን ማዋሃድ
የአሰልጣኞች የስልጠና መምሪያ

አሳታሚ፡ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን
ምክር ቤት የመ. ሳ. ቁጥር 20212/1000  አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: +251 11 124 23 09
ፋክስ: +251 11 124 23 08
ድረ ገጽ: www.hofethiopia.gov.et

© Deutsche Gesellschaft für Internationale Zusammenarbeit
(GIZ) GmbH - Civil Peace Service Service Program 2014
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።
የመጀመሪያ እትም

አዘጋጁ ከኢንሚዲኦ በርሊን የተለያዩ ማጣቀሻዎችና
ማስረጃዎች ለመጠቀም ፈቃድ አለው።
ስለፈቃዳቸው ከልብ ያመሰግናል።

በዚህ መምሪያ የተካተቱት ፎቶግራፎች ከ2009 - 2011
በጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት እና በኢሚዲኦ
በርሊን በጋራ ባዘጋጁት ተከታታይ የሽምግልና ባለሙያነት
የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና የተወሰዱ ናቸው።
መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው።

የቅጂ መብት ባለቤት የሆኑትን ሁሉ ለማስቀመጥ
አስፈላጊው ጥረት ተደርጓል። የተጓደለ ወይም ስህተት
ቢኖር በሚቀጥሉት እትሞች የሚስተካከል ይሆናል።

አስተያየት ቢኖርዎ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ወይንም የጂ አይ
ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት ቢሮዎችን ማናገር ይችላሉ።
የመ. ሳ. ቁ 12631 አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ
የቢሮ መገኛ፡ ሐሻም ህንፃ (4ኛ ፎቅ) ካሳንቺስ አካባቢ
ድረ ገጽ: www.giz.de

በሴንትራል ማተሚያ ቤት ታተመ።
አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

የመጽሐፉ ቅንብር እና ዲዛይን
ማሊ ኮስ Mali Kos (mali.m.kos@gmail.com)
የዝግጅት ቦታ እና ቀን፡ አዲስ አበባ የካቲት 2014

ትርጉምና ረዳት ዲዛይን
ዳዊት ላምቤቦ (dawit.lambebo@gmail.com)
የዝግጅት ቦታ እና ቀን፡ አዲስ አበባ የካቲት 2014

ይህ ህትመት በጀርመን ፌዴሬሽን የኢኮኖሚ ትብብርና
ልማት ሚኒስቴር ድጋፍ በጂ አይ ዜድ ታተመ።

german cooperation
DEUTSCHE ZUSAMMENARBEIT
Implemented by: giz
zfd Ziviler Friedensdienst
Civil Peace Service
inmedio

# ሽምግልና

## በጥላ ስር

የኢትዮጵያ ባህላዊ ሽምግልናንና አመቻች ሽምግልናን ማዋሃድ
የአሰልጣኞች የስልጠና መምሪያ

ቀዳሚ ቃል በስቴላ ሚስቲካ ሳቢቲ

የተከበራችሁ አንባቢያን

ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ጊዜያቸውን መስዋዕት አድርገው ዕውቀታቸውን ለህብረተሰባችን በማካፈል ይህን የሀገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና በተለያዩ የማህበረሰብ ደረጃዎች በሥራ ላይ ሊውል የሚችል የሽምግልና ሥርዓት መምሪያ አዘጋጆች እንዲሁም የተለያየ አስተዋጽኦ ላበረከቱት ክፍሎች ያለኝን ከፍ ያለ ምስጋና እና አድናቆት ማቅረብ እፈልጋለሁ፡፡

ይህ የግጭት አፈታትና የሽምግልና መምሪያ የህትመት ውጤት በሀገራችን በብሄራዊና በክልል ደረጃ ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን አስቀድሞ ለመከላከል የሚጠቅም ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ምክንያቶች የተከሰቱን ግጭቶች የከፋ ጥፋት ከማስከተላቸው በፊት ወደ መልካም ለውጥና የልማት አጋጣሚዎች ለመሸጋገር የጎላ ድርሻ እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከሁሉ በላይ ይህ የካበተ ልምድ ባላቸው ኢትዮጵያውያንና የውጭ ባለሙያዎች የተቀናጀ ጥረት የተዘጋጀው የግጭት አፈታትና የሽምግልና ስርዓት መምሪያ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገ መንግሥታችን የተረጋገጠው የኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእኩልነት ላይ የተመሠረተው አንድነታቸው ሥር እንዲሰድና ተቻችለውና ተከባብረዉ የመኖር ባህላቸው እንዲዳብር ለሚያደርገዉ ብሔራዊ የሰላም ግንባታ ጥረት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ይታመናል፡፡

በአህጉራችን አፍሪካ ብሎም በሀገራችን ኢትዮጵያ ቀደም ሲል የነበረው ልምድ እንደሚያመለክተው አለመግባባቶችና ግጭቶች በሰው ልጆች የማህበራዊ ኑሮ ሂደት ሊኖሩ የሚችሉ እውነታዎች ከመሆናቸውም በላይ በብስለት ቢመሩ የማይቀለበሱ የማህበራዊ ለውጥና እድገት ፈር ቀዳጆች መሆናቸው በተጋጭ ወገኖች ዘንድ ታምኖ የሚወሰድ ሀቅ አልነበረም ቢባል የተጋነነ አይሆንም፡፡

ባንጻሩ ግን ከዚህ የሽምግልና የህትመት ውጤት ተሞክሮ መረዳት እንሚቻለው አለመግባባቶችና ግጭቶች ከሰው ልጆች ማህበራዊ ግንኙነት የማይነጠሉ የማህበረሰብ ተፈጥሯዊ የለውጥ ሂደት አካሎች ናቸው፡፡ ከዚህ እውነታ አንጻር አለመግባባቶችን በጭፍኑ ከመጥላትና በኃይል እርምጃ ለማስወገድ ከመሞከር ይልቅ መንስኤዎቻቸውንና ተዋናዮቹን ጠንቅቆ በመለየትና በመገንዘብ ከግጭቶች ጋር አብሮ በመስራትና ግጭቶችን ወደ በጎ መለወጥ የሁሉን ዜጎች ሚዛናዊ ተጠቃሚነት ሊያረጋግጥ የሚችል ከመሆኑም በላይ የማህበረሰብ እድገትና ልማት ምንጭ ሊሆን እንደሚቻል በማህበረሰብ ግጭት ዙሪያ የተሰሩ የተለያዩ ጥናታዊ ሥራዎች ያረጋግጣሉ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤታችን ከጀርመን የማህበረሰብ አቀፍ የሰላም አገልግሎት ጋር በመተባበር ይህ በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነውን የግጭት አፈታትና የሽምግልና መምሪያ ታትሞና ተመርቆ በተለያየ ደረጃ ለሚገኙ የህብረተሰባችን ክፍሎች ሥራ ላይ እንዲውል ሲያደርግ ከፍ ያለ ኩራት ይሰማዋል፡፡ ስለሆነም አፍሪካዊያን ወንድሞቻችንና በዓለማችን የተለያዩ ክፍሎች በሰላም ዙሪያ የሚሠሩ የተለያዩ ተቋማት፤ ተመራማሪዎችና የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለዓለማችን ሰላም፤ እድገትና ብልጽግና በዚህ መምሪያ እንዲጠቀሙ ግብዣችንን እያቀረብኩ ሰላምና እድገት ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲሆን እመኛለሁ፡፡

ደበበ ባሩድ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጀኔራል ሴክሬታሪ

ሀገራችን የተለያዩ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚኖሩባት ሀገር እንደመሆኗ መጠን የተለያዩ የሽምግልና ስርዓቶች ይገኙባታል። ይህም ከቦታ ቦታ፣ ከብሔር ብሔር እንዲሁም ከሕፃናት እስከ አዋቂዎች የተለያዩ የግጭት መፍቻ መንገዶችን ያካትታል። ከዚህም የተነሳ አፈፃፀማቸውና ስያሜያቸውም እንዲሁ ይለያያል።

ይህ መምሪያ በመጀመሪያ የተዘጋጀበት ቋንቋ እንግሊዘኛ ሲሆን ይህን መምሪያ ወደ አማርኛ ለመተርጎም የተለያዩ ዓይነት የሽምግልና ስርዓቶችን ሊወክል የሚችል ቃል ማግኘት ትልቁና ፈታኙ ሂደት ነበር። ስለዚህም በእንግሊዘኛው Mediation የሚለው ቃል በዚህ መምሪያ ውስጥ 'ሽምግልና' በሚለው ቃል ተተርጉሟል። ይህም የሆነበት ምክንያት ሠልጣኞች ይህን ቃል በተሻለ መልኩ ሊረዱት ስለሚችሉና በሀገራችን በሰፊው የሚታወቅ ቃል በመሆኑ ነው። በመምሪያው ውስጥ 'ሽምግልና' የሚለው ቃል በተጋጭ ወገኖች መካከል የተከሰተን ግጭት ወደ ዕርቅ ለማምጣት የሚደረግን ማንኛውንም ዓይነት ሂደት ያጠቃልላል። በመሆኑም በተጋጭ ወገኖች መካከል ለማስታረቅ፣ ለማደራደር፣ ለማስማማት ወይንም ለማቀራረብ የሚደረጉ የጣልቃ ገብነት ወይም ማንኛውም የመገላገል ተግባራት እንደ ሽምግልና ይቆጠራሉ። ሽምግልና ውጤቱን ብቻ ያተኮረ ሳይሆን በሂደቱ ላይ የተመሠረተ ነው። Wise men council የሚለውን የእንግሊዘኛ ቃል 'ባህላዊ ሽምግልና' በሚል ተተርጉሟል። ይህም በባህላዊ መንገድ የሚከናወነውንና በሀገራችን በስፋት የተለመደውን ነባሩን ስርዓት ያመለክታል። Facilitative Mediation የሚለው የእንግሊዘኛን ቃል አመቻች ሽምግልና በሚል ተተርጉሟል። ይህም ዘመናዊውንና በምዕራባዊያን ዘንድ በስፋት እየተለመደ ያለውን ያመለክታል።

በዚህ መምሪያ ውስጥ በወንድ ጾታ የተገለፁት ሁሉ የሴትንም ጾታ ያካትታሉ። ይህም ለትርጉም ያመች ይሆን ዘንድ የተደረገ እንጂ የሴትን ጾታ አያጠቃልልም ማለት አይደለም። እንዲሁም በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚገኘው የዘመን አቆጣጠር የአውሮፓውያን ሲሆን ይህም የሆነው አብዛኛዎቹ ማጣቀሻዎች በአውሮፓውያኑ የዘመን አቆጣጠር የተዘጋጁ በመሆናቸው ለአንባቢው ግርታ እንዳይፈጥሩ በማሰብ ነው።

የመምሪው አዘጋጆች ይህ የአማርኛ ትርጉም የተሳካ እንዲሆን ጊዜ በመስጠት ተሳትፎ አድርገዋል። አንዳንድ አሻሚ ለሆኑ ቃላት ፍች በመስጠት የትርጉም ስራው እንዲፋጠን አድርገዋል። በተለይም የአዋሳው እና የአዲስ አበባው የሽምግልና ቡድን በዚህ የትርጉም ሥራ ላይ ላደረጉት አስተዋጽኦ ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ። ከነዚም መካከል ለመጥቀስ አቶ መኮንን መርጊያ፣ አቶ ይትባረክ ጽጌ፣ አቶ ግሩም ዘሪሁን፣ አቶ ደርሰማን አንሳ፣ አቶ ብዙነህ አሰፋ፣ አቶ ገመቹ ብርሃኑ እና አቶ ምስጋናው ሙሉጌታን ይገኙበታል። በተጨማሪም ይህ ህትመት እንዲሳካ የሽምግልና ቡድኑና ተርጓሚውን በማገናኘት የላቀ አስተዋጽኦ ያደረጉትን አኒ ዲትሪችን ከልብ አመሰግናለሁ።

ዳዊት ላምቤቦ
ተርጓሚ

# ማውጫ


| | | |
|---|---|---|
| ክፍል አንድ | መግቢያ | 8 |
| I.1 | ቀዳሚ ቃል | 8 |
| I.2 | ዳራ | 9 |
| I.3 | ስለ ስልጠና መምሪያው | 10 |
| I.4 | የስልጠና መምሪያው አጠቃቀም | 11 |
| ክፍል ሁለት | በኢትዮጵያ የሚገኘውን ሽምግልናንና የአመቻች ሽምግልናንን ማዋሃድ | 12 |
| II.1 | በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ሽምግልና ምን ይመስላል? | 13 |
| II.2 | በባህላዊ ሽምግልና እና በአመቻች ሽምግልና መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት | 16 |
| II.3 | የባህላዊ ሽምግልና እና አመቻች ሽምግልና ውህደት | 18 |
| ክፍል ሦስት | የሽምግልና ስልጠና መሣሪያዎች | 19 |
| III.1 | ግጭትን መረዳት | 19 |
| III.1.1 | የግጭት ትርጓሜ | 19 |
| III.1.2 | ተግባር፡ ለግጭት ያለን ዕይታ | 20 |
| III.1.3 | ግላዝል ለግጭት የሰጠው ትርጓሜ | 21 |
| III.2 | ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ለምን አስፈለገ? | 22 |
| III.2.1 | ዓሳ የማስገር ጨዋታ | 23 |
| III.2.2 | ተግባር፡ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ እንዴት መፍጠር እንችላለን? | 29 |
| III.3 | አቋም ፣ ጥቅም ፣ ፍላጎት | 31 |
| III.3.1 | የ1978 እ.ኤ.አ ካምፕ ዴቪድ ስምምነት /በቀላሉ የቀረበ/ | 32 |
| III.3.2 | የብርቱካኑ ምሳሌ | 33 |
| III.3.3 | ተግባር፡ በማንጎ ዛፍ ምሳሌ ውስጥ የሽንኩርት ሞዴልን በመጠቀም አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎትን መተንተን | 35 |
| III.3.4 | የሽምግልና ዛፍ ማማ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን (Grounding Questions) መጠቀም | 37 |
| III.3.5 | ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ከአቋም ወደ ጥቅምና ፍላጎት እንዲሻገሩ መርዳት | 39 |
| III.3.6 | ተግባር፡ መሰላሉ | 42 |
| III.3.7 | የቆሎ ምሳሌ | 43 |
| III.4 | ዕይታን መቀየር | 46 |
| III.4.1 | ተግባር፡ ሶስት ጊዜ ማድመጥ | 47 |
| III.4.2 | ተግባር፡ ሰውና አይጥ | 49 |

| | | |
|---|---|---|
| III.5 | የሽምግልና ሂደት | 51 |
| III.5.1 | የሽምግልና ስነ-ምግባር መርሆች | 51 |
| III.5.2 | ሽምግልና እንዴት ይከናወናል | 53 |
| III.5.3 | የሽምግልና ደረጃዎች | 54 |
| III.6 | ተግባቦት በሽምግልና ሂደት ውስጥ | 56 |
| III.6.1 | ተግባቦት እና የሹልዝ ቮን ዙን አራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴል | 57 |
| III.6.2 | የተግባቦት የተግባር መልመጃ | 60 |
| III.6.3 | በሽምግልና ሂደት ውስጥ የአካላዊ አካላዊ ቋንቋ አስፈላጊነት | 62 |
| III.6.4 | በሽምግልና ሂደት ወቅት ማዳመጥ | 67 |
| III.6.5 | ፈታኝ መልዕክቶችን መጋፈጥ: ንግግርን በራስ አገላለጽ ማቅረብ እና ማጠቃለል | 69 |
| III.7 | የግጭት አተያይ ትንታኔ | 71 |
| III.8 | በግጭቶች መካረር ውስጥ እና በመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ የተናጥል የሽምግልና ሂደት ጠቀሜታ | 76 |
| III.9 | የግጭቶች መካረር ደረጃን መረዳት | 77 |
| III.9.1 | የፍሬዴሪክ ግላስል ዘጠኙን የግጭቶች መካረር ደረጃዎች ማስተዋወቅ | 78 |
| III.9.2 | ተግባር፡ ዘጠኙን ደረጃዎች በናሙና ማሣያ በመጠቀም ወደ ተግባር መቀየር | 79 |
| III.9.3 | ዘጠኙን የግጭቶች መካረር ደረጃዎች ይበልጥ ለመረዳት አማራጭ ተግባራት | 86 |
| III.10 | ለተለያዩ የግጭት ደረጃዎች የተቀረፀ መገላገያ (Intervention) መንገዶች | 88 |
| III.11 | የሽምግልና ቡድንን ማቋቋምና በሽምግልና ቡድን ውስጥ መስራት፡ የግጭት ባለድርሻ አካላትን ማካተት | 92 |
| ክፍል አራት | የአሰለጣጠን ክህሎቶች | 96 |
| IV.1 | ጠቅለል ያለ ምክር ለአሰልጣኞች | 97 |
| IV.2 | በስልጠና ወቅት የሚና-ነጠቃ ጨዋታ ያለው ተግባር | 99 |
| IV.3 | ግብረ-መልስ (Feedback) ለምን ያስፈልጋል እንዴትስ መስጠት ይቻላል? | 101 |
| ክፍል አምስት | ማጣቀሻዎች | 102 |
| ክፍል ስድስት | ስለአዘጋጆቹ | 104 |
| ክፍል ሰባት | እክያ | 107 |
| ሀ | ባህላዊ የግጭት አፈታት መንገዶች በኢትዮጵያ | 107 |
| ለ | የግጭቶች መካረርና ተነፃፃሪ የሽምግልና ዓይነቶቻቸው | 109 |
| ሐ | የሰው እና የአይጥ ምስሎች | 110 |

# ክፍል አንድ መግቢያ

## I.1 ቀዳሚ ቃል

በጂአይዜድ እና በአጋር ድርጅቶች የተሰራው ይህ አስደናቂ ስራ በሰላም ግንባታ ዙሪያ በብሔራዊና በክልል ደረጃ ለሚደረጉ ጥረቶች ለችግሮች መፍትሔ ከመስጠት ባለፈ ግጭቶችን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሻገር ወይንም ለመቀየር ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል። በአለመግባባቶችና በግጭቶች ዙሪያ ከመስራት በፊት አለመግባባቶችና ግጭቶች መኖራቸውን ማመን ያስፈልጋል። ይህ የመጀመሪያው ነገር ነው። በአፍሪካ ግጭቶች ሲፈጠሩ በሰዓቱ መፍትሔ አያገኙም። ምክንያቱም ግጭት የፈጠሩት ወገኖች ግጭት መፈጠሩን አይቀበሉም። ግጭት መፈጠሩን መጠራጠር ወይንም መካድ ነገሩ ስር እንዲሰድ ደግሞም ይበልጥ የከረረ ግጭት ተፈጥሮ ለሽማግሌዎች እንዲከብድ ያደርገዋል።

ይህ መምሪያ ግጭት ምን ያህል የህይወታችን አንዱ አካል መሆኑን ያሳያል። ይህም ማለት ግጭት የተለመደ ፣ ጤነኛ እና ሁሉም አካላት ለችግሩ አጥጋቢ የሆነ መፍትሔ ለማግኘት የሚናፍቁ ንቁ ተሳትፎ ያለው ህብረተሰብ ፣ ማኅበረሰብ ፣ ቤተሰብ ወይም ሌላ ማኅበረሰብ መኖሩን ያሳያል።

በቀድሞ አፍሪካ ባህል ግጭቶች የግለሰብ ግጭት ብቻ እንደሆነ ተደርገው አምብዛም አይታዩም ነበር። ይልቁንም በቤተሰብ ላይ፣ በመንደርተኛው ወይንም በማኅበረሰቡ ላይ ማንኛውም ዓይነት ወንጀል ወይንም ሁከት ቢፈጠር፤ ያ ማኅበረሰብ በአባሉ ላይ የተፈጠረውን ወንጀል ወይንም ሁከት መከላከል አለመቻሉን እንደሚያሳይ ይቆጠር ነበር። ይህም ማለት የማኅበረሰቡ አባል በሆነ አንድ ግለሰብ ብቻ የተፈፀመ ስህተት በፍጥነት የጋራ አንገብጋቢ ችግር ሆኖ ይወሰድ ነበር።

በዛሬይቱ አፍሪካ ግን በከተሞችና በገጠራቱም ከፍል እንደቀደሙት የአባቶቻችንና የእናቶቻችን አኗኗር ዘይቤ መከተል የሩቅ ትዝታ እየሆነ እንደመጣ ይስተዋላል። ይህም ለተለያዩ ተግዳሮቶች አዲስና ፈጠራ የተሞላበት መፍትሔዎችን እንድንፈልግ ያስገድደናል። ግጭት የተለየ ነገር ነው ብለን የምንተወው ጉዳይ አይደለም። ባህላዊ በሆነ መንገድ ሲከናወኑ የቆዩት ሽምግልናዎች ከዘመናዊነት በመነጨ ተግዳሮቶች ሲፈተኑ ቆይተዋል። እነዚህ ማኅበረሰቦች ለውጥን ከመቀበል ውጪ ምንም አማራጭ አልነበራቸውም።

ለዚህም ነው ይህ መምሪያ በተለይ በዚህ ጊዜ በጣም አስፈላጊ የሆነው። ይህ መምሪያ ባህላዊ የሆነውንና ተሞክሮ ያለውን በአዲስና ገና ባልተሞከሩ መፍትሔ መፈለጊያ መንገዶች ከነመከላከያ መንገዶቻቸው በተጨማሪም ከዕርቅ በኋላ ዘላቂና የተረጋጋ ግንኙነት እንዲኖር የሚያስችል ውህደት እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ያሳያል። በዚህ ረገድ የጂአይዜድ የማህኅበረሰብ አቀፍ ሰላም አገልግሎት አጋር የሆነው ኢንሚዶ በርሊን ለዚህ ለተሳካ ስራ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት ይፈልጋል። የዚህ መምሪያ ተጠቃሚ የሁለቱን የሽምግልና መንገዶች ተመሳሳይነት ሊገነዘብ ይችላል። ነገር ግን ግልጽ የሆኑ ልዩነቶች አሉት። ዘመናዊ የሆነው መንገድ ሽማግሌዎች ከማኅበረሰቡ አባል እንዳይሆኑ በማድረግ ገለልተኛ ያደርጋቸዋል። በተጨማሪም ግጭት ለተፈጠረባቸው አካላት ሽማግሌዎችን የመምረጥ መብት ይሰጣቸዋል። በሌላ በኩል ባህላዊው መንገድ ሽማግሌዎች የማኅበረሰቡ አካል እንዲሆኑ፣ ሁለቱንም አካላት የሚያውቁ እናም ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚተዋወቁ እንዲሆኑ ያስገድዳል። እነርሱም የዚያው ማኅበረሰብ ውጤት በመሆናቸው በዚሁ እድሜ ጠገብ በሆነው የሽምግልና ስርዓት የሚኖሩ እና ከዕርቁ በኋላ በሚወሰነው ውሳኔ ተገዥ ስለሚሆኑ ነው።

የዚህ መምሪያ ተጠቃሚ በመምሪያው ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ አማራጭ የግጭት አፈታት መንገዶችና ምክንያቶቻቸው በቀድሞ ጊዜ አፍሪካውያን በባህላዊ መንገድ ግጭቶችን ሲፈቱባቸው የቆዩ እንደነበረ ይገነዘባል። አንዳንድ ጊዜ በዘመናዊ ሽምግልና የተቀመጡት አማራጮች በባህላዊው የአፍሪካውያን ዕርቅ ስርዓት የተለመዱ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህ ለኢትዮጵያውያን ፣ ለአፍሪካውያን ወይንም ፈቃደኛ ለሆነ ማንኛውም አካል ጠቃሚ ተሞክሮዎች የሚያገኙበት እና ዕውቀት የሚጨምርለት ይሆናል።

~ስቴላ ሚስቲካ ሳቢቲ

ስቴላ ሚስቲካ ሳቢቲ የኡጋንዳ ተወላጅ የሆኑ ዝናን ያተረፉ ዓለም አቀፍ የሰላም ግንባታ ባለሙያ እና አቀንቃኝ በመሆን ይሰራሉ። እንደ አፍሪካ ህብረት ላሉ ትላልቅ ድርጅቶች በከፍተኛ ደረጃ የዕርቅ ስራዎችን በተሳካ መልኩ ያከናወኑና በሰላም ግንባታው ትልቅ ተሳትፎ በማድረግ የታወቁ ናቸው።

## 1.2 ጸሯ

የጂ አይ ዜድ የሲቪል ሰላም አገልግሎት እ.ኤ.አ ከ2008 ጀምሮ በኢትዮጵያ በስፋት እየሠራ ይገኛል። የዚህ አገልግሎት ዓላማ በፌዴራል ፣ በክልሎችና ወደታች ባሉ መዋቅሮች የሚገኙትን ባለድርሻ አካላት አቅም በማጎልበት በኢትዮጵያ የተከሰቱትን ወይንም ሊከሰቱ የሚችሉትን ግጭቶች በሰዓቱና በተቀናጀ መልኩ እንዲሁም ዘላቂ መፍትሔ እንዲያገኙ በትጋት ይሠራል። ይህ አገልግሎት በሰላም ግንባታ ዙሪያ ከሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየሠራ ይገኛል። እነዚህ ተባባሪ ድርጅቶች በሰላም ግንባታ እና ግጭቶችን በመፍታት ዙሪያ የራሳቸው የሆነ ኃላፊነት ቢኖራቸውም ሽምግልናው የተሳካ ሲሆን ሁሉንም ተጠቃሚ ከማድረግ ባሻገር ኃላፊነታቸውን በተገቢው መልኩ እንዲወጡ ይረዳል። በተጨማሪም አገር በቀል የሆኑ የሽምግልና መንገዶች በኢትዮጵያውያን መካከል (በተለይም በባህላዊ ተቋማት) የሚፈለጉ እና በስፋት የተለመዱ ከመሆናቸው አንፃር እንደ አማራጭ የሙግት መፍቻ መንገዶች ሆነው ያገለግላሉ።

ከእነዚህ አጋር ድርጅቶችና ማኅበረሰቡን ከሚወክሉ ሌሎች አካላት በቀረበለት ጥያቄ መሠረት የጂ አይ ዜድ የሲቪል ሰላም አገልግሎት ከአጋሩ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት እና ከኢንሚዲኦ በርሊን ፅንስ-ሃሳቡን አምጥተው ካስተባበሩት ከሉቢያና ሹስቴሁቤ እና ከዴርክ ስፕሊንተር ጋር በመተባባር ጠንከር ያለ የሽምግልና ባለሙያነት ማረጋገጫ ስልጠና አዘጋጅቷል።[1]

የጂ አይ ዜድ የሲቪል ሰላም አገልግሎት ፣ አጋር ድርጅቶች እና የሽምግልና ባለሙያነት ስልጠና የወሰዱ ተሳታፊዎች የጋራ ዓላማ ነባሩን የሽምግልና ስርዓት ማጠናከርና አዲስ የሽምግልና ስርዓትን ለማጎልበት ብቻ አይደለም። ነገር ግን ነባሩን ሽምግልና እና የምዕራባዊያኑን አመቻች የሽምግልና መንገዶች በማዋሃድ አገር በቀሉን የግጭት አፈታት መንገዶች ለማበረታታት ነው።

የሽምግልና ማረጋገጫ ስልጠና በሚሰጥበት ወቅት ተሳታፊዎች "ባህላዊ" የሚለውን እና "ዘመናዊ የምዕራባውያን መንገድ" የሚለውን መጠሪያዎች ቃላቱ ሊፈጥሩት ከሚችሉት አሉታዊ ትርጉም የተነሳ "ባህላዊ ሽምግልና" እና "አመቻች ሽምግልና" በሚሉ ቃላት ቀይረዋቸዋል። "ባህላዊ ሽምግልና" (wise-council mediation) የሚለው መጠሪያ በናዲያ አሌክሳንደር[2] የተጻፈው "Mediation Meta-Model" በሚለው መጽሐፍ እንደ ሳይንሳዊ መጠሪያ የተቀመጠ ሲሆን በዚህ መምሪያ ውስጥ ግን አገር በቀል የሆኑትን የሽምግልና መንገዶችን[3] ያመለክታል። በተመሳሳይ መልኩ ምዕራባዊያን በሰፊው የሚጠቀሙበትን የሽምግልና መንገድ ለማመልከት "አመቻች ሽምግልና" ተብሎ ተተርጉሟል።

1 በሽምግልና ባለሙያነት ማረጋገጫ ስልጠና ወቅት የተገኙትን ልምዶች ማጠቃለያ ከፈለጉ Roos. C; Splinter, D & Wüstehube, L (2011) ይመልከቱ።

2 Alexander, N (2011)

3 በእንግሊዘኛው "wise counsel" የሚለው ቃል በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሽምግልና አይነት አይገልጸውም። ይህ ዓይነት ሽምግልና በድርድሩ መጨረሻ ውሳኔውን ለተጋጭ ወገኖች የሚያስቀር ሲሆን በኢትዮጵያ የሚገኘው የሽምግልና አይነት ግን ውሳኔ ሰጪ ነው። ቢሆንም ግን ይህ ሳይንሳዊ ቃል በተለይም በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሽምግልና ዓይነት ባህሪያት ስላለው አገር በቀሉን የሽምግልና አይነት ሊወክል ይችላል።

## 1.3 ስለ ስልጠና መምሪያው

*ይህ መምሪያ የተዘጋጀው የሽምግልና አመቻች ባለሙያ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ስብስብ ነው። እነዚህ ባለሙያዎች የሽምግልና ባለሙያነት ብቃት ማረጋገጫ /በጠቅላላው 177 ሰዓታት የፈጀ/[4] ስልጠና የወሰዱ ናቸው። ለሰልጣኞቹ እንደ መርጃ መሳሪያ የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም ስለአመቻች ሽምግልናና ስለሽምግልና ጥልቅና ተግባራዊ ዕውቀት አግኝተው በኢትዮጵያ የሽምግልና ሂደት ላይ ተጨባጭ ክህሎት እንዲጨምሩ በመርዳት አስተዋፅዎ ማድረግ ነው። ከዚህ የተነሳ በሽምግልና እና በአመቻች ሽምግልና እንዲሁም በውህደታቸው ላይ ምናባዊ ግብዓቶች እና ከሽምግልና ጋር የተያያዘ ተግባራዊ ልምምዶችንና ዕውቀቶችን ያቀርባል።*

*መመሪያው በተለያየ ደረጃ በግጭት አፈታት ዙሪያና በሰላም ግንባታው ላይ ተሳታፊ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን ማዕከል ያደረገ ነው። ይህም ማለት መንግስታዊውና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ፣ ያገር ሽማግሌዎችን፣ ምሁራንን እና ልዩ ልዩ ማዕከላትን ያጠቃልላል። ምንም እንኳ በኢትዮጵያ የሽምግልና ስርዓት ላይ ትኩረት ያደረገ ቢሆንም ለሌሎች ሃገራት ወይንም ባህሎች "አዲስና መጤ" የሆነውን የግጭት አፈታት መንገድ ከተለመደው ጋር ለማዋሃድ እንዴት መስራት እንደሚቻል እንደማሳያ ይጠቅማል።*

*"...ሃሳቡ የፈለቀው ከተለያዩ የሽምግልና ዓይነቶች ጋር እየተዋወቅን ስንመጣ እና እነዚህን ስርዓቶች አጣምረን መስራት በምንፈልግበት ጊዜ ነው። እኔ ራሴ በአውሮፓ ጠንካራና በጣም የሚያነሳሳ የሽምግልና ባለሙያነት ብቃት ማረጋገጫ ስልጠና ወስጃለሁ። ስለዚህ በኢትዮጵያ ገጠራማ አካባቢዎች የተለመዱትን የሽምግልና ዓይነቶች በአውሮፓ ታዋቂ ከሆነው ከአመቻች ሽምግልና ጋር በማዋሃድ ተግባራዊ ሲሆን ማየት ትልቅ ፍላጎት አለኝ። ስለዚህ ይህ ሙከራ ጠቃሚና ተግባራዊ ነበር ማለት እችላለሁ።"*

ክላውዲያ ሩስ ፣ በጂ አይ ዜድ ኢትዮጵያ የመሳሪያዎችና የክሮስከቲንግ ኃላፊ፣ የሲቪል ሰላም አገልግሎት አስተባባሪ (2007-2012)

---

4 በጀርመን ሃገር እ.ኤ.አ. ከሐምሌ 26, 2012 ተግባራዊ መሆን በጀመረው "Act for the Promotion of Mediation and other Procedures of Extrajudicial Conflict Settlement"(Gesetz zur Förderung der Mediation und anderer Verfahren der außergerichtlichen Konfliktbeilegung) መሠረት ፈቃድ ያለው የሽምግልና ባለሙያ/አደራዳሪ/ ለመሆን ቢያንስ የ120 ሰዓታት ስልጠና ያስፈልጋል። http://kluwermediationblog.com/2012/01/09/new-german-mediation-law-passed-in-the-bundestag/. እንደ ጀርመን የሽምጋዮዎች ማህበር (Bundesmediationsverband) መሠረት ከሆነ ደግሞ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የ200 ሰዓታት ስልጠና ያስፈልጋል። (www.bmev.de)

## 1.4 የስልጠና መምሪያው አጠቃቀም

ይህ የስልጠና መምሪያ በግጭት አፈታት ዙሪያ አሳታፊ ስልጠና ለሚሰጡ ሁሉ የተዘጋጀ ነው። ቢሆንም ግን የዚህ መምሪያ ጠቃሚነት ስልጠና ለሚወስዱ ብቻ አይደለም። ሽምግልናን ለማጎልበት ለሚፈልጉ ሰዎች ወይንም ድርጅቶች እንደስራ መመሪያ ወይንም እንደ ዋቢ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

ይህን መምሪያ በአካባቢ ቋንቋ ተተርጉሞም ሆነ ሳይተረጎም በተለይ በኢትዮጵያ ውስጥ መጠቀም ተጨባጭ ለውጥን እንደሚያመጣ ይታመናል። ይዘቱ ተግባር ላይ ያተኮረ በመሆኑ ተሳታፊዎች የተግባር ልምምድ በማድረግ የትምህርቱን ሂደት ይመራሉ። ምንም እንኳ ተሳታፊዎች የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩና ከተለያየ ቦታዎች ቢመጡም የዚህ ስልጠና መምሪያ አቀራረብ ንድፈ ሃሳቦችን ከነባራዊ ህይወት ፣ ከሁኔታዎች ፣ ነገረ ጉዳዮች እና ከግል ተሞክሮ ጋር ያቆራኘ በመሆኑ የትምህርቱን ሂደት አመቺ ያደርገዋል።

አሳታፊ የሆኑ ትምህርታዊ ጨዋታዎች በዚህ መምሪያ ውስጥ ቁልፍ ሚና አላቸው። ብዙ ሰዎች ጨዋታ ይወዳሉ። ነገር ግን ጨዋታን ባቀፈ የትምህርት ሂደት ውስጥ ሰዎች የራሳቸው የተለያየ ፍላጎትና ተሳትፎ አላቸው። ስለዚህም አሰልጣኙ አሳታፊ የሆኑ ትምህርታዊ ጨዋታዎችን በሚመርጥበት ጊዜ ጥንቃቄ በተሞላ መልኩ ሊሆን ይገባዋል። ይህ ማለት ከአካባቢው አኗኗርና ልምድ በመነሳት ፆታን፣ ዕድሜን፣ ማህበራዊ እሴቶችን እና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነታቸውን ያገናዘበ በተጨማሪም የተሳታፊዎችን የልምድ ፣ የአስተሳሰብና የምርጫ ደረጃ ታሳቢ ያደረገ መሆን ይገባዋል። በአጠቃላይ በዚህ መመሪያ የተካተቱት ጨዋታዎችና ልምምዶች በኢትዮጵያ ውስጥ ተስማሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሙከራ ተደርጎባቸዋል።

አሰልጣኙ በመምሪያው ውስጥ ያልተካተቱ ነጥቦች እና ማስተማሪያዎች ካሉ ተጨማሪ ማብራሪያ ትምህርት ማዘጋጀት ይችላል። እንዲሁም አሰልጣኙ የሽምግልናን ሂደት የሚያሳዩ እንደ ጭውውት የመሳሰሉ ወይንም ሌሎች መረጃዎችን ሊጠቀም ይችላል። ተጨማሪ መርጃዎች በሚጠቀምበት ጊዜ ከትምህርቱ ጋር ተዛማጅ የሆኑ፣ ተሳታፊዎች በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉና ጊዜን ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል።

በአጠቃላይ ይህ ሰነድ ከተጠቃሚው ጋር ተስማሚ ሆኖ የተዘጋጀ ነው። የዚህ መምሪያ ዓላማ የሽምግልና ክህሎትን ቀላል ፣ ተግባራዊ እና ተጨባጭ በሆነ መልኩ እንዲቀርብ የታሰበ በመሆኑ ምሁራዊ (academic) ውይይቶችና ጥልቅ ትንተናዎች በዚህ መምሪያ እንዳይካተቱ ተደርገዋል። የዚህ መመሪያ አጠቃቀም የተሳካ እንዲሆን አሰልጣኙ በሽምግልና የስልጠና ልምድ ያለው ቢሆን ተመራጭ ነው።

ይህ መምሪያ የተዘጋጀው የሽምግልናን ክህሎት ለማሠልጠን ሲሆን ሁሉንም ተግባሮች ለማጠናቀቅ ሁለት ሳምንት ይፈጃል። ቢሆንም ግን ይህ መምሪያ አሰልጣኙ ለአካባቢውና ለተደራሽ አካላት ተስማሚ ይሆናል ብሎ ባሰበው መንገድ እንደ “ሰነዶች - ስብስብ” ሆኖ እያገለገለ አካሄድንና የተግባር መልመጃዎቹን እንደአስፈላጊነቱ እየመረጠ ሊጠቀምበት ይችላል። የዚህም ምክንያት እያንዳንዱ ስልጠና የተደራሽ አካላትን ፍላጎት በሚያሟላ መልኩ መዘጋጀት ስላለበት ነው። ስለዚህም የስልጠናው አካሄድና መልመጃዎቹ ይህን ያገናዘቡ በመሆናቸው ስልጠናው በዚህ መልኩ ቢዘጋጅ የተደራሽ አካላትን ጥቅም ያስጠብቃል ተብሎ የተዘጋጀ ቢሆንም እንደአስፈላጊነቱ ሊቀየር ይችላል።

ይህ ሰነድ ስድስት ክፍሎች አሉት። ክፍል አንድ. ቀዳሚ ቃልና ዳራ (Background) ያካትታል። በመቀጠል ክፍል ሁለት. ትኩረት የሚሰጠው የባህላዊ ሽምግልናን እና የአመቻች ሽምግልናን ውህደት ታሪክና ፅንሰ ሃሳብን ሲሆን ከዚያም ያላቸውን ተመሳሳይነት፣ ልዩነትና የጋራ ውጤታቸውን ያካትታል። ክፍል ሦስት. የዚህ መምሪያ ዋና ክፍል ሲሆን በዚህ ክፍል ግጭትን መረዳት፣ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርጉ የመፍትሔ መርሆዎች፣ አመለካከትንን መቀየር ፣ የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች (grounding questions) አስፈላጊነት፣ እንዲሁም አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት የመሳሰሉት የሽምግልና አንኳር ጉዳዮች ይነሳሉ። በተጨማሪም የሽምግልና ሂደትና ባህሪያትን ይዳሰሳሉ።

ይህ የስልጠና መምሪያ እንደመሆኑ መጠን ክፍል አራት. ለሽምግልና የሚያስፈልጉ ጠቅላላ ክህሎቶች ይጠቀሳሉ፤ ዋቢ ማጣቀሻዎች (ክፍል አራት) እና ምስጋና (ክፍል አምስት) ይቀጥላሉ። በመጨረሻም አባሪዎች (ክፍል ስድስት) ተጠቃለውበታል።

የዚህ ስልጠና መምሪያ ተጠቃሚዎች እገዛ በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ ከአዘጋጆች፣ ከጂ አይ ዜድ የሲቪል ሰላም አገልግሎት እና ከኢንሚዲአ በርሊን ጋር ግንኙነት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህን ሰነድ ለተጠቃሚዎች ጠቃሚና ምቹ እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን። ይህን መምሪያ ለሚጠቀሙ ሁሉ ውጤታማ ስራን እንመኛለን!

# ክፍል ሁለት  በኢትዮጵያ የሚገኘውን ሽምግልና እና የአመቻች ሽምግልናን ማዋሃድ

| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች በተዋኸደው የባህላዊ ሽምግልና እና የአመቻች ሽምግልና ላይ ጥልቅ የሆነ ግንዛቤን ያገኛሉ። ይህም የዚህ የስልጠና መምሪያ ዋና አካል ሆኖ ያገለግላል። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 90 ደቂቃ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት (Flipchart) ፣ ማርከሮች ፣ በልዩ ልዩ ቅርፅ የተዘጋጁ ባለቀለም ካርዶች፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳዎች ፣ ስፒሎች ፣ ፕላስተሮች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1፡ ፡ ክፍል  II.1 በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ሽምግልና ምን ይመስላል? የሚለውን ርዕስ አስተዋውቅ። |
| | ደረጃ 2: አገር በቀል የሆኑትን ግጭት አፈታት መንገዶች በተለይም በሽምግልና ውስጥ ያላቸውን ሚና እንዴት እንደሚመለከቱት ተሳታፊዎቹን ጠይቃቸው። ጠንካራ ጎናቸው ምንድን ነው? ውስንነታቸውስ? የአመቻች ሽምግልና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ደካማ ጎን ምንድን ነው? |
| | ደረጃ 3: ክፍል II.2: በሽምግልና እና በአመቻች ሽምግልና መካከል ያለ አንድነት እና ልዩነት የሚለውን ርዕስ አስተዋውቅ። ከዚያም ጥያቄና ውይይት አድርግ። |
| | ደረጃ 4: ክፍል II.3: የሽምግልና እና የአመቻች ሽምግልና ውህደት የሚለውን ርዕስ አስተዋውቅ ከዚያም ጥያቄና ውይይት አድርግ። |

## II.1 በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው ሽምግልና ምን ይመስላል?

ግጭት ሰዎች ባሉበት ቦታ ሁሉ ይኖራል። በቤተሰብ፣ በማኅበረሰብ፣ በብሔረሰቦች፣ በተቋማት ወይም በስራ ግንኙነታችን መካከል ሁሉ ይከሰታል። ስለዚህም ከዕለት ኑሮአችን ጋር የማይነጣጠል ነው ማለት እንችላለን። ለግጭት አለም አቀፋዊ ትርጓሜ ባይኖረውም እንዲህ ብለን ልንተረጉመው እንችላለን፡ “የማይጣጣም ግብ ያላቸው ወይንም አለን ብለው በሚያስቡ ሁለት ወይንም ከዚያ በላይ በሆኑ ወገኖች መካከል ያለ ግንኙነት ነው።”[5]

ግጭት አዲስ ክስተት ይዞ ሊመጣ ስለሚችል እንደ ጠቃሚ ሂደት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል። ቢሆንም ግን አንዳንድ ጊዜ ተጋጭ አካላት የተቆላለፈና የማይፈታ ሁኔታ ውስጥ ገብተው የመውጪያ ቀዳዳ ላይታያቸው ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ እንዲገባ መጋበዝ ይቻላል። ይህም “የሶስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት” ልንለው እንችላለን። ይህን ማድረግ ለተጋጭ አካላትና ለሌሎች ባለድርሻ አካላት ፍላጎታቸውን ለማስጠበቅ ይረዳል።

በህጋዊ መንገድም ሆነ በአማራጭ መንገዶች የሚካሄዱ የግጭት አፈታት ስርዓቶች በሁሉም ባህልና ማኅበረሰቦች ውስጥ ለእድገትና ለውጥ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው። በህጋዊ መንገድ የሚከናወኑትን ብንመለከት የሽምግልና ሂደቱ ከግለሰብ እና ከበጎ ፈቃደኞች ወደ ህዝብ ተቋማት ተሸጋግረዋል። ይህም ሶስተኛው ወገን እንደ እገዳ የመሳሰሉትን ፅኑ ውሳኔዎች ማሳለፍ የሚችልበትን መንገድ ከፍቷል። ነገር ግን አማራጭ የግጭት አፈታት መንገዶች (ADR) በተለይም ሽምግልና በተሻለ መልኩ በበጎ ፈቃድ እንዲከናወን ያበረታታል።

አገር እንደ መንግሥት እየተዋቀረ ሲመጣ እንደ ፍርድ ቤት የመሳሰሉ ህጋዊ ግጭትን መፍቻ መንገዶች ጎልተው መውጣት ጀመሩ። መንግስታት የቀድሞውን (በተለምዶ የሚከናወኑና ማኅበረሰቡ የፈጠራቸውን ወይንም በኃይማኖት ስርዓት የተፈጠሩ የግጭት አፈታት መንገዶችን) በተለያየ ምክንያት ህጋዊ ለማድረግ ጥሯል። በአፍሪካና በእስያ ክፍለ-አህጉራት “አገር-በቀል” የሚባለውን የግጭት የመፍቻ መንገዶች እና ስርዓቶቻቸውን ጠብቀው ሲቆዩ በምዕራባዊያን ማኅበረሰቦች መካከል ግን ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች የተረሱ ይመስላሉ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን አማራጭ የግጭት አፈታት መንገዶች በተለይም ሽምግልናን እንደገና መተግበር ጀምረዋል። ዛሬ ሽማግሌዎች በተለያዩ ዓይነት ግጭት ውስጥ በቤተሰብ፣ በንግድ እንዲሁም በአለም አቀፍ ማኅበረሰብ መካከል ከፍተኛ ተሳትፎ እያደረጉ ይገኛሉ። የሽምግልናና የሽምጋዮች ዓላማ እና ሚና ባህልን እና ሁኔታዎችን ያገናዘበ ከመሆኑ የተነሳ ሽምግልና በልዩ ልዩ መንገድ ትርጓሜ ሊሰጠው ይችላል።

### የማመቻቸትና የማቀራረብ ሽምግልና
### (Facilitative and Transformative Mediation)

ዘመናዊ ወይንም አንዳንዶች እንደሚሉት የምዕራባዊያን ሽምግልና ገለልተኛ የሆነ ሰው ጣልቃ በመግባት ተጋጭ አካላት ውይይትና ድርድር እንዲያደርጉ በማበረታታት ግጭትን የሚፈቱበት መንገድ ነው። መፍትሔው የሚወሰነው ተጋጭ አካላት በሚያደርጉት የጋራ ስምምነት ነው።[6] የዚህም ዓላማ ሁለቱም አካላት በመፍትሔ አፈላለግ እንዲሁም በራሱ በመፍትሔው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ታስቦ ነው። ይህ ሂደት የአመቻች ሽምግልና (Facilitative Mediation) በመባል ይታወቃል። ይህም የተባለበት ሶስተኛው ወገን ሁለቱን አካላት ማደራደር እንጂ ውጤቱ በተጋጭ አካላት መካከል በራሳቸው የሚደረግ ውሳኔ በመሆኑ ነው። የዚህ ዓይነቱ የግጭት አፈታት ዘዴ የመጣው ሰዎች በህጋዊ መንገድ ማለትም በፍርድ ቤት በሚከናወነው የግጭት አፈታት ዘዴ እርካታን በማጣታቸው ነው። በአብዛኛው ምዕራባውያን ሀገራት የሚጠቀሙት ሽምግልና አቀራራቢ የሆኑ መሠረታዊ ነገሮች አሉበት። የማቀራረብ ሽምግልና (Transformative Mediation) ትኩረት ከሚሠጥባቸው ነገሮች ውስጥ በተጋጭ ወገኖች መካከል መግባባት እና መተሳሰብ እንዲሁም ግንኙነታቸውን ወደተሻለ ደረጃ ማሻገር ሲሆን በሽምጋዩ ውጤት ላይ ብቻ አያተኩርም።[7]

### ባህላዊ ሽምግልና

የሀገር ሽማግሌዎች በብዙ የአፍሪካ ባህሎች በማኅበረሰቡ ውስጥ በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ ግጭትን በመፍታት ጭምር ውሳኔ በመስጠት ዋና ተዋናይ ናቸው። በማኅበረሰቡ ዘንድ በመፍትሔ ሰጪነታቸው ይመደባሉ። ጥሩ አድማጭ፣ ጥሩ ውሳኔ ሰጪ እና በሁኔታዎች ልምድን ያካበቱ ተደርገው ይወሰዳሉ። ሽማግሌዎች ትላልቅ ውሳኔዎችን ማስተላለፍ በመቻላቸው እንዲሁም ሁለቱንም ወገኖች በመወከል ውሳኔ ሰጪ በመሆናቸው ከህጋዊ ዳኝነት የተለየ አያደርጋቸውም። ስምምነቱን ወይንም ውሳኔውን በማያከብረው ወገን ላይ እገዳን እስከመጣል ስልጣን አላቸው።

ሽማግሌዎች የሰለጠኑ የሽምግልና ባለሙያ አይደሉም። ከተጋጭ አካላት ጋር በጉርብትና፣ በዝምድና ወይንም የማኅበረሰቡ አካል በመሆናቸው የማኅበረሰቡ ባለድርሻ አካላት ያደርጋቸዋል። ከዚህ የተነሳ የተወሰኑትን ስምምነቶች በመከታተል የድህረ-ዕርቅ ግንኙነቶች እንዲሻሻሉ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋሉ።

ሽምጋዮች መሠረታዊ የሆነው የማኅበረሰቡ ስርዓት እንዲጠበቅ ሰላም እንዲሰፍን ይጓጓሉ። ከዚህ የተነሳ ለወጣቱ ትውልድ አዳዲስ ፍላጎቶች እና

5 Mitchell, C (1989)

6 Chris Moore (2003) ከሰጠው ፍቺ ጋር ያነጻጽሩ “የሽምግልናን ጠቅለል አድርገን ስንተረጉመው ተጋጭ አካላት የተቀበሉት ውስን ወይንም ምንም ዓይነት የውሳኔ ሰጪነት ስልጣን የሌለው ነገር ግን በግጭቱ ወይንም በድርድሩ በመግባት በበጎ ፈቃደኝነት ለግጭቱ በጋራ የሚቀበሉትን መፍትሔ እንዲያመጡ የሚረዳ ሂደት ማለት ነው”።

7 Bush, B. R. A. & Folger, J. P. (1994)

ለሴቶች እኩልነት የሚያደርጉት ሚና እንደ ደካማ ጎን ሊወሰድ ይችላል። ከዚህ ውስንነት በስተቀር ባህላዊ ሽምግልና በማኅበረሰቡ ውስጥና በማኅበረሰቡ መካከል ያሉትን ግጭቶችና አለመግባባቶች ለመፍታት የጎላ ሚና ይጫወታል።

ኢትዮጵያ ከዘመናት ጀምሮ ለማንኛውም ግጭት እንዲሁም በከፍተኛ ፖለቲካዊ ደረጃም ጭምር ሽምግልናን እየተጠቀመች ትገኛለች።[8] በአገሪቱ የብሔር ብሔረሰቦች ስብጥር በመኖሩና ካሉት የተለያዩ ባህሎች የተነሳ ልዩ ልዩ የሽምግልና መንገዶች እንዲገኙ ምክንያት ሆኗል።

የአገር በቀል ግጭት አፈታት መንገዶች በማኅበረሰቡ ውስጥ የጋራ ስምምነት እንዲፈጠርና ዕርቅ እንዲወርድ የሚያደርጉት ጥረት ተመሳሳይ ባህሪ እንዲኖራቸው ያደርጋቸዋል። ለሽምግልና አስፈላጊ የምንላቸው ነገሮች በነዚህ ስርዓቶች ውስጥ ይገኛሉ። አመቻች ሽምግልና የሚያተኩረው በግለሰቦች ላይ ሲሆን በኢትዮጵያ የሚገኘው ባህላዊ ሽምግልና ግን በቡድኖች ላይ ያተኩራል። ይህ ግጭት አፈታት ሰላም እና ብልፅግናን በማኅበረሰቡ ላይ እንዲመጣ ተሃድሶን በመፍጠር ላይ ያተኩራል።

በአፍሪካ የሚገኙት አገር በቀል የግጭት አፈታት መንገዶች በአጠቃላይ ከማኅበረሰቡ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ አኗኗር ሁኔታ ጋር የተቆራኙ ናቸው። "እነዚህ የአፈታት መንገዶች በአፍሪካ ህዝቦች ባህልና ታሪክ ውስጥ የተተከሉ እንዲሁም ለእያንዳንዱ ማኅበረሰብ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ የተለያየ ሆነው ስርዓታቸውን ለማስጠበቅ በማኅበረሰቡ ደህንነት ላይ የተመሠረቱ ናቸው።"[9]

በየአካባቢው የሚገኙት ድርድር የተካተተባቸው የግጭት አፈታት መንገዶች የእያንዳንዱን ማኅበረሰብ ፍላጎት ስለሚያካትት ሁሉንም ወገኖች ተጠቃሚ ወደሚያደርግ መፍትሔ ያመራሉ። የተጋጩት ወገኖች ከሽምግልናው በኋላ የሚያገኙት ነገር እንዳለ ሁሉ የሚያጡትንም በፀጋ ይቀበላሉ። በተለይም የጎሳ ግጭት ሲከሰት የመንግሥት ህጋዊ አካላት ለአካባቢው ሽማግሌዎች የዕርቁን ሂደት እንዲያከናውኑ ድጋፍ ሰጪ ተደርገው ይወሰዳሉ። በኢትዮጵያ እንዲሁም በሌሎች የአፍሪካ አገራት የተፈጠሩ ወይንም ሊፈጠሩ የሚችሉትን ግጭቶች የሚረዷቸው እንደየ ማህበረሰቡ ሁኔታ ይወሰናል። ይህም ማለት እንደአካባቢው ልማድ ፣ እሴቶችና እምነቶች ፣ ፍርሃትና ጥርጣሬ ፣ ፍላጎትና ጥቅም ፣ ዝንባሌና ድርጊት እንዲሁም ግንኙነትና ትስስር መሠረት ያደረገ ነው።[10]

በኢትዮጵያ ከሚታወቁት የግጭት አፈታት መንገዶች ውስጥ በጉራጌ ኪቻ፣ በጋምቤላ አኝዋ አኩድሆ፣ በኦሮሞ ገዳ፣ በአፋር ሚዳ[11] እንዲሁም በአማራ ሽምግልና ተጠቃሽ ናቸው።

አገር በቀል ስርዓቶች እና የመንግሥት አካላት አብዛኛውን ጊዜ በትብብርና በመቀናጀት አብረው ይሰራሉ። ጠንካራ የጎሳ ግጭት በሚከሰትበት ጊዜ ሰላምን ለማውረድ ውጤታማ መንገዶችን በማምጣት ይረዳሉ። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ መፍትሔ ለማምጣት ሲባል የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ሊከሰቱ ይችላሉ። መንግሥት አገር በቀል የሆነውን የሽምግልና ዘዴ የሚያግዘው በአካባቢው የተከሰተውን ከፍተኛ ግጭት ለማብረድ ቢሆንም በዚህ ሂደት ለሰብዓዊ መብት ያላቸውን አመለካከት ይቆጣጠራል/ይቃኛል።

ኢትዮጵያ በዘመናዊ የህግ አሠራሮቿ ውስጥ ለድርድር እድል ትሠጣለች። ይህም የሽምግልናው ሂደት ተጠናቆ ተጋጭ አካላት ራሳቸው ውሳኔ እስኪሰጡበት ዳኞች የመስማሚያ ውሳኔ እንዳይሠጡ የሚያደርግ ነው። የድርድር አማራጮች በ1960ዓ.ም በታተመው ፍትሐ ብሔር ውስጥ ተካተዋል። በንግድ እና በቤተሰብ ህግ ዙሪያ የሚሰሩ የህግ ባለሙያዎች ይህንን ህግ ይጠቀሙበታል። ግጭትን ለመፍታት፣ ለመሸምገል፣ ለህግ ባለሙያዎችና በከተማ ውስጥ ለሚከሰቱ ግጭቶች ሽምግልናን እንደ ህጋዊ መሣሪያነት መጠቀም የተለመደ ነው።

ከላይ እንደተመለከትነው ሽምግልና በኢትዮጵያ ከሚገኙ አገር-በቀል የግጭት መፍቻ መንገዶች ከፍተኛ ድርሻ ይዟል። ከአመቻች ሽምግልና ጋር አዋህደን ከመመልከታችን በፊት ያላቸውን አንድነትና ልዩነትን በዝርዝር እንመለከታለን።

8 Alexander, Nadja (2011)
9 Rabar, B & Karimi, M (2004)
10 Malan, J (1997)
11 በኢትዮጵያ ስለሚገኙት አገር በቀል የግጭት አፈታት መንገዶች የበለጠ ለማወቅ በገጽ 107 ላይ እኪያዎችን ይመልከቱ።

“በሽምግልና ወቅት ዋና ትኩረታችን የተጋጭ አካላትን ችግር ፣ ጥቅምና ፍላጎትን መስማት ነው። ይህን ካደረግን በኋላ ሰላም የሚፈጥሩበትን መንገዶች መምከር እንጀምራለን። የአመቻች ሽምግልናን በመማሬ እንዲሁም ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ በመረዳቴ ተጋጭ አካላት ወደ ሰላም እንዲመጡና የጋራ መግባባት ላይ እንዲደርሱ ረድቶኛል።”

ካላ ገዛኸኝ ወልደዳዊት፤ በኮንሶ የሃገር ሽማግሌና መንፈሳዊ መሪ

## II.2 የባህላዊ ሽምግልና እና የአመቻች ሽምግልና አንድነትና ልዩነት

# አንድነታቸው

- ሁለቱም ሶስተኛ ወገንን ያካትታሉ።
- የመጨረሻው መፍትሔ ሁለቱንም እኩል ተጠቃሚ ማድረግ ነው።
- ሁለቱም በተጋጮች መካከል ሰላምን ለማስፈን ይተጋሉ።

# ልዩነቶቻቸው

### ባህላዊ ሽምግልና

- ሽምጋዮች በማኅበረሰቡ ዘንድ የተከበሩና የዕድሜ ባለፀጋ ናቸው።
- ሽምጋዮች በራስ ተነሳሽነት ሽምግልናውን ሊያከናውኑ ይችላሉ። እንዲሁም ሀሳብ ሰጪዎችና ውሳኔ ሰጪ ናቸው።
- ሽምጋዮች በተናጥል የሚያደርጉት ውይይቶች የመፍትሄው ዋና አካል ተደርገው ይወሰዳሉ።[12]
- የሽምግልና ሂደቱ በአብዛኛው ዕውነታን በመፈለግ ላይ የተመሠረተ ነው።
- ስምምነቶችን ለመግለፅና እንደ መጨባበጥ፣ አብሮ ማዕድ መቁረስ ወይንም መተቃቀፍ ደግሞም እንደ እርድ የመሣሰሉ ምሳሌያዊ ተግባራት አስፈላጊ ናቸው።

### አመቻች ሽምግልና

- ሽምጋዮች ከማህበሩ ውጪ የሆኑና በሙያው የሠለጡኑ ናቸው።
- ሽምጋዮች የሽምግልና ሂደቱን ያበረታታሉ። ተጋጭ አካላት የራሳቸውን የመፍትሔ ሃሳብ እንዲያፈልቁ ያግዛሉ።
- በተናጥል የሚደረጉ ስብሰባዎች ለመዘጋጀነት ብቻ ሲጠቅሙ በጋራ የሚደረጉ ስብሰባዎች ግን ዓላማው ተጋጭ አካላት ተቀራርበው ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን እንዲወያዩ በመሆኑ ተመራጭ ናቸው። የመፍትሄው ዋና አካል ግን ተጋጭ አካላት አመለካከታቸውን ለመቀየር ባላቸው ችሎታ ይወሰናል።
- ሽምግልናው የሚከናወነው ጥቅምን፣ ፍላጎትንና ስጋትን ፈልጎ በማግኘት  ላይ በመሆኑ በአመለካከታቸው የተወሰነ (Subjective Perception) እንጂ ሁሉም የሚቀበለውን እውነት (Objective Truth) በመፈለግ ላይ የተመሰረተ አይደለም።
- የሽምግልናው ሂደት የተለያዩ የሽምግልና ዘዴዎችና ደረጃዎች ሲኖሩት ስምምነቶች በጽሑፍ ውል ይፀናሉ።

12 በተናጥል የሚደረጉ ውይይቶች ሽምጋዩ ተጋጭ ወገኖችን በተናጥል ያነጋግሯቸዋል። ይህም ተጋጭ አካላት ፊት ለፊት ተቀምጠው ለመነጋገር ገና ያልተዘጋጁ እንደሆን ነው። በገጽ 76 ላይ ክፍል III. 8. በግጭቶች መካረር ውስጥ እና በመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ የተናጥል ሽምግልና ጠቀሜታ የሚለውን ይመልከቱ።

# በተጨማሪም

- በባህላዊ ሽምግልና ሽምጋዮች የተጋጭ አካላትን ትኩረት ለመሳብና ያላቸውን አክብሮት ለመግለጽ ባህላዊ እሴቶችንና አካላዊ ቋንቋዎችን ይጠቀማሉ። ገለልተኝነትን ለማሳየት፣ ትኩረትን ለመሳብ እንዲሁም ጥልቅ ስሜትን ለመግለፅ ንግግር ሳይጠቀሙ ግንኙነት ያደርጋሉ። በአመቻች ሽምግልና ሽምጋዩ ንግግሩን እንዲደግፍለትና ከተጋጮች ጋር ያለውን ትኩረት ለማስጠበቅ ይቀጠምበታል።[13]
- በንቃት ማዳመጥ[14] በአመቻች ሽምግልናም ሆነ በባህላዊ ሽምግልና በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ነገር ግን በአመቻች ሽምግልና ጊዜ በንቃት ማድመጥ ትልቅ ክህሎት ሲሆን ንግግር አልባ ግንኙነቶችን፣ መናበብን (mirroring) እንዲሁም ግልፅ ስሜትንና ፍላጎትን መግለፅን ያጠቃልላል።
- በባህላዊ ሽምግልና ሂደት ሽምጋዮች ሁለቱንም ወገኖች ምን እንደሚፈልጉ ይጠይቋቸዋል። ይህም የሚሆነው መጀመሪያ በተናጠል ከዚያም በጋራ ተቀምጠው እንዲነጋገሩ ያደርጋሉ። አማራጭ መፍትሔዎችን ከተቀበሉ በኋላ ሽምጋዮች በነዚህ የመፍትሔ ሃሳቦች ዙሪያ ይመክሩባቸዋል። በተጋጭ ወገኖች መካከል የመፍትሔ ሃሳብ ልዩነት ካሳዩ እንደገና መግባቢያ መፍትሔ ለማግኘት ይመካከራሉ። ከዚያም ተጋጭ አካላት በሽምጋዮቹ በቀረበላቸው የመፍትሔ ሃሳብ ላይ ሊስማሙ ይችላሉ። መስማማት ካልቻሉ ግን ሽምጋዮች ለተጋጭ አካላት ይጠቅማል ብለው ያሰቡትን መፍትሔ እንደ መስማሚያ ውሳኔ ተደርጎ ይቆጠራል።
- በአመቻች ሽምግልና ሂደት ሽምጋዮች የማስታረቅ ሂደቱን ይደግፋሉ እንጂ በተጋጭ አካላት ላይ ውሳኔ አያስተላልፉም። ገለልተኛነት የአመቻች ሽምግልና መሠረት ነው።

---

13 ክፍል III.6.3 በሽምግልና ውስጥ የአካላዊ ቋንቋ አስፈላጊነትን ገፅ 62 ይመልከቱ።
14 ክፍል III.6.4 ተመልከቱ በሽምግልና ውስጥ ማዳመጥን ገፅ 67 ይመልከቱ።

## II.3 የባህላዊ ሽምግልና እና አመቻች ሽምግልና ውህደት

የአመቻች ሽምግልናን አሁን በኢትዮጵያ እየተሰራበት ካለው ባህላዊ ሽምግልና ጋር ማጣመር ጠቃሚ እርምጃ ነው። ምክንያቱም የአንድን አገር የግጭት አፈታት አቅም ያጎለብታል። በዚህ ጊዜ አንድ ሰው "በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ባህላዊ የሽምግልናን ስርዓት ማስተካከል ለምን ያስፈልጋል?" ብሎ ሊጠይቅ ይችላል። ምንም እንኳ በኢትዮጵያ ባህላዊ ሽምግልና የቆየና ተቀባይነትን ያተረፈ ቢሆንም አንዳንድ ክፍተቶች ይስተዋላል። ለምሳሌ ያህል በአንዳንድ አካባቢዎች ባህላዊ የሽምግልና ስርዓቶች ከሰብዓዊ መብት አንፃር በተለይም ለሴቶች መብት መከበር ትኩረት እንደማይሠጡ ይስተዋላሉ። በተጨማሪም የዕርቁ ዘለቄታነት በሽምግሌዎች ስልጣን ስር የወደቀ ሲሆን ሽምጋዮች የሰጡትን ውሳኔ አለመቀበል ስልጣናቸውን ማቃለልና እንዲሁም ባህላዊ መዋቅሩን እንደማፍረስ ተደርገው ስለሚቆጠር በሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። ከዚህ የተነሳ በአመቻች ሽምግልና ውስጥ የሚገኙ የአመለካከት ለውጥን የሙሣሰሉ ባህሪያት በባህላዊ ሽምግልናው ስርዓት ላይ ቢጨመሩ የስምምነቶችን ዘላቂነት ከማዳበር አልፎ የሽምጋዮቹን ተቀባይነት ያጠናክራል።

የአመቻች ሽምግልና እና የባህላዊ ሽምግልና ጥምረት አስፈላጊነት በሁለቱም ዘዴዎች የሚገኙትን ጠቃሚ ደረጃዎች፣ ክህሎቶች እና ዕውቀቶች ስለሚለዋወጡ ሽምግልናውን ወደ ተሻለና ወደ ዳበረ ደረጃ ያሸጋግረዋል። በውህደቱ ጊዜ ሁለቱም ዘዴዎች አንዱ ከሌላው በሚያደርገው የተግባርና ትምህርት ልውውጥ ሂደቱን የተሳካ ያደርገዋል።

የዚህ ስልጠና መምሪያ ተጠቃሚዎች ኢትዮጵያውያን ከመሆናቸው አንፃርና የሽምግልናን ስርዓት የሚያውቁ በመሆናቸው በአመቻች ሽምግልና ስር በሚገኙት ጠቃሚ ነጥቦች (elements) ላይ ትኩረት እንሰጣለን። ስለዚህ ይህ መምሪያ የሽምግልናን ባህሪያት በአመቻች ሽምግልና ውስጥ ምን ያህል እንደምንጠቀምበት አይገልፅም።[15] ይህ መምሪያ የአመቻች ሽምግልና ዘዴዎችንና ስልቶችን በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ ተግባራዊ መሆን አለመሆኑን ለማሳየት የሁለቱ የሽምግልና ዓይነቶች መዋሃድ አስፈላጊ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም በዚህ ሰነድ ውስጥ የተካተቱት የተግባር መልመጃዎችና ገጠመኞች የኢትዮጵያን ባህላዊ የሽምግልና ስርዓት መጠቀም እንድንችል በጥንቃቄ የተመረጡ ናቸው።

15 ስለውህደቱ ይበልጥ መረጃ ለማግኘት ክፍል III.5.3 የሽምግልና ደረጃዎች ገጽ 54 ላይ ይመልከቱ።

# ክፍል ሶስት የአመቻች ሽምግልና ሂደት ስልጠና መሣሪያዎች

ይህ ክፍል የመምሪያውን ዋና አካል የያዘ ነው፡፡ መሣሪያዎቹና የመልመጃዎቹ መዋቅሮች በኢንሚዲኦ በርሊን ለስልጠና የሚጠቀሙበት ቢሆንም በዚያ መልኩ መጠቀም ግዴታ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በዚህ መምሪያ የተካተቱትን ሁሉ ተግባራዊ መልመጃዎች መጠቀም አያስፈልግም፡፡ ከስልጠና በፊት የስልጠናውን አካሄድና የተመረጡትን መልመጃዎች ለተሳታፊዎች ተስማሚና ምቹ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## III.1 ግጭትን መረዳት

“ግራ እና ቀኝ እግርም ይጋጫሉ!”

(አማርኛ ብሂል)

### III.1.1 የግጭት ትርጓሜ

ግጭት ምንድን ነው? ግጭት አለም አቀፍ ትርጓሜ አለው? አንድን ገጠመኝ ወይም ሁኔታ ግጭት ብለን ለመሰየም ሁላችንም ተመሳሳይ ዕይታ አለን? በግጭት ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ስንሆንና ሳንሆን ስለ ግጭት ያለን ዕይታ ምን ይመስላል? ስለ ግጭት ያለን አመለካከትና ባለድርሻ ወይንም ሽምጋዮች እንደመሆናችን እነዚህና ሌሎች መሠል ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው፡፡ ወደ ዝርዝር ሃሳቦች ከመግባታችን በፊት ስለግጭት ላለን ግንዛቤ ይረዳን ዘንድ የሚከተለውን ተግባራዊ መልመጃ እንመልከት፡፡

## III.1.2 ተግባር፡ ከግጭት ያከን ዕይታ

**ዓላማ** ግጭት ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ግንዛቤን ማስጨበጥ ፣ ተሳታፊዎች ግጭትን የሚመለከቱበት መንገድ በግጭቱ ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ መጠን ዕይታቸው እንደሚወሰን ማሳየት።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** አንዱ "አዎን" ሌላው "አይደለም" ተብሎ የተፃፈባቸው ሁለት ካርዶች፣ በክፍሉ ግራ እና ቀኝ የተቀመጡ ጠረጴዛዎች፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: ለተሳታፊዎቹ የተለያዩ ገጠመኞችን እንደምትተርክላቸው ንገራቸው። የነገርካቸውን ገጠመኞች ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ውስጥ በየትኛው ስር እንደሚመድቡት ጠይቃቸው።

ሀ - ግጭት ነው ለ - ግጭት አይደለም ወይንም ሐ - ግጭት ወይንም ግጭት አይደለም ብዬ መመደብ ያስቸግረኛል

ይህን ልዩነት በይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ተሳታፊዎቹን በሶስት ምድብ መድባቸው። ለምሳሌ፡- ግጭት ነው ብለው የመረጡትን የ"ሀ" ምድብ፣ ግጭት አይደለም ብለው የመረጡትን የ"ለ" ምድብ እና መወሰን ያልቻሉትን የ"ሐ" ምድብ በማለት በክፍሉ ውስጥ ስፍራን አዘጋጅላቸው።

ደረጃ 2: የሚከተሉትን ታሪኮች አንብብላቸው።

1) ሁለት ጓደኛሞች በየቀኑ ይፎካከሩ ነበር። ከሁለቱ አንዱ ሁልጊዜ ያሸንፍ ነበር።
2) አንድ ቤተሰብ ሴት ልጃቸው የማታፈቅረውን ሰው እንድታገባ ወሰኑ።
3) ከአንድ ወንዝ አጠገብ ያለ ሰፊ መሬት ነበር። ባለቤት የሆኑት ማኅበረሰቦች ይህን መሬት አይጠቀሙበትም ነበር። በድርቅ ምክንያት ሌሎች ማኅበረሰቦች ወደዚያ መሬት በመምጣት ያንን መሬት ሊጠቀሙበት ሰፈሩ።

ደረጃ 3: ተሳታፊዎቹን የምርጫቸውን ምክንያት ጠይቃቸው። ሌሎቹ ተሳታፊዎች በጥሞና እንዲያደምጡ ጠይቃቸው። እንደአስልጣኝነትህ የጥሩ ሽምጋይ ምሳሌ ልትሆናቸው ይገባል። ይህን በምታደርግበት ጊዜ ግልፅ እንዲሆን ከምታነሣቸው ጥያቄዎች ባሻገር (እንደ ሽምጋይ) ውሳኔያቸውን (ሙሉ በሙሉ ባትስማማበትም) ልታከብር ይገባል። ተሳታፊዎች በሚሰጡት ውሳኔ ግምት ውስጥ እንዳትከታቸው ጥንቃቄ በማድረግ የሚሰጡትን ሃሳቦች ጠቅለል በማድረግ ሀሳባቸውን ግለፅላቸው።

ደረጃ 4: ተሳታፊዎች በዚህ የተግባር መልመጃ ያላቸው አመለካከትና ዕይታ በመጠየቅ ገምግመው። በግምገማው ወቅት መታወቅ ያለባቸው ነጥቦች

- አንድ ገጠመኝ በሁሉም ዘንድ እኩል ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም
- ሰዎች ነገሮችን የሚገነዘቡት በልዩ ልዩ መልኩ ነው
- ለሁኔታዎች ያለን የተለያዩ አመለካከቶች ትክክል ናቸው
- ስለዚህ የግጭት መኖር ወይም አለመኖር እንደ ሰዉ ይወሰናል

**ማሳሰቢያ** ክፍል III.1 ግጭትን መረዳት የሚለውን ርዕስ ስትጀምር ይህን የተግባር መልመጃ ተጠቀምበት። ተሳታፊዎችህ ይህን በምታደርግበት ጊዜ ስለ ግጭት የሰጡት ሀሳብ የተሳሳተ እንደሆነ እንዳያስቡ ጥንቃቄ አድርግ። ምክንያቱም የተለያዩ ዕይታዎች ትክክል /ብቁ/ ናቸው የሚለውን ከሽምግልና ሃሳብ ጋር ስለሚቃረን ነው። የተለያዩ ትርጓሜዎች እንደሚኖሩ አረጋግጥላቸው። ተሳታፊዎቹ በሚናገሩበት አገረሰብ ቋንቋዎች ግጭት ምን ተብሎ እንደሚጠራ ጠይቃቸው። ይህን በማድረግህ በማኅበረሰብ ውስጥ ስለግጭት ያላቸውን አመለካከት እውቀና በመስጠት ይበልጥ እንዲረዱ ታደርጋለህ።

## III.1.3 ግላዝል ለግጭት የሰጠው ትርጓሜ

አንድን ገጠመኝ ግጭት ነው ወይንም ግጭት አይደለም ብሎ ለመለየት የተለየና ሁሉንም የሚያግባባ ፍቺ ማግኘት አስቸጋሪ ቢሆንም ምሁራን ግን ትርጉም መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበው በተለያዩ ጊዜያት ልዩ ልዩ ትርጓሜዎችን እያዳበሩ መጥተዋል። ለዚህ መምሪያ እንዲሆንና ስለ ግጭትና ስለሽምግልና ሂደት ከተረዳነው አንፃር የተለያዩ ምሁራን ከሰጧቸው ትርጓሜዎች መካከል በአብዛኛው ተቀባይነት ያለውን መርጠን እንመለከታለን። በፍሬድሪክ ግላስል በ1997እ.ኤ.አ "Konfliktmanagement" (ግጭትን ማስተዳደር)[16] በሚለው መፅሐፍ ውስጥ ግጭት የሚኖረው የሚከተሉት ባህሪያት ሲገለጹ እንደሆነ ገልጿል።

- በሁለት አካላት መካከል ቢያንስ አንዱ የፍላጎት፣ የአቋም፣ የተስፋ፣ የምርጫ አለመጣጣም ወይንም ልዩነት ሲያሳይ፤
- እነዚህ ልዩነቶች ወይም አለመጣጣሞች የስሜት መረበሽን ሲፈጥሩ። (ስሜታዊም ሆነ ምክንያታዊ)
- ይህ የስሜት መረበሽ በሁለቱም አካላት ፍላጎት፣ አመለካከት እና ዕይታ ላይ ተፅዕኖ ሲያሳርፉ

የግላስል አተረጓጎም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችልበትን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲሁም የሰዎችን የአመለካከት ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት በመሆኑ ግጭትን ገና በእንጭጩ ለመለየት ይረዳል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ እርምጃ እንዲወሰድበት ይጠቅማል። በሽምግልና ሂደት ደግሞ ካየነው "እዚህ ደረጃ ያደረሳቸውን" ግጭት ከስር መሠረቱ ምን እንደሆነ በማሳወቅ ዕይታቸውን እንዲቀይሩ ሊረዳቸው ይችላል።

ነገር ግን አለም አቀፍ ትርጓሜ ስለሌለው[17] በግጭት ላይ ያለህን የራስህን አመለካከት ማስቀመጥ ትችላለህ። በመጨረሻም ልንረዳው የሚያስፈልገው ግጭት ከግለሰቦች ዕይታና ፍላጎት ጋር የተቆራኘ መሆኑን ነው። የጋራ መግባባት ላይ እና ሁሉንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ላይ ለመድረስ እነዚህ ዕይታዎችና ፍላጎቶች በሌሎች ዘንድ መታወቅ ይገባቸዋል። ይህን በማድረግ በሽምግልና ሂደቱ ላይ ያለው ግንኙነት ትልቅ ሚና ይጫወታል።

16 Glasl, F (1997)

17 የተለያዩ ትርጓሜዎችን ከ http://www.campus-adr.org/cmher/ReportResources/Definitions.html ይመልከቱ።

# “ሃይቁ እንዳይደረቅ፣ አንቁራሪቶቹም እንዳይሞቱ”

## (ኦሮምኛ ብሂል)

**ዓላማ** በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች ወደ ግጭት ከሚያመራውና አንዱን ብቻ ተጠቃሚ ወይንም ሁለቱንም ተጎጂ ከሚያደርገው ፋይዳ ከሌለው ከንቱ ፉክክር ይልቅ በትብብር የሚከናወነውና ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርገው መፍትሔ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆን ይረዳሉ።

**የተመደበ ጊዜ** 165 ደቂቃ

**መነሻ ዕውቀት** II. 1. ግጭትን መረዳት

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ ባለቀለም ካርዶች

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: የጋሬት ሐርዲን "Tragedy of the Unmanaged Commons" (የጋራ የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ አለመጠቀም) የሚለውን ኀልዮት (theory) በማቅረብ ይህን የትምህርት ጊዜ ጀምር።

ደረጃ 3: የመልመጃውን አግባብነት ካስረዳህ በኋላ ከገሃዱ አለም ገጠመኞች ጋር አዛምደህ አብራራ።

ደረጃ 4: ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔና ጥቅሞቹን በመጠቅለል ክለሳ አድርግ።

ብዙ ምሁራን የሰው ልጅ በተፈጥሮው በግል ጥቅም የሚመራ ነው ብለው ይከራከራሉ። ከምሁራኑ መካከል “The Tragedy of the Unmanaged Commons”[18] (የጋራ የተፈጥሮ ሃብትን በአግባቡ አለመጠቀም) በሚለው ኀልዮቱ የታወቀው ጋሬት ሐርደን ነው። የእርሱ ትንተና ሰዎች ለተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ያላቸው ዕይታ ላይ ያተኮረ ነው። እንደርሱ አባባል የሰው ልጆች በግለሰብ ወይንም በቤተሰብ ደረጃ ከሌሎቹ ማኅበረሰብ አባላት ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም አስበልጠው ለመጠቀም የመፈለግ ውርስ ባህሪ አላቸው። ሲያክልበትም ፍትሀዊ የሆነ እና በድርድር የተመሠረተ የጋራ ሀብትን የመጠቀም ስርዓት ካልተበጀ በቀር ሰዎች እርስበርስ ሀብትን በመሻማትና በመሽቀዳደም ግጭት ውስጥ ከገቡ ሁለቱም ሽንፈት ሊገጥማቸው ይችላል። የዚህ ትምህርት ዓላማ የሰውን ባህሪ ለማጥናት አይደለም። ነገር ግን በሽምግልና ሂደት ውስጥ ሁለቱ ወገኖች እኩል ተጠቃሚ፣ አንዱ ብቻ ተጠቃሚ ወይም ሁለቱም ተጎጂ የሚሆኑበትን ሁኔታ ምን ይጠቁመናል ብለን ለመማር እንዲያስችለን ነው። ይህን ውይይታችንን ይበልጥ እንዲያጠናክርልን ከዚህ በታች ያለውን ተግባር እንጀምራለን።

18 Hardin, G (1994)

## III.2.1 ዓሳ የማስገር ጨዋታ[19]


**ዓላማ** ተሳታፊዎች የግጭትን ባህሪያት በመገንዘብ ለአንድ ግጭት የተለያዩ መፍትሔዎች ሊኖሩ እንደሚችል በተጨማሪም ተጋጭ አካላትን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ለመፍጠር የሚያስችሉ ክህሎቶችን ይቀስማሉ።

**የተመደበ ጊዜ** 80 ደቂቃ /35 ደቂቃ ተግባር እና 45 ደቂቃ ግምገማ/

**መርጃ መሣሪያዎች** ሥዕል የተሳለበት የሚገለጥ ወረቀት፣ ባለ ቀይና ሰማያዊ ካርዶች፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: የታሪኩን መልከአ ምድር በሚገልጽ ሥዕል አስደግፈህ ገጠመኙን አብራራ

አራት ማኅበረሰቦች በአንድ ትልቅ ሐይቅ ዙሪያ ይኖሩ ነበር። ህይወታቸው የተመሰረተው ዓሳ በማስገር ስራ ነው። ከሚያሰግሩት ዓሳ አብዛኛውን ለመብል የሚጠቀሙ ሲሆን ቀሪውን ለገበያ በማቅረብ ተጨማሪ ገቢ እንዲያመጣ በገንዘቡ ግመል ይገዙበታል። ከዚህ ቀደም የሚቀጠሙት አነስተኛ በእንጨት የተሠራ ቀይ ጀልባ ነበር። ይህ ደግሞ ማኅበረሰባቸውን ለመመገብ እንጂ ምርታቸውን ለማሳደግ አላስቻላቸውም። አሁን ግን መንግሥት /ሌላ አካል ወይንም ሌላ ባለሃብት/ የተሻሻለና ዘመናዊ የዓሳ ማስገር ዘዴ አስተዋወቃቸው። እነዚህ ዘመናዊ ጀልባዎች ከበፊቶቹ ጋር ሲነፃፀሩ ከፍተኛ የማጥመድ አቅም ያላቸው ስለሆነ ከማኅበረሰቡ የምግብ ፍላጎት ባሻገር ግመል በመግዛት አቅማቸውን አሳደገላቸው።



19 ከተለያዩ ምንጮች ተሰባስቦ በ Splinter, D & Wüstehube, L (2006) የተሰበሰበ።

ደረጃ 2: ተሳታፊዎቹን በአራት ቡድን ከመደብካቸው በኋላ አንድ ተወካይ እንዲመርጡ አድርግ። እያንዳንዱ ቡድን በሃይቁ ዳርቻ የሚኖሩትን አራት ማኅበረሰቦች ይወክላል። ለእያንዳንዱ ቡድን አንድ ቀይ እና አንድ ሰማያዊ ካርድ ስጥ። /ካርዶቹ በእጅ መዳፍ ውስጥ ሊደበቁ በሚችሉበት መጠን የተቆረጡ መሆን ይኖርባቸዋል።/ ቀያዩቹ ካርዶች አሮጌዎቹን አነስተኛ ጀልባዎች የሚወክሉ ሲሆን ሰማያዊዎቹ ካርዶች ደግሞ ዘመናዊዎቹን ጀልባዎች የሚወክሉ ናቸው። ተሳታፊዎቹ እያንዳንዱ ቡድን የማኅበረሰቡን የመንግሥት አካል እንደሚወክል ግለፅላቸው። እንዳመቺነቱ የአካባቢው መንግሥት ወይንም ሽማግሌዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ በፊት ነዋሪዎቹ በኑሮዋቸው ደስተኞች /ኑሮዋቸው የሚበቃቸው/ እንዲሁም መሪዎቻቸውን የሚያከብሩ ነበሩ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ተቃዋሚዎች እየመጡ እንደሆነ ንገራቸው። ነዋሪዎቹ አዲስ ትምህርት ቤት፣ የጤና ጣቢያ በመሳሰሉ የልማት ስራዎች በብዛት ስለሌሉ የሚያስተዳድሯቸውን የመንግሥት አካላትን ተጠያቂ እያደረጉ ነው። ከዚህም የተነሳ ተቃዋሚዎች ሰዎችን በማስተባበር አሁን ለውጥ ያስፈልጋል ብለው ድምፃቸውን እያሰሙ ናቸው።


ደረጃ 3: የጨዋታውን ህግ አስረዳቸው።

የእያንዳንዱ ማኅበረሰብ ዓላማ የግመሎቹን ቁጥር በማብዛት የማኅበረሰቡን ዕድገት ለማስጠበቅ ነው። ጨዋታው ሲጀመር እያንዳንዱ ማኅበረሰብ 15 ግመሎች ይኖሩታል። የማኅበረሰቡ አባላት በቂ የዓሳ ምርት ካላገኙ ግመሎቹን በመሸጥ ህይወታቸውን ያቆያሉ። ይህ ማለት ደግሞ የኢኮኖሚ ደረጃቸው ስለሚወርድ ትምህርት ቤት ወይንም ጤና ጣቢያ ለመስራት አይችሉም። /ማኅበረሰቡን የወከሉት አስተዳዳሪዎች በየትኛው ጀልባ ማለትም በአነስተኛውና ባህላዊው /ባለ ቀይ ካርድ/ ወይስ በትልቁና ዘመናዊው /ባለ ሰማያዊ ካርድ/ ማስገር እንዳለባቸው ይወስናሉ። አዲስ ወቅት በመጣ ቁጥር የሚጠቀሙበትን ጀልባ እንደገና ይመርጣሉ። ይህ ጨዋታ በተለያዩ ዙሮች መጫወት ይቻላል። ዙሮቹም የተለያዩ ወቅቶችን የሚወክሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

ደረጃ 4: የጨዋታው ነጥብ እንዴት እንደሚያዝ በሚገለጠው ወረቀት ላይ አብራራ

አራቱ ማኅበረሰቦች ሁላቸውም አነስተኛውን ባህላዊ ጀልባ ቢጠቀሙ: አራቱም ማኅበረሰብ በቂ የዓሳ መጠን ስለሚያሰግሩ ተጨማሪ አንድ ግመል መግዛት ይችላሉ። ይህም ማለት እያንዳንዱ ማኅበረሰብ አንድ ነጥብ /+1/ ያገኛል። በዚህ መሠረት ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናል ማለት ነው።
አንዱ ማኅበረሰብ ትልቁን ሌሎቹ ሶስቱ ማኅበረሰቦች ግን አነስተኛውን ቢጠቀሙ: ይህ ማኅበረሰብ ብዙ ግመሎች መግዛት ስለሚችል ሶስት ነጥብ ያገኛል። ሌሎቹ ግን እያንዳንዳቸው አንድ ግመል መሸጥ ይኖርባቸዋል /+3/-1/-1/-1/ በዚህ መሰረት አንዱን ተጠቃሚ ሌሎቹን ግን ተጎጂ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጠራል። ምክንያቱም ዘመናዊው ጀልባ ከባህላዊው ጀልባ ብዙ ዓሳ ማጥመድ ይችላል።
ሁለቱ ማኅበረሰቦች ትልቁን ጀልባ ቀሪዎቹ ሁለቱ ደግሞ አነስተኛውን ጀልባ ቢጠቀሙ: ሁለቱ ማኅበረሰቦች እያንዳንዳቸው ሁለት ተጨማሪ ግመሎች ሲገዙ ሌሎች ሁለት ማኅበረሰቦች ግን እያንዳንዳቸው ሁለት ግመሎች መሸጥ አለባቸው። ስለዚህም የመጀመሪያዎቹ ሁለት ማኅበረሰቦች ሁለት ነጥብ ሲያገኙ ቀሪዎቹ ሁለት ነጥብ ያጣሉ። /+2/+2/-2/-2/። በዚህ መሠረት ሁለቱን ተጠቃሚ ሌሎቹን ተጎጂ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጠራል። ምክንያቱም ሁለቱ ማኅበረሰቦች ትላልቅ ጀልባዎች ሲጠቀሙ ምንም እንኳ የዓሳውን ምርት ቢካፈሉም ብዙ ምርት ያገኛሉ። ይህ ደግሞ ለሌሎቹ ማኅበረሰቦች ትልቅ ጉዳትን ይፈጥራል።
ሶስቱ ማኅበረሰቦች ትልቁን አንዱ ማኅበረሰብ ደግሞ አነስተኛውን ጀልባ ቢጠቀሙ: ሶስቱ ማኅበረሰቦች እያንዳንዳቸው አንድ ግመል መግዛት ሲችሉ አንዱ ማኅበረሰብ ግን በቂ የዓሳ ምርት ስለማያገኝ ሶስቱን መሸጥ ይኖርበታል። /+1/+1/+1/-3/ በዚህ መሠረት ሶስቱ ተጠቃሚ አንዱ ተጎጂ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጠራል።
ሁሉም ማኅበረሰብ ትልቁን የጀልባ አይነት ቢጠቀሙ: አራቱም ማኅበረሰቦች ከሐይቁ የሚገኘውን የዓሳ ምርት መካፈል ስለሚኖርባቸው በቂ የዓሳ ምርት አያገኙም። ከዚህ የተነሳ እያንዳንዱ ማኅበረሰብ አንድ ግመል ለመሸጥ ይገደዳል። ስለዚህም ከሁሉም አንድ ነጥብ ይቀነስባቸዋል። በዚህ መሠረት ሁሉንም ተጎጂ የሚያደርግ ሁኔታ ይፈጠራል። እያንዳንዱ ማኅበረሰብ ማወቅ ያለበት ነገር የሚቀነስባቸው ግመሎች ነጥብ ለሚያገኘው ማኅበረሰብ የሚጨመሩለት ይሆናሉ።

ደረጃ 5: ጨዋታውን ጀምር ። (ማስታወሻ፡ በውይይት ወቅት አንዱ አንዱን እንዳይረብሽና እንዳይሠማው በያንዳንዱ ቡድን መካከል በቂ ርቀት መኖር አለበት።) እያንዳንዱ ቡድን የሚጠቀምበትን የጀልባ ዓይነት ለመምረጥ 3 ደቂቃ ይኖረዋል። አወያዩ እንደዳኛ በመሆን የእያንዳንዱን ዙር ደቂቃ በመያዝ ይቆጣጠራል። 3 ደቂቃ እንደሞላው አወያዩ ተወካዩችን ወደ መሃል ጠርቶ የተጨበጡ መዳፎቻቸውን እስከሶስት ሲቆጥር እንዲዘረጉ ይጠይቃቸዋል። መዳፎቻቸውን ሲከፍቱ የመረጡት ጀልባ ትልቁን ይሆን ትንሹን ያሳያሉ። ከላይ በተጠቀሰው መሰረት በመረጡት የጀልባ ዓይነት ግመሎች /ነጥቦቹ/ ይጨምሩላቸዋል ወይንም ይቀንሱባቸዋል።








**ማሳሰቢያ**

በጨዋታው ውስጥ ሊያጋጥሙ ይችላሉ የተባሉት ገጠመኞች በሙሉ በህጎቹ ላይ ተዘርዝረዋል ከአንደኛው ዙር ወደ ሌላው ዙር በቡድኖቹ መካከል ያለው ውጥረት እየጨመረ /እየጋለ/ ይመጣል። ነገር ግን ሁሉም ቡድኖች ባህላዊውን ጀልባ /ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርገውን/ የሚመርጡ ከሆነ የማኅበረሰቡ አባላት ተሰላችተዋል “ልማቱ በጣም ዘገምተኛ ነው ዘመናዊ ጀልባዎችን እንዲሁ ነው ያስቀመጣችሁት። ተቃዋሚዎቹ ልክ ናቸው ለውጥ ያስፈልጋል እምነት የሚጣልባችሁ አይደላችሁም። ልማት እያላችሁ ነገር ግን ዘመናዊዎቹን ጀልባዎች እንኳ አትጠቀሙም መሻሻል አትፈልጉም” እያሏችሁ ነው በማለት ጫና ፍጠርባቸው።

አወያዩ ግፊትና ጫና ከፈጠረባቸው ቢያንስ አንዱ ቡድን ትልቁን ጀልባ መምረጥ ይጀምራል። ስለዚህ ጨዋታው አንዱ ተጎጂ ሌላውን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆን ይጀምራል። ከዚህ በኋላ ጨዋታው እየጋለ ይመጣል። በአብዛኛው ጊዜ አንዱ ይህን ከጀመረ ሌሎቹም ይህን ይጀምራሉ። ከጥቂት ዙር በኋላ ሁሉም ዘመናዊ የሆነውን ጀልባ መጠቀም ስለሚጀምሩ ሁሉንም ተጎጂ የሚያደርግ ምርጫ ይኖራቸዋል።

ለሁለት ወይንም ለሶስት ዙር በዚህ መልኩ ከቀጠሉ እንደገና ማኅበረሰቡ እንዳዘነባቸው አንዳንዶች አመፅ እንዳሰቡ ንገራቸው። እንዲሁም እንደገና እንደሽምጋይነታቸው (መሪነታቸው፣ አስተዳዳሪነታቸው) ጊዜ ወስደው እንዲያጤኑበት ንገራቸው።

ከጥቂት ዙሮች በኋላ የቡድኖቹን አካሄድ በማየት ያላቸውን ነጥብ በማሳወቅ ከዚህ በመቀጠል ምን ሊሆን እንደሚችል እንዲገምቱ አድርጋቸው። ከሌሎች ቡድኖች ጋር መደራደር እንደሚችሉ ፍንጭ ልትሰጣቸው ትችላለህ። ነገር ግን ይህ ሃሳብ ከነርሱ ቢመጣ የተሻለ ስለሚሆን ትንሽ ጊዜ ጠብቃቸው ብዙ ጊዜ ቡድኖች መደራደር እና መወያየት ይጀምራሉ ከዚያም ትብብር ሊጀምሩ ይችላሉ። ከዚህም የተነሳ በጨዋታው ውስጥ ስምምነቶች እና ስምምነቶችን መጣስ ሁሉ ሊከሰት ይችላል። ብዙ ነጥብ ለማግኘት አንዱ ቡድን ሆን ብሎ የተስማማበትን ቀይ ትቶ ሰማያዊ ካርድ ሊያቀርብ ይችላል። ይህ ደግሞ በጨዋታው ላይ ውጥረትንና ግለትን ይጨምራል።

ቡድኖቹ ስምምነት ሲጣስ የሚስተዋል ዓይነት ስሜት ይሰማቸው። ከዚያም ለመጀመሪያ ጊዜ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ላይ እንዲደርሱ በጠረጴዛ ዙሪያ ውይይት ያድርጉ። አንዳንድ ቡድኖች ሌሎቹ ቡድኖች ባህላዊ በሆነው ጀልባ በመጠቀም ሁሉም ተጠቃሚ የሚሆኑበት መፍትሔ ላይ ሊያደርሳቸው ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ ተሳታፊዎቹን የሚያረጋጋ መፍትሔ ላይ ያደርሳሉ። ሁሉም ቡድኖች ቀዩን ካርድ መጫወት ሲጀምሩ ከዚህ በፊት የተደረጉትንና የፈረሱትንም ስምምነቶች ይረሳሉ። ስምምነታቸውን ሳያፈርሱ አንድ ወይንም ሁለት ዙሮች ከተጫወቱ ይህን ጨዋታ በዚያ ላይ ማቆም ይመረጣል። ምክንያቱም በተሳታፊዎች ዘንድ የነበረው ውጥረት ረግቦ የደስታና የስኬት ስሜት ውስጥ ይከታቸዋል።

አብዛኛውን ጊዜ ተሳታፊዎች በጨዋታው መጀመሪያ ላይ ሁሉን የሚጎዳ ወይንም አንዱን ጠቅሞ አንዱን የሚጎዳ መፍትሔ በማምጣት ይጫወታሉ። ከጥቂት ዙሮች በኋላ ቢያንስ አንዱ ቡድን ተሸናፊ ሲሆን እናገኘዋለን። ቢሆንም ግን የሌሎች ተሸናፊነት /ተጎጂነት/ በመጀመሪያው ላይታወቅ ይችላል። የዚህን ጨዋታ በማፋጠን እንዲሁም ሁሉም ተጎጂ /አሸናፊ/ የሚሆኑበትን ሁኔታ ለማምጣት አሰልጣኞቹ ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ።



ደረጃ 6: ሁሉን ተጠቃሚ፣ አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ (የዜሮ ድምር ውጤት) እና ሁሉን ተጎጂ የሚያደርግ ማለት ምን ማለት እንደሆነ አብራራላቸው። በሚከተሉት መሪ ጥያቄዎች ተሳታፊዎቹን እንዲወያዩና አስተያየት እንዲሰጡበት ጠይቃቸው።

- በሁሉም ዙሮች ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርገውን ተጫውታችሁ ቢሆን ኖሮ እያንዳንዱ ቡድን ስንት ነጥብ ያገኝ ነበር? /መልስ፡- እያንዳንዱ ቡድን አሁን ካለው ጠቅላላ ነጥብ የበለጠ ነጥብ ያገኝ ነበር/
- ተሳታፊዎች ሁሉን የሚጠቅም መፍትሔ ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ይገነዘባሉ ምክንያቱም አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ መፍትሔ የኋላ ኋላ ሁሉን የሚጎዳ ይሆናል።
- ከጨዋታው መጀመሪያ አንስቶ እስከመጨረሻው ሁሉን ተጠቃሚ በሚያደርግ መፍትሔ እስከመጨረሻው መቀጠል ለምን አልተቻለም።
- ፉክክርና እምነት ምን እንደሚመስሉ ተወያዩበት። በተለይ ብዙ ነጥብ ያጡትን ተሳታፊዎች ያለ ምንም ማካካሻና ካሳ እንደገና ጨዋታውን እንዲቀጥሉ በሚደረግበት ወቅት ምን ዓይነት ስሜት እንደተሰማቸው ጠይቃቸው።

ደረጃ 7: ተሳታፊዎች የተማሩትን ትምህርት በሚገለጠው ወረቀት ላይ እንዲያሰፍሩ ጠይቅ። የተሳታፊዎችን ግንዛቤ ለማሳደግ የሚከተሉት ነጥቦች መካተታቸውን አረጋግጥ።

- ፉክክርና ግለኝነት የሰው ተፈጥሯዊ ባህሪይ በመሆናቸው በደመነፍስ የተፈፀሙ ናቸው። በግጭት ውስጥ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ለማምጣት አንዳንድ ጊዜ ራስ ወዳድነት አዎንታዊ መፍትሔ ሊያመጣ ይችላል።
- ምንም እንኳ በመጀመሪያ ተሳታፊዎች ራስ ወዳድ ቢሆኑም መተባበር ጥሩ መፍትሔ ነው።
- በዚህ ሂደት ውስጥ የግጭቱ መነሻ ምን እንደሆነ ተረስቶ የመተማመን ጥያቄ አስፈላጊ እየሆነ ይመጣል።
- ከዚህ የተነሳ በሂደቱ ውስጥ እምነትን የሚያዳብሩ ተግባራት መካተት አለባቸው።
- አንዳንድ ጊዜ የሶስተኛ ወገን በሂደቱ መግባት በመፍትሔ ሃሳቡ ዙሪያ ለመነጋገርና ለመመካከር ዕድል መፍጠር አስፈላጊ ነው።
- ሁኔታዎች ሚዛናቸውን ካልጠበቁ በመጀመሪያ ድርድሩ በካሳ ጉዳይ ላይ ሆኖ ከዚያም በመቀጠል ሁሉን ተጠቃሚ በሚያደርግ መፍትሔ ላይ ይሆናል።

## የዓሳ ማስገር የተግባር ልምምድ ገለፃ

- መጀመሪያ፡ የተግባቦት ችግር
- እምነትን ማጣት
- ራስ-ወዳድነት አይጠቅምም
- ሚዛናዊ ያልሆነ - ግጭት
- ለመፍትሔው "አይሆንም"
- ብቻዬን ማጣት አልፈልግም
- ውድቀት፣ አለመታመን፣ ቁጭት
- ግጭት፣ በቀል
- ያልተሳካ ድርድር ፡ አለመታመን

## የሰላም መንገድ

- ሚዛናዊ ያልሆኑ ጉዳዮችን መንካት
- መታረም፣ መጀመሪያ ሰላም "ያለፈውን መርሳት

ከዚያ በመቀጠል የሚከተሉትን ሃሳቦች ግለጽላቸው።

- ግጭትን ምን እንደሚገፋፋው፡ የጨዋታው ውጥረት በሚያይልበት ጊዜ ተሳታፊዎች ምን እንደተሰማቸው ጠይቃቸው።
- ሁሉን ተጠቃሚ እና አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ የሚባሉትን ፅንሰ ሃሳቦች
- የአመራርን ጥቅም
- በግጭት ውስጥ የተግባቦት አስፈላጊነት
- ግጭትን በማቀራረብ (conflict transformation) ሂደት ውስጥ መተማመንን መፍጠር፣ ዕርቅና ካሳ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆኑ አብራራ። (አንዱ ቡድን በጣም ተጎድቶ ሌሎችን ተጠቃሚ የሚያደርገውን ጨዋታ እንዲሁ ማቆም በቂ አይደለም። ነገር ግን ሁሉን እንደገና እኩል ደረጃ ለማምጣት ካሳ መክፈል አስፈላጊ ነው።)

ደረጃ 8: ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ከህይወት ተሞክሮ ጋር በማቆራኘት ትምህርቱን የበለጠ አዋህዱት። ተመሳሳይ ግጭት በህይወታቸው አጋጥሟቸው ከሆነ ከተሳታፊዎቹ ጋር ተወያዩበት። ተሳታፊዎች ምንም ምላሽ ከሌላቸው አሰልጣኙ የራሱን ህይወት ተሞክሮ ወይም ሌላ ታሪክ/ምሳሌ ተዘጋጅቶ ማቅረብ ይኖርበታል። ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች አንዱን ልትጠቀምበት ትችላለህ።

**የተኩስ አቁም ስምምነት፡** ሁለት አካላት የተኩስ አቁም ስምምነት ላይ ከደረሱ በኋላ በሁለቱ መካከል ያለው እምነት እየጠነከረ ሲሄድ ስምምነታቸውን ለመቀጠል አንዳንድ ተግባራትን ይፈፅማሉ። ለምሳሌ፡-ምርኮኞችን መቀያየር፣ የድንበር ላይ ፍተሻዎችን ማቆም እና ቀስ በቀስ የጦር መሣሪያ ቅነሳ /ባለቀዩን ካርድ/ ያደርጋሉ። ይህም ወደ ሰላም ይመራቸዋል /ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ/ ነገር ግን በሁለቱም አካላት መካከል ፍራቻ አለ። ይህም ፍራቻ አንዱ ወገን ለጦርነት ለመዘጋጀት ፈልጎ ጊዜ እየወሰደ ይሁን አይሁን እምነት ያጣሉ። በሚስጥራዊ መንገድ መሳሪያን በማካበት ጦርነቱን ለማሸነፍ እንደገና ይንቀሳቀሳሉ /ባለ ነጭ ቀለም፣ አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ በመጨረሻም የተኩስ አቁም ስምምነቶቹን ችላ በማለት የጦርነት ስጋት ውስጥ ይወድቃሉ። /ሁሉን የሚጎዳ/

**የግጦሽ መሬት ስጋት፡** አንዳንድ ቤተሰቦች የሚጠቀሙበት የግጦሽ መሬት አንድ ቦታ ላይ ነው። ይህም ለአጠቃቀም ቀላል እና ምቹ ቢሆንም ሁሉም በአንድ ቦታ በማሰማራቱ የመሬት መራቆት ይፈጥራል ብለው ስጋት አድሮባቸዋል። እነዚህ ቤተሰቦች በመመካከር የተወሰነ የከብት መጠን ብቻ በማሰማራት መሬቱን ለረጅም ጊዜ ለመጠቀም ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። /ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ/ ነገር ግን ሁሉም በምስጢር ብዙ ከብት ለማሰማራት መፈተናቸው አይቀርም። /ባለ ነጩን ቀለም ተጠቀም/ ምክንያቱም ሌሎች ስምምነቱን አክብረው መቀመጣቸው እነሱን ስለሚጠቅም ነው። /አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ እያንዳንዱ ቤተሰብ ይህንን ፈተና ተቋቁሞ በስምምነቱ ስር ካልታቀፈ በስተቀር ሌሎቹም ይህን ስምምነት በማፍረስ ከብቶቹን በማሰማራት መሬቱን ሊያራቁቱት ይችላሉ። /ሁሉን የሚጎዳ መፍትሔ/

**የደህንነት ስጋት፡** ሁለት አርብቶ አደር ማኅበረሰቦች እርስ በርሳቸው ተፈራርተው ይኖራሉ። ይህም የሆነው ከዚህ በፊት አንዱ ማኅበረሰብ በሌላኛው ላይ አደጋ በመጣል ብዙ ከብቶችን ስለዘረፈ ነው። በመካከላቸው ያለውን ውጥረት በመስማማት ከማርገብ ይልቅ /ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ/ አንዱ ወገን የጦር መሳሪያ /በነጭ ካርድ ተጠቀም/ በመግዛት ራሱን ለመከላከል መጠባበቅ ጀመረ /አንድን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/። ነገር ግን ሌላኛውም ማኅበረሰብ የጦር መሣሪያ መግዛት ጀመረ። ስለዚህም የጦር መሣሪያ ግዥ እሽቅድድም ውስጥ ይገባሉ። ሁለቱም ወገኖች ምንም እንኳ ለመሳሪያ ግዥ የሚያወጡት ገንዘብ ብዙ ቢሆንም አሁንም ደህንነት አይሰማቸውም። /ሁሉን ተጎጂ የሚያደርግ/

**የድብቅነት ትሩፋት፡** ሁለት ድርጅቶች “ሀ” እና “ለ” የገበያ ማዕከል እየገነቡ ነው። ባሉባቸው ችግሮች ዙሪያ ለመደራደር ስምምነት ያደርጋሉ። “ሀ” ድርጅት የገባበት ችግር የቴክኒክ ሲሆን ወደዚህ ችግር ውስጥ የገባው በራሱ ምክንያት ነበር። “ለ” ድርጅት ደግሞ በሂሳብ ስሌት ስህተት ምክንያት የገንዘብ ችግር ውስጥ ገብቷል። ሁለቱም ድርጅቶች እርስ በርስ ቢነጋገሩበት /ባለ ቀይ ካርድ ተጠቀም/ ችግሮቻቸውን በቀላሉ ሊፈቱ እንደሚችሉ ያውቃሉ። ነገር ግን አንዱ ላንዱ ድብቅ ሆነ /ለነጭ ካርድ ተጠቀም/ የድብቅነታቸው ምክንያት አንዱ ድርጅት ለሌላው ድርጅት ችግሩን ቢገልፅለት ይህን ክፍተት ተጠቅሞ ሌላውን ከገበያው ውጪ ሊያደርገው እንደሚችል ስጋት አድሮበታል። /አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ ሁለቱም ድርጅቶች ችግሮቻቸውን መፍታት አቅቷቸው አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል። /ሁለቱንም ተጎጂ የሚያደርግ/

**በቱሪዝም ስራ ላይ መሠማራት፡** ሁለት ማኅበረሰቦች የሚኖሩበት አካባቢ ለቱሪዝም አጓጊ የሆነና ቢጎበኝ ትልቅ ውጤት የሚያመጣ ነገር ግን መሠረተ ልማት ባልተሟላበት አካባቢ ይኖሩ ነበር። ቱሪስቶችን ለመሳብ ሁለቱም ማኅበረሰቦች ምንም እንቅስቃሴ ካላደረጉ /ባለ ነጭ ካርድ ተጠቀም/ ሁለቱም አይጠቀሙም /ሁለቱንም ተጎጂ የሚያደርግ/። ሁለቱም መዋዕለ ንዋያቸውን ቢያፈሱ /ባለ ቀይ ካርድ ተጠቀሞ/ ሁለቱም ተጠቃሚ ይሆናሉ። ነገር ግን አንዱ ማኅበረሰብ ሌላው ማኅበረሰብ ከሱ በተሻለ መዋዕለ ንዋዩን እንዲያፈስና ጥቅሙን ግን እኩል በጋራ /አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ ለመካፈል ቢፈልግ ሌላኛው ማኅበረሰብ በዚህኛው ማኅበረሰብ ላይ እምነት በማጣት ሁለቱም ምንም ዓይነት ወጪ ከማውጣት ይመለሳሉ። /ሁለቱም ተጎጂ የሚያደርግ/

**ዋጋ ቅነሳ፡** ሶስት አገሮች በአለም ገበያ እጅግ ተፈላጊ የሆነ ማዕድን ያወጣሉ። በአለም ገበያ ዋጋው ውድ በመሆኑ እነዚህ አገራት ተጠቃሚ ናቸው። /ሁሉን የሚጠቅም/ ከሌሎቹ ሀገራት በተሻለ ለመሸጥ በማሳብ ከሌሎቹ ሀገራት ዋጋውን በትንሹ ይቀንሳል። /አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ ከዚህ የተነሳ ሌሎች ሀገራት ዋጋውን በመጀመሪያ ከቀነሰው ሀገር ይበልጥ አሳንሰው ለመሸጥ ይገደዳሉ። ይህም በዓለም ላይ ያለው ዋጋ እንዲቀንስ ምክንያት ሆኗል። ከነዚህ ሶስት ሀገራት አንፃር ገዢዎች በጣም ተጠቃሚ ናቸው። /ሁሉንም ተጎጂ የሚያደርግ/

**ማሳሰቢያ**

ህይወታችንን ለማቆየትና በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ የተሻለን ነገር ለማግኘት መፈለግ /መሻት/ የተለመደ እንዲሁም ጠቃሚ ነገር ነው። በተለይ ደግሞ ግጭት በሚፈጠርበት ጊዜ ያጋጥማል። ይህ ማለት ደግሞ እኛ ሁልጊዜ ተጠቃሚ ስንሆን ሌላኛው አካል ተጎጂ ነው ማለት ነው። /አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ/ ከዚህ የተነሳ አብዛኛውን ጊዜ ለግጭት መፍትሔ ስንፈልግ የአንዱን ጥቅም የሚያሟላ የሌላውን ፍላጎት የሚጎዳ አድርገን እናቀርባለን። /ወይ ይሔን ወይ ያንን/ በግጭት ወቅት ሁሉም አካላት አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ መፍትሔ የሚፈልጉ ከሆነ በመጨረሻ ሁሉም ተጎጂ ይሆናሉ። ይህም ተመልሰው ሊደራደሩ ወደማይችሉበት እንዲሁም የፈለጉትን ማግኘት የማይችሉበት ነገር ውስጥ ይገባሉ። ሁልጊዜ ሁሉን አካላት የሚጠቅሙ መፍትሔዎች እንዳሉ እንዘነጋለን። ነገር ግን ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መፍትሔዎች አሉ።

## III.2.2 ተግባር፡ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ እንዴት መፍጠር እንችላለን?

**ዓላማ**

ተሳታፊዎች ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ጽንስ ሃሳብ ገብቷቸው እንደሆነ ለማረጋገጥና በጥልቀት እንዲረዱት ለማድረግ፣ ከዚህም የተነሳ በሚያደርጉት ተሳትፎ ላይ ተሳታፊዎች ያላቸው አመለካከት ትኩረት ይሰጥበታል።

**የተመደበ ጊዜ**

60 ደቂቃ።

**መርጃ መሣሪያዎች**

ባለቀለም ካርዶችና ማርከሮች፣ ወረቀት ላይ የተሳለ ሥዕል፣ የሚለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ከነማቆሚያው


**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: "የሁለት አህዮችን ተረት"[20] በሥዕል በማስደገፍ ተርክላቸው።
ከዕለታት አንድ ቀን በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት አህዮች ነበሩ። ከሁለቱም አህዮች ፊት የጭድ ክምር ተቀምጦላቸው ነበር። ነገር ግን እርስ በርሳቸው በገመድ ታስረው ስለነበር የጭዱ ክምር ላይ ሊደርሱ አልቻሉም። (ይህም ታሪክ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ ምሳሌ እንደሆነ አትንገራቸው)።

ደረጃ 2: ከተመለከቱት ሥዕል ምን እንደተረዱ ተሳታፊዎቹን ጠይቃቸው።


ለምሳሌ፡ ሁለቱም አህዮች በገመድ ታስረው ነበር። ከፊት ለፊታቸው የተቀመጠላቸውን የጭድ ክምር ለመብላት መጣላት ነበረባቸው። በመጨረሻም ጥላቸውን አቁመው በጋራ መብላት ጀመሩ።

ቁም ነገሩ ተሳታፊዎች ይህን ታሪክ በሚገባ ማብራራታቸው ብቻ አይደለም። ነገር ግን ከታሪኩ የሚረዱት ሀሳብ /አንዱን ጭድ በጋራ ከበሉ በኋላ ሌላኛውን መብላታቸው/ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ ሀሳብ በመጨረሻ ማምጣታቸውን ማወቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው። ምናልባትም ተሳታፊዎቹ ታሪኩ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ እንደሆነ ካልገባቸው ከአህዩቹ አንዱን ተጠቃሚ ሌላው ግን ተጎጂ የሚያደርግ ምሳሌ እንደገና በመስጠት ከመጀመሪያው መፍትሔ ይህኛው የተሻለ አማራጭ እንደሆነ ጠይቃቸው።



20 ስዕሎችን ከhttp://www.quaker.org.uk/files/makeamarkforpeace-13activity-sharingourresources-thetwomules.pdf ማግኘት ይቻላል።

ደረጃ 3: ሁለተኛ ታሪክ አቅርብላቸው። “የግጦሽ መሬት” አርብቶ አደሩ ይጠቀምበት በነበረበት አነስተኛ መሬት ምክንያት በአርሶ አደሩና በአርብቶ አደሩ መካከል ኃይለኛ ግጭት ይፈጠራል። /ካርታውን ተመልከት/ ይህ መሬት ለግጦሽ አመቺ ስላልነበረ አርብቶ አደሮቹ አይጠቀሙበትም ነበር። ነገር ግን ከዘር ዘር ሲተላለፍ የመጣ የውርስ ቦታ ስለነበረ ለዚህ መሬት ያላቸው አክብሮት ጠንካራ ነበር። ግጭቱ በሚከሰትበት ወቅት አርሶ አደሮቹ ይህን የአርብቶ አደሮቹን መሬት በማረስ ህይወታቸውን ማቆየት ይፈልጉ ነበር። እነርሱም እንዲሁ ለግጦሽ እንጂ ለእርሻ የማያመች ሌላ አነስተኛ መሬት ነበራቸው። ነገር ግን አርሶ አደሮቹ የአርብቶ አደሮቹን ፈቃድ ሳይጠይቁ በውርስ መሬታቸው ላይ ሰፈሩ ይህን ማድረጋቸው ግጭታቸውን ከፍተኛ ደረጃ ላይ አደረሰው። ሁለቱም አካላት በዚህ መሬት ላይ የይገባኛል ክርክር አስነሱ።




ደረጃ 4: ተሳታፊዎቹ የመፍትሔ ሃሳብ እንዲሰጡበት ይወያዩ። ከውይይቱ በኋላ ተሳታፊዎቹ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ይህን መፍትሔ ማምጣት ካልቻሉ ግን የሚከተለውን ሃሳብ አቅርብላቸው። ግጭቱ የተከሰተበት ምክንያት በማንነት /አርብቶ አደሮቹ ያባቶቻችን ርስት ነው/ እና በተፈጥሮ ሃብት ጉዳዮች ነው /አርሶ አደሮቹ በእርሻ የምንተዳደር ስለሆነ ይህ መሬት የኑሯችን ህልውና ነው/። ሁለቱም ወገኖች ለራሳቸው ሳይሆን ለሌላው ወገን የሚጠቅም መሬት ይዘዋል። አርብቶ አደሮቹ ይህን መሬት ለአርሶ አደሮቹ ቢያከራዩዋቸው ካባቶቻቸው የወረሱትን መሬት ከመቀማት ይድናሉ። እንዲሁም የባለቤትነት መብታቸው ይረጋገጥላቸዋል። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ አርሶ አደሮቹ ለአርብቶ አደሮቹ ለእርሻ ተስማሚ ያልሆነውን መሬታቸውን ለግጦሽ ማከራየት ይችላሉ። በዚህ መልኩ ሁሉም ተጠቃሚ ይሆናሉ /ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ/።

ደረጃ 5: ከተሳታፊዎች ጋር በጋራ የተግባር መልመጃውን ገምግሙ።

አሰልጣኙ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርገውን መፍትሔ ካቀረበ በኋላ ይህ መፍትሔ አንዱን ጠቅሞ ሌላውን ከሚጎዳው እንዲሁም ሁለቱንም ሊጎዳ ከሚችል መፍትሔ ጋር ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ ይጠይቅ። ተሳታፊዎች ይወያዩበታል በተጨማሪም የመፍትሔ ሃሳቦቹን ያነፃፅራቸዋል። ተሳታፊዎቹ የሚያቀርቧቸው ልዩ ልዩ ሃሳቦች አሰልጣኙ ይመዘግባል። ከዚያም ዓሳ የማስገር ጨዋታን በማስታወስ በዚያ ክፍለ ጊዜ የተነሱትን ሃሳቦች መከለስ ይኖርበታል።

ደረጃ 6: ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ያስፈለገው አለመግባባት በተሳታፊዎች የህይወት ገጠመኝ ተከስቶ እንደሆነ በመጠየቅ ተሞክሯቸውን ከትምህርቱ ጋር በማያያዝ ተወያዩበት ምናልባትም ተሳታፊዎች ገጠመኝ ከሌላቸው ያንተን የህይወት ተሞክሮ ወይንም ቀድመህ ያዘጋጀኸውን ታሪክ አቅርብላቸው።

የዚህን የስልጠና ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ሃሳቦች በማንሳት ጠይቅ:

- መተባበር ሁሉን ተጠቃሚ ወደሚያደርግ መፍትሔ የሚያመጣ እጅግ ተፈላጊ የሆነ ሂደት ነው።
- ፉክክር ብዙ ጊዜ ሁሉን ተጎጂ ወደሚያደርግ ድምዳሜ ያደርሳል።

ተጋጭ አካላት በመጀመሪያ ደረቅ አቋም እና ራሳቸው ሊያደርጉት የሚገባውን ሳይሆን ሌላኛው ተጋጭ አካል ሊያደርገው የሚገባውን ብቻ ማንፀባረቅ ይወዳሉ። ቢሆንም ግን ሽምጋዩ ሽምግልናው የተሳካ እንዲሆን ፈታኝ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ ማለፍ ይጠበቅበታል። በሚቀጥለው ክፍለ ትምህርት ይህን በጥልቀት እንመለከተዋለን።

# “ነገርን ከስሩ ውሃን ከጥሩ!”

## (አማርኛ ብሂል)

| | |
|---|---|
| ዓላማ | ከትምህርቱ መጨረሻ ተሳታፊዎች የአቋም፣ ጥቅም እና ፍላጎትን ልዩነት መለየት ይችላሉ እንዲሁም ይረዳሉ። |
| የተመደበ ጊዜ | 180 ደቂቃ |
| መነሻ ሰውቀት | II.1. ሽምግልና ምንድን ነው? ፣ III.1. ግጭትን መረዳት ፣ III.2. ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ለምን አስፈለገ? |
| መርጃ መሣሪያዎች | ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ፣ የሚገለጥ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ ባለቀለም ካርዶች |
| ቅደም ተከተል | ደረጃ 1: ፍላጎትን በመለየት ሁሉን ተጠቃሚ በሚያደርግ መፍትሔ እንዴት ማስደሰት እንደሚቻል ለማሳየት የ1978 እ.ኤ.አ ካምፕ ዴቪድ ስምምነትን አቅርብ። (III.3.1)<br>ደረጃ 2: የብርቱካኑን ታሪክ እንደ ሁለተኛ ምሳሌ አቅርብ። (III.3.2)<br>ደረጃ 3: የሽንኩርትን ሞዴል በመጠቀም በማንጎ ዛፍ ግጭት ምሳሌ ውሰጥ አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት የሚባሉትን ሃሳቦች ለያይተህ ተንትንላቸው። (III.3.3)<br>ደረጃ 4: የሽምግልና ዛፍ ማማን አቅርብ። ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን እንደግብዓት ተጠቀምባቸው። (III.3.4)<br>ደረጃ 5: አሳታፊ የሆነ ፊልም በመጠቀም ክፍል III 3.5 ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ከአቋም ወደ ጥቅምና ፍላጎት እንዲሻገሩ መርዳት የሚለውን ርዕስ አሰልጥናቸው።<br>ደረጃ 6: መሰላሉ የተባለውን የተግባር መልመጃ እንዲሰሩ አድርግ። (III.3.6) |

በሽምግልና ሂደት ብዙ ጊዜ ተጋጭ ወገኖች በጉዳዩ ላይ ሃሳባቸውን ስሜታዊ በሆነ መልኩ ይገልፁታል። በዚያን ጊዜ በግጭቱ ላይ ያላቸውን አቋም ያንፀባርቃሉ። አብዛኛውን ጊዜ ግጭት የሚፈጠረው ጥቅምና ፍላጎት ሲጎድል ነው። ከዚህ የተነሳ ለሽማግሌዎች አዳጋች የሆነው ነገር ከነዚህ ተጋጭ አካላት ሃሳብ ውስጥ ይህን ለይቶ ማውጣት ነው። ከዚያም እነዚህን ወገኖች ከአቋማቸው ባሻገር ማራመድ ይጠበቅባቸዋል። ፍላጎት፣ ጥቅምና አስገ ነገሮች ላይ ትኩረት መስጠት ተጋጭ አካላት ሊደራደሩባቸው ከማይፈልጓቸው አቋማቸው ነፃ ወጥተው በፍላጎታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ሊረዳቸው ይችላል። ይህም ጊዜ በተገደበ ስምምነት ሊደገፍ ይገባዋል። ግጭትን ዘላቂ በሆነ መንገድ ለማርገብ ብቸኛው መንገድ እነዚህን ጥቅሞችና ፍላጎቶች ሲታወቁና ሲገለፁ ብቻ ነው። በተጨማሪም ተጋጭ አካላት መሻቶቻቸውንና መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ሲዘረዝሩ (ምንም እንኳ ብዙ ጊዜ ከፍርሃት የተነሳ ቢሆንም) ከጥቅሞቻቸው በስተጀርባ ብዙ ጥቅም እንዲሁም ከፍላጎቶቻቸው በስተጀርባ ብዙ ዓይነት ተጨማሪ ሃሳቦች በስምምነታቸው ውስጥ እንዲካተቱ መፈለጋቸውን በተዘዋዋሪ መንገድ ይገልፃሉ። ከዚህ በመቀጠል በአቋም፣ ጥቅምና ፍላጎቶቻቸው ዙሪያ ያሉ ውይይቶችንና ትንታኔዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ተግባራዊ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ይቀርባሉ ።

## III.3.1 የ1978 እ.ኤ.አ ካምፕ ዴቪድ ስምምነት /በቀላሉ የቀረበ/[21]

**ዓላማ** ሁሉን ተጠቃሚ በሚያደርግ መልኩ አቋምን፣ ጥቅምንና ፍላጎትን በመለየት እንዴት ሁሉንም ወገኖች ማስደሰት እንደሚቻል ማሳየት።

**የተመደበ ጊዜ** 10 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: ነገረ-ጉዳዩን ለተሳታፊዎች እንደሚከተለው ንገራቸው።

“ሀ” የ”ለ” ቀጥተኛ አጎራባች አገር ቢሆንም የ”ለ” ን ነፃ መሬት በመውረሩ ምክንያት (በካርታው ላይ ያለውን ቀይ መስመር ተመልከት) ሁለቱም አገሮች ጦርነት ውስጥ ገቡ። “ለ” የመልስልኝ ጥያቄ ቢያቀርብም “ሀ” አይሆንም አልመልስም ይላል። ተሳታፊዎች በሁለቱ አገራት ባለው የፖለቲካ ሁኔታ አድልኦ ሊያደርጉ ስለሚችሉ እነዚህን ወገኖች መግለፅ አያስፈልግም። (“ሀ” እስራኤል ናት “ለ” ደግሞ ግብፅ ናት) ነገር ግን በካርታው ላይ መጀመሪያ በተለያየ ስም ለምሳሌ “አገር ሀ” እና “አገር ለ” በማለት ብትጠቀምባቸው ከዚያ የሚቀጥሉት ውይይቶች በአገራቱ ጥቅምና ፍላጎት ዙሪያ ባሉ ጥያቄዎች ላይ ያተኮሩ ይሆናሉ። እነዚህን ፍላጎቶችና ጥቅሞች ለመለየት “ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን (grounding questions)”[22] ተጠቀም። ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በተመለከተ በቀጣይ ራሱን የቻለ የትምህርት ክፍል እንደሚኖር ለተሳታፊዎች ግለፅላቸው።

(ማስታወሻ፡ ተሳታፊዎች “ኃያል አገር መሆን ይፈልጋሉ” ካሉ “እሺ በጣም ኃያል አገር መሆን ይፈልጋሉ” ይህ ለነርሱ ለምን አስፈላጊ ሆነ? ብለህ መጠየቅ ትችላለህ። የሌለው አገር ጠንካራ ፍላጎት ተለይቶ ከታወቀ በኋላ እንዲህ ልትላቸው ትችላለህ። “ከዚህ ታሪክ መሬቱ በረሃማ ነዳጅ የሌለበት ወይንም የተፈጥሮ ሃብት የማይገኝበት እና ሰዎች በቅጡ መኖር የማይችሉበት ቦታ ነው።” ተሳታፊዎቹ የሀገራቱ ትልቅ መሻት ብለው የሚያቀርቡት ከተፈጥሮ ሃብት እና ከማንነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደሆኑ መገመት ትችላለህ።)

ደረጃ 2: ተሳታፊዎቹን ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ብለው የሚያቀርቧቸውን አማራጮች ጠይቀህ ወረቀቱ ላይ አስፍራቸው። ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርጉ መፍትሔዎች እነዚህ ናቸው ብለው ከዘረዘሩ በኋላ አገራቱ ግብፅና እስራኤል እንደሆኑ ንገራቸው። በዚህ ጉዳይ ላይ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ተብሎ የተቀመጠው ከጦርነት ነፃ የሆነ ቀጠና ማቋቋም ሲሆን “ለ” ማለትም ግብፅ ጥቅሟ የሆነውን ሉዓላዊነቷን ማስከበር ስትችል “ሀ” ማለትም እስራኤል ደግሞ የደህንነት ጥቅሟን ታስከብራለች።




21 ይህ ስምምነት የካምፕ ዴቪድ ስምምነት ተብሎ ይታወቃል። ይህም በሽምግልና ሂደት ውስጥ ፍላጎትን ለመለየት ከሚያስችሉ የተሻሉ ምሳሌዎች አንዱ ነው። የእስራኤልና የግብፅ ግጭት በቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በጂሚ ካርተር አደራዳሪነት በ1978 እ.ኤ.አ ተከናወነ።

22 በገጽ 37 ላይ ክፍል III 3.4 የሽምግልና ዛፍ ማማ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን መጠቀም የሚለውን ይመልከቱ።

## III.3.2 የብርቱካኑ ምሳሌ[23]

**ዓላማ** ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔን በመጠቀም አቋምን፣ ጥቅምንና ፍላጎትን እንዴት መለየት እንደሚቻልና ሁሉንም ተጋጭ አካላት ማስደሰት እንደሚቻል ማሳየት።

**የተመደበ ጊዜ** 20 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: የብርቱካኑን ታሪክ ለተሳታፊዎች አቅርብ።

ከዕለታት አንድ ቀን አንድ አባት ብሌንና አብዲ (በቀላሉ "ሀ" እና "ለ" ልንለው እንችላለን) ለሚባሉ ሁለት ልጆቹ አንድ ቆንጆ ብርቱካን ይሰጣቸዋል። ሁለቱም ልጆች "ብርቱካኑ የኔ ነው ስጠኝ/ስጪኝ" እያሉ መጨቃጨቅ ጀመሩ። ከዚያም ጭቅጭቃቸው ወደ ጥል ይቀየራል። አባትየው ይህን ጥል እንዴት እንደሚፈታው ማሰላሰል ጀመረ። ልዩ ልዩ ሃሳቦች መጡለት።

ደረጃ 2: ተሳታፊዎቹን ይህንን ጥል እንዴት እንደሚያበርዱ የመፍትሔ ሃሳብ እንዲሰጡበት ጠይቃቸው ሁለቱንም የሚጠቅም መፍትሔ ምንድን ነው?

የተሳታፊዎችን ሃሳቦች በወረቀቱ ላይ አስፍራቸው። የሚሰጡት ሃሳብ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት መካከል ሊሆኑ ይችላሉ።

"ግማሽ ግማሽ እንዲካፈሉ ለሁለት መሰንጠቅ"


"ብርቱካኑ የሚገባው ለታላቅዬው ልጅ ነው"

"አስቀድሞ ለኔ ነው የሚገባው ብሎ የተናገረው ብርቱካኑ ይገባዋል"

"ሁለቱም አያስፈልጋቸውም"

ደረጃ 3: ተሳታፊዎቹ ያቀረቧቸውን የመፍትሔ ሃሳቦች አሰላስሏቸው።
እነዚህ መፍትሔዎች ሁሉን የሚጎዱ ናቸው ወይንስ አንዱን ጠቅመው ሌላውን የሚጎዱ? ምናልባትም ሁሉን የሚጠቅሙ መፍትሔ ሊሆኑ ይችላሉ። ተሳታፊዎች በመጀመሪያ ሁሉን የሚጠቅም የመፍትሔ ሃሳብ ላያቀርቡ ይችላሉ። እስቲ የመጀመሪያውን የመፍትሔ ሃሳብ እንመርምር። "ግማሽ ግማሽ እንዲካፈሉ ለሁለት እኩል መሰንጠቅ" ይህ የተለመደ ባህላዊ የግልግል መንገድ ነው። ግልግል (compromise) ሁለቱንም የሚጠቅም ወይንም ሁለቱንም የሚጎዳ መፍትሔ ተደርጎ ሊቆጠር ይችላል። ይህ ዓይነት መንገድ ሁለቱንም የሚያሳጣ መንገድ ነው ምክንያቱም ምንም እንኳ ሁለቱም ግማሽ ግማሽ ቢያገኙም ግማሽ ግማሽ ደግሞ አጥተዋል ስለዚህም አንዱ ወገን ትልቁን ድርሻ ቢያገኝ ሌላኛው ወገን ደግሞ አነስተኛውን የሚያገኙ በመሆኑ ግልግል አንዱን ጠቅሞ አንዱን በሚጎዳ መልኩ የተቀመጠ የመፍትሔ ሃሳብ ነው።

| | |
|---|---|
| "ብርቱካኑ የሚገባው ለታላቁ ልጅ ነው።" | (አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ) |
| "አስቀድሞ ለኔ ነው የሚገባው ብሎ የተናገረው ይገባዋል" | (አንዱን ጠቅሞ ሌላውን የሚጎዳ) |
| "ሁለቱም አያስፈልጋቸውም" | (ሁለቱንም የሚጎዳ) |



23 ይህ ምሳሌ የ Fisher, R & Ury, W (1981) ሲሆን በሰላም ግንባታ ላይ በሚሰጡ ስልጠናዎች ብዙ ጊዜ ተጠቃሽ ነው።

ደረጃ 4: የዓሳ ማስገር ጨዋታን (III.2.1) በማስታወስ ተሳታፊዎቹን ስለ ጥቅምና ፍላጎት ጠይቃቸው።

ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ አድርግ ደግሞም የመንደርደሪያ ሃሳብ ስጣቸው "ብሌንንና አብዲን ምን ዓይነት ጥቅምና ፍላጎት እንዳላቸው ብንጠይቃቸውስ/ ሁለቱም ብርቱካኑን የፈለጉበት ምክንያት ምንድን ነው?" ተሳታፊዎች የሚያቀርቧቸውን የመፍትሔ ሃሳቦች በወረቀቱ ላይ ዘርዝራቸው። ከዚያም መልሱን ንገራቸው። ብሌን ብርቱካኑን ወስዳ በልጣጩ ኬክ መስራት ስትፈልግ አብዲ ደግሞ በብርቱካኑ ጭማቂ መስራት ይፈልጋል። በዚህ ጉዳይ ላይ ተሳታፊዎቹ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ የመፍትሔ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ጠይቃቸው።

ደረጃ 5: ትምህርቱን ለመከለስ ከዚህ በታች የተቀመጡትን ትርጉሞች በወረቀቱ ላይ ማስፈር ትችላለህ።

- አቋም፡ ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ተጋጭ አካላት የግሌ ጉዳይ ነው ብለው የሚያቀርቡት ተፃራሪ የሆኑ አስተሳሰቦች ናቸው
- ጥቅም፡ በግጭት ወቅት ተጋጭ አካላት ከአቋማቸው የሚመነጭ መነሳሳትና የሚፈልጉት ሁነኛ ነገር ሲሆን
- ፍላጎት፡ በግጭት ወቅት ለተጋጭ ወገኖች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዩች ናቸው እነዚህ ነገሮች የደህንነት፣ የማንነት፣ የማኅበረሰብ፣ ለሰው ሕይወት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዩች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ጉዳዩች ተጋጭ አካላት ለድርድር የማያቀርባቸው በተጠቀሱት መሠረታዊ ፍላጎቶች ላይ ያተኮሩ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

ማሳሰቢያ

ምናልባትም አንድ ተሳታፊ "ብሌን የአብዲ የበላይ መሆን ትፈልጋለች" ወይንም "አብዲ ብሌን ብርቱካኑን እንድታገኝ ስለማይፈልግ ብቻ ነው" ብለው ሃሳብ ቢያቀርቡ የሁለቱን ልጆች የግንኙነት ደረጃ ልታቀርብ ትችላለህ። እንዲህ በማለት ማብራራት ትችላለህ። "ጉዳዩ ይህ ከሆነ እንግዲያው አለመግባባቱ የተፈጠረው በብርቱካኑ አይደለም ባላቸው ግንኙነት እንጂ። እንደሽምጋይ ይህን ጉዳይ በሽምግልና ሂደት ውስጥ ልታካትተው ይገባል።" በተጨማሪም የሹልዝ ቮንትን አራቱ የመልዕክት ሞዴሎችን ማመልከት ትችላለህ።

ይህን ታሪክ ልታሻሽለው ወይንም የቡና ፍሬ በሚል ሌላ ታሪክ ልታቀርብ ትችላለህ። በዚህ ታሪክ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ አንዱ ወገን የቡና ፍሬውን ሲፈለግ ሌላው ደግሞ ገለባውን ሻይ ሊያመርትበት ይፈልጋል። (ይህ ታሪክ ምናልባትም በኢትዮጵያ የተሻለ ምሳሌ ሊሆን ይችላል።) አነዚህን ምሳሌዎች ካቀረብክ በኋላ ተሳታፊዎች አቋም ጥቅምንና ፍላጎትን በሚከተሉት ልምምዶች መቃኘት አለባቸው።



24 ክፍል III.6.1 ተግባቦት እና የሹልዝ ቮን ዙን አራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴልን በገጽ 57 ላይ ይመልከቱ።

## III.3.3 ተግባር፡ በማንጎ ዛፍ ምሳሌ ውስጥ የሽንኩርት ሞዴልን በመጠቀም አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎትን መተንተን

**ዓላማ**

ተሳታፊዎች የሽንኩርትን ሞዴል[25] በመጠቀም ተጋጭ አካላት ያላቸውን ልዩ ልዩ አቋሞች፣ ጥቅሞችና ፍላጎቶችን መለየትና መመርመር ይችላሉ።

**የተመደበ ጊዜ**

60 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች**

የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: በማንጎ ዛፍ ምክንያት በሁለት ሰዎች መካከል ስለተፈጠረው ግጭት ምሳሌ አቅርብ። (ከዚህ በታች እንደ ተቀመጠው ዐይነት ሥዕል በመሳል ለምሳሌነት ተጠቀም) ታሪኩን እንዲህ በማለት መናገር ትችላለህ።


“በማንጎ ዛፍ የተነሳ በሁለት ሰዎች መካከል የተፈጠረውን ግጭት እነግራችኋለሁ። እነዚህ ሰዎች የኔ የቅርብ ጓደኞች ናቸው። የነርሱ ጉዳይ የኔ ጉዳይ ነው። የነርሱን ችግር መፍታተ እንድችል እንድትረዱኝ እፈልጋለሁ።

አንድ ጓደኛዬ ሙሴ ይባላል። አርብቶ አደር ነው። ሌላኛው ጓደኛዬ አዳም ይባላል። እርሱ ደግሞ የማንጎ ዛፍ ገበሬ /አርሶ አደር/ ነው። በዚያ አካባቢ በተነሳ በድንበር ግጭት ምክንያት ለመሰደድ የተገደደው ሙሴ ለዚህ ግጭት የዳረጋቸውን የማንጎ ዛፍ የተከለው እርሱ ነበር። ከስደት ወደ ቤቱ በሚመለስበት ጊዜ አርሶ አደሩ /ገበሬው/ ከማንጎ ዛፍ የተገኘውን ምርት ሰብስቦ ሲጠቀም በማየቱ አልተደሰተም። ከ8 ዓመት በፊት በአርብቶ አደሩ ተተክሎ የነበረውን ይህን የማንጎ ዛፍ አርሶ አደሩ ውሃ ሲያጠጣና ሲንከባከበው ቆይቷል። ሁለቱም የማንጎውን ዛፍ የራሳቸው ንብረት ብቻ አድርገው ይመለከቱታል። አርሶ አደሩ ከማንጎ የሚያገኘውን ምርት መሰብሰብ ቢቀጥል አርብቶ አደሩ ዛፉን እንደሚቆርጠው በመናገሩ ግጭታቸው ጨመረ። አርሶ አደሩም ከዚህ የማንጎ ዛፍ ምርት እንዳይሰበሰብ ቢከለክለው ወደ ጥል እንደሚዞር ይናገራል። በተጨማሪም አርብቶ አደሩ ከስፍራው ለረጅም ጊዜ ርቆ በመቆየቱ የማንጎ ዛፉን እንደሚቆርጠው በመናገሩ ግጭታቸው ጨመረ። አርሶ አደሩም ከዚህ የማንጎ ዛፍ ምርት እንዳይሰበስብ ቢከለክለው ወደ ጥል እንደሚዞር ይናገራል። በተጨማሪም አርብቶ አደሩ ከስፍራው ለረጅም ጊዜ ርቆ በመቆየቱ የማንጎ ዛፉን በተመለከተ የባለቤትነት ጥያቄ ማንሳት አይጠበቅበትም በማለት ይከራከራል።”

**ማሳሰቢያ**

ታሪኩን በምትነግርበት ወቅት:

- ተገቢውን አካላዊ ገለፃ ተጠቀም።
- የፊት ምልክት ተጠቀም።
- ትኩረት የሚስብ የድምፅ አወራረድ ተጠቀም። ነገር ግን የሚጮህ ድምፅን አይሁን።
- ታሪኩን እንደራስህ በማድረግ “እኔ” በማለት አቅርብ።
- ግልፅና አጭር አረፍተ ነገሮችን ተጠቀም።
- በንግግርህ ውስጥ የራስ መተማመን ይታይበት።
- ለምታስተላልፈው ሃሳብ የሚሆኑ ቁልፍ ሀረጎችን ተጠቀም።



25 አንዳንድ ጊዜ የግጭት ንብብር (Conflict Layer Model) ተብሎ ስለሚጠራው የሽንኩርት ሞዴል የበለጠ ማብራሪያ Leonhard, M (2001) ገጽ 66ን ይመልከቱ።

ደረጃ 2: ከዚህ በታች እንደተቀመጠው አቋምን፣ ጥቅምን እና ፍላጎትን በሚያሳይ መልኩ የሽምግልና ሞዴሉን በሚገለጠው ወረቀት ላይ ጽፈህ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አብራራ።

ደረጃ 3: ተሳታፊዎች የአዳምንና የሙሴን አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት ይዘርዝሩ።

**አቋሞቻቸው:**

**አዳም:** "የማንጎው ዛፍ የኔ ነው እኔ ነኝ ያጠጣሁትና የተንከባከብኩት ሙሴ ከ8 ዓመት በኋላ መጥቶ ይገባኛል ሊል አይገባም።

**ሙሴ:** "የማንጎ ዛፍ የእኔ ነው። እኔ ነኝ የተከልኩት በቅድመ አያቶቼ መሬት ላይ ነው ያደገው። አዳም ዛፌንና መሬቴን ይልቀቅልኝ።"

**ጥቅሞቻቸው:**

**አዳም:** ዛፉን ገቢ ለማግኘት ይጠቀምበታል።

**ሙሴ:** ዛፉ ያደገበት የውርስ ቦታ ስለሆነ የመሬቱ ባለቤት እርሱ እንደሆነ እንዲታወቅለት ይፈልጋል።

**ፍላጎቶቻቸው:**

**አዳም:** ሕይወቱ የተመሰረተው በዚህ ማንጎ ዛፍ በሚገኘው ገቢ ነው። ያለበለዚያ መኖር አይችልም።

**ሙሴ:** ህይወቱ የተመሠረተው ከብት በማርባት ስለሆነ መሬቱን ለግጦሽ ይጠቀምበታል።


**ስጋቶቻቸው:**

**አዳም:** ሙሴ ከማንጎ ዛፉ እንዳልጠቀም ይከለክለኛል ብሎ ይሰጋል ።

**ሙሴ:** መሬቱንና የግጦሽ መብቱን አጣለሁ ብሎ ይሰጋል።

ደረጃ 4: በማስተማሪያ ወረቀቱ ላይ የተሰጠውን ትምህርት በመከለስ ክፍለ ጊዜውን አጠናቅ።

- ተሳታፊዎቹ ምሳሌውንና ሞዴሉን ተረድተው እንደሆነ ጠይቃቸው።
- ግብረ-መልስና አስተያየት እንዲሰጡበት ጠይቃቸው።
- ስለሰጡት አስተያየት በማድነቅ ተግባሮችህን አጠቃላቸው።
- ፍላጎታቸውንና ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅ ሁለቱንም የሚጠቅም መፍትሔ ምን እንደሆነ በመጠየቅ የተለያዩ አማራጭ መፍትሔዎችን ተቀበል።



## III.3.4 የሽምግልና ዛፍ ማማ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን (Grounding Questions) መጠቀም

በዚህ ክፍለ ትምህርት ተሳታፊዎች ግጭት በሚፈጠርበት ወቅት ሰዎች ግጭቱን እንዴት እንደሚያስተናግዱት ይማራሉ። የሽምግልና ዛፍ ማማን እንደ ምሳሌነት በመጠቀም ሽማግሌዎች ተጋጭ ወገኖችን ካሉበት ማማ (አቋም) ወደ ታች እንዴት ማወረድ የሚችሉበትን መንገድ ይህም ከአቋማቸው ወደ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚያሸጋግሯቸውን ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ይተዋወቃሉ።

## ተግባር፡ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን እንዴትና ለምን እንጠቀምባቸዋለን

**ዓላማ** ተሳታፊዎች ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ተጋጭ ወገኖችን ካሉበት አቋም ወደ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው እንዴት ማሻገር እንደሚችሉ ይማራሉ።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: ዛፍ ላይ የተቀመጠ ማማ ሳልና በስዕሉ ላይ ያሉትን ሁኔታዎች አብራራ።

ግጭት ባልተከሰተበት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ሰዎች በጋራ መሬታቸው ላይ ይገናኛሉ። ጥሩ ግንኙነት ስለሚኖራቸው ስለ ፍራቻዎቻቸው፣ ፍላጎቶቻቸውና ምኞታቸው ሁሉ ይነጋገራሉ። ነገር ግን ግጭት ሲከሰት ወይንም እየከፋ ሲሄድ ይህ ጥሩ ግንኙነታቸው ይቀንሳል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ተጋጭ ወገኖች ወደ ዛፍ ላይ ማማቸው በመሰላል የሚወጡ ይመስላል። በዚያ ስፍራ ላይ ሲወጡ ደግሞ የይገባኛል ጥያቄያቸውን ወይንም ክሳቸውን በማቅረብ አቋማቸውን ያንፀባርቃሉ። “ይህ ማንጎ የኔ ነው እፈልገዋለሁ” ወይንም “አንተ ሌባ ነህ” ይባባላሉ።

አለመግባባቱ እየተካረረ ሲመጣ ተጋጭ አካላት በምንም አይነት አቋማቸውን የማይለውጡና ለድርድር የማያቀርቡ ይመስላሉ። የጋራ መሬታችን የሚሉት አሁን አይገኝም እንዲሁም አንዱ ካንዱ ጋር ስለማይቀራረቡ ተራርቀዋል። ከአሁን በኋላ የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎታቸውን ማሳወቅ አይችሉም። እስቲ በምናባችሁ አስቡት አንዱ ከዚህኛው ዛፍ  ሌላኛው ከዚያኛው ዛፍ ሁሉም ይጮኻሉ፡። ከዚያም አልፎ ወደ ማማቸው የሚወጡበትን መሰላል አውርደውታል። እነዚህ ሰዎች በፍፁም ዳግም ሊገናኙ የሚችሉ አይመስሉም። እነዚህ አካላት በራሳቸው ተነሳሽነት ከመሰላላቸው መውረድ ስለማይችሉ አስታራቂ ሽማግሌዎች የጋራ በሆነው መሬታቸው ላይ ሊያወርዷቸው ይሞክራሉ። ከዚህ የተነሳ ብዙ ጊዜ ሽማግሌዎች በዚህ በተካረረ ግጭት ወቅት ገላጋይ (intervene) ይባላሉ። ይህ ከዛፉ ላይ እንደመውረድ ቀላል ባይሆንም ግን የማይቻል አይደለም።



ደረጃ 2: የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን ማስተዋወቅ[26]።

ሽማግሌዎች ተጋጭ ወገኖች ካሉበት ማማ አውርዶ በጋራ መሬታቸው ላይ እንዲቀመጡ ለማድረግ ልዩ የሆኑ ጥያቄዎችን ይጠቀማሉ። እነዚህ ጥያቄዎች የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ይባላሉ። እነዚህ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች የተጋጭ አካላት ዕይታ (perspective) ቀይሮ ወደ ጥቅሞቻቸውና ፍላጎቶቻቸው በመመለስ በጋራ መሬታቸው ላይ እንደገና ግንኙነታቸውን እንዲያድሱ ይረዳቸዋል።

## የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች

- ላንተ/ላንቺ በጣም አስፈላጊ የሆነው ምንድን ነው?
- (ይህ ቢሆን) ምን የተሻለ ነገር ይገጥምሃል/ሻል?
- (ይህ ቢሆን) ምን የከፋ ነገር ይገጥምሃል/ሻል?
- ይህ ላንተ/ላንቺ ጥሩ/መጥፎ የሆነው ለምንድን ነው?

## የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ባህሪያት

- ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው።
- ሽማግሌዎች ከተጋጭ አካላቱ አንዱን በሚጠይቁበት ወቅት ሌላኛው ስለጥያቄው የማሰላሰያ ጊዜ ያገኛል።
- ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች አንዱ አካል የሌላውን ሃሳብ በግልፅ እንዲረዳ ያስችለዋል።
- በሁለቱ ወገኖች መካከል የጋራ የሆኑ ነገሮች ሊገኙ ይችላሉ። እነዚህ ነገሮች ለወደፊቱ መፍትሔ ለማምጣት እንደ መንደርደሪያ ሊጠቅሙ ይችላሉ።
- ተጋጭ አካላቱ በሂደቱ የበለጠ ግልጽ ይሆናሉ።
- ለቀጣይ መፍትሔዎች የሚጠቅሙ እንደጋራ መሬት የሚሆን መስማሚያዎች ሊገኙ ይችላሉ።
- ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች የሁለቱንም አካላት ድብቅ ፍላጎት ለመረዳት ይጠቅማሉ።
- አዎንታዊ መፍትሔ በሚያመጡ አማራጮች ላይ ትኩረት ለመስጠት ያስችላሉ።
- ሽምጋዩ በሽምግልና ወቅት ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም በሁለቱም አካላት ንግግር መሃል ጣልቃ ቢገባ እንኳን ተጋጭ ወገኖች ቅር አይሰኙም።

[26] "ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች" የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋወቀው በኢሚዲዮ በርሊን ሲሆን የግጭቱ ምንጭ ለማወቅ እነዚህን ጥያቄዎች በመጠቀም የተደበቁ አቋሞች፣ ጥቅሞችን እና ፍላጎቶችን ለማወቅ ያስችላል።

## III.3.5 ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ከአቋም ወደ ጥቅምና ፍላጎት እንዲሸገሩ መርዳት

የተዘረዘሩትን ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች በማንበብ ብቻ ለሽምግልና ለመጠቀምና ወደ ተግባር ለመለወጥ ቀላል ሊመስል ይችላል። ይልቁንም በጣም ውስብስብ ከመሆናቸው የተነሣ እነዚህን ጥያቄዎች አዘጋጅቶ ለማስቀመጥ የሰለጠነ የሽምግልና ባለሙያ ያስፈልጋል። ስለዚህም ከዚህ በታች የሚከተሉትን መልመጃዎች ከተሳታፊዎች ጋር አከናውን።

**ዓላማ** ተሳታፊዎች ስለማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ያላቸውን ግንዛቤ ይጨምራል። በልምምዳቸውም መተግበር ይችላሉ።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ /ግምገማን ጨምሮ/

**መርጃ መሣሪያዎችና ተፈላጊ ሰዎች** ሁለት አሰልጣኝ፣ ሁለት ሰልጣኝ፣ ሶስት ወንበሮች፣ እንደሪሞት ኮንትሮል ሆኖ የሚያገለግል ዕቃ፣ ሁለት የወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳዎች፣ የሽንኩርት ሞዴል እና የሽምግልና ዛፍ ማማ ሥዕል ያለበት ወረቀት፣ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ተሳታፊዎች ክብ ሰርተው እንዲቀመጡ አድርግ። በሁለቱ የወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳዎች ወይንም በክፍሉ ግድግዳዎች ላይ የሽንኩርቱንና የሽምግልና ዛፍ ቤት ሞዴሎችን ለጥፋቸው። የፊልም አሠራር ስልት[27] በመጠቀም ሰልጣኞቹን በማሳተፍ የሽምግልናውን ሂደት በጭውውት መልክ እንደሚከተለው እንዲጫወቱት አድርግ። ከሰልጣኞቹ አንዱ ሽምጋይ ይሆናል። ሌላው ደግሞ ለተመልካቾች /ለሌሎች ተሳታፊዎች/ የሽምግልናው ሂደት እንዴት እንደሚከናወን የሚያሳይ የፊልም ዳይሬክተር ወይንም አስተባባሪ ይሆናል። የሽምግልናው ሂደት ፊልሙ በሚቀረፅበት ወቅት አስተባባሪው /ዳይሬክተሩ/ በተጋጭ ወገኖች መካከል የሚታየውን የባህሪ ለውጥና ሽምጋዩ የሚጠቀምበትን ቴክኒክ (ስልት) ለተሳታፊዎች ግልፅ አድርጎ ያሳያል። ዳይሬክተሩ ተሳታፊዎቹ ሪሞት ኮንትሮሉን በመጠቀም ፊልሙን በማቆም ጣልቃ በመግባት የሽምግልናውን ሂደት እንዲወያዩበት ይጋብዛል።

ለጭውውቱ የማንጎ ዛፍ ግጭትን ወይንም ተሳታፊዎች ከዚህ በፊት የተለማመዱትን ሌላ ምሳሌ ተጠቀም። አለመግባባቱ እየከረረ በመጣ ወቅት እና ተጋጭ ወገኖች ወደ ሽምግልና ዛፍ ማማ ጫፍ በሚወጡበት ሰዓት ባለው ትዕይንት ጀምር። ያም ተጋጭ ወገኖች ሽምጋዩ በሚመጣበት ሰዓት አቋማቸውን በሚያንፀባርቁበት ወቅት ማለት ነው።

ደረጃ 2: እንደ ዳይሬክተር የመቀመጫዎቹን ቦታ በሶስት ጎን ቅርፅ አስቀምጣቸው። ከዚያም ከተሳታፊዎች አንዱን እንደ ሽምጋይ ሌሎች ሁለት ተሳታፊዎችን እንደተጋጭ አካላት በመሆን እንዲጫወቱ ወደ ወንበሩ ጋብዛቸው። ሁሉም መቀመጫቸውን ይይዛሉ። ስለ ጉዳዩ አጠር ያለ መግለጫ ስጥተህ ሽምጋዩ ሁለቱን ተጋጭ አካላት ከነበሩበት የሽምግልና ዛፉ ቤት ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም የጋራ መሬታቸው ላይ እንደሚያወርዷቸው ለተሳታፊዎች በጭውውቱ እንደሚመሩ ግለፅላቸው።

ደረጃ 3: ሽምጋዩ ተጋጭ አካላትን ስለግጭታቸው እንዲወያዩ ይጠይቃቸዋል። እነርሱም አቋማቸውን ይገልፃሉ። ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ሽምጋዩ የነዚህን አካላት ጥቅምና ፍላጎት ለማወቅ ይጥራል።

ደረጃ 4: ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ዳይሬክተሩ ጣልቃ ይገባና ትዕይንቱን ያስቆማል። ተመልካቾቹን ተጋጭ አካላት ምን ዓይነት የባህሪ ለውጥ አምጥተው እንደሆን በተለይም ሽምጋዩ የባህሪ ለውጥ እንዲያመጡ በማድረግ እንዴት እንደተሳካለት የተገነዘቡት ነገር ካለ ጠይቃቸው።

27 ይህ መልመጃ የሚና ነጠቃ ጨዋታ ሃሳብን ያዘለ ሲሆን የተቀናበረው በMaike van Ueuem (2012) ነው።

ደረጃ 5: ተሳታፊዎች ስለ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች የተገነዘቡትን ከዘረዘሩ በኋላ ዳይሬክተሩ የማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን ጽንሰ ሃሳብ (concept) በጥልቀት አስተዋውቆ በብዛት በስራ ላይ እየተጠቀሙ ያሉትን በወረቀት ላይ በመገልበጥ በሰሌዳው ላይ ይለጥፋል።

ደረጃ 6: ዳይሬክተሩ ተሳታፊዎች ራሳቸው በሽምጋዩ በኩል ተጋጭ ወገኖችን ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች እንዲጠይቋቸው ይጋብዛቸዋል። ሽምጋዩ ጥያቄዎቻቸውን ተቀብሎ ጭውውቱን ይቀጥላል። ይህ ለጥቂት ደቂቃዎች ደጋግሞ ሊሠራ ይችላል።

ደረጃ 7: ተሳታፊዎች በጭውውቱ የቀረበውን ከተወያዩበት በኋላ ለግጭቱ መፍትሔ ይፈልጉለታል።

ደረጃ 8: ዳይሬክተሩ ተሳታፊዎቹ ከጭውውቱ የተማሩትን ትምህርት በማስታወሻው ላይ ይይዛል።

ማሳሰቢያ

ይህ አሳታፊ የሆነ ማስተማሪያ መንገድ ከ10 እስከ 15 የሚደርሱ ተሳታፊዎች ያሉት የተለያዩ ቡድኖችን በመፍጠር ሊከናወን ይችላል።



በሚቀጥለው ገጽ የሚና ነጠቃ ጨዋታ ምሳሌዎች ተዘርዝረዋል። ማስማሚያ መሪ ጥያቄዎች ተሰምሮባቸዋል።

አዳም: የማንጎው ዛፍ የኔ ነው። ስንከባከበው ነበር ለብዙ ጊዜ ተጠቅሜበታለሁ።
ሙሴ: አይ የኔ ነው። እኔ ነኝ የተከልኩት ስለዚህ የኔ ንብረት ነው።
አዳም: አይደለም የማንጎው ዛፍ የኔ ነው ከዚህ በፊት እንደተናገርኩት ውሃ በማጠጣት የተንከባከብኩት እኔ ነኝ።
ሽምጋዩ አዳምን: ለአንተ ይህን የማንጎ ዛፍ ለመጠቀም በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
አዳም: ለኔ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ማንጎዎቹን በመጠቀም ኑሮዬን እመራበታለሁ።
ሽምጋዩ አዳምን: ካሁን በኋላ ይህን የማንጎ ዛፍ ባትጠቀም ምን የከፋ ነገር ሊገጥምህ ይችላል?
አዳም: የኔና የቤተሰቤ የኑሮ መሰረት ስለሆነ ወደፊት ህይወታችንን ለመምራት እንቸገራለን።
ሽምጋዩ ሙሴን: በትክክል ተረድቼህ ከሆነ ይህ የማንጎ ዛፍ ላንተ እንደሚገባህ ተናግረሃል። ይህን የማንጎ ዛፍ እንድትጠቀምበት በጣም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
ሙሴ: ይህማ ግልፅ ነው የተከልኩት እኔ ስለሆንኩ ለኔ ነው የሚገባው።
ሽምጋዩ ሙሴን: እሺ አንተ የተከልከው ስለሆነ ላንተ እንደሚገባህ ገብቶኛል። "እኔ ነኝ የተከልኩት" ብለህ እንድትናገር ያደረገህ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት ምንድነው?
ሙሴ: እኔ የማንጎ ዛፍ ባለቤት ነኝ። የተከልኩት ልጠቀምበት ነው።
ሽምጋዩ ሙሴን: ይህን የማንጎ ዛፍ ባትጠቀምበት ምን የከፋ ነገር ይገጥምሃል?
ሙሴ: ይህን ዛፍ ከተከልኩት በኋላ ከመሬቴ ላይ ተገድጄ እንድነሳና ከዚህ አካባቢ እንድለቅ ተደርግያለሁ። አሁን ግን ከቤተሰቤ ጋር ተመልሻለሁ። የቀረን ይህ ብቻ ነው። መብቴስ?
ሽምጋዩ ሙሴን: ይህን የማንጎ ዛፍ ብትጠቀም ምን የተሻለ ነገር ይገጥምሃል?
ሙሴ: መብቴን አስከብርበታለሁ።
(አስተውሉ: ሙሴ አቋሙን እየቀየረ ነው። ሽምጋዩ በተደጋጋሚ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ቃላታቸውንም በመቀያየር ይጠይቀዋል።)
ሽምጋዩ ሙሴን: የባለቤትነት መብትህን ብታጣ ስጋትህ ምንድን ነው?
ሙሴ: ያፈራነውን ሁሉ ንብረት ከኋላችን ትተን እንድንሄድ ሁኔታዎች አስገድደውን ነበር የማንጎ ዛፉን ማጣታችን የሚያሳየን ነገር አለ። ነገ ደግሞ መላ ንብረታችንንና መሬታችንን እናጣለን። ምናልባትም ከዚያ በኋላ ደግሞ እንደገና ልንሰደድ እንችላለን።

ሽምጋዩ ሙሴን: እንደተናገርከው ስጋትህ ከመሬቱና ከንብረትህ እንዳትፈናቀል ነው። ይህ ላንተ ምን ማለት ነው?
ሙሴ: ይህ ማለት ብዙ ነገር ነው ቤት አልባ እንሆናለን። የሚደግፈን ነገር እናገኝም። እንዋረዳለን እኔ ብቻ ሳልሆን መላ ቤተሰቤንና ዘሬን አሰድባለሁ።
ሽምጋዩ ሙሴን: አመሰግናለሁ በትክክል ተረድቼህ እንደሆነ የፈራኸው ዘርህ እንዳይሰደብ ነው። አሁን ደግሞ አዳምን እጠይቀዋለሁ።
ሽምጋዩ አዳምን: ከዚህ የማንጎ ዛፍ እንዴት ትጠቀማለህ? የማንጎውን ዛፍ መጠቀም ባትችል ስጋትህ ምንድን ነው?
አዳም: ለረጅም ጊዜ ከዚህ የማንጎ ዛፍ ተጠቅሜበታለሁ። ይህን ዛፍ መጠቀም ባልችል ምንም ገቢ አይኖረኝም። በማንጎው ዛፍ ላይ ያለኝ የባለቤትነት መብቴን አጣለሁ።
ሽምጋዩ አዳምን: የባለቤትነት መብት ማለት ላንተ ምን ማለት ነው? ብታጣውስ?
አዳም: ለኑሮዋችን ገቢ ለማግኘት ያለን ብቸኛ አማራጭ ይህ የማንጎ ዛፍ ነው። እርሱ ለረጅም ጊዜ በስፍራው ስላልነበረ እኛ ይህን ማንጎ እንፈልገዋለን። እኔ ባላጠጣው እኔ ባልንከባከበው ኖሮ ምን ይሆን ነበር? እንዲህ ሊያድግ አይችልም ነበር። በዚህ ጊዜ ሁሉ ማንጎውን በማጠጣቴና በመንከባከቤ አመሰግናለሁ እንኳ አላለኝም።
ሙሴ: ትክክል! ነገር ግን ሳይተክሉ የማንጎ ዛፍ የለም።
ሽምጋዩ /የሁለቱንም ሃሳብ ያጠቃልላል/: አመሰግናለሁ። አዳም እንደተረዳሁህ ከሆነ መሬቱንና ንብረቴን አጣለሁ የሚል ስጋት አለህ። ይህን አጣሁ ደግሞ መኖሬ ምንድንነው የሚል ፍራቻ ነው ያለህ።
/ሽምጋዩ ወደ ሙሴ በመዞር/: ሙሴ የማንጎው ዛፍ አንተና ቤተሰብህ እዚህ የመኖራችሁና የንብረታችሁ ምልክት እንደሆነ ስትናገር ሰምቼሃለሁ። እንዲሁም አዳም አንተም ህይወቴ የተመሰረተው ከዚህ ዛፍ ጋር በተያያዘ ነው ስትል ሰምቼሃለሁ ቤተሰብህን ለመመገብ የማንጎውን ዛፍ ትፈልጋለህ። ላንተ አንድ ጥያቄ አለኝ። አዳም ይህን ያህል ጊዜ ሁሉ ውሃ በማጠጣቱ ምን ይሰማሃል?
ሙሴ: አዎ ማንጎው እንዲያድግ ትልቅ አስተዋፅዎ አድርጎል።
አዳም: እኔም የማንጎውን ዛፍ መጠቀም እፈልጋለሁ። ብንካፈለው ደስ ይለኛል። ይህን ዛፍ ስለተከልከው እኔም አመሰግናለሁ።
ሙሴ: ምንም አይደል። ዛፉን ውሃ ስላጠጣኸው በጣም አመሰግናለሁ። እኔም ለማንጎ ዛፍ ያደረኩትን አሁን የተቀበልክልኝ ይመስለኛል። የባለቤትነት መብቴን ተቀብለህ አረጋግጠህልኛል። ስለዚህም ያንተን ምክንያቶች እንደገና ማጤን እፈልጋለሁ። እኔ ለዚህ ዛፍ ያደረግሁትን እንድታውቅልኝ እፈልጋለሁ።

## III.3.6 ተግባር፡ መሰላል[28]

**ዓላማ** ተሳታፊዎች ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ በማቅረብ ላይ ያላቸውን ክህሎት ለማሳደግ እንዲሁም የጥያቄዎቹን አስፈላጊነት በጥልቀት እንዲረዱ ማድረግ።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የተለያየ ቅርፅ ያላቸው ባለቀለም ካርዶች፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: በካርዶቹ በመጠቀም በመሬት ላይ የ“መሰላል” ሥዕል በመስራት /ስዕሉን ተመልከት/ በመሰላሉ አንዱ ጫፍ የሽምግልና ማማ በሌላኛው ጫፍ የ“ጋራ መሬት”ን የሚወክል ሥዕል ወይንም ካርድ አድርግበት።

ደረጃ 2: ለ5 ደቂቃ ያህል ተሳታፊዎቹን “ወደ ሽምግልና ማማ” እንዲመጡ ጋብዛቸው። ይህም ማለት ተጋጭ ወገኖች ግጭታቸው የባሰ ሁኔታ ውስጥ የገባበትን ጊዜ የሚያውቁት ወይንም እነሱም ቢሆኑ ተካፋይ የሆኑበትን ታሪክ ያስታውሱ። እነዚህም ወገኖች በዛፉ ጫፍ ላይ ወጥተው የቀሩበትን ሁኔታ ያስታውሱ።

ደረጃ 3: ታሪኩን እንዲያካፍሉ ተሳታፊዎችን ጠይቃቸው። ታሪኩን ለማቅረብ ፈቃደኛ የሆነው ሰው በክፍሉ ወለል ላይ ባለው የሥዕል መሰላል አንዱ መጨረሻ ላይ በመሆን በሽምግልና ማማው ጫፍ በመቆም የተጋጭ አካላትን አቋም ያቀርባል።

ደረጃ 4: ሌሎች ተሳታፊዎች ይህን ታሪክ ለሚናገረው ሰው እንደሽምጋይ በመሆን ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም እንዲጠይቁት አድርግ።

ደረጃ 5: ታሪኩን የሚነግረን ሰው እየተጠየቀ ያለው ጥያቄ ወደ እውነተኛ ፍላጎቱ (ወደ መሬት) የሚመራው ከሆነ ከመሰላሉ አንድ ደረጃ ወደታች ይወርዳል። ነገር ግን ጥያቄዎቹ ወደ አቋሙ (ወደ ሽምግልናው ማማ) የሚመሩት ከሆነ አንድ ደረጃ ወደ ላይ እንደገና ይመለሳል። ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎቹን መሬት እስኪወርዱ ድረስ መቀጠል።

ደረጃ 6: በዚህ የተግባር ልምምድ ያገኙትን ልምድ ጠይቀህ የሰሩትን በመገምገም መልሶቻቸውን በወረቀቱ ላይ አስፍር።

ደረጃ 7: በወረቀቱ ላይ የተዘረዘሩትን ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች እንደገና በመከለስ እነዚህን ጥያቄዎች ምን ዓይነት ባህሪ እንዳላቸው ተሳታፊዎቹ እንዲደጋግሙት አድርግ። እነዚህም ባህርያት ግልፅነታቸው፣ ስሜትን የሚነኩ መሆናቸውና የመሳሰሉት ናቸው። ከዚህ በፊት ግጭት በተፈጠረበት ወቅት እንደዚህ ዓይነት ጥያቄዎች ተጠቅመው ከሆነ ልምዳቸውን እንዲያካፍሉ ጠይቃቸው።




28 ይህ የተግባር መልመጃ በአቶ አትክልት ዳንኤል የቀረበ ነው።

## III.3.7 የቆሎ ምሳሌ[29]

የቆሎ (የድምፅ አልባ እንቅስቃሴ) ምሳሌ የሽምግልና ሂደቱን ደረጃ የምንረዳበት ዘይቤ ነው። ይህም በአቋምና በጥቅም መካከል ያለውን ልዩነት የምንረዳበት መንገድ ነው። ብዙ ጊዜ ከክፉ ንግግር /አቋም/ በስተጀርባ የተለያዩ ድብቅ ጥቅሞችና ስጋቶች መኖራቸውን ያሳየናል።

የተጋጭ አካላትን ክፉ አቋም የሚያሳይበት ዘይቤ የተጨበጠ እጅ ነው። ጠበኛ ያስመስላል። ነገር ግን የተጨበጠው እጅ ሲከፈት የተለያየ ቁጥር ያላቸው የቆሎ ፍሬዎች ይገኛሉ። የዚህም ምሳሌ የሚያሳየው በተደበቀ አቋም "ውስጥ" የተለያዩ ፍላጎቶች ፣ ስሜቶችና ፍራቻዎች እንደሚገኙ ነው።

በሽምግልና ሂደት ውስጥ ተጋጭ አካላት በመጀመሪያ ፍላጎታታቸውን ግልፅ ያደርጋሉ። ሽምጋዩም አማራጭ ጥያቄዎችን በመጠቀም ሊረዳቸው ይችላል። በመቀጠልም እነዚህ አካላት ሃሳቦቻቸውን በማሰባሰብ በጉዳዩ ላይ ይወያዩባቸዋል። በሶስተኛ ደረጃ እነዚህ አካላት (በፊት የተደበቀውን) ፍላጎቶቻቸውን ይገላለጣሉ። ሽምጋዩ በመካከላቸው የጋራ መረዳት እንዲፈጠር እየረዳቸው ሁለቱም አካላት አንዱ የሌላኛውን አካል ፍላጎት ለመረዳት ቢያንስ ቢያንስ ለማክበር ይጥራል። በመጨረሻም በጋራ ከፈጠሩት መረዳት የተነሳ መፍትሔ ለመፈለግ አንዳንድ ፍላጎታታቸውን ብሎም የሌላኛውን አካል አንዳንድ ፍላጎቶች ማጠቃለል (መጭመቅ) ይጀምራሉ።



**ሥዕል 1**
ቡድን "ሀ" እና ቡድን "ለ" ፊት ለፊት ተቀምጠዋል። ፊታቸው የተኮሳተረና የተጨበጠውን መዳፎቻቸው ከፍ አድርገው ያሳያሉ።
**ይህ ምን ማለት ነው?**
እነዚህ ወገኖች መካከል ግጭት አለ ማለት ነው። በሚገናኙበት ወቅት የተካረረ አቋማቸውንና ስድብ ይገልጻሉ። የተጨበጠው መዳፋቸው ያላቸውን አቋም ያሳያል። የሌላኛውን አካል አቋም ሊያዩ ቀርቶ የራሳቸውን ስሜት፣ ስጋትና ተስፋ ማየት ተስኗቸዋል።

29 Wüstehube, L (2009)











## ምስል 2 እና 3

ሽምጋዩ ተጋጭ አካላትን ያነጋግራል። በእጃቸው መዳፍ ያለውን ሲከፍቱት ቆሎ (የቆሎ ፍሬዎች) ያገኛሉ። በዚህ ደረጃ ያለ ሽምግልና በተናጥል ሊደረግ ይችላል።

## ይህ ምን ማለት ነው?

ሽምጋዩ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች ወይንም ሌሎች የተግባቦት ክህሎቶችን በመጠቀም ግልፅ እንዲሆኑ (መዳፎቻቸውን እንዲከፍቱ) ጣልቃ ይገባል። ሽምጋዩም ከአቋማቸውና ከሚጠይቁት ነገር ይልቅ በጥቅሞቻቸው፣ ፍላጎታቸውና ፍራቻዎቻቸው (የቆሎ ፍሬዎቹ) ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ይረዳቸዋል። አሁን እያንዳንዱ ተጋጭ አካል የራሱ የሆነውን ጥቅም ለማየት ዕድል ያገኛል። ይህም ሌላኛውን አካል ለመረዳት የመጀመሪያው ደረጃ ነው። ለራስ ግልፅ ማድረግ (self-clarification) ለሁለተኛው ደረጃ ቅድመ ሁኔታ ያመቻቻል። ይህም አመለካከትን መቀየር ነው።

## ምስል 4 እና 5

ሶስቱም ሰዎች በሶስት ጎናዊ አቀማመጥ ተቀምጠዋል። በዚህ ጊዜ ሽምጋዩ በሁለቱ ወገኖች መካከል ይገኛል። አሁን ሁለቱም ወገኖች እርስ በርስ ይተያያሉ። አሁን ፊታቸው ፊታ ያለ እንዲሁም አይን ለአይን ይተያያሉ። አልፎም ለአመል ያህል ፈገግ ይላሉ። በመዳፎቻቸው የቆሎ ፍሬዎችን ይዘው አንዱ ላንዱ እያሳየ ስለያዙት ቆሎ ያብራራሉ። በምስል 5 ላይ ብለውም የተወሰነ ቆሎ ይሰጣጣሉ።

## ይህ ምን ማለት ነው?

እነዚህ ወገኖች አሁን ስለተደበቀው ጥቅማቸው፣ ስሜታቸው፣ ፍላጎታቸውና ስጋታቸው (የተለያዩ የቆሎ ፍሬዎች) ለመነጋገር ፈቃደኛ ናቸው። በተጨማሪም ሌላውን አካል በትኩረት ለማዳመጥ፣ ለመረዳት እንዲሁም ለመቀበል ተዘጋጅተዋል። የአመለካከት ለውጥ አሁን ሊመጣ ይችላል።

## ምስል 6

ሁለቱ ወገኖች ይተቃቀፋሉ።

## ይህ ምን ማለት ነው?

እነዚህ አካላት እርስ በርስ ከተግባቡ እና አመለካከታቸውን ከቀየሩ በኋላ የሚጠቅማቸውን /ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ/ መፍትሔ ለማግኘት ተዘጋጅተዋል። ነገር ግን ልንገነዘበው የሚገባው ነገር መግባባት ማለት መስማማት ማለት አይደለም። መግባባት ማለት የሌላኛውን አካል የተለየ አመለካከት ማክበር ማለት ነው። በሌላ አነጋገር "ለክፉ" ባህሪም ቢሆን መቶ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በሽምግልና ሂደቱ መጨረሻ እነዚህ አካላት ዘላቂ በሆኑ መፍትሔዎች በመስማማት ግንኙነታቸውን ያሻሽላሉ ወይንም ያድሳሉ። ግጭቱ ተወግዷል።

እስከአሁን እንዳየነው የተጋጭ አካላትን አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም ለግጭት የዳረጋቸውን ውስጣዊ ግፊት ልንረዳበት እንችላለን። ስለዚህ ይህን አውቆ መልሶ ለራሳቸው ማሳየትና ለችግሮቻቸው የሚሆኑ ልዩ መፍትሄዎች እንዲያገኙ መርዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ሽምጋዮች የተጋጭ አካላትን ጉዳይ ፈልፍሎ ማግኘት እንዲሁም ተጋጭ አካላት ስሜቶቻቸውን ማንፀባረቅ ብቻ በቂ አይደለም። ሽማግሌዎች እነዚህ አካላት በትብብርና ለመተባበር ዝግጁነት በተሞላ ስሜት በጋራ ለችግሮቻቸው እንዲሰሩና ዕይታቸውን እንዲለዋወጡ ሂደቱን ማስተባበር ይጠበቅባቸዋል። በሚቀጥለው ክፍል ይህን የሚያከናውኑበትን ስልት እንመለከታለን።



## “Yoo waligalaan alaa galaan.”

### “ሰዎች እርስ በርስ የሚግባቡ ከሆነ ይስማማሉ።”

### (ኦሮምኛ ብሂል)



| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | በስልጠናው መጨረሻ ሰልጣኞች በተጋጭ ወገኖች መካከል የሚታየውን የዕይታ ልውውጥ ለማስተባበር የሚያስፈልጋቸውን እውቀት ያገኛሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 170 ደቂቃ |
| **መነሻ ዕውቀት** | III.3 3 አቋም፣ ጥቅምና ፍላጎት። |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ፣ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ባለቀለም ካርዶች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: ሰውና አይጥ የተባለውን የተግባር ልምምድ ማቅረብ (III.4.2)። |
| | ደረጃ 2: የግጭት ዕይታ ትንተናን ማስተዋወቅ (III.7)። |
| | ደረጃ 3: የመልመጃውን አግባብነት ከሌሎች የህይወት ተሞክሮዎች ጋር በማዛመድ አብራራ። |
| | ደረጃ 4: የእርሻ ልማት (III.7) ግጭት ምሳሌን በመጠቀም ተግባራዊ ልምምዶችን ማቅረብ። |

ለግጭት ያለን ዕይታ በሚለው ልምምድ /III 1.2/ ስር እንደተመለከትነው ሰዎች ግጭትን በተለያዩ ምክንያቶች በልዩ መልኩ ይረዱታል። በሽምግልና ሂደት ውስጥ ተጋጭ አካላት አንዱ ለሌላው ያለውን ዕይታ /ግንዛቤ/ እንዲገልፅ መርዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ከዚህ በመቀጠል የሚቀርቡት ልምምዶች እና ተከታታይ ውይይቶች ተጋጭ አካላት እርስ በርስ ያላቸውን ዕይታ እንዲለዋወጡ እንዴት መርዳት እንዳለብን ያተኩራል።

## III.4.1 ተግባር፡ ሶስት ጊዜ ማጽመጥ

| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | በሽምግልና ወቅት ማድመጥ በጣም አስፈላጊ እንደሆነና በንቃት የመከታተል ልምድ እንዲያገኙ ማድረግ፣ በንግግር ወቅት አካላዊ ቋንቋ፣ ምልክት መስጠት እንዲሁም የፊታችን ሁኔታ ምን ያህል አስተዋፅዎ እንደሚያደርግ ይረዳሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 20 ደቂቃ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ባለቀለም ካርዶች፣ ማርከሮች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: ተሳታፊዎቹን በሶስት መድባቸው። አንድ ሰው እንደታዛቢ በመሆን ትንሽ ራቅ ብሎ ይቀመጣል። ሁለቱ ቡድኖች ፊት ለፊት እየተያዩ ይቀመጣሉ። አንዱ ተራኪ ሲሆን ሌላኛው አድማጭ ይሆናል። እያንዳንዱ ጭውውት ሶስት ደቂቃ የሚፈጅ ሶስት ዙር ይኖረዋል።<br><br>ደረጃ 2: ተራኪው የግሉን ታሪክ (አንድ የሚኮራበትን ነገር) ለሰሚው ይነግረዋል። በመጀመሪያ ዙር ሰሚው የሰለቸው በመምሰል መቅረብ አለበት። ይህን ሲያደርግ ምንም ዓይነት ቃላትን መጠቀም አይችልም። ነገር ግን በአካላዊ ቋንቋ፣ በምልክት ወይንም በማስመሰል ይገልፀዋል። ታዛቢው የተመለከተውን ድርጊት /እንቅስቃሴ/ ይመዘግበዋል። |



ደረጃ 3: በሁለተኛው ዙር ተራኪው ሌላ ታሪክ /አንድ የተናደደበትን ነገር/ ለሰሚው ይነግረዋል። በዚህ ጊዜ ሰሚው በጣም በትኩረት ነገር ግን የተለየ ነገር በሌለበት መልኩ ማለትም ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ሳያሳይ ያዳምጠዋል። አሁንም ምንም ዐይነት ቃላት መጠቀም አይችልም። ምንም ዓይነት ስሜት አያሳይም። አሁንም ታዛቢው የተረዳውን ነገር ይመዘግባል።







ደረጃ 4: በመጨረሻ ዙርም ተራኪው የመጀመሪያውንና ሁለተኛውን ታሪክ ደግሞ በሚናገርበት ጊዜ በልዩ ስሜትና በንቃት ይከታተለዋል። ሰሚው ቃላት ሳያወጣ ነገር ግን በአካላዊ ቋንቋ፣ በምልክቶችና ራስን በመነቅነቅ ብቻ ታሪኩን ይከታተላል። አሁንም ታዛቢው የሚረዳውን ይመዘግባል።

ደረጃ 5: የተሳታፊዎቹን ልምምድ ገምግም። መጀመሪያ ታዛቢዎቹ የተረዱትን በወረቀቱ ላይ ያስፍሩት። ሁለተኛ የታሪክ ተናጋሪዎቹን ስሜት እንዲሁም ታሪኩ በሚነገርበት ወቅት ሰሚው የነበረውን ስሜት በወረቀቱ ላይ ያስፍሩት።

ደረጃ 6: ከዚያ በመቀጠል ከሽምጋዩ በተገኘው ትምህርት ላይ ውይይት አድርጉበት። በመጨረሻም ከዚህ የተግባር ልምምድ የተገኘውን ትምህርት ከልሱ።

ማሳሰቢያ

ሰሚው ምንም ዓይነት ምልክት ሳያሳይ ሲቀር ወይንም መስሎ ሲቀርብ ንግግራቸው ብዙም ሳይቆይ ይቆማል። ወይንም ደግሞ ሰሚው በአጠገቡ ሌላ ታሪኩን የሚሰማ ሰው እንዳለ ይቃኝና ሌላኛውም ሰው እንደሱ ዓይነት ስሜት ውስጥ እንደገባ ዓይነት አድርጎ ይመለከተዋል።

ተግባቦት (communication) በንግግርም ሆነ ያለ ንግግር የሚከናወን የማድመጫ መንገዶች አሉት። እነዚህ በሽምግልና ሂደት ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነገሮች ናቸው። ስለዚህም በተገቢውና ትክክለኛ በሆነ መልኩ (መንገድ) መነጋገርና መስማት መቻል ለሽምጋዮች መሠረታዊና አስፈላጊ ክህሎት ነው። ይህ ክህሎት ሽምግልና በተገቢው መንገድ እንዲከናወን ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያደርጉ በመሆናቸው ከዚህ በመቀጠል የምናገኘው ምዕራፍ በሽምጋዮች ዘንድ ሊገኝ ስለሚገባው አስፈላጊ ክህሎቶችና በየትኛው ሰዓት እንደምንጠቀምባቸው ትኩረት ሰጥቶ ያቀርብልናል።

## III.4.2 ተግባር፡ ሰውና አይጥ[30]

**ዓላማ**

በሰዎች መስተጋብር በተለይም በግጭት ወቅት ፍፁም ዕውነት የሚባል ነገር እንደሌለ ይመለከታሉ። እያንዳንዱ ገጠመኝ የአመለካከታችን ጥገኛ ነው። አመለካከታችን ደግሞ ባለን ታሪክና ባገኘነው ልምድ ይወሰናል። በተጨማሪም አንዱ አካል በድንገት የሌላው ሃሳብ ሲገባው ወይንም ልክ ስሜቱ ተሰምቶት አሁን ገባኝ በማለት የሚረዳበትን ቅፅበት ምን እንደሆነ ተሳታፊዎች ይለማመዳሉ። ይህ አረዳድ ወይንም የዕይታ ለውጥ በያንዳንዱ በማመቻቸትና በማቀራረብ የሽምግልና ሂደት ውስጥ ወሳኝ ለውጥ የሚያመጣበት ደረጃ ነው።

**የተመደበ ጊዜ**

30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች**

የሚገለጥ ወረቀት፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ፣ ስፒል፣ ካርዶች፣ ባለቀለማት ማርከሮች፣ አስቀድሞ የተሣለ የሰውና የአይጥ ሥዕል /ሥዕሉ በእኪያ ሐ ላይ ይገኛል/።

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ተሳታፊዎች በሁለት መደዳ ወንበሮቻቸውን ጀርባ ለጀርባ በማድረግ በጥንድ ይቀመጣሉ።



ደረጃ 2: በሁለቱም መደዳ የመጀመሪያውን ሥዕል ያለ ማብራሪያ አሳያቸው ከዚያም ይህን ያሳየኋችሁ ለልምምዳችን ዝግጅት እንዲሆን ነው ብለህ ንገራቸው። ከዚያ በመቀጠል ለመጀመሪያው መደዳ የአይጥ ምስል አሳያቸው መደዳውን ካሳየህ በኋላ ወደሚቀጥለው መደዳ በምትዞርበት ጊዜ ተሳታፊዎች ሳያዩህ/ሳያስተውሉ የምታሳያቸውን ምስል ቀይረህ የሰው ፊት ያለበትን ምስል አሳያቸው። ምናልባት ከመጀመሪያው መደዳ አንዱ ተሳታፊ ዞር ብሎ እንዳይመለከት በመጠንቀቅ ምስሉን ዝቅ በማድረግ አሳያቸው።



ደረጃ 3: ለሁለቱም መደዳ ተመሳሳይ ምስል አሳያቸው። የምታሳያቸው የሰው ፊትና የአይጥ ምስል ያለበትን ጥምረት ይሁን።

ደረጃ 4: ጀርባ ለጀርባ የተቀመጡት ሁለቱም ተሳታፊዎች በጋራ አንድ እስክርቢቶ በመያዝ ለአምስት ደቂቃ ያህል የተመለከቱትን ሥዕል እንዲስሉ አድርግ። ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ መነጋገር እንደማይቻል ግለጽላቸው።

ደረጃ 5: ተሳታፊዎቹ ስዕላቸውን እንዲያቀርቡና በሚስሉበት ወቅት የተሰማቸውን ስሜትና የተለማመዱትን ነገር እንዲያብራሩ ጠይቃቸው።

30 ምንጩ አይታወቅም ነገር ግን በ Splinter, D & Wüstehube, L የተጠናከረ።

ማሳሰቢያ

ተሳታፊዎቹ ምናልባት በሚስሉበት ወቅተ ተቸግረው ሊሆን ይችላል። አብሯቸው የሚስለው ሰው ያልሆነ ነገር ለምን እንደሚስል ግራ ገብቷቸው ሊሆን ይችላል። እያንዳንዱ ጥንድ በሃሳባቸው ተመሳሳይ ምስል የሚስሉ መስሏቸዋል። ከዚህ የተነሳ ትዕግስት ያጡ፣ ግራ መጋባት ወይንም የመናደድ ስሜት ሊሰማቸው ይችላል። የከበዳቸው ነገር ምን እንደሆነ ጠይቃቸው። አንዱ ተሳታፊ ሌላኛው ተሳታፊ ሌላ ዓይነት ሥዕል መስራት የሚፈልግ ይመስላል ብሎ ሊናገር ይችላል። ምስሎቹን እንደገና በማሳየት ምን ዓይነት ምስል እንደሆኑ ጠይቃቸው። በመጀመሪያ ተሳታፊዎቹ የተለያዩ ምላሾች ሊሰጡህ ይችላሉ። ነገር ግን ምስሉ የሰው ፊትም የአይጥም ምስል ሊሆን እንደሚችል ሲረዱ ታያቸዋለህ። ይህን የሚረዱበት ቅፅበት የ"አሁን ገባኝ" ውጤት ይባላል።




በድንገትም ከነርሱ ጋር ያለው ሰው ከነበረው ልምድ የተነሳ በፍፁም የተለየ ነገር እንዳየ ይረዳሉ። ስለዚህም የተለየ ምስል ለመሳል መሞከራቸው አሳማኝ እንደሆነ ይረዳሉ። በዚህ ጊዜ የሌላውን ሰው አቋም ተረድተው ራሳቸውን በርሱ ቦታ በማየት የዕይታ (አረዳድ) ለውጥ ያመጣሉ። ይህም ራስን በሌላው ቦታ በማስቀመጥ እንደመረዳት ማለት ነው።

አሁን ውይይቱን ከሥዕል ወደ ግጭት እውነታ ቀይረው። እንዲህ ብለህ ልትጠይቅ ትችላለህ፤ በውስጣችን ያለው ጥያቄ እንዲህ ሆኖ ሊቀርብ ይችላል? ሐቁ ምንድን ነው? ሰው ወይ አይጥ ወይስ ሁለቱም? ወይንም አንዱ ተሳታፊ ምስሉን እንደ አይጥ ሌላው ተሳታፊ ደግሞ እንደ ሰው እንዴት ሊረዳው ይችላል።

የመጀመሪያውንና የሁለተኛውን ሥዕሎች ስታሳያቸው በግጭት ወቅት አሳማኝ ሐቅ የሚባል ነገር እንደሌላ ይገባቸዋል። በዚህ ጊዜ የቀድሞ ልምዳችንና ያለን መረጃ አመለካከታችንን እንደሚቀይሩ ውይይት አድርጉበት። ሽምጋዮች ይህን አውቀው ተጋጭ አካላት ያላቸውን የኋላ ታሪክ እንዲገነዘቡ ማድረግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን በአፅንዖት ንገራቸው።

ከዚያ በመቀጠል ይህ አሁን ገባኝ ብለው የተረዱበት ቅፅበት በማመቻቸትና በማቀራረብ የሽምግልና ሂደት በጣም አስፈላጊና አመለካከትን የሚቀየር ወሳኝ ወቅት መሆኑን አብራራላቸው። ከዚህ በኋላ መፍትሔ ማምጣት ይቻላል።



ደረጃ 6: ተሳታፊዎቹ ይህ ሃሳብ ገብቷቸው ከሆነ ከእውነተኛ የህይወት ተሞክሯቸው ጋር እንዲያዛምዱ ጠይቃቸው። ደግሞም እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ የት እንደተገነዘቡ፣ ምናልባትም በሽምግልና ከተሳተፉ፣ ወይንም በግጭት ውስጥ ራሳቸው ገብተው ከሆነ ጠይቃቸው። ባገኙት ተሞክሮ አሁን ገባኝ ያሉበትንና አረዳዳቸውን የቀየሩበት ሁኔታ ካለ ያካፍሉ።

ደረጃ 7: እንደ ርዕስ "ከዚህ ልምምድ ምን እንማራለን?" በሚል የተሳታፊዎችን ሃሳቦች በሚገለጠው ወረቀት ላይ ዘርዝራቸው። በግምገማው ሂደት ወቅት የሽምጋዮች ትልቁ ሚና በግጭቱ ተካፋይ የሆኑት አካላትን ዕይታ ማወቅ እንዲሁም ሚዛናዊነቱን መጠበቅ እንደሆነ ትኩረት ሰጥተህ ግለፅላቸው። ከሽምግልናው በፊትም ሆነ በሂደቱ ውስጥ ሽምጋዮች የሁለቱንም ወገኖች ታሪክ ያሳለፉትን ልምድ መጠየቅ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው።

## III.5 የሽምግልና ሂደት

# “Jaarsii waan sadii: Jaarsii Ifa, Jaarsii karaa Jaarsii bishaan.”

“አንድ ሽማግሌ ሶስት ነገሮችን ይወክላል፤ እነዚህም ብርሃን ፣ መንገድ እና ውሃ ናቸው።”

(ኦሮምኛ ብሂል)

### III.5.1 የአመቻች ሽምግልና ስነ - ምግባር መርሆች

ሽምግልና ጥንቃቄ የተሞላበት የገላጋይነት ስራ ነው። ይህም ማለት በትክክል ካልተከናወነ በተጋጭ ወገኖች ሕይወት እና ጉዳዩ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል። ጥንቃቄ የተሞላበት የሽምግልና ሂደት ሊከተላቸው የሚገባ የስነምግባር መርሆች አሉት። ዴቪድ ኤ ሑፍማን እና የአውሮፓ የሽምግልና ሂደት ስነ-ምግባር መርሆች ባስቀመጡት መሠረት ከዚህ በታች አስር ጠቃሚ መርሆች ተዘርዝረዋል።[32]

**1. የፍላጎት አለመጣጣም**

ሽምጋዮች ግጭት በመፈጠሩ ምክንያት ቀጥታ የሚገኝን ማንኛውም ግላዊ፣ ሙያዊም ሆነ ንዋያዊ ጥቅሞችን ማስወገድ አለባቸው።

**2. ብቃት / ልዕቀት**

ሽምጋዮች አቅማቸውን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። ከአቅማቸው በላይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መሸምገል የለባቸውም። ለተጋጭ አካላት ስለችሎታቸውና ልምዳቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

**3. ገለልተኝነት**

የሽምግልና ሂደት መሰጠትን ይጠይቃል። ለተጋጭ ወገኖች ውስጣዊ ስሜት ወይንም አዘኔታ መፍጠር ካልተቻለ የሽምግልናው ሂደት አስቸጋሪ ይሆናል። እንደዚህ ዓይነት ስሜት በመሰማቱ ምክንያት ሚዛናዊነቱን በመስጋት የሽምግልናውን ሂደት አቋርጦ መውጣት አያስፈልግም። ይልቁንም እነዚያ ስሜቶችን ለራሳቸው ለተጋጭ ወገኖች ማስቀረት ያስፈልጋል። አንዱ አካል ከፍተኛ ሃዘን ሲሰማው ሽምጋዮች ያ አካል እንዲህ እንዲያዝን ያደረገው ምክንያት ምን እንደሆነ ለመረዳት ምን ያህል ትልቅ ስራ መስራት እንዳለባቸው የሚያሳይ ነው።

የሽምግልና ሂደት እንደዳኝነት አንዱን አካል ብቻ መርዳት ሳይሆን ሁለቱንም አካላት የሚያሳስባቸውን ሃሳብ በመግለጽ እና ሁሉንም የሚያግባቡ ነገሮችን በመፈለግ ተጋጭ አካላትን ተጠቃሚ ማድረግ ነው።

**4. በጎ ፈቃደኝነት**

ምንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ ሽምግልናዎች በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ወይንም ግጭትን በሚፈቱ ድርጅቶች የሚከናወን ቢሆንም በሽምግልናው ሂደት መካከል የተሰጣቸውን ኃላፊነት ማቋረጥ ቢፈልጉ ይህ መብታቸው ሊጠበቅላቸው ይገባል። ይህ ዓይነቱ የሽምግልና ሂደት በበጎ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ሽምግልና ይባላል።

**5. ሚስጥራዊነት**

የሚስጥራዊነት መርህ ሁለት ዐይነት መልክ አለው። አንደኛው፤ አንዱ ተጋጭ ወገን ሽምጋዩን በግል በሚያገኝበት ወቅት በምስጢር የተነገረውን ለሌላኛው ተጋጭ ወገን/ወገኖች እንዲነገርበት የማይፈልገውን ነገሮች በሚስጥር መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ሁለተኛው፤ ሽምጋዩ ሽምግልናው ከማይመለከታቸው ሶስተኛ ወገኖች የሽምግልና ሂደቱን ሚስጥራዊነት መጠበቅ ይኖርበታል።

**6. አይጎዱነት** (Do No Harm)

የአይጎዴነት መርህ ሽምጋዮች የግጭት ተሳታፊዎችን የሚጎዳ ወይንም ግጭቱን ሊያብስ የሚችል ሁኔታ ሲከሰት ሽምግልናውን ማቋረጥ እንደሚገባቸው ያስገነዝባል። ሰዎች ከግጭቱ የተነሳ ትልቅ አደጋ ደርሶባቸው ወይንም ስሜታቸው ተነክቶ ከሆነ የሽምግልናውን ሂደት መጀመር በራሱ የራሱን አስተዋፅዖ ስለሚጨምረ አንዳንድ ጊዜ ተጋጭ አካላት በጋራ በሽምግልና ሂደቱ ላይ ለመሳተፍ ወይንም ሂደቱን ለመቀጠል እንደማይችሉ ሽምጋዮቹ ሊገነዘቡ ይገባል።

31 Hoffman, D.A. (2003) )ን ይመልከቱ።

## 7. አቅምን ማሳደግ

ተጋጭ ወገኖች ራሳቸውን መቻላቸውና ነፃ መሆናቸው የሽምግልና ዋና-መርህ /መሪ ሃሳብ/ ነው። ተጋጭ ወገኖች ግጭታቸውን ለመፍታት ሽምጋዩ ወይንም ሌሎች አካላት የውሳኔ ሃሳብ ከመስጠታቸው ይልቅ (በግል ይሁን በጋራ) የራሳቸው ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ መርዳትና ማበረታታት የሽምግልናው መሠረታዊ ነገር ነው።

## 8. የውሳኔ ስምምነት

በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተና በራስ ተነሳሽነት የሚደረግ የግጭት አፈታት የተጋጭ ወገኖችን ፍላጎት ሊያስከብር የሚችለው የሚወሰነው ውሳኔ የሚያስከትለውን ነገር አምኖ በመቀበል ነው። ምንም እንኳ ሽምጋዮች ለሁለቱም ወገኖች የመረጃ ምንጭ መሆን እንደሌለባቸው ቢታወቅም ተጋጭ ወገኖች ለሽምግልናው የተለያዩ አማራጭ ለማግኘት በቂ የመረጃ ልውውጥ ማግኘት አለማግኘታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። የተጋጩት ወገኖች የመረጃ እጥረት ቢያጋጥማቸው ሽምጋዮች እንዴት ሊያገኙ እንደሚችሉ ሊያነጋግሯቸው ይገባል።

## 9. ኃላፊነት

ሽምጋዮች ተጋጭ ወገኖች እንዲጎዱ ያለማድረግ ኃላፊነት እንዳለባቸው ሁሉ የውሳኔ ስምምነቱ በሽምግልናው ያልተሳተፉ ወገኖችንም እንዳይጎዳ ጥረት ማድረግ አለባቸው። ከሽምግልናው የሚገኘው ውጤት እንደ ህፃናት ወይንም ተጋላጭ ወገኖች ያሉ ሶስተኛ ወገኖችን እንዳይጎዳ አስፈላጊው ጥንቃቄ መወሰድ አለበት።

## 10. ታማኝነት

የሽምጋዮች ሚና ታማኝ ሊያስብል የሚችለው የሚከተሉትን በግልፅ ሲያስቀምጡ ነው:

- የትምህርት ደረጃቸውንና የቀድሞ ልምዳቸውን
- በሽምግልናው ወቅት የተጋጩት ወገኖች ለሽምግልና ሂደቱ ሊከፍሉት የሚያስፈልግ ወጪ ካለ
- የሽምጋዩን ተሳትፎ ሊጎዳ የሚችለውን ማንኛውንም ጉዳይ

ታማኝነት ከተጋጭ አካላት ጋር በሚደረግ የተናጥል ስብሰባዎች ሁሉ እውነተኛ ሆኖ መገኘትን ጭምር ይጠይቃል። ለምሳሌ፡- አንደኛው ወገን የመጨረሻ አቋሜ ይህ ነው ብሎ በሚስጥር ያስቀመጠውን ሁለተኛው ወገን ቢጠይቅ ሽምጋዩ አይሆንም ብሎ መመለስ አለበት። ሆኖም ውይይት እንደተካሄደ መገለፅ አለበት። በተጨማሪም የሁለተኛው ወገን ዝርዝር ሃሳቦችና መረጃዎች ሁሉ ሚስጥራዊ እንደሚሆን ማስገንዘብ ተገቢ ነው።

## “Jaarsii kan mataan harrii otoo hin ta’in kan garaan harriiti.”

“ብልህ ሽማግሌ እድሜ ጠገብ ብቻ ሳይሆን በሳል ዕይታ ያሉትም ነው።”

(ኦሮምኛ ብሂል)

| | |
|---|---|
| ዓላማ | በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች የሽምግልና ሂደትን እና ልዩ ልዩ ደረጃዎች ይረዳሉ። |
| የተመደበ ጊዜ | 45 ደቂቃ |
| መነሻ ዕውቀት | የቀደሙት ምዕራፎች ሁሉ። |
| መርጃ መሣሪያዎች | የወረቀት ሠሌዳ፣ ማርከሮች፣ ባለቀለም ካርዶች |
| ቅደም ተከተል | ደረጃ 1: ምዕራፉን አስተዋውቅ። |
| | ደረጃ 2: በሽምግልና ሂደት ደረጃዎች ላይ የተፃፈውን ማስታወሻ ለተሳታፊዎች በማደል ለ10 ደቂቃ ያህል እንዲያነቡት ጊዜ ስጣቸው። እያንዳንዱን ደረጃ በማብራራት እና የተሳታፊዎችን ጥያቄ በመመለስ ተሳታፊዎች እንዲወያዩበት አድርግ። |

## III.5.3 የሽምግልና ደረጃዎች

የተሳካ ሽምግልና በተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል። እነዚህ ደረጃዎች ዘላቂና ውጤታማ የሆነ መፍትሄ የሚያመጡ ሁነኛ መሣሪያዎች ናቸው።[32]

### 1. ከጉዳዩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ተጋጭ አካላት መለየት፣ ለሽምግልናው ፈቃዳቸውን ማግኘትና እምነት እንዲጥሉ ማድረግ

ይህ አብዛኛውን ጊዜ የሚከናወነው በተናጥል በሚደረግ ሽምግልና ሲሆን በአመቻች የሽምግልና መንገድ ሽምጋዮች ከተጋጭ ወገኖች ጥያቄ እስኪቀርብላቸው ሲጠብቁ በባህላዊ ሽምግልና መንገድ ግን ሽምጋዮች ራሳቸው ሽምግልናውን ይጀምሩታል። እምነትን ማሳደር በተለይም በአመቻች ሽምግልና በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ወደ ሽምግልናው እንዲገቡ ከተጋጭ ወገኖች ፈቃድ ስለሚያስፈልጋቸው ነው። በባህላዊ ሽምግልና ተጋጭ ወገኖች የሽምጋዮችን ሃሳብ ላለመቀበል ብዙም አይደፍሩም።

### 2. ሽምግልናውን የመክፈቻ ደረጃ

በዚህ ጊዜ ተጋጭ ወገኖች በአካል አንድ ቦታ በመገኘት በጥላ ስር ወይንም ሽምጋዮች በመረጡት መንገድ የሚከናወን ነው። እነዚህ ወገኖች ምንም አይነት ንግግር ከመጀመራቸው በፊት ሽምጋዩ የሽምግልናውን አካሄድ፣ ያላቸውን ሚና፣ የሽምግልናውን ህግ እና ባጠቃላይ የሽምግልናውን መርህ (መመሪያ) ለተጋጭ አካላት ግልፅ ያደርጋል። ስለዚህም ሽምጋዩ ደህንነቱ የተጠበቀና ለሽምግልናው የሚመች ቦታ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል። ይህን በማድረጉ ሂደቱ ያለእንቅፋት እንዲከናወን ያስችለዋል። በዚህ መንገድ ተጋጭ ወገኖች በሽምግልናው አካሄድ ላይ ያላቸውን ሀሳብ ወይንም በሂደቱ ላይ ያላቸውን አስተያየት ሊጨምሩበት ይጋበዛሉ። በአመቻች የሽምግልና ሂደት ሽምግልናው በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ፣ የሽምጋዮች ሚና ደግሞ ለመመርመር ወይንም ለመዳኘት ሳይሆን ተጋጭ ወገኖች የራሳቸውን የመስማሚያ ሃሳብ እንዲያመጡ መርዳት እንደሆነ በአፅንዖት ሊገለፅ ይገባል። ይህ በባህላዊ ሽምግልና አይጠበቅም ምክንያቱም የመጨረሻውን ውሳኔ የሚሠጡት ራሳቸው ሽምጋዮቹ ስለሚወስኑ ነው። በተጨማሪም በአመቻች ሽምግልና ሽምጋዩ ሁሉም ነገር ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ እንደሆነ በማረጋገጥ ሚስጥራዊ በሆኑ ጥያቄዎች ላይ ምን እንደሚያደርጉ ራሳቸው ባለጉዳዮቹ እንዲወስኑ መተው አለበት። ባህላዊ ሽምግልና በምርቃት ወይንም በፀሎት መጀመር በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ ረገድ ሁለቱንም የሽምግልና መንገዶች በማጣመር የተለያዩ መንገዶችን መፍጠር ይቻላል። በተለይም በኢትዮጵያ በምርቃት መጀመር የተለመደ ቢሆንም አካሄዱን ማሳወቅ እና የተጋጭ ወገኖችን ፈቃድ መጠየቅም በተወሰነ መልኩ ተግባራዊ ሊሆን ይችላል።

### 3. የነገሩን ምንነት ለይቶ ማወቅና ታሪኩን መንገር

በኢትዮጵያ ባህል ሽማግሌው ከተጋጮቹ አንዱን ወገን የግጭቱን ምክንያት እንዲገልፅ ያደርጋል። ይህን የሚወስንበት ባህሉን ተከትሎ ማለትም እንደ እድሜውና በማኅበረሠቡ ዘንድ ባለው ተቀባይነት ነው። በአመቻች ሽምግልና ግን ሽምጋዩ ወገንተኝነት እንዳይፈጠር ለማድረግ ከሁለቱ ወገኖች አንዱ እንዲጀምር ለሁለቱም ወገኖች ጥያቄ ያቀርባል።

የትኛውንም የሽምግልና ዓይነት ብንጠቀም ተጋጭ ወገኖች ሽምጋዮቹ ገለልተኛ እንደሆኑ ሊረዱ ይገባል። አንዱ የጉዳዩን ምንነት ገልፆ ሲጨርስ ሽምጋዩ የተናጋሪውን ሃሳብ ግልፅ በሆነ ቋንቋ ጠቅለል አድርጎ ካቀረበ በኋላ ተጋጮቹ መስማማት አለመስማማታቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ታሪኩ ረጅም ከሆነ (መጥፎ ስሜት የማይሰማው ከሆነ ) ሃሳቡ ግልፅ እንዲሆን ታሪኩን በሚያቀርብበት ጊዜ በየመሃሉ እየገባ የተነገረውን ማጠቃለያ እየሰጠ ያልፋል። ሽምጋዮቹ እየተናገረ ያለው ወገን እንዲናገር እያበረታቱ በንቃት መከታተል አለባቸው። ይህም እንደ ባህሉ በቃላት ወይንም ቃላትን ሳንጠቀም ሊገለፅ ይችላል።[33]

32 የተለያዩ ጸሐፊዎች ከአራት እስከ አስራ ሁለት የሚደርሱ የተለያዩ የሽምግልና ደረጃዎችን በመስጠት በተለያየ ስያሜ ይከፋፍሏቸዋል። ቢሆንም ግን የሂደቱ አስተሳሰብ በሁሉም አከፋፈሎች ተመሳሳይ ናቸው። በዚህ አከፋፈል የተለያዩ ሞዴሎችን ለማጠቃለል ተሞክሯል።

33 ክፍል III.6.3 በሽምግልና ሂደት ውስጥ የአካባቢ ቋንቋ አስፈላጊነት የሚለውን በገጽ 62 ይመልከቱ።

## ፋ. በጥልቀት መረጃትና ዕይታን መጋራት

በዚህ ደረጃ ሸምጋዩ ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት የሆነበትን ሥረ-መሠረቱን፣ ጥቅማቸውንና ፍላጎቶቻቸውን እንዲያሳውቁ ሁለቱንም ወገኖች መጠየቅ አለበት። እንደ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች[34] የመሳሰሉትን በመጠቀም የተጋጭ ወገኖችን ጥልቅ ጥቅም፣ ፍላጎት እና ፍራቻ ይረዳል። በመቀጠልም ሸምጋዩ ተጋጭ አካላቱን "አንዱ በሌላው ቦታ ቢሆን" (ዕይታን መጋራት[35]) እንዴት ሊረዱ እንደሚችሉ ለማድረግ ያበረታታቸዋል። ይህን በሚያደርጉበት ወቅት የጋራ የሆነ መረዳትና እምነት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። በባህላዊ ሽማግሌና ሸምጋዮች የተጋጭ ወገኖችን ጥቅም ሳይሆን እውነታውን ለማውጣት ጥያቄዎች ይጠይቃሉ። ነገር ግን በዚህ ሂደት የጋራ መረዳት ውስጥ እንዲገቡ ፍላጎታቸውንና ስሜቶቻቸውን ለማወቅ የሚያስችል ጥያቄዎች ለማቅረብ የተመቻቸ ሁኔታ አለ።

በአመቻች ሽምግልና የተጋጭ አካላት ፈቃድ ውሳኔ ለማምጣት ብቸኛ አማራጭ ሲኖረው በባህላዊ ሽምግልና ሂደት ውስጥ ደግሞ ልምዱን እንደገና ማምጣት (መገንባት) አስፈላጊ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ተጋጭ ወገኖቹ ከሚያገኙት መፍትሔ ይልቅ ይህ መሆኑ ብቻ አስፈላጊ ሆኖ ያገኙታል። ነገር ግን ሸምጋዩ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ስሜቶቻቸውን ፍራቻቸውንና ፍላጎታቸውን ለማወቅ ጊዜ የሚሠጥ ከሆነ ተጋጭ ወገኖች በመፍትሄ ሃሳቡ ላይ ቅር መሰኘታቸው ይቀንሳል።

## 5. አማራጭ ሃሳቦችን ማመንጨት

ይህ ደረጃ በባህላዊ ሽምግልና እና በአመቻች ሽምግልና መካከል ያለውን ልዩነት ጉልህ በሆነ መልኩ ያሳያል። በአመቻች ሽምግልና ተጋጭ አካላት ራሳቸው የመፍትሄ ሃሳቦችን ያመነጫሉ። ሸምጋዩ እነዚህ ወገኖች የሚያመነጩት የመፍትሔ ሃሳብ ሁለቱንም ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑን ብቻ ይከታተላል። ነገር ግን በባህላዊ ሽምግልና ሽማግሌዎቹ ያስማማቸዋል ብለው የሚገምቱትን የመፍትሔ ሃሳቦች ለተጋጭ አካላቱ ያቀርባሉ።

ተጋጭ አካላትን የተሻለ ሃሳብ እንዲያመጡ የሚደረጉ ጥያቄዎች በኢትዮጵያ ተግባር ላይ ያልዋለ ቢመስልም በሽምግልና ብቃት ስልጠና ላይ የተገኙት እውነታዎች እንደሚያረጋግጡት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጋጮቹን ስለጥቅማቸውና ፍላጎታቸው መጠየቅ በራሱ የራሳቸውን የመፍትኄ ሃሳብ እንዲፈልጉ ይጋብዛቸዋል። በተጨማሪም የቢሆን ጥያቄዎችን በመጠየቅ (አንዱ ወገን እንደዚህ ቢሆን እንደዚህ ለማድረግ ትፈቅዳለህ?) ሸምጋዮች የመፍትሔ ሃሳብ ለማግኘት ሰፊ እድል ያገኛሉ። እንዲሁም በተዘዋዋሪ መንገድ ተጋጮቹ በመፍትሔ ሃሳቦቹ ላይ መስማማታቸውን የሚያውቁበትን መንገድ ይፈጥራሉ ማለት ነው። አሁንም ቢሆን ግን ሸምጋዮቹ የመፍትሔ ሃሳቡን ያቀርባሉ።

## 6. ስምምነት ላይ መድረስ

ስምምነቱ የሚፈጸምበት መንገድ እንደባህሉ ሊለያይ ይችላል። ስምምነቱን በጽሑፍ በማስፈር ወይንም የተለመዱ ባህላዊ የሆኑ መንገዶች በመከተል ሊፈፀም ይችላል። በዚህ ረገድ ሁለቱም የሽምግልና መንገዶች ተደጋጋፊ ናቸው። በተለይ በአመቻች ሽምግልና ወደፊት ሌላ አለመግባባት ተፈጥሮ ግጭት እንዳይከሰት ስምምነቱ ግልፅ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል።

---

34 ክፍል III.3.4 የሽምግልና ዛፍ ማማ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን (grounding questions) መጠቀም የሚለውን በገጽ 37 ይመልከቱ።

35 ክፍል III.4 ዕይታን መቀየር የሚለውን በገጽ 46 ላይ ይመልከቱ።

# “Afaan Gaariin Hafaa Gaarii Caala.”

## “ከጥሩ መኝታ ጥሩ ቃል ትበልጣለች።”

## (ኦሮምኛ ብሂል: በተለይም ሁከት አልባ ተግባቦት ላይ ትኩረት ሲሰጥበት)

| | |
|---|---|
| **ግላማ** | በሽምግልና መጨረሻ ተሳታፊዎች ተግባቦት በሽምግልና ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይገነዘባሉ እንዲሁም መሠረታዊ የተግባቦት ክህሎቶችን ይማራሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 240 ደቂቃ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ በልዩ ልዩ ቅርፅ የተዘጋጁ ባለቀለም ማወያያ ካርዶች፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳዎች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: ለተሳታፊዎች የተግባቦት አስፈላጊነትን ካስተዋወክ በኋላ በርዕስ III.6.1 ስር የሚገኘውን የሹልዝ ፎን ዙን አራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴልን አቅርብ።<br>ደረጃ 2: የተግባቦት መልመጃውን እንዲያከናውኑ አድርግ (III.6.2)።<br>ደረጃ 3: የመልመጃውን አግባብነት ከሌሎች የህይወት ተሞክሮዎች ጋር በማዛመድ አብራራ።<br>ደረጃ 4: ድምጽ አልባ ተግባቦትን እና አካላዊ ቋንቋን አስተዋውቅ (III.6.3)። |

## III.6.1 ተግባቦት እና የሹልዝ ቮን ዙን አራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴል[36]

ተግባቦት ውስብስብ ነው። በንግግር ወቅት ከተርጉሞችና ከማሳሰቢያዎች ያለፈ ብዙ ነገሮችን ያቀፈ ነው።። ስለዚህም በሚገባ አለመረዳትና አለመግባባት እንዲፈጠር በር ይከፍታል። በመደበኛ የዕለት ተለት ኑሮዎችን፣ በህይወት ገጠመኞቻችን እና ግንኙነታችን የተለመደ ከሆነ ተግባቦት በግጭትም ሆነ በሽምግልና ወቅት በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። የሽምግልና ውጤት የሚወስነው ታዲያ በተጋጭ ወገኖች መካከልና ሽምጋዮች በተግባቦት ላይ ባላቸው የላቀ ክህሎት ላይ የተመሠረተ ነው። ከአንድ ሽምጋይ ከሚጠበቁ ነገሮች መካከል:

- በትኩረት ማዳመጥ
- የተጋጭ ወገኖችን ፍላጎትና ስሜት መግለጥ
- በተጋጭ ወገኖች መካከል የሀይልና የተግባቦት አለመመጣጠን ሲከሰት ሚዛናዊ ማድረግ
- በንቃት በማድመጥ ሙሉ ታሪኩንና ሂደቱን መምራት

ተግባቦት የመልዕክት ልውውጥ ተብሎ ሊተረጐም ይችላል። መልዕክቶችን በማድረስና በመላክ መግባባት እንዲፈጠር የሚያደርግ መንገድ የሚጠርግ ነው። ይህ ውስብስብ ሂደት በጥንቃቄና በክህሎት ሊያዝ ይገባዋል። የተሳካ ተግባቦት እንግዲህ እያንዳንዱ ተግባቦት እንዴት እንደተረጎመ እና ምን ዓይነት እርምጃ እንደተወሰነ የሚያካትት ጭምር ነው። በጣም ከሚታወቁ የተግባቦት ሞዴሎች መካከል የሹልዝ ቮን ዙን አንዱ ነው። የአራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴሉ የተግባቦት ካሬ ወይንም የአራቱ ጎን ሞዴል ተብሎ ሊጠራ ይችላል። ቮን ዙን[37] የመልዕክትን አሰራር ሲተነትነው በሁለት አካላት መካከል የሚደረግ እያንዳንዱን የመልዕክት ልውውጥ በአራት ደረጃ በመመደብ ነው። እነዚህም:

### የሀቅ ደረጃ
ማንኛውም መልዕክት አስተላላፊ እንዲተላለፍ የሚፈልገውን እውነትን ያዘለ /ሀቅ/ መረጃ ይዟል።

### ራስን መግለጽ
መልዕክት አስተላላፊው በመልዕክቱ ውስጥ ራሱን ያሳያል። ራሱን እንዴት እንደሚመለከትና ሌሎች እርሱን እንዴት እንዲመለከቱት እንደሚፈልግ ያስተላልፋል። ስለዚህም ራስን መግለጥ አንድ ሰው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ራሱን የሚያሳይበትና ማንነቱን የሚያጋልጥበት ነገሮች ያቅፋል።


### ግንኙነት
አንድ መልዕክት አስተላላፊና ተቀባዩ ያላቸውን ግንኙነት ያጋልጣል። በዚህ የመልዕክት ጎን ብዙ ጊዜ በድምፅ፣ በአካላዊ ገለፃና በሌሎች ድምጽ አልባ ምልክቶች እንዲሁም በቃላት አገባብ ይገለጣል።

### ቅሬታ
አንድ መልዕክት ከአስተላላፊው ወደ ተቀባዩ ቅሬታን ያቀፈ ሊሆን ይችላል።

በየዕለት ተለት ተግባቦታችን እነዚህን አራቱንም ገፅታዎች ግልፅ ባልሆነ መንገድ እናስተላልፋለን። በመሆኑም ሰሚው በሚመቸው መልኩ እንዲተረጉመው የሚያስችለውን ክፍተት እንተዋለን። ይህም በአብዛኛውን ጊዜ አለመግባባት ብሎም ግጭት እንዲፈጠር በር ይከፍታል።

36 Schulz von Thun, F (2012)።
37 መጀመሪያ በ Schulz von Thun, F (1981) ታተም።

## የመልዕክት አራት ጎኖች






የሚከተለውን ምሳሌ መጠቀም ትችያለሽ/ህ:
አዲስና እና ኢትዮጵያ መኪና ውስጥ ተቀምጠዋል። መንገዱን ለማቋረጥ እየጠበቁ ሳለ የትራፊክ መብራቱ ቀይ መብራት ጠፍቶ አረንጓዴው በራ።
ኢትዮጵያ: “አረንጓዴው የትራፊክ መብራት በርቷል።”
አዲስ: “እንዲህ ትዕግስትሽን አትጪ።”
—ከዛም መጨቃጨቅ ጀመሩ። ችግሩ ምን ይመስልሃል?

የመልዕክት ይዘትን ከተመለከትክ ፣ አራቱን የአረፍተ ነገር ደርዞች ልትለይ ትችላለህ ፤ “አረንጓዴው የትራፊክ መብራት በርቷል።” በመልዕክቱ ውስጥ ሃቅ የሆነው ነገር አረንጓዴው የትራፊክ መብራቱ ነው። ኢትዮጵያ አዲስን መኪናውን እንዲነዳ ቅሬታ አቀረበችለት። ኢትዮጵያ የተናገረችው በልቧ ያለውን /ራስን መግለጥ/ ነው ፤ ቸኩላለች ትዕግስት የላትም። መልዕክቷ በአዲስ እና በኢትዮጵያ መካከል ያለውን ግንኙነት ፍንጭ ይሰጣል ፤ እሷ አለቃ ነች እሱ ሹፌር ነው። መስራት ያለበትን እና የሌለበትን ልትነግረው ትችላለች።

ምናልባት ኢትዮጵያ አዲስን መንቀፍ ፈልጋ ላይሆን ይችላል። አለመስማማት በማንኛችንም መካከል ሊፈጠር ይችላል። ምክንያቱም ሰዎች የሰሙትን መልዕክት የሚረዱበት መንገድ የተለያየ በመሆኑ ነው። ይህ ደግሞ ለአለመግባባት እና ለግጭት መነሻ ሊሆን ይችላል። ቀጣዩ መልመጃ ተሳታፊዎቹ አራት ጐናዊ ሞዴሉን እንዲጠቀሙና ተግባቦት ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ ያስረዳል።

## III.6.2 የተግባቦት የተግባር መልመጃ

**ዓላማ** ውስብስብ የሆኑ የተግባቦት ሃሳቦችን እንዴት በገሃዱ አለም እንደሚከሰቱ ለማሳየትና ተሳታፊዎች ለሹልዝ ቮን ዙን ሞዴል ያላቸውን ግንዛቤ ለማስፋት።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** ሁለት የወረቀት ሠሌዳዎች ፣ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ መልዕክቶችን ያቀፈው የአራት ጐን ሥዕል ፣ የተለያዩ ባለቀለም ካርዶች ፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ሁለቱን ሥዕሎች በተናጥል በሠሌዳዎቹ ላይ ሳል። በሠንጠረዥ ውስጥ ያለውን መልዕክት በቡኒ ወረቀት ወይም በሌላ ወረቀት ሸፍን። አንዱ አራት ጐናዊ መልዕክትን የሚያሳየው ሲሆን በሥዕሉ መሃል ላይም ካሬ አለ። ሌላኛው ምስል ሰዎች በአውቶቡስ ውስጥ ተቀምጠው የሚያሳይ ነው። አንዲት ሴት በአውቶቡሱ ውስጥ ደረጃ ላይ ቆማ ከመንገዱ ባሻገር የሆቴል መተላለፊያ ላይ የቆመን ልጅ ትጣራለች።

ደረጃ 2: ይህ ምሳሌ ከሽርሽር በሚመለሱ ተማሪዎች መካከል የተካሄደ የተግባቦት ሂደት መሆኑን ግለጥላቸው። በአውቶቡሱ ውስጥ ያሉ ተማሪዎች በሞላ ለመሄድ ተዘጋጅተዋል። ነገር ግን ከሽርሽር አዘጋጆች አንዱ የሆነው ሰለሞን አሁንም በሆቴሉ መተላለፊያ ላይ ቆሞ ከአንድ ሰው ጋር እያወራ ነው። በአውቶቡሱ በር ላይ የቆመችው ሰናይት "ሰለሞን እየጠበቅንህ እኮ ነው" እያለች ትጣራለች።

ደረጃ 3: አሁን የሰናይትን መልዕክት በአራት ማዕዘኑ የቮን ዙን ሞዴል በመጠቀም ፃፍ፤ "እየጠበቅንህ እኮ ነው።" ተሳታፊዎቹን "ሰናይት ምን ለማለት ፈልጋ ነው ሰለሞንስ ምን ተረዳ?" ብለህ በመጠየቅ በአራቱ የተለያዩ የመልዕክት አቅጣጫዎች ላይ ሀሳብ እንዲሠጡ አድርግ።

ደረጃ 4: የበርካታ ተሳታፊዎች አስተያየት የተራራቀ ምላሽ ቢሆንም እንኳ ለመፃፍ ሞክር። ይህ ምናልባት:

የሀቅ ይዘት: ሁሉም አውቶቡሱ ውስጥ ተቀምጠው ለመሄድ ተዘጋጅተዋል።

ራስን ማግለጥ: "ስላንተ እንጨነቃለን።" ፣ "ስላንተ ግድ ይለናል።" "ትዕግስታችንን አጥተናል ፣ ተናደናል።" "እንዳንዘገይ እንፈራለን።"

ግንኙነት: "ባንተ ላይ ልንተማመን አንችልም።" "አንተ ታስፈልገናለህ።"

ቅሬታ: "አትጨነቅ ፣ ዘና ብለህ ተጫወት።" "ትተንህ ልንሄድ ነው አታስረፍድብን ፍጠን።"

ተሳታፊዎቹ የሚሉት ከሌላቸው የራስህን ግምት ጨምርበት።

ደረጃ 5: መልመጃው ሞዴሉን እንዴት አድርጎ እንዳብራራላቸው ከተሳታፊዎቹ ግብረ መልስ (feedback) ተቀበል። መልዕክት ላኪው የተናገረው እና መልዕክት የተረዳበት መንገድ በሚለያይበት ጊዜ አለመግባባት እንዴት እንደሚከሰት አፅንዖት ስጥበት። ከተጋጭ አካላት አንዱ የራሱን ሃሳብ በበቂ ሁኔታ ካልገለጠ ከአራቱ መልዕክቶች አንፃር ትክክለኛውን ፍቺ ለመፈለግ ሸምጋዮች ጥያቄ ሊጠይቁት እንሚገባ አለበለዚያ ግን የሚያስከትለውን ውጤት ግለጥላቸው። በተጨማሪ አስረጂዎች በማምጣት ከተሳታፊዎች ጋር ልትሠራ ወይንም ከተሳታፊዎች በሚመጣ ምሳሌ በትናንሽ ቡድን በመከፋፈል መልመጃውን ልትደግመው ትችላለህ።



### ራስን መግለጥ

“ስላንተ እንጨነቃለን።”
“ስላንተ ግድ ይሰጠናል።”
“ትዕግስታችንን አጥተናል ፣ ተናደናል።”
“እንዳንዘገይ እንፈራለን።”

### ሀቅ

“ከሰለሞን በስተቀር ሁሉም አውቶቡስ ውስጥ ተቀምጧል።”

“እየጠበቅንህ ነው።”

### ቅሬታ

“አትጨነቅ ፣ ዘና ብለህ ተጫወት።”
“ትተንህ ልንሄድ ነው።”
“ፍጠን።”
“አታስረፍድብን።”

### ግንኙነት

“አርፍደሃል።”
“ባንተ ላይ ልንተማመን አንችልም።”
“አንተ ታስፈልገናለህ።”



## III.6.3 በሽምግልና ሂደት ውስጥ የአካካዊ ቋንቋ አስፈላጊነት[38]

| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | ከስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች በሽምግልና ውስጥ ስለአካላዊ ቋንቋ አስፈላጊነት አዲስ እውቀት ይኖራቸዋል። በተጨማሪም አካላዊ ቋንቋን በሽምግልና ውስጥ ለመጠቀም ሦስት ተግባራዊ መሳሪያዎች ይጠቀማሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 120 ደቂቃ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ ፣ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ ማርከሮች ፣ የተለያዩ ባለቀለም ማወያያ  ካርዶች ፣  ሶስት ወንበሮች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: በሽምግልና ውስጥ አካላዊ ቋንቋ አስፈላጊነትን አስተዋውቅ።<br>ደረጃ 2: የአካላዊ ቋንቋ ጥቅም መልመጃን አሰራቸው። |

### አካካዊ ቋንቋ በሽምግልና ሂደት ውስጥ ወሳኝ ሚና ለምን ኖረው?

አካላዊ ቋንቋ ከአንደበታችን አንድ ቃል ከመውጣቱ በፊት ከሰዎች ጋር ያለ ችግር የምንግባባበት የመጀመሪያው ቋንቋችን ነው። ምንም እንኳ ከአንደበታችን ቃል ባይወጣም ድምፃችን ባይሰማም በሁለት ሰዎች መስተጋብር ውስጥ የሚነገር ነው። በፊት ለፊት ውይይት ጊዜ ያለ ማቋረጥ ድምፅ አልባ ምልክቶችን እንለዋወጣለን። ለተናገርነው ምስጋና እና ምላሽ ይሆኑናል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሆነ ምልክት በመጠቀም የምናስተላልፈው ቋንቋ በውሳኔ አሰጣጣችን ወቅት አንድ ሰው ታማኝ፣ እምነት የሚጣልበት እና ተወዳጅ መሆኑን ለመወሰን ወሳኝ ሚና አለው።[39] በንግግራችን ወቅት ቃላቶችን በጥንቃቄ ልንመርጥ እንችላለን። በአካላችን የምንገልፀውን ግን መቆጣጠር የምንችለው እስከ ተወሰነ ደረጃ ድረስ ብቻ ነው። ምንም እንኳ የውስጣችንን ፍላጐት ስሜት በንግግራችን ለመደበቅ ብንሞክርም አካላዊ ቋንቋን ግን ሁልጊዜም ስሜታችንን ያሳብቅብናል።

ድምጽ አልባ ተግባቦት ቀጥተኛ፣ ተገማች ወይም ውስን ነው ልንል አንችልም።[40] ጥቂቶቹ እንደ ንዴት ፣ ፍርሃት ፣ መጸየፍ ፣ ደስታ ፣ ሐዘን ፣ መደነቅ ያሉ የፊት ግላፄዎች ብቻ አለም አቀፋዊ ናቸው። ቢሆንም የተከሰቱበት ሁኔታ እና የገለጻዎቹ ጥልቀት ከባህል ባህል ልዩነት ሊኖራቸው ይችላል። የሚኖረን ባህላዊ ዳራ፣ ልማድ እና ህግ በአካላዊ ቋንቋችን ላይ ተፅዕኖ አለው። ለምሳሌ፡- የአይን ለአይን ግጭት ፣ አካላዊ ቅርበትና ርቀት ወይም የድምፃችን አወራረድ ከባህል ባህል ልዩነት አለው። በተጨማሪም እያንዳንዱ ግለሰብ የተለየ የራሱ የሆነ የፊት ግላፄ ወይም አካላዊ አገላለጽ አለው። ስለዚህ አንዱ ከሌላኛው ወገን የሚያየው አካላዊ ግላፄ ከራሱ የተለየ ስለሚሆን አለመግባባቱን ሊያሰፋው ይችላል። ሽምጋዮች በሽምግልና ሂደቱ መካከል የተጋጭ ወገኖችን አካላዊ ቋንቋዎች በአንክሮ በመመልከት የውስጥ ስሜታቸውን፣ ገለፃቸውን ፣ ሀሳባቸውን እና ምኞታቸውን ተረድቶ ጥንቃቄ በተሞላበት መልኩ ጣልቃ በመግባት እርምጃ ለመውሰድ የጐላ ሚና ይኖራቸዋል። ቢሆንም በፍጥነት ያየነውን ከመተርጐም እና ለተጨማሪ ድምጽ አልባ ንግግሮች እና ፍቺዎች ክፍት ከመሆን መታቀብ አለብን። ስለዚህ በተቃራኒ ባህሎች መካከል እንኳ ቢሆን በንግግር ውስጥ የሚኖረው አካላዊ ቋንቋ ፍሬ ነገሩ ይህ ነው ለማለት በራሱ ማረጋገጫ የሆነ ምንም ነገር የለም ነው።

ሽምጋዮች የሌሎችን ድምጽ አልባ ምልክቶችን ማስተዋል እና መመዘን ላይ ብቻ ሳይሆን የራሳቸውንም በንቃት ሊያስተውሉ ይገባል። የሽምጋዮች የንግግር ችሎታና አካላዊ ቋንቋቸውን መቆጣጠር መቻላቸው ባህሪያቸውን፣ እርጋታቸውንና አመለካከታቸውን ለማጣናከር እንዲሁም በራሳቸውና በተጋጮች መካከል እምነትንና ጥሩ ግንኙነትን ለመፍጠር እንደመሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

---

38 ይህ ጽሑፍ መሠረት ያደረገው ከWüstehube, L. (2005), Wüstehube, L & Specht, H., Knapp, P (Ed) (2013) ነው።
39 Mehrabian, A (1981) Burgoon, JK & Birk, T & Pfau, M (1990)።
40 Ekman, P., Friesen, WV & Ellsworth, P (1972)።

## ሶስትዮሽ መሳሪያ ፡ አስተውል - ተንትን - ሽምግል

ሽምጋዮች ተጋጭ ወገኖችን በመረዳትና አዘኔታ በተሞላበት መልኩ ገንቢ ሀሳቦችን እንዲያፈልቁ ሊረዷቸው ይፈልጋሉ። እነዚህ መሳሪያዎች በሽምግልና ወቅት የተቻኮለ አጠቃላይ ድምዳሜ ላይ ከመድረስ ይታደጋሉ። በተጨማሪም ሽምጋዮች በአግባቡ እና ከህሎት በተሞላበት መንገድ እንዲሸመግሉ ይረዳቸዋል። እንዲሁም ተጋጮች መፍትሔ ወደማይገኝበት አጣብቂኝ ውስጥ እንዳይገቡ እና በአረዳድ ስህተት ምክንያት የሽምጋዮች ገለልተኝነት ጥያቄ ውስጥ እንዳይገባ ያግዛል። ፍርደ ገምድል ሽምግልና ተጋጮቹንም ሆነ የጥቃት ሰለባዎቹን አደጋ ላይ ይጥላል። ስለዚህ በገላጋይነት ሽምግልና ከመግባታችን በፊት የተፈጠሩ ነገሮች ቢኖሩ የማስተዋል ችሎታችን የሠላ መሆን አለበት። ድምጽ አልባ ምልክቶችን የምንረዳበት ጊዜ ቀጣዩቹን ሶስት ነጥቦች እንድንጠቀምባቸው ይመከራሉ።:

1. በቅርበት ተጋጭ ቡድኖችን አስተውል
2. የተለያዩ መላምቶችን አዳብር
3. ሽምግል

እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በመከተል ሽምጋዩ ማስተዋልን ከመተርጎም ጋር ማደባለቅ ያለውን አደጋ ይገነዘባሉ ለተጨማሪ ትርጉሞችም ክፍት ይሆናል።

አስረጅ: አቶ ትዕግስቱ - ከተጋጮቹ ቡድን አንዱ - አይኖቹን ወደ ጐን አንከባለላቸው ፣ በረጅሙ ተነፈሰ ፣ ከንፈሮቹን አሞጣሞጠና ፣ የእጆቹን ጣቶች አቆላልፎ የግራና ቀኝ አውራ ጣቶቹን ያሽከረክረዋል። ከዚህ በመነሳት ሌሎቹ የሚገምቱት “አቶ ትዕግስቱ ትዕግስት አልባና የተረበሸ ነው” የሚል ይሆናል። እዚህ ላይ የተለያዩ የማስተዋል ደረጃዎች እና ትርጉሞች (ትንታኔዎችን) ልብ ሳይባሉ ተደበላልቀው በአንድ ታይተዋል። ሽምጋዩ ራሱ ሳያስተውል የአካላዊ ቋንቋዎችን አሳይቶ ሊሆን ይችላል። ይሄኔ ምንም እንኳ ለዚህ ጠባዩ ሌላ ምክንያት ቢኖረውም የአቶ ትዕግስቱ ታጋሽ አለመሆን እንደእውነታ ይቆጠራል።

እንደ አማራጭ የሶስትዮሹን መሣሪያ በቅደም ተከተል ለመጠቀም መጀመሪያ ሽምጋዩ ዝም ብሎ መቃኘትና ያለውን ለውጥ ሊገልፅ ይችላል። “አቶ ትዕግስቱ ፊቱን ዘወር አደረገ ፣ እጆቹን አቆላለፈ፣. . . ።” በዚህ ጊዜ ሽምጋዩ እንቅስቃሴውን እየተረጎመ እና ድምዳሜ እየሠጠ አይደለም። ይህን በማድረግ ራሱን ከትዕይንቱ ዞር በማድረግ እንቅስቃሴውን ለመረዳት ጊዜ እና ክፍተት ይገኛል።

በሁለተኛ ደረጃ ከተፅዕኖ ነፃ በሆነ አስተሳሰብ የተለያዩ መላምቶችን ማዳበር ይችላል። “አቶ ትዕግስቱ ከራሱ ጋር ይብሰለሰላል ፣ አልተረጋጋም ፣ ተረብሿል ፣ ተቆጥቷል ፣ በሆነ ነገር ተመስጧል ፣ መልስ ሊሠጥ ፈቃደኛ አይደለም ፣ ራሱን እያረጋጋ ነው ፣ መናገር ይፈልጋል. . .” ወዘተ። አሁን ሽምጋዩ በተረጋጋ መንፈስ ያዳበረውን መላምት መገምገም ስለሚችል ይህ ነፃ አስተሳሰብ ባለው አመለካከት ላይ ተፅዕኖ ያሳድርበታል።

በሶስተኛ ደረጃ በተቻለ አቅም የተሻሉ ትርጉሞችን ለሙፈተን እድል ይኖረዋል። ጥያቄዎችን በመጠየቅ የተለያዩ መላምቶችን ታቀናጃለች። “አዲስ ሀሳብ ካለህ በጣም ደስተኛ ነኝ” ወይም “በፍጥነት ለመቀጠል ፍላጐት አለህ?” አንዳንዴ ያየነውን ነገር ለጥያቄ መልክ መንገር ጥሩ ይሆናል። “ፊትህ ላይ ብልጭ ያለች ፈገግታ አይቻለሁ?” ሽምጋዩ ንቁ ስላልሆኑ (unconscious) ጠባዮች በሚናገርበት ወቅት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። ተጋጩን ወገን ተያዝኩ ወደ ሚል ስሜት ሊመራ ይችላል። ሰውየውን ላለማሸማቀቅ ሲባል ያየነውን በሙሉ በግልጽ ላንናገር እንችላለን። ጥያቄው አቶ ትዕግስቱ በራሱ ላይ ሃሳብ እንዲሰጥ ወይንም ስሜቱን እንዲገልፅ የሚጋብዝ መሆን መቻል አለበት። ሽምጋዩም የተወሰኑት መላምቶች በራሱ ስሜት የተቃኙ መሆናቸውን ማስተዋል ይገባዋል።

## የሶስትዮሽ መሣሪያ

ደረጃ 1: ማስተዋል
ድምዳሜም ትርጉምም አይኖርም

ደረጃ 2: መላምትን መተንተን
ማስተዋሉን በተለያዩ መላምቶች መተርጎም

ደረጃ 3: መሸምገል
የመላምቶችንና የትርጓሜዎችን እውነታነት አመሳክር

ውስጣዊ ተግባር:
ራስን መግዛት

ውጫዊ ተግባር:
ለምሳሌ: በቃላት መግለጽ / መናበብ

## ራስን መግዛት

ሽምጋዮቹ ያላቸውን ማንኛውንም ሀብት በአግባቡ እንዲጠቀሙ ይረዳቸዋል። ይህ መሳሪያ የሚመጣውን/የሚሆነውን አስቀድሞ እስከ መናገር ድረስ በሚያስችል ሁኔታ የሽምግልና ሂደቱን መልካም ጅማሮና መሻሻል አጎልቶ ሊያሳይ ይችላል።

በህሊናችን እና በአካላዊ ቋንቋዎቻችን መካከል ቀጥተኛ የሆነ ተዛምዶ አለ። አቀማመጥ (posture) ወይንም ባህሪ (behavior) የውስጣዊ ማንነታችን መገለጫ ሆኖ ያገለግላል። በሌላ ጎኑም አቀማመጣችን ውስጣዊ ማንነታችን ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ሲሆን ከዚያ የተነሳ ከራሳችን ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር የሚችል ሲሆን ከዚያ የተነሳ ከራሳችን ጋር በሚኖረን ግንኙነት ላይ ተፅዕኖ አለው። ሽምጋዮቹ በሽምግልና ወቅት ይህንን ዕውቀት ሆን ብለው በንቃት መጠቀም ይችላሉ። በይበልጥ አስቸጋሪ በሆኑ ወቅቶች እና ሽምጋዮች ከአቅማቸው በላይ ሲሆን በአቀማመጣቸው ላይ የሚያሳዩት ትንሽ ለውጥ ወደ ትንሽ "ተዓምር" ሊመራ ይችላል። ብዙ ጊዜ ዘና ብለው በግልፅ እና በራስ መተማመን ስሜት የተሞላ አቀማመጥ የውስጣዊ ስሜታቸው ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያመጣል። በአማራጮች እና በጉልበት የተሞላውን የራሳችንን "ሃይለኛ አቀማመጥ" በልባችን ማስታወስ መቻል አለብን። ይህን ሀይለኛ አቀማመጥ ለማግኘት ሽምጋዩ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች በሚገባ መለማመድ ይኖርበታል።

1. ቀጥሎ የተዘረዘሩት ዐረፍተ ነገሮች እውነት በሆነበት አውድ ውስጥ ራስህን አስቀምጥ:

   "በሀይል እንደተሞላሁ ይሰማኛል።"

   "ደኅንነት ይሰማኛል።"

   "ከአካባቢዬ ጋር ቁርኝት እንዳለኝ ይሰማኛል።"

   "በቁጥጥር ውስጥ ነኝ።"

2. አሁን ስሜትህን አድምጥ እንዲሁም አስተውል:

   "እንዴት ነው የተቀመጥኩት?"

   "እንዴት ነው በእግሬ የቆምኩት? በምን መንገድ ነው እግሮቼ ከመሬት ጋር የተገናኙት?"

   "አካሌ ወደፊት እና ወደኋላ ይንቀሳቀሳል? የወንበሬን የኋላ ክፍል መንካት እችላለሁ?"

   "የእጄ አቀማመጥ እንዴት ነው? የጭንቅላቴስ?"

   "እንዴት ነው የምተነፍሰው?"

   "የአካሌ ውጥረት እንዴት ነው?"

   ውጥረት በተሞላበት ሁኔታም ቢሆን ለማስታወስ ቀላል እንዲሆንልህ ይህንን አቀማመጥ አስታውስ።

3. ሁሉ ነገር የጠፋብህን ሁኔታ በሚያስታውስህ አቀማመጥ ተቀመጥ። በመቀጠልም ከ"ተሸናፊ አቀማመጥ" ወደ "አሸናፊ አቀማመጥ" የሚወስድህን ቅደም ተከተል ደረጃ በደረጃ አከናውን። ይህ ቅደም ተከተል ተፈጥሯዊ እስኪመስል ድረስ ተለማመደው። ተጋጭ ወገኖችም ይህ ተፈጥሯዊ ይመስላቸዋል። ለበርካታ ጊዜያትና ለብዙ ቀናት ብትለማመደው ጥሩ ውጤት ታገኝበታለህ። ይህ የአቀማመጥ ለውጥ ሽምጋዮች ውጥረት በነገሰበት የሽምግልና ሂደት ወቅት እንዲጠቀሙበት ያስቀመጡት ዐይነት አቀማመጥ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። በተጨማሪም በተስፋ የተሞሉ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል። አብዛኛውን ጊዜም ወደ ተጋጭ ወገኖችም ተዛምቶ እነርሱም ተስፋ ይሞላባቸዋል።

### በእግሮቹ ማደራደር

ይህ ስልት በሸምጋዩ እና በተጋጮቹ መካከል መተማመን እንዲዳብር ይረዳል። ይህም ሸምጋዩ የተጋጭ አካላትን ስሜት እንዲረዳ ይረዳዋል። እግር ሸምጋዩ ግንኙነት/ንግግር እንዲፈጥር፣ እንዲቀጥል እና እንዲያቋርጥ ይረዳዋል። ይህም የሚሆነው እግርን ወደ ፈለጉት አካል አቅጣጫ በማዞር ወይንም በመመለስ ይሆናል። በተጨማሪም በሁለቱ ወገኖች መካከል የሚደረግን ንግግር ለማበረታታት ወይንም ለገለልተኛነት (all-partisanship) ይጠቅማል።

የአካላዊ ቋንቋ መሠረታዊ ነገሮች ማለትም ማስመሰል፣ የፊት ገፅታ እና አቀማመጥ በተወሰነ ደረጃ ልንቆጣጠራቸው እንችላለን። ለምሳሌ ያህል ስሜትን በሚጎዳ ሁኔታ (ገጠመኝ) ውስጥ የለበጣ (የማስመሰል) ፈገግታን ማሳየት የፊታችንን ገፅታ መቆጣጠር የምንችል ቢመስለንም ብዙ ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ሆኖ እናገኘዋለን። በተለይም ደግሞ የፊታችንን ገፅታ ከእግሮቻችን አቀማመጥ ጋር ለመቆጣጠር መሞከር ከሁሉም አስቸጋሪ ነው። እግሮቻችንን በተወሰነ አቀጣጫ አውቀን አስቀምጠናቸው ቢሆንም ትኩረታችን በሌላ ነገር ላይ ከሆነ ተመልሰው ወደ ቀድሞ ስፍራቸው ተመልሰው እናገኛቸዋለን። በሚገርም ሁኔታ በቀላሉ ልንቆጣጠራቸው የምንችላቸው እግሮቻችንን ቢሆንም በታማኝነታችን ላይ ትልቁን አስተዋፅኦ የሚያመጡት እነዚሁ የአካል ክፍሎቻችን ናቸው። ይህም ማለት በቃላችን የምንናገረው እና የአስተሳሰባችን አለመጣጣም በእግራችን በግልፅ ይታወቃል። ሰዎች ይህን ጉዳይ በደመነፍስ እንኳ ያውቁታዋል።

በሽምግልና ሂደት ላይ የተጋጭ ወገኖች እግር አቀማመጥ ከሌላኛው ተጋጭ ጋር ለመወያየት ፈቃደኛ መሆን አለመሆናቸውን ፍንጭ ይሰጣል። ሸምጋዩች ልብ ብለው እግሮቻቸውን መጠቀም እና አካላቸውን ሊያስተላልፉ በሚፈልጉት መልዕክት መሠረት ማስቀመጥ ያስፈልጋቸዋል። ይህን በማድረግ ራስን የመግዛት መሳሪያ በመጠቀም ያለማቋረጥ አቀማመጣቸውን ማሳየት (ማንፀባረቅ) ይገባቸዋል።

### ሀ ከተጋጮች ጋር ከመገናኘት :

1. የእግር ጣቶችህን ጫፍ ወደ ተጋጮቹ አዙር።
2. ከሁለቱም ተጋጮች ጋር በተመሣሣይ ጊዜ ለመገናኘት እና ከሁለቱም ጋር አብሮ ለመቆየት አንዱ እግርህን ወደ አንዱ ሌላኛውን ወደ ሌላኛው ተጋጭ ወገን በመጠቀም አስቀምጣቸው። አይን ለአይን በምትነጋገርበት ጊዜ እግሮችህ እንዳሉ ሆኖ አንደኛውን እጅህን ወደምታናግረው ተጋጭ አቅጣጫ አኑረው። ከዚህ በታች የምታየው ምስል እግርህን እንዴት መጠቀም እንደሚገባህ ያሳይሃል።

### ተጋጭ ወገኖች ወደ ውይይት እንዲገቡ እንዴት ማነሳሳት ይቻላል :

3. ከሁለቱም ተጋጮች ጋር የእግር ለእግር ግንኙነቱን ፍጠር።
4. ቀስ ብለህ ከአንደኛው ተጋጭ እግርህን ዘወር አድርግ። ከዚያ ቀጥሎ ከሁለተኛው ተጋጭ እግርህን ዘወር አድርግ።። ይህን በምታደርግበት ጊዜ በእጅህም ጭምር በማሳየት “በቀጥታ ለራሱ ልትነግረው ትችላለህ” በላቸው።
5. ተጋጮቹ አሁንም እርስ በርስ ከማውራት ይልቅ አንተን የሚያናግሩህ ከሆነ የሚያወራህን ሳይሆን የሚያደምጥህን ቡድን እያየህ የእግር ስራውን ከቡድን አንድ እንደገና ጀምር።



### ከረዳት ሸምጋይህ ጋር እንዴት ግንኙነት መመስረት ወይም ማጠናከር ይቻላል :

6. የእግር ጣቶችህን ወደ ረዳት ሸምጋዩ አቅጣጫ ጠቁም።
7. አያይዘህም እየተመለከተው ላፍታ ቆይ።

## ተግባር፡ የአካባቢ ቋንቋ ጥቅም

**ዓላማ** ተሳታፊዎች በተግባቦት ሂደት ውስጥ የአካባቢ ቋንቋ ያለውን አስተዋፅኦ እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1፡ ተሳታፊዎ በሶስት ቡድን ተከፋፍለው እየተወያዩ “የራስ መግዛት”ን እና የ”እግር ማደራደር”ን መሣሪያ እንዲጠቀሙ አድርጋቸው።

ደረጃ 2፡ ተሳታፊዎቹ ስለተጠቀሙት እና ስላስተዋሉት አካባቢ ቋንቋዎች ግብረ-መልስ እንዲሰጡበት አድርጋቸው።



## III.6.4 በሽምግልና ሂደት ወቅት ማዳመጥ

| | |
|---|---|
| ዓላማ | በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች በንቃት የማዳመጥ ክህሎት የሚያስገኘውን ጥቅም ይረዳሉ። |
| የተመደበ ጊዜ | 30 ደቂቃ |
| መነሻ ዕውቀት | II.3 የባህላዊ ሽምግልና እና አመቻች ሽምግልና ውህደት። |
| መርጃ መሣሪያዎች | የወረቀት ሠሌዳ ፣ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ ማርከሮች ፣ የተለያዩ ባለቀለም ማወያያ ካርዶች |
| ቅደም ተከተል | ደረጃ 1: ርዕሱን ካስተዋወቅ በኋላ በንቃት የማድመጥ ክህሎት ጠቀሜታን እና ባህሪን አመላክታቸው። |
| | ደረጃ 2: የሦስት ጊዜ ማድመጥ መልመጃን አቅርብላቸው (III.4.1)። |

ተጋጭ አካላትን ለማስማማት እና የተፈጠረውን ችግር ከመፍታታቸው በፊት ሽምጋዮች በግጭታቸው ምክንያት የያዙትን አቋም ፤ ማለትም ስጋታቸውን ፣ ጥቅማቸውንና ፍላጐታቸውን መረዳት አስፈላጊ ነው። ይህንን ለማድረግ ደግሞ ሽምጋዮች ንቁ አድማጭ መሆን አለባቸው። በንቃት ማድመጥ ምንም ዓይነት ምላሽ ለተናጋሪ ሳይሰጡ በአካልም በመንፈስም ተመስጦ ማድመጥ ነው። (በአካላዊ ቋንቋ ላይ የሚያትተውን ቀዳሚ ምዕራፍ ተመልከት።) የተጋጭ ቡድኖቹን ችግር እንደራስ ችግር አድርጐ ማየት እንዲሁም ምንም ፍርድ ሳይሰጡ ነገሩን በጥሞና ማድመጥ መሞከር በአንድ ሽምጋይ በወጥነት ሊተገብራቸው የሚጠበቁ የሽምግልና ክህሎቶች ናቸው።

### በንቃት የማድመጥ ጥቅሞች :

- አዎንታዊ እና ምቹ ድባብን ይፈጥራል። ተጋጭ ወገኖች ሀሳባቸውን ስሜታቸውን እና ልምዳቸውን ለማስረዳት በቂ ስፍራ ፣ ጊዜና ትኩረት ያገኙበታል። ይህ ደግሞ ከዚህ በፊት ያልተለመደ እና የሚያረካ ልምድ የሚያገኙበት ሊሆን ይችላል። ይህ ሲሆን ሊበረታቱና ነፃነት ሊሰማቸው ይችላሉ።
- ግልፅነትን ይፈጥራል። ተጋጭ ወገኖች ሽምጋዩ ችግራቸውን ለማዳመጥ እና ለመርዳት ከልብ የመነጨ ፍላጉት እንዳለው በተረዱ ጊዜ ያለባቸውን ችግር ለመፍታት ይነሳሳሉ። እንዲሁም ሌሎችን ለማድመጥ እና ለመረዳት ዝግጁነት ያጎናፅፋሉ።
- ተናጋሪው እንደተደመጠ ፣ በሚገባ እንደተረዱት ፣ እንደተቀበሉት እና እንደተከበረ ይሰማዋል።
- ለሽምጋዩ መልካም አመለካከት እንዲኖራቸውና እምነት እንዲጥሉበት ያደርጋል።
- ውጥረትን እና ንዴትን ያረግባል። ተጋጭ ወገኖች ፍላተ ስሜታቸውን እና ንዴታቸውን እንዲያበርዱ ያደርጋል።
- ራስን ማሳያ እና ግልፅ የመሆንን እድል ይሰጣል። በሚገባ ያለባቸውን ችግር ማስረዳት እንዲችሉ ሲሉ የተፈጠረውን ጠብ በአግባቡ ለመረዳት ይሞክራሉ። ይህ ደግሞ የስሜታቸውን እያንዳንዷን ቅንጣት እንዲመለከቱ እና ሀሳባቸውን እና የነገሩን ትርክት በአግባቡ እንዲያደራጁ ያደርጋቸዋል።

### በንቃት የማድመጥ ሂደቶች

በንቃት ለማድመጥ ዋናው ነገር ሽምጋዩ የተጋጭ ወገኖችን ሀሳብ እና መልዕክት በንግግርም ሆነ ያለንግግር እያደመጠ መሆኑን መግለፅ ነው።

### ተናጋሪውን እያደመጥን መሆኑን የምናሳውቅባቸው የንግግር መንገዶች :

- ደጋፊና አበረታች ዐረፍተ ነገሮችን በመጠቀም: “ቀጥል” ፣ “ከዛ ምን ሆነ” ፣ “አዎ ገባኝ” ፣ “ሌላስ” ፣ “ምን እንደተፈጠረ ልታብራራልኝ ትችላለህ” ፣ ወዘተ
- እንደተረዳን መግለፅ: “ተረድቻሃለሁ” ፣ “አሃ” ፣ “እሺ”
- መልዕክቱን እየተረዳኸው እንደሆነ እውቅና መስጠት: “እ” ፣ “አሃ” ፣ “በጄ”
- ይዘቶቹን ማረጋገጥ: “እንዲህ ያልከው ትክክል ነው” ፣ “በዚህ ጉዳይ ላይ የተናደድክ ይመስላል”
- ማብራሪያ መጠየቅ: “የገባኝ አይመስለኝም” ፣ “እንደዚህ ነው ያልከው” ፣ “ምሳሌ ልትሰጠኝ ትችላለህ”

### እንደዚህ ግን አታድርግ :

- የራስህን ሃሳብ ወይም ማንኛውንም አተረጓገም ፣ አረዳድህንም ሆነ የራስህን ምክር አትስጥ። በንቃት ማድመጥ ማለት ማድመጥ ብቻ ነው።
- ፍረጃዎችን አትጠቀም: “ያን ያህል መጥፎ የሚባል ነገር አይደለም” ፣ “አትናደድ” ፣ “ትንሺን ነገር አገዘፍካት” ፣ “ተረጋጋ እንጂ” ። እነዚህ አገላለፆች መረዳትህን ሳይሆን ለመፍረድ መቻኮልህን ያሳያሉ።
- ስሜታዊ አትሁን፣ አትናደድ፣ አትቆጣ ወይም ተከራካሪ አትሁን።
- ባደመጥከው ነገር ላይ ያንተን እሴት እና ያንተን ትርጉም አትጨምርባቸው። አእምሮህን ክፍት አድርገህ ለመረዳት ሞክር።

### ተናጋሪውን እያደመጥከው መሆኑን የምታሳውቅበት ያከድምጽ የሚከናወኑ ስልቶች : [41]

- አካላችንን ወደ ተናጋሪው ዘንበል በማድረግ ሌላውን ወገን ባለመርሳት ግልፅነትን በሚያሳይ መልኩ መቀመጥ።
- ተገቢ የሆነ አካላዊ ገለፃ ማድረግ / ራስን ማወዛወዝ/።
- ተገቢ የአይን ለአይን ግንኙነት ማድረግ።
- ተገቢ የሆነ የድምጽ አወጣጥ መጠቀም።

በአጠቃላይ በንቃት ለማድመጥ ሌሎች ሰዎችን የመረዳት ፍላጐት ሊኖረን ይገባል። ተናጋሪውን ማክበርና መቀበል እንዲሁም ከልብ በመነጨ ስሜት ችግሩን የራስ ችግር አድርጐ ማየትን ይጠይቃል። ሽምጋዮች የራሳቸውን ሐሳብ ፣ አጀንዳ እንዲሁም ፍረጃ ወደ ጎን አድርገው የተናጋሪውን ነጥቦች ፍላተ ስሜቶች እና አመለካከቶች ሊያደምጡ ይገባል። ይህ ፈታኝ የሆነ እና ሊለማመዱት የሚገባ ተግባር ነው።[42]

41 ክፍል III.6.3 በሽምግልና ውስጥ የአካላዊ ቋንቋ አስፈላጊነት የሚለውን በገጽ 62 ይመልከቱ።

42 ይህ ክፍል በኢትዮጵያ በ2010-2011ዓ ም በጂ አይ ዜድ ሲፒኤስ ኢሜዲኦ በተዘጋጀው የሽምግልና ስልጠና ላይ ከተዘጋጀው ፅሑፍ የተመሰረተ ሲሆን ይህም በከፊል በNiederberger von Wyl, J (2009) የሽምግልና ስልጠና መምሪያ ከሚለው የተወሰደ ነው። ከBurgess, G & Burgess, H (2003) ጋር ያነጻጽሩ።

## III.6.5 ፊታኝ መልዕክቶችን መጋፈጥ፡ ንግግርን በራስ አገላለጽ ማቅረብ እና ማጠቃለል

በተካረረ ግጭት ውስጥ ወይም ተጋጭ ወገኖች በሽምግልና ሂደት ውስጥ ስሜታዊ ሆነው ሲቀርቡ ሽምጋዩ እነዚህን ስሜቶች ይዞ ከዕውነታው ይልቅ ስሜቱ ላይ ማተኮር ይኖርበታል። ሽምጋዩ ተጋጮቹን መልሶ ራሳቸውን ለማሳየት (መናበብን) በቃላት የሚጠቀምበት ንግግርን በራስ አገላለጽ ማቅረብ ወይም ማጠቃለል ይባላል። የሚከተለውም ውይይት እና ተግባር የሚያሳየው ይህንኑ አስፈላጊ የሽምግልና ስልት ነው።

## ተግባር፡ በራስ አገላለጽ ማቅረብ እና ማጠቃለል

**ዓላማ** በራስ አገላለጽ ማቅረብ እና ማጠቃለል።

**የተመደበ ጊዜ** 30 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ ማርከሮች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: በማሳጠር ንግግር ወቅት የ“አድርግ” እና “አታድርግ” ምሳሌዎችን ስጥ።[43]

ደረጃ 2: ተሳታፊዎቹ ሁለት ሁለት ሆነው እንዲቧደኑ አድርግ እና ፊት ለፊት ተቀምጠው በአከራካሪ ርዕስ ጉዳይ ላይ ይወያዩ።

ከሁለቱ ተሳታፊዎች አንዱ ንግግር ያደርጋል። ከዚያም ሁለተኛው ተሳታፊ የሠማውን ንግግር በራሱ አገላለጽ ማቅረብ ይጠበቅበታል። የመጀመሪያው ተሳታፊ በሌላኛው ተሳታፊ የቀረበው አገላለጽ ወይም ማጠቃለል ትክክል መሆኑን ምልክት ሲሰጥ ብቻ ሁለተኛው ተሳታፊ ሌላ አዲስ ንግግር ያቀርባል።

ተሳታፊዎቹ ስሜታቸውን እና አትኩሮታቸውን የገዛው ነገር ላይ መወያየት ከመጀመራቸው በፊት ከ5-10 ደቂቃ ድረስ የመለማመጃ ጊዜ ስጣቸው።

በሚለማመዱበት ወቅት የራስህን ምልከታ በማድረግ ለተሳታፊዎቹ አካፍላቸው። በችኮላ ነገሮችን በራስ አገላለጽ ማቅረብ በንግግር ወቅት ያለውን ጉዳት በመጠየቅ ገምግም። ተሳታፊዎች የዚህን ስልት አዎንታዊ ጐን እንዲገልፁ ጋብዛቸው። ከዛ በመቀጠል በተጋጭ ወገኖች መካከል ይህ ስልት ያለውን አስተዋፅኦ ተወያዩበት።

### በቃላት የሚገለጡ “አድርግ”

“በትክክል ተረድቼህ ከሆነ ያልከው...”

“እንደዚህ የተሰማህ ይመስለኛል...”

“እንዲህ አይነት ስሜት አለኝ...”

### በቃላት የሚገለጡ “አታድርግ”

“እንደዚህና እንደዚህ አስብ ነው ያልከው።”

“...ያልከው እውነት ነው።”

“...ስትል ሌሎቹን የተረዳህበት መንገድ ስህተት ነው።”

“ሌላውን ወገን አልተረዳኸውም። አንተ የመሰለህ...”



43 ክፍል III.6.4 በሽምግልና ወቅት ማዳመጥ በገጽ 67 ይመልከቱ።

ደረጃ 3: ይበልጥ ፈታኝ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መልመጃ ስሩ:

አጠር አድርገህ ሃሳብን የመከተልና የመናበብን (mirroring) ፅንሰ ሃሳብ ካብራራህ በኋላ የድምጽ አልባ ተግባቦት ነጥቦችን አስተዋውቃቸው[44]። መከተል እና መናበብ (mirroring) ማለት የተጋጭ ቡድኖችን ምኞት ለመጠበቅ ሲባል የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ መከተል ማለት ነው። ለተሳታፊዎቹ ቀጣዩን ቅደም ተከተል በማቅረብ "መከተልን" ልታሳያቸው ትችላለህ።

**በድምጽ አልባ የሚገለፁ "አድርግ"**

ሁሌም አንድ እግርን ወደምታደምጠው ሰው ሰንዘር ማድረግ።


እንቅስቃሴያቸው ተከታተል /መናበብ/።

**በድምጽ አልባ የሚገለፁ "አታድርግ"**

ወደ አንዱ ተጋጭ ወገን አካልን ዘንበል ማድረግ ።

አንደኛው ተጋጭ ሌላኛውን ሲዘልፍ ጭንቅላትህን በአዎንታ መነቅነቅ።

በባዶ አየር ወይም በጣት ጥፍሮችህ ላይ ማፍጠጥ።




ተሳታፊዎቹ መናበብን (mirroring) እና መከተልን በመጠቀም ልምምዱን እንዲጀምሩት ጠይቃቸው። የማረካቸውን ነገር ወይም ስሜታቸውን ከመወያየታቸው በፊት ከ5-10 ደቂቃ ድረስ ስጣቸው። በልምምዱ ወቅት ቡድኖቹን በሚገባ ተመልከት እና ያየኸውን ለተሳታፊዎቹ አካፍላቸው።

ደረጃ 4: .የተማሩትን ትምህርት በማስተማሪያ ወረቀቱ ላይ አስፍር።

---

44 ክፍል III.6.3 በሽምግልና ውስጥ የአካባዊ ቋንቋ አስፈላጊነት የሚለውን በገጽ 62 ይመልከቱ።

## III.7 የግጭት አተያይ ትንታኔ (Conflict Perspective Analysis)

የግጭት አተያይ ትንታኔ[45] የዳበረው በአንሚዲዩ በርሊን ሲሆን ከተለያዩ ተዋናዩች አንፃር ጥልቅ የሆኑ ጉዳዩችን ለመረዳት እና ለመፈተሽ እንድንችል ያደርገናል። በተጨማሪም ተጋጭ ወገኖች ሌላው ወገን ምን እንደሚሰማው እና እንደሚያስብ እንዲረዱ ያደርጋል። የግጭት አተያይ ትንታኔ ሸምጋዮች የሽምግልና መድረኩን በሚገባ እንዲያዘጋጁ ፣ የችግሩን ሥረ-መሠረት በተሻለ ሁኔታ እንዲረዱ እናም በሽምግልና ወቅት ማድረግ የሚጠበቅባቸውን በተነሳሽነት እንዲያከናውኑ ያግዛቸዋል።

ሽምግልና ከመጀመሩ በፊት ሸምጋዮች እያንዳንዱን ተጋጭ ወገን በሚመለከት ምኞታቸውን ፣ ስጋታቸውን እና ስሜታቸውን የሚያሳይ "የግጭት ጥንቅር (conflict map)" ያዘጋጃሉ። በጥንቅሩ መካከል "የመነካት መላምት (empathy hypothesis)" የምንለው ይገኛል። ይህ ጥንቅር ከሌላ ሸምጋይ ጋር ወይም ከስራ ባልደረባ ጋር ቢሠራ ይመከራል። "የመነካት መላምት" የሚዘጋጀው በእያንዳንዱ ተጋጭ ቦታ ራስን በማስቀመጥ ነው። ይህ ስልት ሸምጋዮች የሚፈቱት ችግር ምን ያህል ውስብስብ እንደሆነ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። ሸምጋዮች በሽምግልና ወቅት የግጭት አተያይ ትንታኔ ጥንቅርን በመጠቀም የተጋጭ ወገኖችን የጋራ መግባባት ለመረዳት የመላምት ዝርዝር ያዘጋጃል። ይህም ዝርዝር የሌሎችን ተጋጭ ወገኖች ስሜት ፣ ስጋት እና ምኞት ለማገናዘብ ይጠቀማል።

## ተግባር ፡ የግጭት አተየይ ትንታኔ እንዴት ይዘጋጃል፡ የአርሻ ባለሀብት ነገረ ጉዳይ

**ዓላማ** ተሳታፊዎች ተግባራዊ የሆነ የግጭት አተያይ ትንታኔ ክህሎትን ነጠላ ታሪክን በመውሰድ እንዲያዳብሩ መርዳት።

**የተመደበ ጊዜ** 120 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ ማርከሮች፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ ፣ ስፒል

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: አራቱ የግጭት አተያይ ደረጃዎችን አስተዋውቅ:

1. ባለ ድርሻ አካላትንና ባለጉዳዩችን መለየት።
2. በጉዳዩ ላይ እያንዳንዱ ተጋጭ ወገን ያስቀመጠውን አቋም እና ዕውነታን መሰብሰብ።
3. በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን ስጋት ፣ ስሜት እና ምኞት መለየት።
4. ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ ጠንካራ መፍትሄን ለማስቀመጥ የጋራ ፍላጐቶችን ፣ ልዩነቶችን እና የመግባቢያ ድልድዮችን መለየት።

ደረጃ 2: በነጠላ ታሪኩ ላይ የተዘጋጀውን ፅሁፍ ስጣቸው፤ ለማንበብ እና ጥያቄያቸውን ለመለየት 15 ደቂቃ ፍቀድላቸው።

ደረጃ 3: ነጠላ ታሪኩን አራቱን የግጭት አተያይ መንገዶችን በመጠቀም አብራራ። ሁለት እኩል የተከፈሉ ቡድኖችን መስርት። እያንዳንዱ ቡድን በግጭት ውስጥ የራሱ አቋም ያለውን አንድ ተጋጭ ቡድንን ይወክላል።

1. ተጋጭ ቡድኖቹን ለይ።

ቡድን 1 ባለሀብት።

ቡድን 2 የአካባቢው ማኅበረሰብ።

[45] Wüstehube, L (2004)

2. በተጋጭ ቡድኖቹ የተቀመጡትን ነጥቦችን (አቋምን፣ ዕውነታን) ዘርዝር።

### ስለ ባለሀብቱ ያሉ ዕውነታዎች /ቡድን 1/ እና ያቀረባቸው ጉዳዮች

- ባለሃብቱ መሬቱን ለማግኘት ሁሉንም ህጋዊ መንገዶች አሟልቷል።
- ባለሃብቱ ለስራው የሚያስፈልጉ የሰው ሃይልና የማምረቻ መሣሪያዎችን በስፍራው ላይ አሰማርቷል።
- ባለሃብቱ በአካባቢው ማኅበረሰብ ጥቃት ደርሶበታል።
- ባለሃብቱ መንግሥትንና የአካባቢው ማኅበረሰብን ለደረሰበት ጉዳት ካሳ እንዲከፈለው ጠይቋል።
- ባለሃብቱ ለክልሉ እድገት አስተዋፅኦ የማድረግ ከፍተኛ ፍላጐት አለው።
- ባለሃብቱ በምርት ወቅት የአካባቢውን ማኅበረሰብ በመቅጠር የስራ ዕድልን የመፍጠር እቅድ አለው።

### ስለአካባቢው ማኅበረሰብ ያሉ ዕውነታዎች /ቡድን 2/ እና ያቀረቧቸው ጉዳዮች

- በመጀመሪያ አካባቢ በልማቱ የተስማሙ ይመስሉ ነበር።
- ማንነታቸውን እንዳያጡ ፍርሃት አድሮባቸዋል።
- መሬታቸውን ለልጅ ልጆቻቸው ማቆየት ይፈልጋሉ።
- መንግሥት ላይ አመኔታ አጥተዋል።
- ማምረቻ መሣሪያዎችን አውድመዋል፤ ሠራተኞቹ ላይ ጥቃት አድርሰዋል።
- ራሳቸውን በቀውስና ነውጥ ውስጥ ከተውታል።

3. የእያንዳንዱን ቡድን ስጋት ፣ ስሜትና ምኞት ለይተህ አስቀምጥ።

ስለተጋጭ ቡድኖች ማመላከት ሳይሆን ከተጋጮቹ አንፃር ዐረፍተ ነገሮችህን እንዲህ በማለት ማስቀመጥ ትችላለህ።

እንዲህ እሰጋለሁ / እንሰጋለን　　　እንዲህ ይሰማኛል / ይሰማናል　　　እንዲህ እመኛለሁ / እንመኛለን

## ባለሀብቱ /ቡድን 1/

### እሰጋለሁ

- በአካባቢው ማኅበረሰብ ጥቃት ይደርስብኛል ብዬ እሰጋለሁ።
- በማኅበረሰቡ ማስፈራሪያ ይደርስብኛል ብዬ እሰጋለሁ።
- ያለኝን ተቀባይነትና የስራዬን ዋጋ አጣለሁ ብዬ እሰጋለሁ።
- ንብረቴን ይደርስብኛል ብዬ እሰጋለሁ።
- የክልሉ የልማት እቅድ ላይ ያለኝ ተሳትፎ ይደናቀፋል ብዬ እፈራለሁ።
- በአካባቢው ማኅበረሰብ እና በሌሎች ወገኖች እጠቃለሁብዬ እፈራለሁ።

### ይሰማኛል

- በመንግሥት እና በማኅበረሰቡ እንደተታለልኩ ይሰማኛል።
- በአካባቢው ልማትና ሰላም ለማምጣት ጠንክሬ መስራቴ ሌላ ጣጣ እንዳመጣብኝ ይሰማኛል።
- በመንግሥት ቸልተኝነት ቅር ተሰኝቻለሁ
- ተስፋ እንደቆረጥኩ ይሰማኛል።
- ሌላ ፍላጐት ያላቸው ቡድኖች ጣልቃ እንደገቡ ይሰማኛል።
- ሰዎቹ በሌሎች ኢንቨስተሮች የተገፋፉ እንደሆነ ይሰማኛል።

### እመኛለሁ

- መንግሥት ችግሩን እንዲፈታው እመኛለሁ።
- ወጣቱ ትውልድ ከዚህ ኢንቨስትመንት በርካታ ጥቅም እንዲያገኝ እመኛለሁ።
- የማኅበረሰቡ አኗኗር ደረጃ እንዲሻሻል እመኛለሁ።
- በዚህ አካባቢ ሰላምና ብልፅግና እንዲሰፍን እመኛለሁ።

## የአካባቢው ማኅበረሰብ ተወካይ /ቡድን 2/

### እሰጋለሁ

- የባለሀብቱን ፍላጐት ለማሟላት ሲባል እንዳንሸጥ እሰጋለሁ።
- ልጆቻችንን መመገብ እንዳያቅተን እሰጋለሁ።
- የልጅ ልጆቻችን እንዳይሰቃዩ እሰጋለሁ።
- እንደ ተወካይነታችን በማኅበረሰቡ ያለንን ተቀባይነት እንዳናጣ እሰጋለሁ።
- ማንነታችንን እናጣለን ብዬ እፈራለሁ።

### ይሰማኛል

- ይህ የቅኝ ገዥነት አንደኛው መንገድ እንደሆነ ይሰማኛል።
- እንደተሸጥን ይሰማኛል።
- የመንግሥት ኃላፊዎች ጉቦ እንደተቀበሉ ይሰማኛል።
- የሚመጣው ትውልድ በባህል ወረራ የሚጠቃ ይሰማኛል።
- መሬታችንን መጠበቅ እንዳለብን ይሰማኛል።
- እንደተወረርን ይሰማኛል።

### እመኛለሁ

- ባለሀብቱ መሬታችንን ለቆ ቢሄድ እመኛለሁ።
- መንግሥት ጣልቃ ገብቶ ለኛ በቂ መፍትሔ የሚሆን ነገር እንዲሰጠን እመኛለሁ።
- መሬታችንን እና ህዝባችንን ከባህል ወረራ መከላከል እመኛለሁ።

4. ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም በግጭቱ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑ አካላትን የጋራ ፍላጐቶች ፤ ልዩነቶች እና የመግባቢያ ድልድዮች ለይተህ አስቀምጥ።

ከተጋጮቹ ፍላጐት የትኛዎቹ ተመሳሳይ ናቸው? የትኞቹስ ይለያሉ? የመግባቢያ ድልድዮች የምንላቸው ተመሳሳይ የሆኑ ነገር ግን የተለያዩ መሠረት ወይም መዳረሻ ያላቸው ስሜቶች ፤ ጥቅሞች (ምኞቶች) እና ስጋቶች ናቸው። ለምሳሌ:- ማንኛውም ተጋጭ አካል ሊታለል (ridiculed) አይፈልግም። ነገር ግን ሌላኛው ተጋጭ አካል ያን ሊያደርግ ይችላል ብሎ ይሠጋል። ይህ ስጋት ሁለቱም ተጋጭ አካላት ሊጋሩት የሚችል ነው። ምንም እንኳ የስጋታቸው ምንጭ ቢለያይም ይህ ስጋት ሁለቱም የሚግባቡበት ነው።

ደረጃ 4: ተሣታፊዎች እንዲወያዩ በማድረግ ምላሻቸውንም በሚገለጠው ወረቀት ላይ ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ መሠረት ዘርዝራቸው።

| ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች | የባለሀብቱ ምላሽ | የማኅበረሰብ ተወካዩች ምላሽ |
|---|---|---|
| በግጭት ውስጥ መሳተፍ ላንተ ምን ይጠቅምሃል? | | |
| ከዚህ ግጭት ብትወጣ ምን የከፋ ነገር ይገጥምሃል? | | |
| ሰላም ቢኖር አንተ ምን የተሻለ ነገር ታገኛለህ? | | |

በዚህ ምሳሌ መሠረት የሚጠበቀው ውጤት ከዚህ በመቀጠል የተዘረዘሩትን ሊመስል ይችላል።

| ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎች | የባለሀብቱ መልስ | የማኅበረሰብ ተወካዩ መልስ |
|---|---|---|
| በዚህ ግጭት ውስጥ መሳተፍህ ላንተ ምን ይጠቅምሃል? | ንብረቴን አጥቼያለሁ።<br>የመስራት መብቴን ተነፍጌያለሁ።<br>በርካታ ሀብቴን ካፈሰስኩ በኋላ በስተመጨረሻ ባዶዬን ቀርቻለሁ።<br>ህጉን ተከትዬ ነው እየሠራሁ ያለሁት።<br>አለም አቀፍ ህጎች ተጥሰዋል።<br>መንግሥት ላይ ያለኝን እምነት ተሟጧል።<br>ሥራው አዋጭ እና አትራፊ ሆኖ አግኝቸዋለሁ።<br>የድኾችን ህይወት የመለወጥ ብርቱ ፍላጎት አለኝ። | ባህላችንና ማንነታችን ተደፍሯል።<br>መሬታችን ሊጠበቅልን ይገባል።<br>እምነት የሚጣልበት ስራ አይደለም።<br>የልጆቻችንን ጉልበት እንዲበዘበዝ ያደርጋል።<br>መንግሥት ላይ ያለንን እምነት አጥተናል።<br>መሬታችንን ልንከላከል ይገባል።<br>ባህላችንን እና መሬታችንን ለሚቀጥለው ትውልድ ጠብቀን ማቆየት ይኖርብናል።<br>ባለሀብቱ የውጭ ዜጋ በመሆኑ ሀብቱን በሞላ ወደ ሀገሩ ያሻግረዋል። |
| ከዚህ ግጭት ብትወጣ ምን የከፋ ነገር ይገጥምሃል? | በዚህ ስራ ላይ ለመቆየት የራስ መተማመኔን አጣለሁ።<br>ስሜ ሊጠፋ ይችላል።<br>ለወደሙብኝ ንብረት ካሳ አላገኝም።<br>የሞራልም ሆነ የስነ ልቦና ውድቀት ይደርስብኛል። | ወጣቱ ትውልድ በአባቶቹ ላይ እምነት ያጣል።<br>መሬታችን ይወሰዳል፣ ባህላችን ይበረዛል።<br>የግለሰብ ጠብ ሊነሳ ይችላል።<br>መንግሥት ማኅበረሰባችንን የሚጎዳ ሌላ ተግባር ሊፈፅም ይችላል። |
| ሰላም ቢኖር ምን የተሻለ ነገር ታገኛለህ? | የአካባቢው ማኅበረሰብ ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ጠንክሬ እሰራለሁ።<br>ሥራዬን ዘላቂ በሆነ መልኩ ለመስራት ሰላም እንዲሰፍን እጥራለሁ። | በመንግሥትና በሁሉም አካላት መካከል የጋራ መግባባት ይፈጠራል።<br>ከልማቱ የአካባቢው ማኅበረሰብ በተጨባጭ ይጠቀማል። |

ደረጃ 5: ሁሉን ተጠቃሚ ለሚያደርግ መፍትሔ አማራጭ መፈለግ። እነዚህ የጋራ ፍላጎቶች ልዩነቶች እና የመግባቢያ ድልድዮች በተጋጭ ቡድኖች መካከል ዘላቂ ሰላም እንዲሰፍን ሸምጋዮች ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሄን የሚያንጸባርቁበት አምድ ናቸው። ከተሳታፊዎች ጋር ተመራጭ እና ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉትን ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሄዎች ተወያዩበት።

| ጥያቄዎች | ባለሀብት | የአካባቢው ማኀበረሰብ ተወካዮች |
|---|---|---|
| ከአማራጮቹ ተግባራዊ ይሆናሉ ተብለው የታሰቡት የትኞቹ ቅደም ተከተሎች መወሰድ አለባቸው? | | |
| ለነዚህ ቅደም ተከተሎች ምን ማበርከት ትችላለህ? | | |
| ስለግጭቱ ምን አዲስ ነገር ተረዳህ? | | |
| ለአንተ ጥቅም ሲባል ምን ተለወጠልህ? | | |
| ከሂደቱ ምን ዓይነት መደምደሚያ ላይ ደረስህ? | | |

በዚህና በቀጣዩቹ ክፍለ ጊዜያት ጠቃሚ የሽምግልና ክህሎቶችና መሣሪያዎች ዙሪያ ጠቃሚ ነጥቦችን አይተናል። በተጨማሪም ተግባቦት በጣም ውስብስብ ብቻ ሳይሆን አስቸጋሪም መሆኑንም ተመልክተናል። ነገር ግን መልካም ተግባቦት በሽምግልናው ሂደት ወቅት ውጤት እንዲገኝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ተጋጮች አመለካከታቸውን እንዲለውጡ እና በመጨረሻም በጋራ ወደተቀበሏቸው መፍትሔዎች እንዲመጡ፤ ሁለቱም ቡድኖች እርስ በእርሳቸው እንዲግባቡና የበለጠ ደግሞ አንዱ ሌላው ተረድቶኛል የሚል መረዳት ውስጥ መግባት አለባቸው። ይህን ማድረግ ደግሞ የሽምጋዩ ሥራ ነው። ቀጣዩ ምዕራፍ ይህንን እንዴት ማሳካት እንደምንችል ያሳየናል።

## III.8 በግጭቶች መካረር ውስጥ እና በመጀመሪያ ደረጃዎች ላይ የተናጥል የሽምግልና ሂደት ጠቀሜታ

በአጠቃላይ የተናጥል የሽምግልና ሂደት ማለት ሽምጋዩ እንደሽማኔ "መወርወሪያ" ከአንዱ ቡድን ወደሌላኛው ቡድን እየተዘዋወረ አንዳንዴ ደግሞ በሁለቱ መሃል ያለውን መረጃዎችን እየያዘ ይሠራል ማለት ነው። ሽምጋዮች በተናጥል የሚደረግ ውይይትን በሽምግልና መጀመሪያ ጊዜ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠርና በተጋጭ ወገኖች መካከል ለውይይት ፈቃደኝነት መኖሩን ለማሰስ ይጠቀሙበታል። በአንደኛው ቡድን አነሳሽነት ሽምጋዮች ሲጋበዙ ሌላኛው ተጋጭ ወገን ዘንድ ቀርቦ ለሽምጋይነታቸው ያለውን ፈቃደኝነት ማረጋገጥ ይገባል። የተናጥል ሽምግልና ተጋጮቹ በግጭቱ ዙሪያ የራሣቸውን አስተያየት በግልጽ እንዲናገሩ ዕድል ይሠጣል። ሽምጋዮችም ግጭቱን በጥልቀት ለመመርመር ፣ የመነሻውን ዳራ ፣ ሥር መሠረቱን ለመለየት እና የግጭቱን መንስኤ አበጥሮ ለመረዳት ዕድል ይሠጣቸዋል። ይህ ደግሞ የሂደቱን ተገቢ ስልት እንዲነድፉ ያግዛቸዋል።

### የቅድመ - ሽምግልና ክፍለ ጊዜ

የተናጥል ሽምግልና የኢትዮጵያ ባህላዊ ሽምግልና ሥነ ስርዐት ጠባይ አለው። በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በቤተሰብና በማኅበረሰብ ግጭት ወቅት ሽምጋዮች ብዙውን ጊዜ ለማስታረቅ የራሳቸውን ተነሳሽነት ይወስዳሉ፤ ወይም የተፈጠረውን ችግር እንዲፈቱ በሌሎች ይጋበዛሉ። ሽምጋዮች የሽምግልና ሂደቱን ከመጀመራቸው በፊት በተጋጭ ወገኖች መካከል ተቀባይነት ለማግኘት እንደአገናኝ ይጠቀሙበታል። በዚያውም ስለግጭቱ ዕውቀት ይኖራቸዋል። እንዲሁም የመገናኛ ጊዜ ቀጠሮም ይወስዳሉ። የመገናኛ ጊዜ ቀጠሮ መውሰድ ብቻ ሳይሆን የግጭቱን ደረጃ አውድ ፣ እንዲሁም የተጋጮችን አቋም ለመረዳት ይህ ጥሩ ዕድል ይሆናቸዋል።

### በተናጥል የሚደረግ ውይይት (Caucus Group Discussions)

በተናጥል የሚደረግ ሽምግልና ብዙ ጊዜ የምንጠቀመው ግጭቱ በከረረበትና ተጋጮቹ እርስ በእርስ ለማውራትም ሆነ ዐይን ለዐይን ለመተያየት ፍላጎት ባጡበት ጊዜ ነው። እንዲሁም ደግሞ ተጋጮች ውይይታቸውን ለመቀጠል አጣብቂኝ ውስጥ በገቡበት ጊዜ ያገለግላል። በዚህ ወቅት ሽምጋዮቹ የጋራ ውይይቱን አቋርጠው ከእያንዳንዱ ተጋጭ ቡድን ጋር በተናጥል የሚደረግ ውይይት ማካሄድ ይገባል። ይህን ማድረግ ቡድኖቹ እንዲወያዩ ጊዜ ያገኛሉ ፣ በሽምጋዮች ድጋፍ አዲስ አመለካከት እንዲያገኙ እና ወደጋራ ውይይቱ ከመምጣታቸው በፊት አቋማቸውን እንዲፈትሹ ይረዳቸዋል። በተመሣሣይ ወቅት ሽምጋዮች ብዙ ዝርዝር ጉዳዮችን ሊደርሱበት ይችላሉ። ወይም አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ቀጣይ ሂደቱን መከለስ ይችላሉ። ይህ የሁለትዮሽ ውይይት በሽምጋዮችና በተጋጮች መካከል ዕምነት እንዲኖር ያደርጋል።

የተናጥል ሽምግልና በሚካሄድበት ጊዜ ሚስጢራዊ መረጃዎች ይፋ ከሆኑ ሽምጋዮችን ፈተና ላይ ሊጥላቸው ይችላል። ስለዚህ በሽምግልናው ወቅት ፈቃድ ካላገኙ በቀር እነዚህን ሚስጥሮች መጠቀም አይቻልም። አንዳንዴም እነዚህ ሚስጥራዊ መረጃዎች ግጭቱን ለማብረድ ወሣኝ ሚና ይኖራቸዋል። ሽምጋዮች ማድረግ የሚችሉት ተጋጮቹ ወደ ውይይቱ ሲመለሱ በግልጽ ስለዕውነታዎቹ እንዲነጋገሩ ማበረታታት ብቻ ነው። አንዳንዴ ተጋጭ ወገኖች ሽምጋዮች ሚስጥራዊ የሆኑ መረጃዎችን ይፋ እንዲያደርጉ ጫና ይፈጥራሉ። እውነተኛ የሽምጋይ ባለሙያ በዚህ ወቅትም ገለልተኛ የመሆንን መርህ ይከተላል።

> በተናጥል በሚደረግ ሽምግልና ከሽምጋዩ አንዱ ሰው ምስጢር ቢነግረው ጉዳዩን እንዴት መመልከት ይኖርበታል?
>
> - ይህን ለምን ነገርከኝ?
> - ምን እንዳደርግ ትጠብቃለህ?
> - የፈራህበት ምክንያት ምንድን ነው?
> - በሽምግልናው ሂደት ውስጥ በምን መልኩ ልንነጋገርበት እንችላለን?
> - ይህን ሃቅ በመያዝ በሽምግልና ሂደቱ ላይ እንዴት ተጽዕኖ ልታደርግ ታስባለህ?
> - አካላቱ የመፍትሄ ሃሳብ እንዲያመጡ ይገደዳሉ።
>
> 1. ድብቅ አጀንዳ?
> 2. የመስማሚያ ሃሳብ ማግኘት መረጃን እንዴት ማስተላለፍ ይቻላል።

# “ሳይቃጠል በቅጠል!”

## (አማርኛ ብሂል)

| | |
|---|---|
| **ግለማ** | በስልጠናው መጨረሻ ተሣታፊዎች የፍሬዲሪክ ግላዝልን ዘጠኙን የግጭቶች መካረር ደረጃዎችን ይረዳሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 150 ደቂቃ |
| **መነሻ ዕውቀት** | III.1 ግጭትን መረዳት። |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የተለያዩ ባለቀለም ካርዶች፣ ማርከሮች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: የፍሬዲሪክ ግላዝል ዘጠኙን የግጭቶች መካረር ሞዴል አስተዋውቅ።<br>በዚህ ርዕስ ላይ የተዘጋጀውን ማስታወሻ ለተሣታፊዎቹ ስጥ።<br><br>ደረጃ 2: ሞዴሉን ወደ ተግባር ቀይር።<br><br>ደረጃ 3: ተሣታፊዎች እንዲወያዩ አድርግ። |

የሽምግልናው ዛፍ ማማ የተግባር መልመጃ[46] ላይ እንዳየነው ሽምጋዮች ጣልቃ እንዲገቡ የሚጠየቀው ግጭቱ ተካሮ ሶስተኛ ወገን ጣልቃ /መሐል/ እንዲገባ ሲፈለግ ነው። “መካረር” የሚለው አገላለጽ የሚያይዘው ከአካላዊ ጥቃት መጨመር ጋር ነው። ፍሬዲሪክ ግላዝል ግጭቶችን መጋፈጥ (Confronting Conflict)[47] በሚለው መጽሐፉ  የግጭቶች መካረር በዘጠኝ ደረጃዎች ከፋፍሏቸዋል። ሽምጋዮች ሊገነዘቡ የሚገባው የመንደርደሪያ ነጥቦችን እንዲዘጋጁ እና የሽምግልናውን ሚና ሲወስዱ ተገቢውን ስልት እንዲቀይሱ ስለሚረዳቸው ነው።

46 ክፍል III.3.4 የሽምግልና ዛፍ ማማ መልመጃን በገጽ 37 ላይ ይመልከቱ።
47 Glasl, F (1999)

## III.9.1 የፍሬደሪክ ግላስል ዘጠኙን የግጭቶች መካረር ደረጃዎች ማስተዋወቅ[48]

**1. ግትርነት**

ግጭቶች የሚጀምሩት በገጠመኝ የሃሣብ ፍጭት ውስጥ እንደግጭት ሳይስተዋሉ ከጊዜ በኋላ ሃሣቦች ወደጠርዝ እየተገፉ ይመጣሉ፡፡ በዚህ ደረጃ ከሁለቱም ወገኖች ጋር በማውራት መፍትሔ ለመፈለግ ዕድል አለ፡፡

**2. ክርክርና ተቃርኖ**

የተለያዩ አመለካከቶች ወደግጭት ያመራሉ አንዱ ቡድን ሌላይኛውን መጫን ይፈልጋል፡፡ አንደኛው ቡድን ሌላኛውን ለማሣመን ሲል ክርክር ውስጥ በመግባት ድጋፍ ፍለጋ ይጀምራል፡፡

**3. ንግግርን አቁሞ ተግባር ውስጥ መግባት**

ተጋጭ ቡድኖች የራሣቸው ሃሣብ ተቀባይነት እንዲያገኝ ስለሚፈልጉ ጫና ያሣድራሉ ከዚያም ውይይቱ ከመስመሩ ይወጣል፡፡ ከዚያ በኋላ ምንም አይነት ተግባቦት አይካሄድም፡፡ ግጭቱ ውጥረት ውስጥ ይገባና ወደማይሆን ደረጃ ይገባል፡፡

**4. ፍረጃና ቅንጅት**

ከክርክሩ ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው ተገቢ ያልሆነ ምስል /ፍረጃ/ ይፈጠራል፡፡ ቡድኖች ሀዘኔታን በመሻት አሉባልታዎችን እንዲሁም ስም ማጥፋቶችን ይነዛሉ፡፡

**5. በሰው ፊት ሞገስ ማጣት**

የተቃራኒ ቡድኖቹ ማንነት ይጠፋል፡፡ በሰው ፊት ሞገስ ማጣት ስንል የሞራል የበላይነትን ማጣት ማለታችን ነው፡፡

**6. የማስፈራራት አርምጃ**

የተጋጩት ቡድኖች ሁኔታውን ለመቆጣጠር የሚሞክሩት በማስፈራራት ይሆናል፡፡ አንዱ ቡድን የሚፈልገውን ነገር ሌላኛው ቡድን ወዲያው ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ይህ ደግሞ ግጭቱን እንዲካረርና እንዲፈነዳ ዕድል ይሰጣል፡፡

**7. የተወሰነ ውድመት**

ተቃራኒ ቡድን እንደሰው አይቆጠርም፤ በየትኛውም መንገድ ቢሆን ይዋሻሉ፤ ጉዳት ይደርስባቸዋል፤ ትንሽም ቢሆን የግለሰቦችን ንብረት ማውደም ተቀባይነት አለው፡፡ የተቃራኒው ቡድን ዕሴቶች እስከተጎዳ ድረስ መገልበጥ ተቀባይነት ያገኛል፡፡

**8. መነጣጠል**

ዓላማውም ተቃራኒ ቡድኖችን መነጣጠል መለያየት ነው፡፡ የስርዓቱን ወሣኝ አካላት ማውደም ከቁጥጥር ውጭ ወደሆነ የአካል ፣ የስነ-ልቡና የማህበራዊ እና ወይም ወደማህበራዊ ውድመት ያመራል፡፡

**9. ተያይዞ ገደል**

ወደ ኋላ የማይባልበት ሁሉንም ነገር ፊት ለፊት መጋፈጥ፡፡ ተቃራኒ ቡድንን ለማሸነፍ የግል ውድመት ቢሆን እንኳ ስሌት ውስጥ ይገባል፡፡ ተቀባይነትን ያገኛል፡፡ ሌሎችን ማጥፋት ምናልባት ሊቋቋሙት የማይችሉት ሁኔታ ውስጥ ቢከትም ዕርካታን ይሰጣል፡፡

48 Glasl, F (1998)

## III.9.2 ተግባር፡ ዘጠኙን ደረጃዎች በናሙና ማሣያ በመጠቀም ወደ ተግባር መቀየር

ሞዴሉን በየትኛውም የግጭት አይነቶች በቤተሰብ ፣ በማኅበረሰብ ፣ በሀገር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ልትጠቀምበት ትችላለህ። የተሳታፊዎችን መረዳት ለማስፋት ሞዴሉን ቀጥለን በናሙና ማሣያ ላይ እንጠቀማለን።

**ዓላማ** ተሣታፊዎች የግጭቶች መካረር ስላላቸው ዕምቅ ኃይል ያላቸው መረዳት ማስፋት።

**የተመደበ ጊዜ** 60 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች


**ቅደም ተከተል** ደረጃ 1: ነገረ ጉዳዩን አስተዋውቅ። ታሪኩን በሚከተለው መንገድ ልትነግራቸው ትችላለህ።

በድልድዮች በተገናኘ የወንዝ ዳርቻ አካባቢ የሚገኙ ሁለት ማኅበረሰቦች ጥሩ በሆነ ወንድማማችነት ይኖሩ ነበር። በጋብቻ መተሳሰር የተለመደ ነበር። የንግድ ልውውጡም ጥሩ ነበር። አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የማኅበረሰብ ክፍሎችም ተከብረው ይኖራሉ። የሁለቱ ማኅበረሰብ መሪዎች በጋራ በመሆን የአዲስ ትምህርት ቤት ፕሮጀክት ግንባታ ሀሳብ አረቀቁ። ትምህርት ቤቱ ወደፊት የት ይገንባ ከሚለው በስተቀር በሁሉም ነጥቦች ላይ ተግባብተዋል። የሁለቱም ማኅበረሰቦች መሪዎች ትምህርት ቤቱ በነሱ ወንዝ አጠገብ እንዲሠራ ይፈልጋሉ።

ደረጃ 2: ይህ ምሳሌ ጉዳዩን ከዘጠኙ ደረጃዎች አንፃር እንዴት እንደሚታይ የሚያሳይ ነው።

**ደረጃ 1 ግትርነት**

ግጭቶች የሚጀምሩት ይሁነኝ ተብሎ ባልተጀመረ የሀሳብ ፍጭት መካከል ነው። ሰዎች የተለያዩ ሃሳቦችን ግልጽ በሆነ መልኩ ሲለዋወጡ የነበረ ቢሆንም በዚህ ደረጃ ግን ፍላጐታቸው ይቀንሳል። ቢያንስ አንዱ ቡድን ይጐረብጠው ይጀምራል። ስሜታቸው ይወጣጠራል፤ አንዳንዴ የማኅበረሰቡ አባላት በንዴት ሊናገሩ ይችላሉ። ነገር ግን ሌላኛውን ቡድን አሳምኖ መፍትሔ ለማስገኘት ተስፋ ያደርጋሉ።



**የናሙና ማሣያ:** ብርቱካናማው ማኅበረሰብ /በግራ በኩል/፡ “ይህ ስፍራ ጥሩ ነው፣ ለድልድዩም ቅርብ ነው ስለዚህ ማንኛውም ሰው ያለችግር ትምህርት ቤት ይደርሳል።”

አረንጓዴው ማኅበረሰብ /በቀኝ በኩል/፡ “በእውነት በርካታ ሰዎች እኛ ባለንበት አካባቢ ይኖራሉ። ስለዚህ ትምህርት ቤቱ በኛ በኩል ነው መገንባት ያለበት።”

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ፡ “በእናንተ በኩል ምንም ያህል ሰው ቢኖር ችግር አይፈጥርም። ያን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ከአካባቢ ሰዎች ሽማግሌዎች ጋር ተመካክሬ ለዚህ ጉዳዩ መፍትሔ ለማግኘት ተመልሼ እመጣለሁ።”

## ደረጃ 2 ክርክርና ተቃርኖ

ሁለቱም ቡድኖች ሌላኛውን ወገን ለማሳመን በሚያደርጉት ጥረት ላይ በራስ መተማመናቸውን ያጣሉ። ሌላኛውን ቡድን አሁንም ያናግራሉ፤ ነገር ግን በንግግራቸው ወቅት ዓላማቸው ከተቃራኒ ወገን ይልቅ ከራሳቸው ወገን ድጋፍ ማግኘትና ተቃራኒ ወገንን ማሳመን ነው። በቃል ንግግር የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት ይሞክራሉ። ስለዚህ ክርክሩ በንግግር ብልጣ ብልጥነት የተሞላ ይሆናል። የንግግራቸው ስውር መልዕክት ሌላውን ወገን የሚነቅፉ መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይሆናል።

የናሙና ማሣያ: ከአካባቢው ሬዲዮ ጣቢያ የሚተላለፍ የቀጥታ ስልክ ውይይት:

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "ይህንን ጉዳይ ካሁን ቀደም በቦታው ከነበረው ኃላፊ ጋር መወያየት ባለመቻሌ በጣም አዝናለሁ አሁን ከቢሮ ልናገኘው አንችልም። እሱ ሁል ጊዜ ለመልካም ውይይቶች ክፍት ነበር።"

አረንጓዴው ማኅበረሰብ: "ይህ እኮ የታወቀ ነው። ከከተማችሁ ምክር ቤት አባላት ሳይቀር ከማድመጥ ይልቅ ሰው መዝለፍ እንደሚቀናቹ ሠምቻለሁ።"

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "እንተማመን እንጂ በነገሩ ላይ በጥልቀት እንዳላሰባችሁበት ብታምኑ ጥሩ ነው። ለናንተም ቢሆን ትምህርቱ ቤቱ በኛ በኩል ቢገባ ይጠቅማል። የማኅበረሰባችሁን ጥቅም ለማስጠበቅ አትጥሩም።"

አረንጓዴው ማኅበረሰብ: "ምን አይነት ስራ ነው የምትሠራው? ከዚህ በፊት እኮ ምክረ ሃሳባችንን ተቀብላችሁ ነበር። አታስታውስም እንዴ? የማስታወስ ችሎታህ በሌላም ህይወትህ ላይ እንዲሁ ደካማ ነው?"


## ደረጃ 3 ከቃል ያለፈ ተግባር

ያለምንም ውጤት ከተነጋገሩ በኋላ ቡድኖቹ ስምምነት ላይ መድረስ አንችልም በሚል ተስፋ ይቆርጣሉ። ነገሮችን ወደፊት ለማሻገር ካላቸው ከፍተኛ ፍላጐት የተነሳ ብቸኛ አንዱ ቡድን ሌላኛውን ቡድን ሳያማክር አማራጭ ብለው በተናጥል እርምጃ መውሰድ ይጀምራሉ። ብዙ ጊዜ ይህንን የሚያደርገው በንቃት የሚሳተፈው ቡድን ነው። ሌላኛው ቡድን ግን እንደተሸነፈ ፣ እንደተታለለ ወይም እንደተሸጠ ስለሚሰማው ይናደዳል። አንዴ ይህችን መስመር ካለፉ ያለ ሶስተኛ ወገን ሽምጋይነት ወደ ውይይት መምጣት አስቸጋሪ ነው። ምክንያቱም ጥልቅ የሆነ አለመተማመን ተፈጥሮአልና ነው።

አንደኛው ቡድን እርምጃ ከወሰደ ሌላኛውም ቡድን ያንን እርምጃ ይወስዳል፤ ችግሩን ተወያይቶ መፍታት ላይ እምነት አጥተዋል። በተደጋጋሚ ይነጋገራሉ ነገር ግን ሀሳባቸውን ከሚተማመኑ ይልቅ አንዳቸው የሌላኛው ድርጊትን ትርጉም መስጠትን መርጠዋል። አላስፈላጊ የሆነ አተረጓጐም ቀስ በቀስ ከፍተኛ ቦታ እያገኘ ይሄዳል።

የናሙና ማሣያ: የተወሰነ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሁለቱ ማኅበረሰብ መሪዎች ደግመው ተገናኙ።

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "ታውቃለህ አንድ ባለስልጣንን አናግሬ የትምህርት ቤቱን የግንባታ ፕላን አስገብቻለሁ። ይኸውልህ የትምህርት ቤቱን የግንባታ ፕላን እየው። በሀሳቦቼ በጣም ተደስቶ ወዲያው ተስማማ።"



አረንጓዴው ማኅበረሰብ: "እንዴት ይህንን ታደርጋለህ? መጀመሪያ ማኅበረሰቦቻችንን እናወያይ የተባባልን መስሎኝ ነበር። አታለኸኛል።"

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "ሞኝ አትሁን። ለዘላለም ስንወያይ እንደማንኖር ታውቃለህ። ተወካዩቹ ሲመጡ እድሌን ሞከርኩ"

እንደገና የተወሰነ ጊዜ አለፈ. አሁን አረንጓዴ ማኅበረሰብ በምላሹ እርምጃ ወሰደ።

አረንጓዴው ማኅበረሰብ: "በዚህ ጉዳይ በጣም ደስተኛ እንደምትሆን አውቃለሁ። ማኅበረሰባችንን አወያየሁ እና ትምህርት ቤቱን እኔ በምፈልግበት ቦታ ላይ መገንባት እንድችል የሚከፍል ለጋሽ ድርጅት አገኘሁ። ይሄ ትልቅ ዜና ነው አይደለም? በዚያ ላይ አንተ ነህ መፍጠን እንዳለብኝ የነገርከኝ። እርግጠኛ ነኝ በዚህ ሃሳብ ደስተኛ ሆነሃል!"

## ደረጃ 4 ፍረጃና ቅንጅት

ግጭቱ በቀጣይ ቡድኖቹ ቀጥሎ ምን ያደርጋሉ? ጥንካሬ ለማግኘት ሲሉ ድጋፊ ስለሚያሰባስቡ በርካታ ሰዎች ይሳተፋሉ። ብዙሃን መገናኛዎችን ይጠቀማሉ ፣ ደብዳቤ ይፅፋሉ ፣ ድረ ገፅ ላይ መረጃውን ያወጣሉ ወዘተ። ወይ ወዳጄ ነህ ወይ ጠላቴ በሚል ክፍፍል ውስጥ ይገባሉ። የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው ወይም የጠላቴ ወዳጅ ጠላቴ ነውም ጭምር። ቡድኖቹ ቅንጅት ለመፍጠር ይጓጓሉ። ቅንጅቱ ግን ግትር አቋም ያለው ከራሱ ቡድን ሂስ የማይቀበል ይሆናል። አስተያየት /ሂስ/ መስጠት በራሱ እንደ ጠላት ያስፈርጃል /ወይ ከኛ ጋር ነህ ወይም ደግሞ የኛ ጠላት ነህ/። በቡድኑ ውስጥ ገንቢ ለሆነ አስተያየት ትንሽ ክፍተት አለ።


ፍረጃ እና ማጥላላት ይጀመራል፤ ከአሁን በኋላ ችግሩ በአንድ ሃሳብ ላይ አለመስማማት ብቻ ተብሎ አይወሰድም። አንደኛው ቡድን በአጠቃላይ እንደ ችግር ሆኖ ይታያል፡ እነሱ ኋላ ቀር፣ ራስ ወዳድ፣ አቅም የሌላቸው ናቸው ወዘተ

በድብቅ ማነሳሳት ይጀመራል። ይህም "የምፈልገውን ወስጄያለሁ" /ሶስተኛ ደረጃ ላይ እንዳለው ከቃል ያለፈ ተግባር/ የሚል መሪ ሃሳብ ይዘው ብቻ ሳይሆን ምንም እንኳን ጥቅም ባያገኙበትም የአንደኛውን ወገን ዓላማ ማጠልሸት፣ ባልበላውም ልድፋው ወይም ላበላሸው ዓይነት ሁሉን ተጐጂ የሚያደርግ አስተሳሰብ ይነግሳል። ይሄኔም እንዲህ ዓይነት ተግባር ሆን ተብሎ መፈፀሙን ይክዳሉ። ነገር ግን ሌላኛው ቡድን ሆን ተብሎ እንደተፈፀመ ከተሠማው አለመግባባቱ ይጠዛል።

**የናሙና ማሣያ:** ብርቱካናማው ማኅበረሰብ ለቡድኑ አባላት: "ዕሮብ እለት የሊጋሾቹ ተወካዮች መጥተው ትምህርት ቤቱ እንዲገነባ በፈለጉበት ቦታ ላይ የመሠረተ ድንጋይ እንደሚያኖሩ ሲወራ ሰምቻለሁ። የሚመጡት በኛ መንገድ ስለሚሆን ድልድያችንንም ይጠቀማሉ። ስለዚህ እኛ መንገዱን በመዘጋት ክብረ በዓሉ እንዳይካሄድ እናስተጓጉላለን። ከዛም በማግስቱ ክብረ በዓሉ ያልተካሄደው እነሡ በሚገባ ስላልተዘጋጁ ነው ብለን ሪፖርት እናደርጋለን። ስለመንገዱ መዘጋጋት ከጠየቁንም በአደጋ ምክንያት እንደተዘጋ እንመልስላቸዋለን" ይላቸዋል።

አረንጓዴው ማኅበረሰብ: "ይህ ከሆነ በኋላ ለህዝባቸው ይህ የሆነው በአደጋ ምክንያት አይደለም ሆን ተብሎ ነው። እኛ ቤቶች ለመስራት በማቀድና በመገንባት በቂ ልምድ አለን። እነሡ ልምድ የላቸውም። ኋላ ቀሮች እና ያልተማሩ ናቸው፤ ስለዚህ እኛ ወደ መንግሥት አካላትና ወደምናውቃቸው ሁሉ ሄደን ቤት መገንባት የማይችሉ ያልተማሩ እንደሆኑ እናሳምናቸው።"

ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "ምን እናደርጋለን ለማኅበረሰባችን አረንጓዴው ማኅበረሰብ ሊጋሽ ድርጅት ያገኘው ከውጭ ሀገር እንደሆነ እንነግራቸውና እኛ ግን በውስጥ ጉዳያችን ማንም የውጭ ድርጅት እንዲገባ እንደማንፈቅድ እናስረዳቸዋለን። የጋዜጣዊ መግለጫ ርዕሱን "የአረንጓዴው ማኅበረሰብ አባላት የልጆቻችንን የወደፊት ህይወት ለውጭ ባለሃብቶች ሊሸጡ ነው" ብለን እንፅፋለን። ሠላማዊ ሠልፍ እናደራጃለን። ጀግና የሆኑት ወጣቶቻችን የአረንጓዴ ማኅበረሰብ አባላት ትምህርት ቤቱን ለመገንባት ያሰቡበት ስፍራ ሄደው የሆነ ነገር ሊያጠፉባቸው ይችላሉ። ይህንን የሚያደርጉት እኛ ስላዘዝናቸው አይደለም። ይህ ሊሆን የሚችለው ከተፈጠረው ውጥረት እና ከአረንጓዴው ማኅበረሰብ አባላት በአንዳንድ ተንኮለኞች ምክንያት ይሆናል።




## ደረጃ 5 ሞገስ ማጣት

እስከአሁን ጥቃቱ ያነጣጥር የነበረው ተቃራኒው ብቃት ላይ መሠረት ያደረገ ነው (ያልተማሩ፣ ኋላ ቀሮች፣ የማያስቡ ወዘተ።) ቀጥሎ ቡድኖቹ እርስ በእርሳቸው ስለ ሞራል ብቃታቸው ይጠያየቃሉ። ተቃራኒው ቡድን ደደብ እና ብቃት የሌለው እንደሆነ ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛ እንደሆኑ፣ እእምሯቸው እንደታመመ ውሸታም እንደሆኑ ክፉ ከሃዲዎች እንደሆኑ ነው የሚያስቡት። ሰብዓዊ ገፅታቸውን ያሳጧቸዋል። ይህን ተግባር ያሰበው ቡድን ደግሞ ማስረጃ ለማግኘት ይሯሯጣል። አንዴ ካገኙም ወዲያውኑ ለህዝቡ ይፋ ያደርጋሉ። በዚህ ጊዜ የተበዳዩ ቡድን ምላሽ ጠንከር ያለ ይሆናል። በምላሹም ሌላኛው ቡድን ወንጀለኛና ውሸታም እንደሆነ ለማረጋገጥ ይጥራሉ። ስለዚህ ነገሩን ለማብረድ የአፀፋ እርምጃ መውሰድ ይጀምራሉ። የአለመግባባቱ መንስኤ የሆነው ጉዳይ ፈፅሞ ይረሳል። አሁን የክብር ጉዳይ ይሆናል። እኛ ከነፍስ ጉዳዮች ጋር አንተባበርም እናስወጣቸዋለን።

የናሙና ማሣያ: የአረንጓዴው ማኅበረሰብ አባላት ትምህርት ቤቱን መገንባት ጀመሩ። አንድ ለሊት ድንገት እሳት ይነሳና ለትምህርት ቤቱ ግንባታ ሊውል የመጣው አጣና በሞላ ይወድማል። በጣም ተናደዋል፡ “የብርቱካናማው ማኅበረሰብ ናቸው ሆን ብለው እሳት የለኮሱት። እነሱ ታጣቂ ወንጀለኞች ናቸው፤ ሰው ገድለው ግድ የማይሠጣቸው ናቸው፤ ይህ ደግሞ የሚያሳየው ምን ያህል ክፉ እንደሆኑ ነው።”

የብርቱካናማው ማኅበረሰብ አካላት በምላሹ: “እነሡ ውሸታም ናቸው። እኛን ለመወንጀል አስበው እሳቱን ሆነ ብለው ነው የለኮሱት። ከአንድ ወር በፊት በነሱ የተደፈረች ሴት በመካከላችን አለች። እነዚህ ሰዎች ያሰጉናል። አደገኛ ሰዎች እንደሆኑ እስከዛሬ እንዴት ማየት አልቻልንም? ከነዚህ ጋር ከዚህ በኋላ መተባበር አያስፈልግም።”

ቀደም ብሎ የአረንጓዴው ማኅበረሰብ እና የብርቱካናማው ማኅበረሰብ ተወካዮች በጋራ በመሆን ደፋሪ ቢሆን ወይም መሳሪያ ታጥቆ ወንጀል የሠራ ወንጀለኛ የየትኛውም ማኅበረሰብ አባል ቢሆን ይዞ ለመቅጣት አብረው ይሰሩ ነበር። በዚህ ውጥረት በነገሠበት ወቅት ግን ይህን ክስተት የአንደኛው ወገን “እውነተኛ ማንነት” እንደሆነ በመስበክ ማኅበረሰቡ ለብቀላ እንዲነሳሳ ይጠቀሙበታል።




## ደረጃ 6 የማስፈራራት ስልት

አብዛኛውን ጊዜ በዚህ ደረጃ ነገሮች በፍጥነት ወደ ከፋ ደረጃ በቀላሉ ይደርሳሉ። ግጭቶቹ ዛቻና ማስፈራሪያ እንዲሁም መልሶ በማስፈራራት ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ነገር ግን እንደ ደረጃ ሁለት በሽንገላ ቃላት የተሞሉ ማስፈራሪያዎች ሳይሆኑ ጠንካራ ማስፈራሪያዎች ናቸው። እነዚህም ማዕቀብ በመጣልና የጊዜ ገደብ በማበጀት የተደገፉ ጠንካራ ፍላጎቶችን በማስቀመጥ የሚከናወኑ ናቸው። እነዚህ ማስፈራሪያዎች ጠንከር ያሉ ናቸው። ቢሆንም ግን ተቃራኒው ቡድን ፍላጎታቸውን ያሟላል ማለት ዘበት እንደሆነ ማየት ይሳናቸዋል።

የናሙና ማሣያ:

አረንጓዴው ማኅበረሰብ ፡ "ወንጀለኞቹን እና የፖሊስ አዛዡን ጨምሮ እንድታስረክቡን እንጠይቃለን፤ ምክንያቱም መረጃ ደርሶት እንደነበር እናውቃለን። እናም በይፋ ይቅርታ ጠይቁ። ይህ መሆን ያለበት ደግሞ በ48 ሰዓት ውስጥ ነው። ለለበለዚያ ንብረታችንን ከአደጋ ለመከላከል ስንል ድልድዩን እንዘጋለን።"


ብርቱካናማው ማኅበረሰብ: "ማንንም አሳልፈን አንሰጥም ምክንያቱም ማንኛችንም ምንም አላደረግንም። እኛን መወንጀል አቁሙ። የእናንተ አዛዥ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደዋሸ እናውቃለን፤ ስለዚህ ስራውን ሊለቅ ይገባል። አለበለዚያ ከሀይል ማመንጫችን /ማከፋፈያችን/ የሸጥንላችሁን መብራት እናቋርጠዋለን። ከእንዲህ ከሚዋሹ ሰዎች ጋር ምንም አይነት ስራ መስራት አንችልም።"



## ደረጃ 7 መጠነኛ ውድመት

ሁለቱም ወገኖች የሚጠይቁትንና የተጠየቁትን ማሟላት አለሟሟላታቸው አጠራጣሪ ስለሆነ ማስፈራሪያው መተግበር ስላለበት አንደኛው ቡድን በሌላኛው ቡድን ላይ መጠነኛ ጉዳት ያደርሳል። “ውሱን” ናቸው፤ ምክንያቱም ሌሎች ስርአቶችን በአካል፣ በኢኮኖሚ ወይም በማህበራዊ መልኩ ሙሉ ለሙሉ ለማውደም የታቀዱ አይደሉም። ይልቅስ የታቀዱት አንደኛው ወገን በተሸናፊነት እጁን እንዲሰጥ በማሰብ ነው። አንዳንዴ ቡድኖቹ በተስፋ መቁረጥ “ይህን ማድረጋችን አያስደስተንም ነገር ግን እስካልተሸነፋችሁ ድረስ አማራጭ የለንም” ሲሉ ይደመጣል። ሁለቱም ቡድኖች በውድመቱ እና ጥፋቱ ተጐድተዋል ፤ነገር ግን በነርሱ አስተሳሰብ የሌላኛው ጉዳት ትልቅ ከመሠላቸው አሸናፊነት ይሠማቸዋል፤ ሌላው ውድመት ደግሞ በአደባባይ ማጠልሸት ነው። ተቃራኒ ቡድንን ልክ እንደ ጠላት፣ ጥገኛ ተህዋሲያን፣ አይጥ ወዘተ በመሳል ማቆሸሽ ይቀጥላል። ይህ ምላሽ የመስጠት ተግባር በማኅበረሰቡ እንደ ተገቢ እርምጃ ይታያል። ለምሳሌ አይን ያጠፋ፤ አይኑ ይጥፋ አንድ ሰው የገደለ ሰላሳ ላሞች ይከፈል፣ አንድ ሰው የገደለ መላ ቤተሰቡ ይገደል፣ ለአንድ ሰው ሞት የአንድ ሄሊኮፕተር ጥቃት ወዘተ።

የናሙና ማሣያ: ድልድዩቹ ተዘግተዋል። ንግድም ሙሉ በሙሉ እየቆመ ነው። የመብራት ሀይሉ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል። የአረንጓዴው ማኅበረሰቦች ገንዘባቸውን ለጄነሬተር ነዳጅ ለማውጣት ተገደዋል። በሌላኛው ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ይሸሻሉ፣ የሌላኛው ማኅበረሰብ አባላት ሲንቀሳቀሱ ከተያዙ ይደበደባሉ፣ ይታሰራሉ እንዲሁም ይባረራሉ። ገንዘባቸው ይወሰዳል/ ይነጠቃሉ/ ወይም ቤታቸው ይቃጠላል።



### ደረጃ 8 ጠላትን መነጣጠል


ትናንሽ ውድመቶች ሌላኛውን ቡድን እጁን እንዲሰጥ ወይም እንዲሸነፍ ካላደረጉት፣ ቡድኖች ቀጥሎ መውሰድ ያለባቸው እርምጃዎች የተቃዋሚያቸውን "ስርአት" ማፈራረስ እንደሆነ ያስባሉ። እንደ ግጭቱ አይነት ስርዓት ስንል ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ማኀበረሰብ፣ ድርጅት፣ ግዛት ወዘተ ማለት ሊሆን ይቻላል። ማፈራረስ ማለት መግደል ማለት ላይሆን ይችላል። ቤተሰብ ሊገደል ይችላል። ይህ ማህበራዊ ውድመት ነው፤ ድርጅት በኢኮኖሚ ሊፈራርስ ይችላል። በወታደራዊ ቋንቋ ብንጠቀም ይህ ማለት /ልክ እንደ ደረጃ 7/ በተቋማት ላይ ቦንብ መወርወር ብቻ ሳይሆን የጠላትን የኃይል ማዕከል መቆጣጠር ማለት ነው።

የናሙና ማሣያ: የብርቱካናማው ማኀበረሰብ የውሃ መሠረተ ልማት ተቋም ወደመ። የምግብ አቅርቦትን ለማቆም ወደ አረንጓዴው ማኀበረሰብ የሚወስዱ መንገዶች ተዘጋ። "አጠገባችን ያሉትን ማኀበረሰቦች ልንቀበላቸው አንችልም። የደህንነታችን ስጋቶች ናቸው። እነሱን ከእኛ የሚለየው ወንዝ እንኳ ለደህንነታችን አስተማማኝ አይደለም። በቁጥጥራችን ስር መዋል አለባቸው።" ከሁለቱም ወገኖች በኩል ያሉ ቁልፍ ፖለቲከኞች ተገለዋል። ተባባሪ ናቸው ተብለው የተጠረጠሩ ከነቤተሰቦቻቸው በተኩስ ልውውጥ ህይወታቸው አልፎዋል። ሁለቱም ቡድኖች አንደኛው የሌላኛው አስተዳደር ሲወድቅ ለማየት ይሮጣል፤ ወታደራዊ አቅም ስለሌላቸው ብቻ ነው ወረራ ያላካሄዱት።

### ደረጃ 9 በጋራ ወደ ገደል /ተያይዞ ገደል/

አንደኛው ቡድን /ወይም ሁለቱም/ ሌላኛውን ለማሸነፍ እንደማይችሉ ሲረዱ እና እነሱም ሁሉን ነገር እያጡ እንደሆነ ሲገባቸው አሁንም ሌላኛውን ወገን ለማጥፋት አንድ መንገድ እንዳለ ይረዳሉ። ይህም ራሳቸውን ማጥፋት ወይም በዘመኑ ቋንቋ አጥፍቶ መጥፋት ማለት ይቻላል።

ደረጃ 3: የተሳታፊዎቹን አስተያየት አጠቃለህ አቅርብ።



## III.9.3 ዘጠኙን የግጭት መካረር ደረጃዎች ይበልጥ ለመረዳት አማራጭ ተግባራት

### ተግባር አንድ፡ የገሃዱ ዓለም ልምዶች

**ዓላማ** ተሳታፊዎች በዘጠኙ የግጭት መካረር ደረጃዎች ላይ ያላቸውን ዕውቀት ይሰፋል።

**የተመደበ ጊዜ** 60 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት ፣ ማርከሮች ፣ የወረቀት ሠሌዳ ፣ ባለቀለም ካርዶች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ከእያንዳንዱ የግጭት ደረጃዎች ከሶስት እስከ አምስት የሚሆኑ ባህሪያትን አስታውስ። እነዚህን ያስታወስካቸውን በካርዱ ላይ ፅፈህ ግድግዳ ላይ ወይም ሠሌዳው ላይ ለጥፋቸው።

ደረጃ 2: ተሳታፊዎችህ ሊለማመዱት ያለው ዓይነት ግጭትን በሚመለከት አንድ ናሙና ታሪክ አዘጋጅ። ትርጉም የሚሠጥ ውይይት ለማካሄድ ግማሹን የቡድን አባላት አንዱ ተጋጭ ወገን ግማሹን ደግሞ ሌላኛው ተጋጭ ወገን በማድረግ ከፋላቸው። የመሪነት ድርሻውን በመውሰድ ቀጥለን ምን እናድርግ በማለት ጠይቃቸው። የሚሰጡትን አስተያየቶች ከግላዝል ሞዴል ቀጣይ ደረጃዎች ጋር አያይዘው። ቡድኑ አስተያየቶች ካልሰጡህ በሞዴሉ መሠረት አንተ አስተያየትህን ስጥበት።

ደረጃ 3: ዘጠኙን የተለያዩ ደረጃዎች ከነካካሃቸው በኋላ ከገባቸው አስተያየት እንዲሰጡበት ጠይቃቸው። እንዲሁም ተሳታፊዎቹን ሞዴሉ በነሱ አውድ እና ባህል ይሰራ እንደሆን ጠይቃቸው።



## ተግባር ሁለት፡ የተካረሩ ግጭቶች አማራጭ

| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | ተሳታፊዎች ስለዘጠኙ የግጭት መካረር ደረጃዎች ያላቸውን ዕውቀት ይሰፋል። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 15 ደቂቃ/አጭሩ/ 60 ደቂቃ /ረጅሙ የቡድን ስራን ጨምሮ/ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ የወረቀት ሠሌዳዎች ፣ ባለቀለም ካርዶች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: ከዚህ በፊት ስልጠና ላይ የተጠቀምክበትን የሚና ነጠቃ ጨዋታ ወይም ግጭት አስታውሳቸው፤ ካልሆነ ተሳታፊዎቹ የሚያውቁትን የግጭት ታሪክ ተጠቀም። |

ደረጃ 2: ተሳታፊዎቹን የተጠቀሰው ታሪክ የትኛው የክረት ደረጃ ላይ እንደደረሰ እየጠየቅህ የተለያዩ መልሶችን ተቀበል። እዚህ ደረጃ ላይ ነው ያለው ለምን እንዳሉ በመጠየቅ ያልገባቸውና ግራ የገባቸው ነገር ካለ አርማቸው። ተሳታፊዎቹን ወደ ተለያየ አነስተኛ ቡድን በመከፋፈል እና የተለያዩ ነገረ ጉዳዮችን በመስጠት እንዲሠሩ አድርግ። ተሳታፊዎቹን የሚያውቁትን እውነተኛ ታሪክ መጠቀም ጥሩ ነው። አንድ ሰው ጉዳዩን ለቡድን አባላት ይንገራቸው እና የቡድን አባላቱ የግጭቱን ክረት የት ደረጃ ላይ እንዳለ ይፈትሹ።

ደረጃ 3: እያንዳንዱ ቡድን የትኞቹ ፍንጮች (ሁነቶች) የክረቱን ደረጃ እንዲለዩ እንዳስቻላቸው ለሌሎች ያቅርቡ። አብዛኛውን ጊዜ ግጭቶች እያንዳንዱን የክረት ደረጃ ያልፋሉ። ስለዚህ ለምሳሌ ከደረጃ አንድ ወደ ስድስት በአንዴ ጊዜ እንዲዘሉ አትፍቀድ። በሽምግልና ሂደት ወቅት ተጋጭች ግጭቱ እንዴት እንደተከሰተ ቀስ በቀስ እየተረዱ ሲመጡ የከረረው ግጭት እየረገበ ይመጣል። ምክንያቱም ለክረቱ ምን ያህል አስተዋፅዖ እንዳደረጉ ይረዳሉ። እጅግ በተካረረ ግጭት ውስጥ ይህንን በተናጥል ከቡድኖቹ ጋር ስራ። ሞዴሉ የሚቀድመውን ደረጃ መለየት እንድትችል ለጥያቄዎችህ የሚሆን ፍንጭ ይሠጥሃል። ለምሳሌ:

- *መቼ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ውጥረት የተሰማህ? /ደረጃ 1/*
- *መቼ ነው የናንተ ተቃራኒ ወገኖች በእናንተ ማማከር ሲገባቸው ሳያማክሯችሁ ይህንን ያከናወኑት /ደረጃ 3/*
- *እስካሁን ከተፈፀመው የከፋው ጉዳት የትኛው ነው? /አሁን ክረቱ ያለበት ደረጃ/*

ቡድኖች ቀጥሎ ምን ለመስራት እንዳሠቡ በግል ሊነግሩህ ይችላሉ። ይህን ከሞዴሉ ጋር በማያያዝ እና ሌላኛው ወገን ምን ሊያደርግ እንደሚችል ልትገምት ትችላለህ። ይህ አንዳንዴ ቡድኖቹ ክረት እንዲያቆሙ ማሳመኛ ይሆናል። ክረት የደረጃ በደረጃ ሂደት ጉዳይ ከሆነ የሚረግብበትም መንገድ እንደዛው ደረጃ በደረጃ ነው የሚሆነው። ስለዚህ በሽምጋዮችም ሆነ በሶስተኛ ወገን የሚፈፀም /መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም መንግሥት/ ማንኛውም እርምጃ ክረቱ አሁን ያለበትን ደረጃ ባገናዘበ መለኩ መቀየስ እና መሰራት አለበት።

ሽምጋዮች በየደረጃው የሚያደርጉት አማራጭ ጣልቃ ገብነት ወይንም መግቢያ ነጥቦችን በቀጣዩ ምዕራፍ እንመለከታለን።

## III.10 ከተከያዩ የግጭት ደረጃዎች የተቀረፀ ማግባቢያ (Intervention) መንገዶች[49]

### ደረጃ 9 ተያይዞ ገደል

ሁከቱን የፖሊስ ወይም የጦር ሠራዊት ተጠቅሞ ከማስቆም ውጭ የውጭ ጣልቃ ገብነት መጠቀም አይታሰብም።

### ደረጃ 8 ጠላትን መከፋፈል

ቡድኖች ለፖሊስ እርምጃ ወይም ለጦር ሠራዊት ጣልቃ ገብነት ምላሽ ይሠጣሉ ወይም በግጭቱ በራሳቸው ጊዜ ይሰላቻሉ።

**ናሙና ማሳያ:** አማራጭ 1፡ ማዕከላዊ /ብሔራዊ/ መንግስቱ ግጭቱን ለማስቆም ከፍተኛ የሆነ የፖሊስ ጣልቃ ገብነትን ይጠቀማል።
አማራጭ 2፡ ምንም ጥረት ቢደረግም ቡድኖቹ አንዳቸው በሌላኛው አይሸነፉም። በጦር ኃይሉ ጭምር አይግባቡም። ስለዚህ ድል እውን የሚሆን አይመስልም። ቡድኖቹ በግጭቱ የተነሳ ብዙ ተጐድተዋል ተሰላችተዋል። ከፍተኛ የሆነ ጉዳት/አደጋ/ ማድረስ አቁመዋል። ይህ የሆነበትም አቅማቸው ስለተሟጠጠና ስለማይችሉ ነው። ስለዚህ አነስተኛ ጥቃቶች እና ራስን መከላከል ላይ ያተኩራሉ። ስለዚህ ወደ ደረጃ 7 ይመለሳሉ።

### ደረጃ 7 መጠነኛ ውድመት

ከደረጃ 7 ወደ 6 መውረድ ተኩስ ለማቆም የሚደረግ ድርድር ማለት ነው። ምክንያቱም ተኩስ ማቆም ማለት ሁለቱም ቡድኖች በቋሚ ስጋት ውስጥ የሚኖሩበት እና ጊዜ የሚገዙበት ብቻ ነው። አቅም ባገኙ ጊዜ ወደ ላይኛው የግጭት ደረጃ በማንኛውም ሰዓት ሊመለሱ ይችላሉ /ደረጃ 6/። በብዙ ግጭቶች ውስጥ የሲቪል ማህበራት መደበኛ ባልሆነ ውይይት ላይ የሚሳተፉ ሲሆን የመግባቢያ መንገዶችን በመፍጠር እና ከቡድኖቹ ጋር የሚደረግ ኢ-መደበኛ ግንኙነትን ያግዛሉ። የተኩስ አቋም ስምምነቱ በሶስተኛ ወገን ሽምጋይነት የተፈፀመ ከሆነ ሽምጋዩ የተወሰነ ድጋፍ ማለትም እገዳ ወይንም ማበረታቻ (incentives) መጠቀም ያስፈልጋል። ይህም ብዙ ጊዜ ካሮት ወይንም ዱላ በመባል ይታወቃል። በዚህ ደረጃ ምንም ያልተደባለቀበት ሽምግልና የለም ነገር ግን የበረታ ግፊት /ተፅዕኖ/ አይጠቀምም።

**ናሙና ማሳያ:** አማራጭ 1: ከማዕከላዊ/ብሔራዊ/ መንግስቱ የመጡት ልዑካን የሁለቱን ማኅበረሰብ አመራሮች በተናጠል ያነጋግራሉ። ከዚያ በኋላ ደግሞ ሁለቱንም በጋራ ተቀምጠው ያናግራሉ። ልዑካኑ የተወሰኑ ተፅዕኖዎችን እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ። ነገር ግን ማዳላት አይኖርባቸውም። ሁለቱ ቡድኖች በልዑካን ቡድኑ ድጋፍ የሚፈፀመው የሽግግር ስምምነቱ የሚሆነው ችግሩን እንዴት መፍታት እንደሚቻል ይሆናል።
አማራጭ 2: ህጋዊ ባልሆነ መልኩ በሚስጥር ቡድኖቹ ከውጭ ያሉ ወገኖችን የሚያናግሩ ልዑካን /ለምሳሌ የተከበሩ የኃይማኖት መሪዎች፣ የቀድሞ ፖለቲከኞች፣ አለምአቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች/ ይልካሉ። እናም በሚስጥር ሌላኛው ወገን ጥቃቶችን ለማቆም እና ለመወያየት ያለውን ፈቃደኝነት /ዝግጁነት/ ይሰልላሉ። በተናጠል የሚደረግ ውይይትን በመጠቀም እጅግ የተከበሩ የኃይማኖት መሪ እና የግጭት አፈታት ባለሙያዎችን የያዘ ቡድን ስምምነት እንዲፈፀም እና ግጭት እንዲቆም የተለያዩ እርምጃዎችን በመውሰድ ያግባባሉ።

49 inmedio Berlin, በገጽ 109 ላይ ያለውን አኪያ ይመልከቱ።

## ደረጃ 6 ማስፈራሪት ስልት

በሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት ድጋፍ ይፋ ያልሆነ ውይይት እና እምነትን የሚጥሉ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። ንግግሩን የሚያደርጉት ግለሰቦች የተጋጭ ወገኖች አመራሮች መሆን የለባቸውም። መተማመንን ለመገንባት የሚያስችላቸውን መንገዶች ያስባሉ። የፍተሻ ቦታዎችን ስለማቋቋም፣ እስረኛ ስለመለዋወጥ የመሳሰሉትን። ይህን ደግሞ የሚያደርጉት ከመሪዎቻቸው ጋር በመመካከር ነው። ንግግሩን የሚመሩት የሽምግልናን ስልት ይጠቀማሉ። ዓላማው መተማመንን መገንባት እስከሆነ ድረስ ብዙ ጊዜ በጥያቄ ውስጥ ያለው ግጭት በቀጥታ ላይዳሰስ ይችላል። ነገር ግን ሌሎች በአቻነት የተከሰቱ ግጭቶች እንደ አስረጅነት ሊጠቀሙ ይችላሉ። በዚህ ጉዳይ በሌላ ሀገራት ያሉ እና ግጭት በመፍታት ልምድ ያላቸው ግለሰቦች ሊጋበዙ ይችላሉ። እምነት ከማደራጀት ጐን ለጐን ፍርሃትን እና ሌሎች ግጭቱን እንደገና ሊቀሰቅሱ የሚችሉ ነገሮችን ለመቀነስ ይሰራል።

ናሙና ማሳያ: የመንግሥት እና የሲቭክ ማኅበረሰብ አካላት እጅ ለእጅ ተያይዘው ይሰራሉ። ጥንካሬያቸው የሚገለፀውም ወርክሾፕ በማዘጋጀት እና በመካከላቸው አምነትን ለማሳደር በሚያስፈልጋቸው በተለያዩ ማኅበረሰቦች መካከል ንግግር እንዲኖር በማድረግ ጭምር ነው። ሌላኛው አካል ምንም እንኳ ጥንካሬውንና ኃይሉን ቢያሳይም ፍራቻ እንዳለበት በማስገንዘብ የእመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ ይጥራሉ።

በመጨረሻም ከሚወሰዱ እርምጃዎች መካከል፡ የተወረሱ ባለቤቶች ወደቀድሞ ባለቤታቸው ይመለሳሉ። ወይም ኪሳራቸው ይከፈላል፣ የተወሰነ ለትራፊክ ክፍት የሚሆን መንገድ ይኖራል፣ የሞቱ ሰዎች አስክሬን ይረካከባሉ። ድባቡ ሌላኛው ወገን ችግሮችን መፍጠር ማቆም እንዲወስንና ለሠላም ፍላጐት እንዳለው ወደ ማሳየት ይቀየራል።

## ደረጃ 5 ሞገስ ማሳጣት

ሁለቱም ቡድኖች በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግጭት እንደማይከሰት እርግጠኞች ይሆናሉ። አሁንም ሌላኛው ወገን ወንጀለኞች እና ነፍስ ገዳዮች እንደሆኑ ያምናሉ። የመንግሥት አመለካከት የህግ የበላይነት እንዲከበር እና እውነትን የማፈላለግ ተልዕኮዎች በዚህ "ያልበረደ" የግጭት ደረጃ ላይ ወንጀል ተፈፅሞ እንደሆነ ለመመርመር ይጥራሉ። ብዙውን ጊዜ የሽግግር መንገዶች ተግባራዊ ይሆናሉ። ይህ ስልት ምህረትን በተወሰነ ደረጃ በመስጠትና እና በተወሰኑ መስፈርቶች የቀድሞ ታጋዮችን እንደገና ለማገናኘት ለማሰብ ይተገበራል። በሩዋንዳ ባህላዊ ችሎት ለዚህ ተግባር ውሏል። ደቡብ አፍሪካ ደግሞ የእውነት እና ዕርቅ አፈላላጊ ኮሚሽን አላቸው።

የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት በይፋ ይቅርታ የመጠየቅ ስራ እንዲሰራ ወሳኝ ሚና አላቸው። በተወያዩ ቡድኖች መካከል ጥሩ አደረጃጀት ያስፈልጋል። ሰዎች ወደኋላ በመመለስ በነሱ ወገን ለተፈጠረው ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ሃላፊነት መውሰድ ይጀምራሉ። ባለስልጣናት ይቅርታ ለመጠየቅ ዳተኛ ቢሆኑ እንኳ ግለሰቦች እና የሚዲያ ተቋማት ይቅርታውን በመጀመር ተፅዕኖ ይፈጥራሉ። በመጨረሻም ለዕርቅ ወሳኙ መንገድ በይፋ ይቅርታ መጠየቅ ነው። ይህ የሚረዳው ግን በትክክል ፀፀት ተሰምቶን ይቅርታውን የጠየቅነው ከሆነ እንጂ እንደ ማስቀየሻ ዘዴ ብቻ መሆን የለበትም ። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የቀድሞው የጀርመን ቻንስለን ዊሊ በራንድ ነው። በፖላንድ በተደረገ ጦርነት የመታሰቢያ በዓል ሲከበር በጉልበቱ የተንበረከከው ትዕይንት ነው። ይህ ለፕሮቶኮል የሆነ ሳይሆን በድንገት የውስጥ ስሜቱ ፈንቅሎ ያደረገው ነው። በብዙ ጉዳዮች የተወሰነ ማካካሻ መኖር አለበት። እንዲሁም ይህን የሚጠግን ባህላዊ ስነስርዓት ሊካሄድም ይችላል። በዚህ ነጥብ አንዳንድ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሽምግልና ስነስርዓቱ ደስተኛ ላይሆኑ ይችላሉ። ካልተሳተፉ በስተቀር ተመልሶ አደጋ ሊፈጥር ይችላል።

ናሙና ማሳያ: የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት ወንዝ ተሻግረው ከሌላ ቡድን ጋር እንዲሁም ከሚመለከታቸው የራሳቸው ማኅበረሰብ ጋር ውይይት እንዲኖር ያበረታታሉ። በነዚህ የተወሰኑ ፕሮጀክቶች ሰዎች ጉዳታቸውን ብቻ ሳይሆን ሀላፊነታቸውን እና የሌሎችን ጉዳት የሚያዩበት የፈጠራ ስራዎች ይቀርባሉ። አውደ ርዕዩች ዶክመንተሪዎችና የራዲዮ ፕሮግራሞች ይቀርባሉ። ማዕከላዊ

መንግሥት ከሁለቱም ወገኖች አመራሮች ጋር የተፈፀሙ ወንጀሎችን ለማጣራት ይስማማል። በግጭቱ የተጎዱ ሰዎች በይፋ የደረሰባቸውን ይናገራሉ። የምርመራው ውጤት ለህዝብ ይገለፃል ምህረት ስለማድረግ እንዲሁም ከሁለቱም ወገን አጥፊዎችን ለመቅጣት የሚያስችል ስምምነት ይደረጋል። ለተጎዱ ወገኖች ካሳ ይከፈላል። ከተወሰኑ አመታት በኋላ በሁለቱም ወገኖች በተውጣጡ የስነ-ቅርፅ ባለሙያዎች የተሠራ የመታሰቢያ ሀውልት ይቆማል። የማኅበረሰቡ ተተኪ መሪዎች በመክፈቻ ንግግራቸው ላይ የተሰማቸውን ሀዘን ይገልፃሉ። የማኅበረሰቡ ሽምጋዮች ይፋዊ ስሜትን የሚጠግን ስነ-ስርዓት ያከናውናሉ። ይህ ክስተት በፍጥነት የማኅበረሰቡን የንግድ እና የትብብር ግንኙነቶቹን ወዲያው ያሳድጋል።

## ደረጃ 4 ፍረጃና ቅንጅት

እርስ በርስ ይቅርታ ከተጠያየቁ በኋላ ቡድኖቹ እንደገና እንደሰው መተያየት ይጀምራሉ። ነገር ግን አሁንም በርካታ አለመተማመን እና ብስጭት አለ። ምክንያቱ ደግሞ አንዳቸው ሌላኛው ላይ ካደረሱት ጉዳት የተነሣ ነው። ችግር ወይም ግጭት ቢሆን እንኳ ይህ ስሜት ወዲያው ፈጦ ይታያል። ለምሳሌ አንድ ህፃን ልጅ በአጋጣሚ በሌላኛው ማኅበረሰብ በደረሰ የመኪና አደጋ ህይወቱ ቢያልፍ መገናኛ ብዙሃን በፍጥነት ወስደው ነገሩን ያራግቡታል ከዛም የተቃውሞ ሰልፍ ይካሔዳል። ጥቃቅን በሆኑ ቴክኒካዊ ጉዳዮች አለመግባባቶች ሲፈጠሩ "እነሱ ድሮውንም ከኛ በተቃራኒው የቆሙ ናቸው" ወደሚል የተቻኮለ ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ። ከዛም የቀደመውን ታሪክና ክስተት በመጥቀስ ማንቋሸሽና መንቀፍ ይጀምራሉ።

ሽምጋዩ በዚህ ደረጃ ማተኮር ያለበት በእጅ ያለው የግጭት ወሳኝ ጉዳዩች ላይ እና ከግንኙነቱ ስር ባሉ ችግሮች ላይ ነው። ከራስ ወገን ጋር ብቻ ከመስራት ይልቅ ከሌላኛው ወገን ጋር አብሮ መስራት በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ሰዎቹን ቡድናቸው በያዘው አቋም ላይ ድርቅ እንዲሉ የሚያደርግ ከፍተኛ የሆነ የአቻ ግፊት አለ። ሰፊው ህዝብ ቢሳተፍበት (በዚህ በተባባሰ ግጭት ደረጃ ውስጥ ይህ የተለመደ ነገር ነው) ሽምጋዮች በቀጥታ ከፀበኛ ቡድኖች ጋር ብቻ ሳይሆን ህዝቡንም ማሳተፍ አለባቸው (መገናኛ ብዙሃን፣ ወሳኝ ባለድርሻ አካላት ወዘተ የመሳሰሉትንም ጭምር)።

ናሙና ማሳያ: መንግሥት እና የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት ሰዎች ያላቸውን ስሜት፣ ፍራቻዎቻቸውን ማንፀባረቅ እንዲችሉ የሚረዳ በርካታ ስልጠናዎችን እና ወርክሾፖችን ያካሄዳሉ። ዕርቅ እንደትዕዛዝ ከላይ ወደ ታች መውረድ የለበትም። በተለይ ደግሞ ወሳኝ የሆኑ ሰዎችን ማድመጥ አለበት። በዚህ መሃል አንድ የተፈጠረን ግጭት እንዲያገረሽ የሚያደርግ ነገር ከተፈጠረ የአስተዳደር አካላት እና የሲቪክ ማኅበረሰብ ተቋማት መሪዎቹ ነገሮችን ሌላ መልክ እንዳይሰጧቸው እርምጃ ይወስዳሉ። በመኪና አደጋ ህይወቱ ያለፈው ልጅ ምሳሌን ብንወስድ የቀብር ስነ ስርዓቱ ሲፈፀም የኃይማኖት አባቶች እና የፖለቲካ መሪዎች በተገኙበት መከናወኑ የህዝቡን ስሜት ያቀዘቅዘዋል።

## ደረጃ 3 ንግግርን አቁሞ ተግባር ውስጥ መግባት

በዚህ ደረጃ በሁለት ቡድኖች መካከል ግጭት ሲከሰት አሁንም ግጭቱ በማኅበረሰቡ መካከል እንደተከሰተ ሳይሆን በተወሰኑ ችግሮች ምክንያት እንደተፈጠረ ነው የሚታየው። አሁንም የመግባባት ችግሮች ጉልህ ሚና ይጫወታሉ። ሌላኛው ቡድን የጋራ መግባቢያ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስጠበቅ እንደሚጥር እንዲያስብ ያደርጋል። ስለዚህ ሽምጋዮች ለሽምግልና የሚሆን ምቹ ጊዜ እንዲሁም የተጋጮች ክብር የሚጠበቅበትን ሁኔታ እንዴት መፍጠር እንደሚቻል ጥያቄ ሊያነሱ ይገባል። ሽምግልናው ከመጀመሩ በፊት በግል ብቻ የተፈፀመ ተግባር ካለ /ቢያንስ ለማሳየት ያህል/ ክብርን በሚያስጠብቅ ሁኔታ ተመልሶ ነገሮችን ማየት ያስፈልጋል። በዚህ ደረጃ የአመቻች ሽምግልና ስልትን መጠቀም ሂደቱን ተጨባጭ ያደርገዋል። ሽምጋዩ ማተኮር ያለበት ጥቅም/ፍላጎት/፣ ስጋቶች እና ግንኙነታቸው ላይ ሲሆን የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ መጣር ይጠበቅበታል።

**ናሙና ማሳያ:** የንግድና የሽርክና ስራ ፕሮጀክቶች የተለመዱ ናቸው። በጋብቻ መተሳሰር አልፎ አልፎ ቢሆንም አሁን ግን እየጨመረ ነው። ግጭት በማንም መካከል ቢፈጠር እንደተለመደ ተግባር ይቆጠራል። ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕርቅ እየተካሄደ ቢሆንም ማኅበረሰቡን ግን ይህን ያህል አያሰጋውም።

## ደረጃ 2 ክርክርና ተቃርኖ

ክርክርና አወዛጋቢ የሆኑ ውይይቶች በብዙዎች ዘንድ እንደ ዋነኛ ችግር አይታዩም። አሁንም ድረስ ንግግርን አጣፍጦ የመሸንገል ነገር ይከሰታል። ሁኔታውን ለማሻሻል የሽምጋዮች እርዳታ ቢኖር ባይኖርም አብይ ተግባቦት /እርስ በእርሳችን እንዴት መነጋገር እንዳለብን/ ወሳኝ መንገድ ነው። እንደ ማርሻል ቢ እና የሮዝንበርግ ሁከት- አልባ ተግባቦት[50] ወይም ባለ አራት ጎኑ የመልዕክት[51] ሞዴል በዚህ ረገድ ጥሩ ረጂ መሣሪያዎች ናቸው። ነገሮች በስህተት እንዴት እንደሚተረጐሙ እና ሌላውን ሳይጐዱ በነፃነት ሀሳብን እንዴት መግለፅ እንደሚቻል በጥልቀት መመልከት ጠቃሚ ነው።

**ናሙና ማሳያ:** ከዓመታት በኋላ በአረንጓዴዎች ወገን አዲስ ትምህርት ቤት ይገነባል። በብርቱካናማዎቹ ወገን ደግሞ በጥምረት ሆስፒታል ለመገንባት እቅድ ይያዛል። ታሪኩ እዚህ ላይ ያበቃል።

## ደረጃ 1 ግትርነት

ቡድኖቹን ለመርዳት አንድ ግለሰብ እንደሽምጋይ ሳይሆን እንደአወያይ እንዲረዳቸው ይጠየቃል። በዚህ ደረጃ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ቀላል ነው። ምክንያቱም ግንኙነቶቹ መልካምና የተረጋጉ ናቸው።

### ተግባር: ክረቱን ለማርገብ ስልቶችን መንደፍ

**ዓላማ** ተሳታፊዎች ክረቱን ለማርገብ እንዲሁም ወዳጅነትን ለማጎልበት የሚያስችላቸው ተገቢ ስልቶች ለመንደፍ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ዕውቀቶች ያገኛሉ።

**የተመደበ ጊዜ** 180 ደቂቃ

**መርጃ መሣሪያዎች** የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ ማርከሮች፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ፣ ባለቀለም ካርዶች

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ከራሳቸው ልምድ ተነስተው አንድ ግጭት የክረት ደረጃው የት እንደደረሰ የሚመረምሩ ቡድኖችን መድብ።

ደረጃ 2: ከግጭቱን ክረት ደረጃ ከለዩ በኋላ ቡድኖቹ ተገቢ ነው የሚሉትን የመፍትሄ ስልት እንዲጠቁሙ አድርግ /45 ደቂቃ/።

ደረጃ 3: እያንዳንዱ ቡድን ስልቶቹን ሁሉም ተሳታፊዎች ባሉበት እንዲያቀርብ አድርግ /45 ደቂቃ/።

ደረጃ 4: /እንደአማራጭ/ እያንዳንዱ ቡድን በሚና ነጠቃ ጨዋታ ከሶስተኛ ወገን ጋር አንድ ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ከተጋጭ ወገኖች ጋር በመገናኘት አስፈላጊ ስልቶችን እንዲረዱ በሚችሉበት መልኩ ስብሰባ ያድርግ /90 ደቂቃ/።

ግጭቶች ሊገመት በሚችል መልኩ ሊባባሱ የሚችሉት ዘላቂና አስተማማኝ የሆነ ጣልቃ ገብነት ሳይገኝ ሲቀር እንደሆነ አስተውለናል። ግጭቶችን ለማስወገድ /ለመቀልበስ ስንሰራም ተገቢውን ስልት በተገቢው ሰዓት መጠቀም እንዳለብንም ተመልክተናል። ሽምግልና ግጭት ለመከሰት አፋፍ ላይ ካለበት ደረጃ ጀምሮ ልንጠቀመው የምንችለው ቁልፍ ስልት ነው። በቀጣዩ ክፍል የቡድን ሽምግልና መመስረት እና መጠቀም እንደምንችል እንመለከታለን።

---

50 http://www.cnvc.org/

51 ክፍል III.6.1 ተግባቦት እና የሹልዝ ቮን ዙን አራት ጎናዊ የመልዕክት ሞዴል የሚለውን በገጽ 57 ላይ ይመልከቱ።

## III.11 የሽምግልና ቡድንን ማቋቋምና በሽምግልና ቡድን ውስጥ መስራት፡ የግጭት ባለድርሻ አካላትን ማካተት

### “Fara abbatu fale olaan gumaata naqaa.”

### “አንድ ሰው ችግሩን ለመፍታት ዝግጁ ሲሆን ጎረቤቶቹ ይተባበሩታል።”

### (ኦሮምኛ ቢሂል)

| | |
|---|---|
| **ዓላማ** | በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች የግጭት ባለድርሻ አካላትን በመጠቀም የሽምግልና ቡድን እንዴት መመስረት እንደሚቻል ይረዳሉ። |
| **የተመደበ ጊዜ** | 60 ደቂቃ |
| **መነሻ ዕውቀት** | የቀደሙት ምዕራፎች በሙሉ |
| **መርጃ መሣሪያዎች** | የሚገለጡ ማስተማሪያ ወረቀቶች፣ የተለያዩ መጠን ያላቸው ባለቀለም የማወያያ ካርዶች፣ የተለያዩ ቀለማት ያላቸው ማርከሮች፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳ እና ስፒሎች |
| **ቅደም ተከተል** | ደረጃ 1: የቡድን ሽምግልና የሚለውን ርዕስ አስተዋውቅ ውይይትህን ለማጠናከር የሚከተለውን መጠቀም ትችላለህ። |

ሽምግልና በዚህ መምሪያ መሰረት ሲተረጎም “በግጭት ውስጥ ያሉ ሁሉም ተዋንያን የተቀበሉት የሶስተኛ ወገን ድጋፍ” ማለት ነው። እዚህ ላይ እውነተኛ ሽምግልናን በሚመለከት ልንጠይቀው የሚገባን ነገሮች፡ ማነው የሚሸመግለው? እና እንዴት ነው የሚሸመግሉት? ናቸው። በአመቻች ሽምግልና ሽምጋዮች በተለምዶ የሚወክሉት ወይንም የሚሰሩት ለድርጅት ነው። በተጨማሪም የራሣቸው የሆነ ስብዕና አላቸው። አንዳንድ ጊዜ የነርሱ ማንነት ከድርጅት ግንኙነት ይበልጥ አስፈላጊ የሚሆንበት ጊዜ አለ። በባህላዊ ሽምግልና ግን ሽምጋዮች የተከበሩና ከማኅበረሰቡ የወጡ አባላት ናቸው።

የግጭት ነገር ጉዳዮች የተለያዩ ናቸው። በመሆኑም እንደግጭቶቹ ባህሪያት አንድ ወይንም ከአንድ ላይ ሽምጋዮች ሊያስፈልጉ ይችላል። እንደ ምሳሌ ወስደን ተንትነን የምንወያይበት ርዕስ “በሁለት የሃይማኖት ቡድኖች መካከል የተከሰተ ግጭት” ሲሆን ይህም የቡድን ሽምግልናን የሚፈልግ ይሆናል። በቡድን ሽምግልና ከተካተቱት አባላት አንዳንዶቹ የግጭቱ ተሣታፊ ወይንም የተጋጭ አካላት ወኪሎች ስለሆኑ “ባለድርሻ አካላት” እንላቸዋለን። አንዳንዶቹ ከተጋጬት የሃይማኖት ክፍሎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሲሆኑ አንዱ ደግሞ በአካባቢው በሰላም ግንባታ ዙሪያ የሚሰራ ባለሙያ /የሰላም ግንባታ ባለሙያ/ በመሆን ይሠራል። ከዚህ የተነሣ ሁሉም የቡድን ሽምግልና አባላት ስለ ግጭቱ ምንነት ያውቃሉ ማለት ነው። እነዚህ ሰዎች የተመረጡት ስብዕናቸው ታይቶና የየእምነቱን ቡድን ይወክላሉ ተብሎ ነው የተመረጡት ምንም እንኳ ይህ የቡድን ሽምግልና ግጭቱን ለመፍታት ተነሳሽነቱን የወሰደ፤ አስፈላጊና ጊዜያዊ ስብስብ ቢሆንም የራሱ ጥቅምና ጉዳት አለው። ከነዚህ መካከል አንዳንዶቹ ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

## የቡድን ሽምግልና ጥቅሞች

- ተጋጭ አካላት የሽምግልና ቡድኑን ገለልተኝነት ይቀበላሉ።
- የሽምግልናው ቡድን አባላት እርስ በርሳቸው ጥንካሬያቸውንና ድካማቸውን ይፈታተሻሉ።
- አባላቱ የተለያየ ስብዕና ስለሚኖራቸው ለአንድ ነገረ ጉዳይ ያላቸው አመለካከት የተለያየ ይሆናል። ይህም የሽምግልና ሂደቱን ሥራ ያጎለብተዋል።
- የቡድኑ አባላት እርስ በርሳቸው መቀባበልን ያዳብራሉ።
- ሽምጋዮቹ አንዱ ለሌላው ምክርን ሊሰጣጡ ይችላሉ።
- የቡድኑ አባላት አንዱ ከሌላው ሊማር ይችላሉ።

## የሽምግልና ቡድን ጉዳቶች

- የሽምግልና ሂደቱ ረዘም ያለ ጊዜ ሊወስድ ስለሚችል በተጋጭ አካላት እንዲሁም በሽምግልና ቡድኑ መካከል መሰላቸት ሊያመጣ ይችላል።
- የቡድኑ አባላት ሁሉም በሽምግልና ሂደቱ ላይ እኩል ተሳትፎ ላያደርጉ ስለሚችል ሂደቱን ሊያጓትተው ይችላል።
- ከሽምግልናው ቡድን አባላት ቁጥር የተነሣ ልዩ ፍርድ ቤት ውስጥ እንዳሉ ሊሰማቸው ይችላል።
- ተጋጭ አካላት ከሽምግልናው ቡድን አባላት መካከል አንዳንዶቹ አድልዎ እንደሚያደርጉ ሊሠማቸው ይችላል። ይህም ሂደቱን ሊያበላሸው ይችላል።

ደረጃ 2: "በሁለት የኃይማኖት ቡድኖች መካከል የተከሠተ ግጭት" የሚለውን ናሙና ማሳያ አስተዋውቅ።

ይህ ነገር ጉዳይ የሚያሳየን አብረው በአንድ መንደር የሚኖሩ፣ ብዙ የሚያመሣስላቸው ነገሮች ያላቸው እና አብዛኛውን ነገሮች ተጋርተው የሚኖሩ የሁለት ኃይማኖት ቡድኖችን ግጭት ሲሆን እንዴት ወደ መፍትሄ እንደሚመጡ ያሳየናል። ግጭቱ የተጀመረው እነዚህ የተለያዩ የኃይማኖት ቡድኖች በነበራቸው የመሬት አጠቃቀም ነው። የመሬቱ ባለቤት የሆነውና ለሁለቱም ቡድኖች እንዲገለገሉበት ፈቃድ የሠጠው መንግሥት ነው። የዚህ ቦታ አጠቃቀም የተመሠረተው አብዛኛውን ጊዜ በጋራ መተሣሠብ ቢሆንም በዚህ ጊዜ ግን ሁለቱም ቡድኖች የኃይማኖት ሥርዓት ለመፈፀም በተመሣሣይ ቀን ፈቃድ ይጠይቃሉ። ቢሆንም ግን አንዳቸውም ቡድን ሌላ ቦታ ለውጠው መጠቀም አልቻሉም። ከዚህ የተነሣ ግጭት ይፈጠርና የቀበሌው ሊቀመንበር /የመንደሩ አስተዳደሪ/ የመንደር ሽማግሌዎቹን፣ የኃይማኖት መሪዎችን የመያድ (NGO) የሠላም ግንባታ ባለሙያ እና የመንግሥት ባለስልጣናትን ለግጭቱ መፍትሔ ለመፈለግ ይሰበስባል።

የመንደር ሽማግሌዎች ተወካይ፣ የሰላም ግንባታ ባለሙያ እንዲሁም የመንግሥት ባለስልጣኖች በመሰባሰብ የሽምግልና ቡድኑን ይመሠርታሉ። በእያንዳንዱ የእምነት ቡድን ብዙ የሚጋጩ ጉዳዮች ከመኖራቸው የተነሣ ቡድኑን ለማዋቀር ከሃይማኖት ቡድኖቹ ተወካዮችን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ተገኘ። ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ በኋላ በእያንዳንዱ ቡድን በኩል ተወካዮች ተመርጠው ለሽምግልናው ቡድን ተላኩ። ሽምግልናው ከመጀመራቸው በፊት የሽምግልና ቡድኑ የተጋጭ አካላትን አመኔታ ማግኘት ይኖርበታል። ይህንን ለማግኘት ደግሞ የተሻለው መንገድ በተጋጭ አካላት ጉዳይ ጥልቅ ሃዘናቸውን፣ ተዓማኒነታቸውን፣ ሃቀኝነታቸውን እንዲሁም ከሁሉ በላይ አድሎ የሌለባቸው መሆናቸውን ማሳየት ይኖርባቸዋል። ገለልተኛ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የቡድኑ አባላት ራሳቸውን መጠየቅ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መካከል:

- በተጋጭ አካላት መካከል ሽምጋይ ለመሆን በዕውነት ከልባችን ገለልተኛ ነን?
- ዕውን ተጋጭ አካላት ገለልተኛ ሽምጋዮች እንደሆንን ይቆጥራሉ?
- ከመካከላችን አንዱ በቡድኑ ካለው ተሳትፎ ወይንም ዝምድና ምክንያት አድልዎ የሚያደርግ ወይንም የማይታማን ሆኖ በመገኘቱ ቡድኑ ገለልተኛ ባይሆን አዲስ የቡድን አባል እንተካለን?
- ነገረ-ጉዳዩ እኛ ልንሸመግለው የምንችለው ጉዳይ ነው?

ከጊዜ ወደ ጊዜ አመለካከታችን ሊቀየር ስለሚችል እነዚህን ጥያቄዎች በሽምግልና ሂደቱ መሃል ደጋግመን ልንጠይቅ ይገባል። ሽምግልናውን ለመጀመር ቡድኑ ከላይ የተዘረዘሩትን የቡድን ሽምግልና ጥቅሞችና ጉዳቶችን ደግመው ሊያጤኑ ይገባል።

የቡድኑ አሰባሳቢ (የቀበሌው ሊቀመንበር) በሽምግልናው ቡድን አይካተትም። ነገር ግን ከበስተጀርባቸው በመሆን ድጋፍ ያደርግላቸዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ሰላም በአካባቢው እንዲሰፍን የመንግሥት ፍላጎት ቢሆንም ኃይማኖት እና መንግሥት የተለያዩ በመሆናቸው የቀበሌው ሊቀመንበር (የመንደሩ አስተዳዳሪ) መንግስታዊ ስልጣን ስላለው የሽምግልና ቡድኑ አባላት በነፃነት የራሳቸውን ሚና ለመጫወት ያዳግታቸዋል። ሊቀመንበሩ የሽምግልና ቡድኑን በተለያዩ መንገዶች ተፅዕኖ ለመፍጠር ስለሚሞክር ቡድኑ ግጭቱን ለመፍታት በሚያደርገው እንቅስቃሴ ድፍረትን ያጣሉ። ስለዚህም መንግሥት የአካባቢውን ሰላም የማስጠበቅን ዓላማ ለማሳካት ሊቀመንበሩ በሽምግልናው ውስጥ ጣልቃ ከመግባት ተቆጥቦ ይልቁንም ቡድኑን በተለያዩ አስተዳደራዊ ጉዳዮች መደገፍ ይኖርበታል። ለምሳሌ፡ ስብሰባ የሚከናወንበትን ስፍራዎች ማመቻቸት ወይንም የገንዘብ ድጋፍን ማድረግ ሊሆን ይችላል።


የቀበሌው ሊቀመንበር በሽምግልናው ቡድን አይካተትም። ነገር ግን ከበስተጀርባቸው በመሆን ድጋፍ ያደርግላቸዋል።


የሽምግልና ቡድን በጥላ ስር።


ሽማግሌዎች ተጋጭ አካላትን ይሰማሉ።

## የሽምግልና ቡድን በጥካ ስር

### በሰላም ግንባታ ባለሙያው ሚመራው የሽምግልና ቡድን ከተመሠረተ በኋላ ሽምግልናውን በሚከተለው መልኩ ይጀምራል:

1. ግጭቱ እንዲባባስ ትልቅ አስተዋፅዎ የሚያደርጉትን፣ እንደሚከሰት የሚገምቱትን እንዲሁም ሰላምን የሚያስፋፉትን ጨምሮ የግጭቱ ወሳኝ ተዋናዮችና ባለድርሻ አካላትን መለየት እና ንድፍ ማውጣት።
2. የግጭት አተያይ ትንተና ማዘጋጀት።[52]
3. አዎንታዊ የሆኑ መልካም ገጠመኞችን ከአስከፊ ጎናቸው የተሻለ የሚባሉትን ሁኔታዎች በማጤን ሁኔታዎችን መቅረፅ።
4. ውጥረትን የሚያበርዱ እና ለግጭቱ ሁከት አልባ የሆኑ መፍትሄዎችን ያስተዋውቃሉ የሚባሉትን እርምጃዎችን በመለየት የተቀላጠፈ ምላሽን ማቀድ።

### በመቀጠልም የሽምግልና ቡድኑ:

5. የተመረጡትን ጉዳዮች እና መፍትሔዎቻቸውን ለያንዳንዱ የኃይማኖት ቡድን ቁልፍ ተዋናዮች ያቀርባል። ከዚያም ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ያደርጋል።
6. በእያንዳንዱ የኃይማኖት ቡድን የተመረጡትን መፍትሄዎችና አማራጮች በመጠቀም ለግጭቱ እንደ ግብዓት ይጠቀማል።
7. የተመረጡትን አቋሞች፣ ጥቅሞችና ስጋቶች በመመዝገብ ለቀጣይ ውይይት ይጠቀምባቸዋል።
8. አቋማቸውን እንዲያለዝቡ፣ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሄ በማፈላለግና ስጋታቸውን ለመለየት የማያቋርጥ ውይይት ይካሄዳል።
9. የጋራ መድረክ ላይ እንዲመጡ ከሁለቱንም ወገኖች ጋር ያለማቋረጥ ምክክር ይካሄዳል።

### ከዚያ በመቀጠል የሽምግልናው ቡድን እነዚህን የመጨረሻ እርምጃዎች ይወስዳል:

10. ሁለቱም የኃይማኖት ቡድኖች አንገብጋቢ የሆነውን የጋራ ጉዳያቸው እንዲፈታ የሚፈልጉትን ግልፅ አድርገው የሚመካከሩበትን መድረክ በማዘጋጀት ሁለቱንም ይጋብዛል።
11. ሰላም ለሁለቱም የኃይማኖት ቡድኖች እንዴት እንደሚጠቅማቸው ለማሳየት ለሁሉም ተጋጭ ቡድኖች ወይንም ማኅበረሰቦች መረጃውን ያሰራጫል።
12. ወደፊት ሊከሰቱ የሚችሉትን ግጭቶች በሰላም ሊፈቱ የሚችሉ መፍትሄዎችን የሚያስተዋውቁ የተሳኩ የግጭት አፈታት መንገዶችን ይቀርፃሉ።

ደረጃ 3: የግጭት ባለድርሻ አካላትን ጨምሮ የቡድን ሽምግልና ጥቅምና ተግዳሮቶች ላይ ትኩረት በመስጠት ውይይቱን አጠቃል።

52 ክፍል III.7 የግጭት አተያይ ትንታኔ (Conflict Perspective Analysis) የሚለውን በገጽ 71 ላይ ይመልከቱ።

# ክፍል IV የአሰለጣጠን ክህሎቶች

## "Kan qabutu keena kaan beekutuu hima."

"ያለው ይሰጣል የሚያውቅ ይናገራል።"

(ኦሮምኛ ብሂል)

| | |
|---|---|
| ዓላማ | በስልጠናው መጨረሻ ተሳታፊዎች በሽምግልና ስልጠና አሰጣጥ ዙሪያ ክህሎታቸውን ያሳድጋሉ። |
| የተመደበ ጊዜ | 90 ደቂቃ |
| መርጃ መሣሪያዎች | የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀት፣ የተለያየ መጠን ያላቸው ማወያያ ባለቀለም ካርዶች ፣ ባለቀለም ማርከሮች ፣ ወረቀት መለጠፊያ ሰሌዳና ስፒሎች |
| ቅደም ተከተል | ደረጃ 1: ርዕስ IV.1 ጠቅለል ያለ ምክር ለአሰልጣኞች የሚለውን ርዕስ አቅርብ። |
| | ደረጃ 2: ርዕስ IV.2 በስልጠና ወቅት የሚና ነጠቃ ጨዋታ ተግባር የሚለውን ርዕስ ተወያይበት። |
| | ደረጃ 3: ርዕስ IV.3 ግብረ መልስ እንዴትና ለምን ይሰጣል የሚለውን ርዕስ አብራራ። |
| | ደረጃ 4: የትምህርቱን ጊዜ አጠቃል። |

## IV.1 ጠቅለል ያለ ምክር ለአሰልጣኞች

እንደ አሰልጣኝነትህ የሚከተሉትን ነጥቦች ከስልጠናው በፊት እንዲሁም በስልጠናው ወቅት ልታጤናቸው ይገባል።

ተሣታፊዎች ካንተ የሚጠብቁትንና የትምህርቱን ዋና ዓላማ ጠንቅቀህ እወቅ። የመጨረሻ የስልጠና ንድፍ/መዋቅር ከማዘጋጀትህ በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ፡

- ዋና ዓላማዬ ምንድን ነው? ተሣታፊዎቼ እንዲለወጡ የምፈልገው ምንድን ነው?
- ተሣታፊዎቼ የሽምግልና ክህሎቶችን ለምን ይፈልጋሉ?
- እንዴት ሊጠቀሙበት ይችላሉ?
- ክህሎቶቻቸውን እንዴት ሊተገብሯቸው ይችላሉ?
- ጥቅማቸው ምንድን ነው?
- ምን ይጠብቃሉ?
- ስልጠናውን በተመለከተ ምን ስጋት አለባቸው?

ተሣታፊዎች እንዲረዱ እና እንዲገነዘቡ ለማስቻል ጥረት ልታደርግ ይገባል፡

- በመጀመሪያ ጥቅል ሀሳብ በመስጠት ከዚያ ከመዋቅሩ በመነሳት ወደ ዝርዝር ጉዳዮች መግባት።
- በመጀመሪያ ሀሳብን ለማንሸራሸር (brain storming) ጥያቄዎች ካቀረብክ በኋላ በመጨረሻ ደግሞ ውጤቱን በማጠቃለል ተሳታፊዎቹ መረጃውን በሚገባ እንደተገነዘቡት እርግጠኛ ሁን።
- በሚና ነጠቃ ጨዋታ በመደገፍ ስልጠናህን አጠናክረው።
- ራስህም ተሣታፊ ሁን። ተመልካች ወይም ታዛቢ ብቻ ከሆንክ በስልጠናህ ስኬታማ አትሆንም።

በአነስተኛ ቡድን በመከፋፈል ወይንም አንድ ሙሉ ክፍለ ጊዜ ለግምገማ ስጥ፡

- በስልጠናው ወቅት ያለው ተጨባጭ አማራጭ አንድ ቋንቋ ብቻ መጠቀም ከሆነ ለተሣታፊዎቹ በዚያ ቋንቋ ብቻ መጠቀም ያስፈለገበትን ከነምክንያቱ በማቅረብ ይቅርታ መጠየቅ ይገባል። አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ አስተርጓሚ መጠቀም ይቻላል።
- የሚና-ነጠቃ ጨዋታን እንዴት መገምገም እንደሚቻል መመሪያዎቹን አስተዋውቅ። ለምሳሌ፡ አንድ ሰው "እባካችሁ አካላዊ ቋንቋ በሽምግልና ሂደት ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ተወያዩ" ሊል ይችላል። በሽምግልና ክህሎት አጠቃቀም ጠቀሜታ እንዲኖረው ትኩረት ስጥበት።
- ተሣታፊዎቹ በቴክኒክና ስልት አጠቃቀም ዙሪያ በሚያደርጉት ውይይትና ግምገማ ላይ አተኩር። ከዓላማው ውጪ የሆኑ ማንኛውም ስሜቶችና አመለካከቶች ግብረ-መልሱንና የትምህርቱን ሂደት ግልፅ አያደርጉትም። ተጋጭ አካላት ምን ተሰማቸው? አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ መጠይቆችን ተጠቀም።
- ተሳታፊዎችህ መሪ ተዋናይ እንዳይሆኑ ተጠንቀቅ። የሚና-ነጠቃ ጨዋታን ማከናወንና አትኩሮታቸውን ማግኘት ከባድ ነው። የሚያበረታታና ጠቃሚ እንዲሆን አድርገው።
- ተሣታፊዎች የመጨቆን ስሜት እንዳይሰማቸው ተከታተል። ለተሣታፊዎች ዕድል ስጣቸው። በአነስተኛ ቡድኖች ሲከፋፈሉ ሀሳባቸውን አስፍረው እስካልጨረሱ ድረስ ጣልቃ አትግባባቸው። አሰልጣኙ በሃሳባቸው ውስጥ ከገባበት በኋላ ተሣታፊዎቹ የቀረቡትን አስተያየቶች እንዲቀበሉ ወይንም እንዲወያዩበት ዕድል ስጣቸው። አንዳንድ ጊዜም ክፍሉን በመልቀቅ ተሣታፊዎች የማስማሚያውን ሀሳብ ለማሰላሰል ዕድልና ጊዜ ይሰጣቸዋል።
- በሚና-ነጠቃ ጨዋታ ተሣታፊዎቹን ለማበረታታት ራስን መነቅነቅ ወይንም ፈገግታ ማሳየት ተመራጭ ነው።
- ለተሳታፊዎች አሰልጣኝ ሁን። አሰልጣኙ ሁል ጊዜ የተሣታፊ-ሽምጋዮችን የሚደግፍ ነው።
- የጊዜ ገደብህን ጠብቅ።
- ግልጽ የሆነ ሃሣብና ግልጽ ቃላት ተጠቀም።
- ከተሣታፊዎች ጋር ነገረ-ጉዳዩን በግልፅነት ተወያዩበት።
- ስዕላዊ መግለጫዎችን ተጠቀም።
- ትላልቅ ፊደላትን ተጠቀም።
- ለተሣታፊዎች ግልፅ እንዲሆን ርዕሶችን ፃፍ።
- በያንዳንዱ የሚገለጥ ማስተማሪያ ወረቀቶች ላይ ርዕሶቹን ፃፍ።
- ፍሬ ሀሳቦችን ለይተህ አውጣ /ሙሉ ዐረፍተ ነገር ለመፃፍ አትሞክር/።
- የምትፅፍበትን ቀለም መቀየር ባስፈለገህ ጊዜ ብቻ ቀይር።
- ግብረ-መልሶችን /ገንቢ አስተያየቶችን/ አዎንታዊ በሆነ መልኩ አሳጥረህ ፃፋቸው።

### አትኩሮትን እንዲስቡ ማድረግና ማነቃቃት:

- በስልጠናው መክፈቻ ንግግር ላይ የተሣታፊዎችን ፍላጎት የሚዳስስና ተደራሽ መሆኑን ግልፅ አድርግ።
- በስልጠና ወቅት ከተሣታፊዎች ጋር የአይን ለአይን ግንኙነት አድርግ።
- ለአድማጮችህ በቀጥታ ተናገር።
- እንደ ድምፅ አጠቃቀም ፣ የፊት ገፅታ ፣ ቦታ ወይንም ዕይታ የመሳሰሉትን እንደ ሁኔታው በመቀያየር ተጠቀም።
- መልካም ነገሮችን የምትጠብቅ ሁን-በችግሮቹ ላይ ሳይሆን በመፍትሔው ላይ አትኩር።
- መወያያ ርዕሱን ከተሳታፊዎች ልምድ እና እውነታ ጋር አዛምደው።
- ሰልጣኞች የተገኙት በራሳቸው ተነሣሽነት እንዳልሆነ ካወቅክ ለስልጠናው ያላቸውን ቸልተኝነት እንደምትረዳ ነገር ግን መገኘታቸውን እንደምታደንቅ ግልፅ አድርግላቸው። ይህ ብዙ ጊዜ የነገሩን ድባብ ስለሚያጠራው መተባበርን ያመጣል።
- ሰልጣኞች በንቃት እንዲከታተሉ የሚያነቃቁ ዘዴዎችን ተጠቀም። ከነዚህም መካከል ከስልጠናው በፊት ወይንም ከእረፍት በኋላ ወይም ደግሞ ያስፈልጋቸዋል ብለህ በምታጠብበት ወቅት ሁሉ ማነቃቂያ ጨዋታዎችን ማዘጋጀት ትችላለህ። ነገር ግን የምትጠቀማቸው ማነቃቂያ ዘዴዎች ከተሣታፊዎች ባህል፣ ፆታ፣ እድሜ፣ ማህበራዊ ደረጃ ጋር የማይቃረን እንዲሁም እነዚህን ያገናዘበ መሆን ይኖርበታል።



## IV.2 በስልጠና ወቅት የሚና - ነጠቃ ጨዋታ ያለው ተግባር

በሚና ነጠቃ ጨዋታ የሚሳተፉ ተዋናዮች በምንም ዓይነት መልኩ ቢተውኑትም የሚና-ነጠቃ ጨዋታ የእውነተኛ ህይወት ነፀብራቅ ነው። ስለዚህም የሚና-ነጠቃ ጨዋታ በመጠቀም አስተሳሰብ፣ ገጠመኖች እንዲሁም ልምዶች በጭውውት እና አስደሳች በሆነ መንገድ ወደ ህይወታችን ይመጣሉ። በተጨማሪም ተሣታፊዎች የተማሩትን ክህሎቶች እንዲተገብሩበት እና ስሜቱን በማወቅ ልምድ እንዲያካብቱ ይረዳቸዋል።

የሚና-ነጠቃ ጨዋታ በማንኛውም የስልጠና ክፍለ ጊዜ መጠቀም ቢቻልም አብዛኛውን ጊዜ ከስልጠናው ክፍለ ጊዜ መጨረሻ መጠቀሙ የተሻለ ያደርገዋል። ተሳታፊዎች በሚና-ነጠቃ ጨዋታ ውስጥ "እንዲሳተፉ" ለማድረግ የጨዋታውን አዘገጃጀት በሚገባ እንዲያጤኑት ጊዜ ወስዶ ማስረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ይህም የሚሆነው በተመደቡበት ሚና በሚገባ እንዲጫወቱት ለማድረግ ነው አሰልጣኞች ሰልጣኞች የሽምግልና ሂደትን መሠረታዊ ሀሳቦችን በተሻለ መልኩ እንዲረዱ ለማድረግ የሚና-ነጠቃ ጨዋታን ሊጠቀሙ ይችላል። በዚህ መምሪያ ውስጥ የተካተቱ የሚና-ነጠቃ ጨዋታ ምሳሌዎች የሚከተሉትን ይመስላሉ።

### የተግባቦት ተግባራት

ተግባቦት ለውጤታማ ሽምግልና (በተለይም በሽምጋዮች መካከል) አንዱ የሌላውን አቋም መገንዘብ እንዲችሉ ይረዳቸዋል። እዚህ ላይ ተግባቦት የተጋጭ አካላትን ስሜት፣ ስጋት፣ ጥቅምና የመሳሰሉትን አትኩሮ ተገቢ መፍትሄ ላይ እንዲደርሱ ያስችላል።

### የሽምግልናው ዛፍ ማማ ፣ የማንጎ ዛፍ ፣ የመሳሰሉ የሚና-ነጠቃ ተግባራት

እነዚህ ጨዋታዎች የተጋጭ ወገኖችን አቋም ለውጥ በመግለጥ ከአቋማቸው ወደ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው እንዴት እንደሚመጡ ያሳያል። በመጀመሪያ ሁለቱም ወገኖች ሊያገኙት የሚፈልጉትን የመፍትሄ ሃሳብ ያቀርባሉ ነገር ግን አንዱ ወገን የሌላውን የመፍትሔ ሃሳብ ውድቅ ያደርጋል። እነዚህ የሚና-ነጠቃ ጨዋታዎች የሽምግልና ክህሎታቸውን በማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን በመጠቀም ተጋጭ አካላትን ወደ ፍላጎታቸውና ጥቅማቸው እንደሚያመጧቸው የሚለማመዱበት ነው።

### የአሳ ማስገር ጨዋታ ፣ የአህዮቹ ታሪክ

ተጋጭ ወገኖች የአመለካከት ለውጥ እንዲያመጡ የሚረዳ ጠቃሚ የሚና-ነጠቃ ጨዋታ። ከላይ እንደተጠቀሱት ጨዋታዎች እነዚህም ተጋጭ ወገኖች አቋማቸውን ከሚያንፀባርቁበት ደረጃ ላይ ጭውውቱ ይጀምራል። ጠንካራ ግንኙነት በሚያደርጉበት ሂደት ውስጥ ግን ሁለቱም ወገኖች አቋማቸው እየተሸረሸረ እየመጣ እንደሆነ እና እንደገና አቋማቸውን ማጤን እንዳለባቸው መፈተሽ ይጀምራሉ። ከዚያ በመቀጠል የሌላኛውን ወገን ፍላጎት ማወቅ ሲጀምሩ የተለያዩ አማራጮችን በማፍለቅ ሁሉን ተጠቃሚ የሚያደርግ መፍትሔ ለማምጣት ጥረት ያደርጋሉ።



## የሽምግልና ገፀታዎች

**ዓላማ**

የሚና-ነጠቃ ማግባቢያ መሪ ጥያቄዎችን እንዴት እንደምንጠቀምና እና ንግግርን በራሳችን አገላለፅ እንዴት እንድምንገልጽ እና እንደምናጠቃልል ያሳየናል።

**ቅደም ተከተል**

ደረጃ 1: ዝግጅት

- ነገረ-ጉዳዩን በሚመለከት ሊረዱት በሚችል መልኩ የተዘጋጀ ታሪክ በማዘጋጀት ለሚና-ነጠቃ ተዋናዮች ጉዳዩን ለይተህ ተናገር።
- ተሣታፊዎች በሚና-ነጠቃ ጨዋታ ውስጥ እንደ ተጋጭ ወገኖች ሚናቸውን ይይዛሉ።
- አንድ ወይንም ሁለት ተሣታፊዎች የሽምጋይነት ሚና ይሰጣቸዋል።
- ተሣታፊዎችህ ጨዋታውን እንዴት እንደሚያቀርቡት የማሠላሠያ ጊዜ ስጣቸው።

ደረጃ 2: ተጫዋቾችን አሳትፍ

ወንበሮቹን በሶስት ማዕዘን ቅርፅ አስተካክላቸው። ይህም ተጋጭ ወገኖች ሽምጋዩን እኩል ማየት ስለሚችሉ ነው። ሽምጋዩ ሞቅ ባለ ሰላምታ እንደሚጀምርና ሁለቱንም ወገኖች በዚህ ወቅት ምን እንደሚሰማቸው እንደሚጠይቃቸው ግለፅላቸው። ከዚያ በመቀጠልም ቅደም ተከተሉን በማዘጋጀት የጋራ መግባቢያ ደንቦችን ይቀርፃሉ።

ደረጃ 3: ተሣታፊዎች የተሰጣቸውን ሚና መተግበር ይጀምራሉ።

ደረጃ 4: አዘጋጁ የሚና-ነጠቃ ጨዋታውን ይዘጋዋል። ከተገነዘቡት ነገር በመነሳት ተጫዋቾቹ በሚና -ነጠቃ ጨዋታው ጊዜ የተሰማቸውን ያካፍላሉ።

**ማሳሰቢያ**

የሚና-ነጠቃ ጨዋታ ህጎች ቀላል፣ ተፈፃሚ፣ ግልፅና የሚገቡ መሆን አለባቸው። የመማርና የማሳደግ ባህሪ አካል ከሆኑት አማራጮች ወደኋላ በመመለስ እንደገና መከለስ የተወሰኑትን ወይንም ደግሞ ሙሉ በሙሉ የሚና-ነጠቃ ጨዋታውን መከለስ አስፈላጊ ነው። ይህ ማለት ለአንድ ግለሰብ የሚመቸውን፣ የማይመቸውን እና የባህሪውን ደረጃ ለመለየት ይጠቅማል። ማወቅና መጠንቀቅ ያለብህ ነገር ለአንዳንድ ተሣታፊዎች የሚና ነጠቃ-ጨዋታው ሊረብሻቸው ይችላል። ስለዚህም እነዚህ ጨዋታዎች በስልጠና ተሳታፊዎች መካከል መተማመን ከዳበረ በኋላ ነው። ከሚና ጨዋታው በኋላ ጠለቅ ያለ ማብራሪያ ለማድረግ (እያንዳንዱ ተጫዋች ምን እንደተሰማው) ከሚናው በመውጣት (እያንዳንዱ ተጫዋች ከሚናው ወጥቶ) እንዲሁም የተማሩትን ትምህርቶች ለማጠቃለል እንዲችሉ በቂ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ ነው። ያለበለዚያ ግን ከልምምዱ በኋላ ተሣታፊዎች አላስፈላጊ ስሜትና አስተሳሰብ የመያዝ አደጋ ሊኖራቸው ይችላል።



## IV.3 ግብረ - መልስ (Feedback) ለምን ያስፈልጋል እንዴትስ መስጠት ይቻላል?

ግብረ-መልስ (feedback) የስልጠና ዋና አካል ነው። መደበኛ ወይንም መደበኛ ባልሆነ መልኩ መስጠት ይቻላል። በተለያየ የስልጠና ደረጃ ላይ ሰልጣኞች ብቃታቸው እንዲያድግ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን በማሳየት ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ ይጠቁማል። ሰልጣኞች ለግብረ-መልስ ትልቅ ግምት አላቸው። በተለይም ደግሞ ከእውቀታቸው፣ ከአመለካከታቸው እና ከክህሎታቸው ጋር ተዛምዶ ያለው ወይንም እንደ ሞዴል በሚመለከቱት ሰው የተሰጠ ሀሳብ ከሆነ ግምታቸው ከፍተኛ ይሆናል።

### የግብረ-መልስን አንዳንድ ጥቅሞች ለመጥቀስ ያህል:

- የአሰልጣኙን ትምህርት አሰጣጥ መንገድ ያሻሽላል።
- በሰልጣኞቹና በአሰልጣኙ መካከል መግባባትንና መተማመንን ያዳብራል።
- ትምህርቱን ያጎለብታል።
- አዳዲስ ሀሳቦች እንዲፈልቁ መንገድ ይከፍታል።
- አዳዲስ ልምዶችንና መሻሻሎችን ያመጣል።

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አንዳንድ ምክሮች ተሣታፊዎችን በሚያበረታታ መልኩ እንዴት ግብረ-መልስ /ገንቢ አስተያየት/ መስጠት እንደሚቻል ያሳያል። ይህም እውቀታቸውን ግጭትን ወደ በጎ መለወጥን (conflict transformation) እና የሽምግልና ሂደትን በሚመለከት ክህሎታቸውን እንዲሁም ባህሪያቸውን እንዲያሳድጉ ይረዳቸዋል።**

- ተሣታፊዎች ከተለያየ አስተዳደግና ባህል የሚመጡ ከመሆናቸው የተነሣ ግብረ-መልስ (feedback) አንዳንድ ጊዜ አለመግባባት ሊፈጠር ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በተለየም በጥሩ ሁኔታ ካልተቀመጥ፣ አሉታዊ ጎኑ ገዝፎ ከተቀመጠ፣ ካልተብራራ፣ ከርዕሱ ውጭ ከሆነ ወይንም ስብዕናን የሚነካ ከሆነ ግጭትን ሊፈጥር ይችላል። በሌላ መልኩ ግብረ-መልስ አለመስጠት በራሱ በሰልጣኞች ዘንድ ያልታሰበ መልዕክትን ሊያስተላልፍ ይችላል። በቡድኑ ላይ ያለንን ዕምነት ሊያሳጣ ይችላል።
- ግብረ-መልስን መስማት ሁልጊዜ አስቸጋሪ ነው። ሚና ነጠቃ ጨዋታ፣ ውይይት ወይንም ገለፃ እና የመሣሠሉት ከተፈፀሙ በኋላ ወዲያው ግብረ-መልስ መስጠት በጣም አስፈላጊ ነው። ንግግርንና ሂደቶችን ከማቋረጥ ይልቅ ማስታወሻ በመያዝ ጊዜ በምታገኝበት ጊዜ ግብረ-መልሱን መስጠት ይሻላል።
- የግብረ-መልስ አሰጣጥ መንገድ እንደአውዱ ይለያያል። ነገር ግን ጠቅለል ባለ መልኩ ግብረ-መልስ ለመስጠት መጀመሪያ ከተሣታፊዎች ጥያቄ መቅረብ ወይንም ጥያቄው ሲቀርብ ተቀባይነት ስታገኝ ብቻ ነው። ግብረ-መልስ በሚገለጠው ማስተማሪያ ወረቀት ፣ በወረቀት ላይ ወይም በቃል ሊሰበሰብ ይችላል።

### ግብረ-መልስ የመስጠት መሠረታዊ ህጎች

- አንድ ነገረ-ጉዳይ ከተነሣ በኋላ በተቻለው ፍጥነት ወዲያውኑ አዎንታዊ በሆነው ጎኑ ላይ በማተኮር ግብረ-መልስ መስጠት።
- ግብረ-መልስ በምትሰጥበት ጊዜ መልዕክትህ ሊያስተላልፈው የሚችለውን ተፅዕኖ በማሰብ ተጠንቅቀህ አቅርብ። የመልዕክትህን ይዘት፣ የግብረ-መልስ አሰጣጥህን እና በምትናገረውና በእንቅስቃሴህ መካከል ያለውን መጣጣም ግምት ውስጥ በማስገባት አቅርብ። ስለዚህ እንደ አሰልጣኝነትህ መጠቀም ያለብህ ቋንቋ "ይህን እወዳለሁ <u>ነገር ግን</u> ሊሻሻል እንደሚችል አስባለሁ።" ከማለት ይልቅ "ይህን እወዳለሁ <u>እንዲሁም</u> ሊሻሻል እንደሚችል አስባለሁ።" ምክንያቱም "ነገር ግን" በሚለው ቃል ውስጥ አዎንታዊ የሆነውን የሰው አመለካከት ብዙ ጊዜ ሊያጠፋ ይችላል።
- መናበብን የመሣሰሉ ስልቶችንና ግልጽ ጥያቄዎችን ተጠቀም።
- በሠልጣኞችህ መካከል አክብሮትንና አመኔታን ፍጠር።
- ግብረ-መልስ በምትሰጥበት ጉዳዮች ላይ ግልጽ ሁን። ይህንንም ከሠልጣኞች ሙያዊ ክህሎት ዕድገት ወይንም በፕሮግራሙ ዓላማ ጋር አዛምደው።
- ለተሳታፊዎቹ ብዙ መረጃ በመስጠት አታጨናንቃቸው። በሁለት ወይም ሦስት ቁልፍ መልዕክቶችን በማጠቃለል አቅርብ።
- በማንነታቸው ላይ ሳይሆን ሊለወጡ በሚችሉ ባህሪያት ላይ ትኩረት ስጥ።
- ግብረ-መልሶች በተለይም አሉታዊ የሆኑት በግል ሊነገሩ ይገባል።
- አሉታዊ ግብረ-መልሶች በሚሠጡ ጊዜ አማራጭ ባህሪያትንም አክሎ አስተያየት መስጠት ያስፈልጋል።
- የተለዩ ባህሪያትን አብራራ። የሚቻል ከሆነ ደግሞ ምሳሌዎችን ስጥ እንጂ ምክንያታቸውን አትገምት እንዲሁም አትመርምር።

# ክፍል ፬ ማጣቀሻዎች


Alexander, N. (2011). The Mediation meta-model—the realities of mediation practice. *ADR Bulletin*, 12 (6) Article 5. Retrieved from: http://epublications.bond.edu.au/adr/vol12/iss6/5.

Burgess, G. & Burgess, H. (Eds.). (2003). Empathic listening. *Beyond intractability*. Boulder: Conflict Information Consortium, University of Colorado. Retrieved from: http://www.beyondintractability.org/bi-essay/empathic-listening.

Burgoon, J.K., Birk, T. & Pfau, M. (1990). Nonverbal behaviours, persuasion, and credibility. *Human Communication Research,* 17 (1), 140–169.

Bush, B. R. A. & Folger, J. P. (1994). *The Promise of mediation: responding to conflict through empowerment and recognition*. San Francisco: Jossey-Bass.

Ekman, P., Friesen, W. V. & Ellsworth, P. (1972). *Emotion in the human face: guidelines for research and an integration of findings*. New York: Pergamon Press.

Fisher, R. & William, U. (1981). *Getting to yes: negotiating agreement without giving in* (3rd ed.). New York: Penguin.

Girshaw, T. (2004). Indigenous conflict resolution mechanisms in Ethiopia. *Federalism, conflict and peace building*. Addis Ababa: Ministry of Foreign Affairs and GTZ.

Glasl, F. (1998). *Selbsthilfe in Konflikten*. Bern: Haupt Verlag.

Glasl, F. (1999). *Confronting conflict. A first-aid kit for handling conflict*. Pennsylvania: Hawthorn.

Glasl, F. (1997). *Konfliktmanagement: Ein Handbuch für Führungskräfte, Beraterinnen und Berater*. Bern, Stuttgart: Haupt, Verlag Freies Geistesleben.

Hardin, G. (1994). The tragedy of the unmanaged commons. *Trends in ecology & evolution*, 9 (5), 199.

Hoffman, D.A. (2003). Ten principles of mediation ethics. reprinted in *Mediation: approaches and insights*. Juris Publishing. Retrieved from: http://bostonlawcollaborative.com/blc/72-BLC/version/default/part/AttachmentData/data/2005-07-mediation-ethics.pdf?branch=main&language=default

Institute for Peace and Security Studies (IPSS/AAU) in collaboration with Friedrich Ebert Stiftung (FES). (2010). *An anthology of peace and security research*, Addis Ababa. 82–83.

Leonhard, M. (2001). *Conflict analysis for project planning and management—A practical guideline*. (Draft). Eschborn: Deutsche Gesellschaft für Technische Zusammenarbeit (GTZ) GmbH. Retrieved from http://www.giz.de/Themen/en/dokumente/en-conflictanalysis.pdf

Malan, J. (1997). *Conflict resolution wisdom from Africa.* Durban: African Centre for the Constructive Resolution of Disputes.

Mehrabian, A. (1981). *Silent messages: Implicit communication of emotions and attitudes.* Belmont: Wadsworth Publication.
Mitchell, C. R. (1989). *The Structure of international conflict*. London: Palgrave Macmillan.
Moore, C.W. (2003). *The mediation process: Practical strategies for resolving conflict* (3rd revised ed.). San Francisco: Jossey-Bass Publishers.
Niederberger von Wyl, J. (2009). *Trainer's manual in mediation. A practical guide for community-level skill-building trainings in Afghanistan*. Mazar-e Sharif: Deutscher Entwicklungsdienst (DED) Ziviler Friedensdienst (ZFD).
Rabar, B. & Karimi, M. (Eds.) (2004). *Indigenous democracy: Traditional conflict resolution mechanisms—Pokot, Turkana, Samburu, and Marakwet*. Intermediate Technology Development Group-Eastern Africa (ITDG-EA), Kenya.
Reda, K.T. (2011). Conflict and alternative dispute resolution among the Afar pastoralists of Ethiopia. *African journal of history and culture (AJHC),* 3 (3), 38–47.
Roos, C., Splinter, D. & Wüstehube, L. (2011). Facilitative wise-counsel mediation—Zur Verbindung von "westlichen" und "traditionellen" Mediationsansätzen in Äthiopien. *Perspektive Mediation*, 2, 86-90.
Schulz von Thun, F. (1981). *Miteinander reden 1: Störungen und Klärungen. Allgemeine Psychologie der Kommunikation*. Hamburg: Rowohlt.
Schulz von Thun, F. (2012). *Das Kommunikationsquadart*. Retrieved from www.schulz-von-thun.de/index.php?article_id =71 (available only in German). Translation by ForumZFD retrieved from: http://www.forumzfd-akademie.de/files/va_media/nid1517.media_filename.pdf
Wüstehube, L. (2004). Konflikt-Perspektiv-Analyse (KPA). Ein mediationsanaloges Instrument zur konstruktiven Analyse und Bearbeitung von Konflikten. *Perspektive Mediation*, 1, 18-22. Retrieved from: http://www.inmedio.de/papers/pdf_010207/wue_Konflikt-Perspektiv-Analyse.pdf
Wüstehube, L. (2005). Vom Umgang mit non-verbaler Kommunikation in der Mediation. *Zeitschrift für Konfliktmanagement*, 3, 1-5. Retrieved from: http://www.inmedio.de/papers/pdf_010207/wue_Nonverbale_Kommunikation.pdf
Wüstehube, L. & Specht, H. Knapp, P. (Ed.) (2013). Körpersprache gewinnbringen nutzen. Der Körper ist der Übersetzer der Seele ins Sichtbare. Konflikte lösen in Teams und großen Gruppen. Bonn: managerSeminare Verlags GmbH.

# ክፍል VI ስለአዘጋጆቹ

ይህ መምሪያ የተዘጋጀው ከዚህ በታች ስማቸው በተጠቀሱ ጸሀፊዎች የማይታከት ጥረት ነው። እነዚህም ፀሃፊዎች በጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት እና በኢሚዲዮ በርሊን (Institut fuer Mediation, Beratung, Entwicklung GbR/Institute for Mediation, Consulting, Development)። የሽምግልና ባለሙያነት፣ የምክር እና የልማት ማስልጠኛ ተቋም) በመተባበር ባዘጋጁት የሽምግልና ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና የወሰዱና ሲያሠለጥኑ የነበሩ ናቸው። ከነዚህም አብዛኞቹ የአመቻች ሽምግልና ምስክር ወረቀት ተቀብለዋል።

**አቶ አድማሱ ኰካካይ** የሰላም ባለሙያ ሲሆኑ በኢትዮጵያ በታችኛው የኦሞ ስምጥ ሸለቆ በሰላም ግንባታ እና ግጭትን ማሻገር ዘርፍ የስድስት ዓመት ልምድ አላቸው። በደቡብ ኦሞ በሚገኘው የጂ አይ ዜድ ምርምር ጣቢያ እንደ ብሔራዊ የሰላም ባለሙያ በመሆን አገልግለዋል። አቶ አድማሱ በጀርመን ቦን ከተማ ለዘጠኝ ሳምንታት የሲቪል ሰላም አገልግሎት ግጭትን የማሻገር መድረክ አካዳሚ (Academy for Conflict Transformation of Forum Civil Peace Service) ትምህርታቸውን በመከታተል እ.ኤ.አ በ2011 የሰላም እና የግጭት አማካሪ ባለሙያነት ፈቃድን አግኝተዋል። በአሁኑ ሰዓትም በአ.አ.ዩ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በሰላምና ደኅንነት ጥናቶች (IPSS) ተቋም እየተከታተሉ ይገኛሉ።

**አቶ አትክልት ዳኘኤል** በተባበሩት መንግስታት የልማት ኘሮግራም (UNDP) ተወክለው በኢትዮጵያ ፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የግጭት መከላከል እና የሰላም ግንባታ ኘሮግራም ሃላፊ በመሆን እየሰሩ ይገኛሉ። በሰላም እና ደኅንነት ክፍል ለመንግሥት፣ ለሲቪክ ማህበራት ፣ ለአለም አቀፍ መንግስታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች ፣ ለተባበሩት መንግስታት የደኅንነት ተንታኝ ፣ አሰልጣኝ እና የአቅም ግንባታ ኃላፊ በመሆን በሰላም ግንባታ ዙሪያ በአጠቃላይ የ18 ዓመት ልምድ አላቸው። በእጅግ ከፍተኛ ማዕረግ የሁለተኛ ዲግሪያቸውን በልማት ጥናቶች የተመረቁና በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጪ የተለያዩ ስልጠና ወስደዋል። አቶ አትክልት በኢትዮጵያ ሁከትን በመከላከል ዘላቂ ስርዓትን በመዘርጋት የላቀ እውቅና ከተሠጣቸው ከፍተኛ ባለሙያዎች መካከል አንዱ ናቸው።

**አቶ ብዙነህ አሰፋ ኢማሙ** በፌዴሬሽን ምክር ቤት የጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት ብሔራዊ የሰላም አማካሪ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። አቶ ብዙነህ እ.አ.አ. ከ1996-2010 ዓ.ም. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በተለያዩ የሙያና የሃላፊነት ቦታዎች ላይ አገልግለዋል፡፡ እ.ኤ.አ. ከ2000-2003 ዓ.ም. በኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት የተቀናሽ ሠራዊት መቀላቀልና መልሶ ማቋቋሚያ ኘሮጀክት አስተባባሪ በመሆን ሰርተዋል። የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀትና የፖሊሲ ሃሳቦችን በማመንጨት በተለይም በግጭት መከላከልና የሰላም ግንባታ ስራዎች ሰፊ ድርሻ አበርክተዋል፡፡ በአሁኑም ወቅት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽ/ቤት በግጭት መከላከልና የሰላም ግንባታ ሥራዎች ዙሪያ የተለያዩ የአቅም ግንባታና የምርምር ሥራዎችን በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በፌዴሬሽን ምክር ቤትና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሰላምና ደኅንነት ጥናት ተቋም በጋራ በሚመሩት የብሔራዊ የግጭት አትላስ ጥንቅር እና ትንተና ፕሮጀክት (እ.አኤ.አ. ከ2011-2013) ከፕሮጀክቱ አማካሪዎች አንዱ በመሆን እየሠሩ ይገኛሉ።

**ክላውዲያ ሩስ** በሶሺዎሎጂ በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና ፈቃድ ያላቸው የዕርቅ ባለሙያ ናቸው። በእስራኤል፣ በዙምባብዌ እና በኢትዮጵያ በሰላም ግንባታ ዙሪያ ብዙ ሰርተዋል። እ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በሲቪል የሲቪል አገልግሎት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች አገልግለዋል። እ.ኤ.አ በ2007 በኢትዮጵያ የሚገኘውን የሲቪል የሰላም አገልግሎት ከመመስረት ጀምሮ እስከ 2012 ድረስ የኘሮግራሙ አስተባባሪ በመሆን ሰርተዋል። ሚስ ክላውዲያ የሽምግልና ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና እንዲዘጋጅ እንዲሁም ሽምግልናና አመቻች ሽምግልና በውህደት እንዲሰሩ ከፅንሰ-ሀሳቡ ጀምሮ እስከ ማስተባበር ድረስ ሳይታክቱ ሠርተዋል።

**ዶግማር ክሊክ ቪዶክ** በተግባራዊ ጋዜጠኝነት እና ፖለቲካ ትምህርቶች በበርሊን ጀርመን በመከታተል በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ለአስር አመታት አገልግለዋል። እ.ኤ.አ በ2002 ዓ.ም በጀርመን ቦን ከተማ የሲቪል ሰላም አገልግሎት መድረክ ግጭትን የማመቻቸትና የማቀራረብ አካዳሚ (Academy for Conflict Transformation of the Forum Civil Peace Service) ለአራት ወራት ትምህርታቸውን በመከታተል ፍቃድ ያላቸው የግጭትና የሰላም አማካሪ ሆነዋል። ከዚያም በላይ በተለያዩ አገሮች ሰላምን በመገንባትና ግጭትን በመከላከል ዙሪያ ብዙ ሰርተዋል። በሰሜን አየር ላንድ (የሰሜን አየርላንድ ሽምግልና)፣ በኮሶቮ (UNOP/ONV) እና በፊሊፕንስ (የጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት) ካገለገሉ በኋላ እ.ኤ.አ በ2012 የጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት በኢትዮጵያ በአስተባባሪነት የስራ ድርሻ ተቀላቅለዋል።

**ዴርክ ስኘኪንተር** በጀርመን ፌደራላዊ የሽምግልና ማህበር (BM) እንደ ዕርቅ ባለሙያ፣ አሠልጣኝ እንዲሁም በኢሚዲዮ ከአስርተ አመታት በላይ አገልግለዋል። በተለያዩ ዐውዶች ማለትም በማኅበረሰብ፣ በንግድ፣ በአለም አቀፍ መያዶች እና የእርዳታ ድርጅቶች መካከል የሽምግልና ስራዎች ይሰራሉ። በተጨማሪም በትላልቅ ድርጅቶች ውስጥ ግጭትን የማስተዳደር ስርዓትን (conflict-management systems) በመንደፍና በመተግበር ተሳትፈዋል። ከነዚህም መካከል ሆስፒታሎች፣ ትላልቅ ድርጅቶች እና የህዝብ አስተዳደሮች ተጠቃሽ ናቸው። በጀርመንና በስዊዝ ዮኒቨርሲቲዎች በድህረ ምረቃ ኘሮግራሞች የሽምግልና ስልጠና ይሰጣሉ። ለአጭር ጊዜ አማካሪነት በእርስ በርስ ጦርነት ለተጠቁ አገሮች እንዲሁም በዘውግ-ፖለቲካ የውስጥ ግጭት ያለባቸው አገሮች በልማት ትብብርና በሰላም ግንባታ ኘሮጀክቶች ተሳታፊ ሆነው ሠርተዋል። በፍልስጤም፣ ቱርክ፣ ኮሶቮ፣ ግብፅ፣ ሲሪላንካ፣ ኔፖል፣ ኢትዮጵያና ኬንያ ቡድኖችን በመገንባት፣ በማስታረቅ ፣ ግጭትን በመፍታትና የውይይት መድረኮችን (ዐወደ ርዕዮችን) በማዘጋጀት መርተዋል። በተጨማሪም በማሳቹሴትስ የሚገኘው Reflecting-on-Peace-Practices Learning Community የቦስተን የልማት ትብብር እንቅስቃሴዎች አባል ናቸው።

**አቶ ገመቹ ብርሃኑ** በኦሮሚያ አርብቶ አደሮች ማህበር በዳሬክተርነት ደረጃ የጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት ብሔራዊ የሰላም ባለሙያ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ። እ.ኤ.አ በ2010 የሲቪል የሰላም አገልግሎትን ለመጀመሪያ ጊዜ ሲቀላቀሉ በፌደሬሽን ምክር ቤት የተመደቡ ሲሆን ምክር ቤቱ ግጭትን በመከላከል እና በማስወገድ ስራ ተሳትፎ እንዲያደርግ አነሣስተዋል። ከዚህም በተጨማሪ በዚህ ስራ ከመሠማራታቸው በፊት በልዩ ልዩ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሲቪክ ማህበር ዘርፍ ድርጅቶች ሠርተዋል። ከሚጠቀሱት ድርጅቶች ውስጥ ዋነኛው በሰብዓዊ መብት እና የሲቪክ ትምህርት ምርምር ማዕከል (ReCHRCE) አንዱ ናቸው።

**ኩቢያና ሹሄስት ሃኬ** በጀርመንና በኦስትሪያ ፌዴራላዊ የሽምግልና ማህበራት የዕርቅ ባለሙያ አሰልጣኝ በመሆን ፈቃድ ያገኙ ሲሆን ከ15 ዓመት በላይ በመስራትና በማሠልጠን ልምድን አካብተዋል። ለብዙ ዓመታት በስዊዝ የልማት ትብብር እና በኖርዝ ዌስተርን በሚገኘው የስዊዘርላንድ የአኘላይድ ሳይንስ ዮኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለ200 ሰዓታት በሚሰጠው የሽምግልና ትምህርቶች አብረው መርተዋል እ.ኤ.አ በ1998 ኢንሚዲዮ ሲመሰረት ከመስራቾቹ አንዱ ናቸው። ከተለያዩ ደንበኞች፣ ከታለሙ ቡድኖች እና ባህሎች ጋር ሰርተዋል። እነዚህም ከአስቸጋሪ ወጣቶች ፣ አስተማሪዎችና ማህበራዊ ሰራተኞች አንስቶ እስከ ነጋዴዎች ፣ ዲኘሎማቶች እናም በኢትዮጵያ፣ ግብፅ፣ ኔፖል እና ፍልስጤም ከሚገኙ የታጠቁ አማፅያን ቡድን ጋር በውክልና ሰርተዋል። ከሌሎች ጋር በመተባበር በምዕራባዊያን ባልካን ሀገሮች ለሚገኙ የዘውግ ጦርነት ስደተኛ ቡድኖች “ድልድይ-ግንባታ” የሚባል የስልጠና አይነት አዘጋጅተዋል። ይህም በጀርመን ፌዴራላዊ ሽማግሌዎች ማህበር መለኪያዎች ሲቀርፁ እንዲሁም ፈቃድን ለማግኘት በሚደረግ ቅድመ ሁኔታዎች እንደዋነኛ መሳሪያ በመሆን አገልግሏል።

**ማይከ ቫን ኡዌም** በህዝብ አለምአቀፍና አውሮፓውያን ህግ ላይ ያተኮረ የህግ ባለሙያነት ልምድ አላቸው። በጀርመን አገር ቦን ከተማ ከሚገኘው የሲቪል ሰላም አገልግሎት መድረክ ግጭትን የማመቻቸትና የማቀራረብ አካዳሚ (Academy for Conflict Transformation of the Forum Civil Peace Service) የዘጠኝ ሳምንት ትምህርት ተከታትለዋል ስለዚህም የሰላም እና የግጭት አማካሪነት ፈቃድ አግኝተዋል። ከሶስት ዓመታት በለይ የጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት ኢትዮጵያን በመቀላቀል ግማሹ ጊዜያቸውን የሰላም ባለሙያ በመሆን በሙያዊ ትስስር፣ በፕሮጀክት ቀረፃ፣ በቁጥጥርና ግምገማ እንዲሁም በዕውቀት አስተዳደር ዘርፎች ሠርተዋል። በተጨማሪም የሽምግልና ባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና ከፅንስ-ሀሳቡ ጀምሮ እስከ ትግበራው ድረስ በዋነኝነት ተሳትፈዋል።

**አቶ ስከሺ መልሴ ጌታሁን** በ1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለዘጠኝ አመታት ከሰሩ በኋላ በትምህርት አስተዳደር በዲፕሎማ ከዚያም በመቀጠል በትምህርት ዕቅድ እና አስተዳደር በአ.አ ዩኒቨርሲቲ ዲግሪያቸውን አግኝቷዋል። ከዚያም በኋላ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በወረዳ ትምህርት ቤት ቢሮ ውስጥ የፕሮግራም ዋና ሃላፊ በመሆን አገልግለዋል። በመቀጠልም በፋርም አፍሪካ (በእንግሊዝ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት) በሚረዳ የአቅም ግንባታ ፕሮጀክት ውስጥ የመስክ አስተባባሪ ሆነው አገልግለዋል። በገጠር ልማት ላይ የሁለተኛ ዲግሪ ከመስራታቸው በፊት የደራሼ ህዝቦች ልማት ማህበር ውስጥ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆነው አገልግለዋል። ከዚህም በመቀጠል በደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች የልማት ማህበር ውስጥ የክልል ትምህርት ፕሮግራም አስተባባሪ እንዲሁም የፕሮግራም ልማት እና የማስተባበር ክፍል ዋና ኃላፊ ሆነው በጠቅላላ ለአምስት አመታት አገልግለዋል። ከግንቦት 2010 እስከ ጥቅምት 2012 ድረስ የክልል ፕሮግራም ከፍተኛ መኮንን በመሆን በፖክት ኢትዮጵያ /በአሜሪካ  መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት/ ሲሰሩ ቆይተው አሁን ግን በብሪትሽ ካውንስል የሲኤስኤስፒ ፕሮግራም የክልሉ መኮንን (CSSP Programme regional officer) በመሆን እየሰሩ ይገኛሉ።

**አቶ ታሪኩ ወልደዳዊት ከዮቴ** የታላቅ ወንድማቸውን የካላ ገዛኸኝ ወልደዳዊት ዱካ እና ምክር በመከተል በአሁኑ ሰዓት በአርባ ምንጭ ኮሌጅ ውስጥ የአይሲቲ እና የአውቶ ሜካኒክ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ። በሰላም ግንባታ ላይ ጥልቅ ጉጉት ስለነበራቸው በጂ አይ ዜድ የሲቪል የሰላም አገልግሎት ከኢንሚዲኦ በርሊን ጋር በመተባበር ባዘጋጁት ተከታታይ የሽምግልና የብቃት ማረጋገጫ ስልጠና ተካፋይ በመሆን እንዲሁም የአሰልጣኞች ስልጠና በመከታተል በአመቻች ሽምግልና ሰርተፊኬት አግኝተዋል።

**አቶ መኮንን መርጊያ ማጩ** በአሁኑ ጊዜ በደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል የብሄረሰቦች ም/ቤት የብሄረሰቦች የጋራ እሴቶች ማጎልበትና አለመግባባቶችን መፍታት ዋና የስራ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ባለሙያ በመሆን እየሰሩ ይገኛሉ። አቶ መኮንን ቀደም ሲል የህብረተሰብ ሳይንስ መምህር በሞሆን በቀድሞው ኢሉባቡርና ሸዋ ክፍለ ሀገራት ለአስር ዓመታት አገልግለዋል። አቶ መኮንን የሙያ መስካቸውን በመቀየር በህግ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን ካገኙ በኋላ በጋሞ ጐፋ ዞን የፍትህ መምሪያ ኃላፊ፣ የጋሞ ጐፋ ዞን ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች መምሪያ ከፍተኛ ባለሙያ፣ በብሄረሰቦች ም/ቤት የብሄረሰቦች መብት ማስከበርና የህገ መንግሥት ጉዳዮች መምሪያ ሃላፊ ሆነው አገልግለዋል።

**ፖቅላ ካላ ገዛኸኝ ወልደዳዊት** በደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል የኮንሶ ህዝብ ባህላዊ እና የመንፈሳዊ መሪ ናቸው። የህንፃ ምህንድስና ባለሙያ ሲሆኑ በኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ውስጥ አንቱታን አትርፈዋል። አባታቸው ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው ምክንያት ከማኅበረሰቡ በቀረበላቸው ጥሪ መሰረት የባህላዊ መሪነት ስልጣን ተረክበዋል። ከምህንድስና ሙያቸው በተጨማሪ በግጭት አፈታት እና ሽምግልና ላይ  የተለያዩ ስልጠናዎችን ወስደዋል። በተጨማሪም በህዝቡ መካከል በየቀኑ በሽምግልና ሥራዎች ይሳተፋሉ።

**ቄስ ፀጋነሽ አየለ** ተወልደው ያደጉት በዱራሜ ከተማ በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ሲሆን በስነ መለኮት ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪያቸውን አግኝተዋል። ከተመረቁ በኋላም በስነ መለኮት ሴሚናሪም በአስተማሪነት አገልግለዋል። በዚያም የተከበሩና የተመሰገኑ አስተማሪ ናቸው። የቅስና ማዕረግ ካገኙበት ጊዜ አንስቶ በሴቶች አገልግሎት ውስጥ በአስተባባሪነት በተለያዩ ቦታዎች እና ሃላፊነቶች አገልግለዋል። በአሁን ጊዜ በኢትዮጵያ ወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያን ህብረት የሴቶችና ቤተሰብ አስተባባሪ በመሆን እንዲሁም በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ በአንዱ ማህበረ ምዕመናን በበጎ ፍቃድ የክህነት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ። ከስራቸው በተጓዳኝ እንዲሁም በበጎ ፈቃደኝነት በተለያዩ ማኅበረሰባዊ ጉዳይ ኮሚቴዎች እና የሴቶች አቅም ግንባታ ስራዎች ውስጥ ይሳተፋሉ።

## ባህላዊ የግጭት አፈታት መንገዶች በኢትዮጵያ

ሌላው የአስተዳደርና የግጭትን አፈታት መንገድ በኦሮሞ ህዝብ መካከል ያለው “የገዳ” ስርዓት ነው። ገዳ ሲተረጎም በየስምንት አመቱ የሚለወጥ የመደብ ስርዓት ሲሆን ይህም የጦር ሰራዊትን፣ ምጣኔ ሀብትን /ኢኮኖሚን/ እና ባህላዊ ኃላፊነቶችን ታሳቢ ያደረገ ው። እያንዳንዱ “ገዳ” ለተወሰነ ጊዜ ብቻ በስልጣን ላይ ይቆያል። የስልጣን ሽግግር በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ትልቅ ክብረ በዓል ይደረጋል። የገዳ ስርዓት ግጭቶች ወደ ሁከት እንዳያድጉ የሚከላከሉ የግጭት አፈታት መንገዶች አሉት። ወደ ሁከት ደረጃ ከደረሰ ደግሞ ከስር መሠረቱ በመነሳት ለግጭቱ መፍትሔ የማግኛ መንገዶች አሉት።[53]

በአፋር ክልል ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ግጭቶች ከፍርድ ቤት ውጪ ነው የሚፈቱት። በክልሉ “ማዳ” የሚባል ባህላዊ የአስተዳደር ስርዓት ይገኛል። ስለዚህም ግጭቶች ሲከሰቱ ለዚህ ስርዓት ታልፈው ይሰጣሉ። በባህላዊ ሽማግሌዎች የሚደረገው አፈታት አብዛኛውን ጊዜ የዳኝነት ዓይነት ባህሪ ያለው ሲሆን የአፋር ልማዶች እና እሴቶችን ባቀፈ መልኩ ይከናወናል። በጣም የተለመዱ የግጭት አፈታት መንገዶች በሽማግሌዎች እገዛ የሚደረግ ዕርቅ እና በማኅበረሰቡ መሪዎች ወይንም በኃይማኖት አባቶች የሚደረግ የዳኝነት ዓይነት ነው። አነስተኛ ግጭቶች ሽማግሌዎች የሚያስተናግዱ ሲሆን ከፍተኛ ጉዳዮች ግን ወደ ማኅበረሰቡ መሪዎች ዘንድ ይቀርባሉ። ባህላዊ ተቋማት ስልጣናቸውን ከልማዳዊ ህግ (communal laws) የሚያገኙ ሲሆን አንዱ ማኅበረሰብ ከሌላው የሚለይበት እና ውስብስብ ህግጋት አሉት።[54]

አቶ ቀለምወርቅ ታፈረ ረዳ በጥናታቸው በአፋር የሚገኙትን የተለያዩ የባህላዊ ሽምግልና መንገዶች በዝርዝር ያብራራሉ። አቶ ቀለም ወርቅ እንደሚሉት “ማንኛውም የዘር ግጭት በመካከላቸው ቢከሰት ለረጅም ዘመን የቆየውን ማዳ የተባለውን ባህላዊ ህግ በመጠቀም ግጭቶቹን ሰላማዊ በሆነ መልኩ መፍታት እንደሚያስፈልግ የአፋር ህዝብ ያምናል። ማዳ ግጭትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን እንዴት መፍታት እንደሚያስፈልግ ግልፅ የሆኑ መመሪያዎችና ህጎችን አካቷል።”[55]

እንደ አቶ ቀለም ወርቅ ከሆነ የአፋር ህዝብ ከአባቶቹ የወረሳቸውን እነዚህን ህጎችንና መመሪያዎች የሚያከብር ህዝብ ነው። ጥፋት በሚከሰትበት ጊዜ እነዚህን በባህሉ ውስጥ አስገዳጅ አሠራር (framework) እና ባህላዊ እሴት የሚሰጡ ያልተፃፉ ባህላዊ ህጎችን ማጣቀስ የተለመደ ነው። ኅብረተሰቡ ከተቀበሏቸው አንዱና ዋነኛው ባህል ለመንደር ሽማግሌዎች ያለው አክብሮት ነው። ህዝቡ የመንደር ሽማግሌዎች በዕድሜ ብዛት ያካበቱት እውቀት እንዳላቸው ያምናል። በተጨማሪም ባህላዊ ዕውቀታቸውንና ባህላቸውን ለተተኪው ትውልድ እንደ አስተላላፊ ይመለከቷቸዋል። ወ/ሮ ትርሲት ግርሻው እንደሚሉት ከሆነ የእድሜ ባለጠጎችና የጎሳ መሪዎች እውቀት የሞላቸውና በባህሉ እንደ ሽምጋዮች[56] የተቀበሏቸው የተከበሩ ሰዎች ናቸው። ይህም ማለት የሽማግሌዎቹ ሚና የሚፈለግና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ነው።

ሽማግሌዎቹ ለሽምግልና ሂደቱ የሚመች ቦታ ይመርጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ ከዛፍ ጥላ በታች የተለመደ ቦታ ነው። እንዲሁም ስፍራው ከውሃ አጠገብ፣ ቅርብ የሆነ እና ለሽማግሌዎቹና ለተጋጭ አካላት መካከለኛ የሆነ ሊሆን ይገባዋል። ሽማግሌዎቹ ከመካከላቸው በቃሉ በመድገም ልምድ ያለውን አንድ ሰው ይመርጣሉ። የዚህ ሽማግሌ ሚና እንዲሁ ባህሉን በጠበቀ መልኩ ንግግሮችን መድገም ብቻ አይደለም። ነገር ግን ተጋጭ አካላት እንደተደመጡ እንዲሠማቸው ያደርጋል። ስለዚህም ንግግሩን የሚደግሙ ሰዎች በሽምግልና ሂደቱ የተግባቦቱን ቁልፍ ሚና በመጫወት ሽምጋዮቹ ጉዳቶችን እንዲለዩና ነጥቦቹ ግልፅ እንዲሆኑ ይረዳቸዋል።

አንድ ጊዜ የግጭቱ ጉዳይ በሽማግሌዎች እጅ ከደረሰ በኋላ አንድ ግለሰብ አቋሙን ጉልበት በመጠቀም ለማስፈፀም ብዙ ክፍተት አይኖረውም። ይህ ከአመቻች ሽምግልና የሚለይበት አንዱ ገፅታው ነው። በርግጥ ይህ የማዳ ባህላዊ የሽምግልና መንገድ ከአስታራቂነት ሚናው ይልቅ ወደ ዳኝነቱ ይጠጋል። የሽምግልናው ሂደት ምንም ያህል ቢቆይ ሽማግሌዎቹ ችግሩን ለመፍታትና መፍትሔ ለማግኘት ቢቆዩ መጠበቅ ከባህሉ አንዱ አካል ነው።

በተደጋጋሚ ግጭትን የመፍታት ሂደት ሁለቱንም ወገኖች የሚያግባባ መፍትሄ እስኪገኝ እና ዕርቅ እስኪወርድ ድረስ ረዘም ያለ ጊዜ ይፈጃል። ግጭቱ የተፈታው በካሳ ከሆነ፣ የካሳው መጠን የሚወሰነው እንደ ደረሰው የጥፋት መጠን እና እንደ ግጭቱ አውድ ይሆናል። ለምሳሌ አነስተኛ ጉዳት በደረሰበት አውድ በጐሳ መሪዎች በሚደረግ ጣልቃ ገብነት መፍትሄ ላይ ከመደረሱ በፊት ሊከናወን የሚገባ ልዩ ሂደት አለ። ጉዳቱ በባህላዊ ሐኪም ታይቶ አጥንቱ ካልተጐዳ መጠነኛ እንደሆነ ይቆጠራል። ስለ ጉዳቱ በዳይ ለተበዳይ ለፈሰሰው ደም መተኪያ ፍየል መስጠት አለበት። ከአንድ ከሁለት ቀን በኋላ ደግሞ ሌላ ፍየል ለፈሰሰው ደም መተኪያ ብሎ ይሰጣል። ይህ “ማልዲኖ” በመባል ይታወቃል። በመጨረሻም የካሳ ክፍያው /ሞሩሶ/ እንደ ጉዳቱ መጠን ከ12 ብር እስከ ግመል ድረስ ይኖራል።

---

53 Institute for Peace and Security Studies in collaboration with Friedrich Ebert Stiftung. (2010).
54 Ibid.
55 Reda, K.T. (2011).
56 Girshaw, T. (2004).

ቅጣቱ እና የካሳ ክፍያው እንደ ተጐዳው አካል አይነት ይለያያል። ለምሳሌ አፋሮች ትንሿን ጣት እንደ ሠላማዊ፣አመልካች ጣትን እንደ አቅጣጫ መጠቆሚያ፣ ሶስተኛው የቀለበት ጣትን ደግሞ ለትዳር ወሳኝ እንደሆነ ስለሚያምኑ በነዚህ አካላት ላይ የሚደርስ አደጋ ከፍተኛ ነው። የፊተኛው የአካል ክፍላችን እና የኋለኛው የአካል ክፍላችንም የተለያየ ዋጋ ተሰጥቷቸዋል። ለምሳሌ ግንባር ላይ የሚደርስ ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ ይቆጠራል። ምክንያቱም ምንጊዜም ለተመልካች የተጋለጠ የአካል ክፍል ስለሆነ ሁሌም ለሰዎች ዘለፋ ስለሚያጋልጥ ነው። ካሳን የሚያስቀምጡ ህጐች ዝርዝር እና ጥልቅ ናቸው። እያንዳንዱ ጥፋት ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ ተቀምጦለታል። የጥፍር መጐዳት እንኳ ተለይቶ የካሳ ክፍያ ተቀምጦለታል። በመርህ አፋሮች እያንዳንዱ የካሳ ክፍያ በባህላዊ ህግ እንዲታይ ያደርጋሉ። በተግባር ግን ክፍያው በድርድር ይካሄዳል። ለምሳሌ ነፍስ ያጠፋ ካሳ እንዲከፍል የሚጠየቀው 100 ግመሎች ነው። ነገር ግን በድርድር ግማሹን ብቻ እንዲከፍል ይደረጋል።

የአፋር ባህላዊ ህግ ምርጥ እንደሆነ ይነገራል። ከጊዜ ወደ ጊዜ የተወሰነ ለውጥ ማድረጋቸው ብቻ ሳይሆን ከቦታ ቦታም ይለያያል። አፋሮች የካሳ ክፍያ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱን ብቻ ሳይሆን በቀንድ ከብቶች ይደረግ የነበረው ክፍያ በገንዘብ እንዲለወጥ መደረጉንም ይናገራሉ። በተጨማሪም ዛሬም ድረስ አርብቶ አደርነት ተጠብቆ በቆየበት አካባቢ ክፍያ ከፍ ብሎ እንዲፈፀም ይጠበቃል።

ለምሳሌ አንድ የጐሳ መሪ ከቤተሰብ አባል አንድ ሰው ሲሞት አንድ ግመል /ሎይን አላህ/ ይቀበላል። የመጨረሻው የዕርቅ ስነስርአት ከዳምሂታ እና ሴካ ጐሳዎች የተውጣጡ ሽማግሌዎች በተገኙበት በግ ታርዶ ይከናወናል። የዳምሂታ ጐሳ ሽማግሌዎች ከቅዱስ ቁርአን /ፊቲሃ/ የእርቁን መጠናቀቅ የሚያጐላ ጥቅስ ይጠቅሳሉ የሴካ ጐሳ ሽማግሌ ደግሞ ይመርቃሉ /ዱአ/። የመጨረሻው እርድ የሚካሄው እግረኛ መተላለፊያ ላይ ነው። ይህም አላፊ አግዳሚው በሚንቀሳቀስበት ወቅት ይቅር ስለመባባል እና ባህሉ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲቀጥል ትምህርት እንዲወሰድ ነው። በጥቁር ድንጋይ ላይ እሳት እየነደደ በጉ ይጠበሳል። ድንጋዩ ለአመታት ከዛ ቦታ አይነሳም። በአንድ አጋጣሚ መስዋዕት የተደረገው /ሶላ/ ሆን ተብሎ በመንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አካባቢ ነበር። አንደ መረጃ ሰጪዎቹ ከሆነ ቦታው የተመረጠው በትምህርት ቤቱ የሚማሩ ህፃናት ከመደበኛው ትምህርት ጐን ለጐን ለአፋር የይቅርታ ባህልን /አፉ/ እንዲያሰርፁ ለማድረግ ነው። ለካሳ የሚሰጡ ከብቶች ጤነኛ የሆኑ እና ያልከሱ መሆን ይኖርባቸዋል። በከብቶቹ ጤንነት ላይ ቅሬታ ካለ ለበለጠ አለመግባባት በር ይከፍታል ተብሎ ይታመናል። ጤነኛ ያልሆነ ከብት መስጠት እንደ መናቅ ይቆጠራል።

በጐሳዎች መካከል የሚፈጠሩ የግድያ ወንጀሎች የሚጠናቀቁበት ሁሉም ለማለት በሚናስደፍር መልኩ በዕርቅ ነው። በአንዳንድ ጉዳዩች ግን ገና ዕርቁ ሲጀመር የተበዳይ ቤተሰቦች ይቅርታ ለማድረግ አሻፈረኝ ይላሉ። ሽምግልናውን አይቀበሉም። ለበቀልም ይዝታሉ። እንዲህ ባለ ወቅት የተወሰኑ የገዳዩ የጐሳ አባላት የተበዳይ ጐሳ መሪን /ሎይና፤ ጠባቂ ማለት ነው/ ለመለመን ይሰባሰባሉ /ዱበሪቲ/። የጐሳው መሪ የበቀል እርምጃ ለመውሰድ እያስፈራራ(ሩ) ያሉት ሰዎች ላይ ጫና ያደርጋል። ይህንን ሁሉ ባህላዊ ስርዓት ገፍቶ እርቁን እንቢ ያለ ግለሰብ ከጐሳ አባልነቱ ይገለላል፣ እውቅና ይነፍገዋል። ይህ ማግለል ደግሞ በተለያዩ ማህበራዊ ግንኙነቶች እና ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይም ይንፀባረቃል።

አቶ ቀለምወርቅ በአፋር የሚገኑትን “ባህላዊው አና ዘመናዊው የግጭት አፈታት መንገዶች” ያላቸውን ልዩነቶች ተንትነዋል። ጥፋት ለተቀላቀለበት ማንኛውም ግጭት አፋሮች ሁለት አይነት የግጭት አፈታት መንገዶች ይጠቀማሉ። እነዚህም ዘመናዊው በፍርድ ቤት ስርዓት ወይንም በባህላዊ ህጐች የሚከናወኑት ናቸው። በርካታ የአፋር ተወላጆች ባህላዊውን ስርዓት ይመረጣሉ።

አያይዘውም ከባህላዊው መንገድ ውጪ፣ በቀበሌ ደረጃ ያለው የህግ ዳኝነት ሂደቱም ሆነ ደረጃው ለአፋር ተወላጆች አመቺ አይደለም ይላሉ። ህጐቹና መመሪያቹ የወጡት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉ ማዕከላዊ አካላት በመሆናቸው ምናልባትም የአፋርን ልማዳዊ ህግ እና እሴት (ወይንም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብን ጭምር) ያላገናዘበ ሊሆን ይችላል። ዘመናዊው የፍርድ ስርዓት ለተራው የአፋር ተወላጅ ሩቅ ነው፤ ይህም በግጭት አፈታቱ ላይ መተማመን እንዳይኖር አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተጨማሪም የችሎቱ ውሳኔ ከችሎቱ ውጪ ያሉ አውዶችን ለተረጋጋና ቀጣይ ለሆነ ማህበራዊ ግንኙነት አስተዋፅኦ የሚያደርጉትን ከግንዞቤ አያስገባም። በመጨረሻም የችሎቱ ሰዎች ራሳቸው የተውጣጡት ከሌላ ቦታ ነው። አፋሮች “ለእንግዶቹ” የቤተሰባቸውን እና የንብረታቸውን ጉዳይ ከማስረዳት ይቆጠባሉ። በአፋሮች መካከል የሚነሳ ግጭትን ለመፍታት አፋር በቀል የሆኑ ተቋማት አዋጭ ይመስላሉ።

ይህ ጥረት የሀገሪቱን ፍርድ ቤቶች በሚወዳደር መልኩ አይደለም። ነገር ግን ሀገር በቀል ተቋማት እና ፍርድ ቤቶች በመተባበር እና በመደጋገፍ በአፋሮች ዘንድ ብቻ ሳይሆን በሁሉም አካባቢ እንዲሠሩ ነው።

inmedio
institut für mediation . beratung . entwicklung

# የግጭቶች መካረርና ተነፃፃሪ የሽምግልና ዓይነቶቻቸው

በF. Glasl 2003 የቀረበ

ግትርነት

ክርክርና ተቃርኖ

ንግግርን አቁሞ ተግባር ውስጥ መግባት

ፍረጃና ቅንጅት

በሰው ፊት ሞገስ ማጣት

የማስፈራራት እርምጃ

የተወሰነ ውድመት

መነጣጠል

ተያይዞ ገደል

**መሸምገል**

**አመቻች ሽምግልና**

**ችግሮችን ፈቺ ሽምግልና**

አወዛጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚሠጥ

**የማመቻቸትና የማቀራረብ ሽምግልና**

**“ፈዋሽ” ሽምግልና**

የግጭቱን ስረ-መሠረቱ ታሳቢ በማድረግ ሂደቱን በሚመለከት የበዛ መመሪያዎችን ሰጪ

**በተናጥል የሚደረግ ሽምግልና**

**እውነታን መሠረት ያደረገ ሽምግልና**

በጉዳዮቹ ላይ ትኩረት የሚሠጥ፣ ሂደቱን በሚመለከት መመሪያ ሰጪ

**የሽምግልና ዳኝነ**

**“የሀይል ሽምግልና”**

በጉዳዮቹ ና በሂደቱ ላይ በሚመለከት መመሪያ ሰጪ

© inmedio. www.inmedio.de/en







